
# ሐመር

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሐመር ፲፫ኛ ዓመት ቁጥር ፪ ሚያዝያ/ግንቦት ፲፱፻፺፱ ዓ.ም



## ቲ ውኀ አቡነ አረጋዊ ቤተ ክርስቲያን (መቄት - ሰሜን ወሎ)

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## ኢትዮጵያዊ ማንነት የተንጸባረቀበት

የዛሬው ብዕሬን ከወረቀት ያገናኙት በአንድ ሰርግ ተገኝቼ የተመለከትኩት ነገር ስላስደሰተኝ፣ በቅዱስ ጋብቻው የተሰማኝን ደስታ እና ያየሁትን ፍጹም ኢትዮጵያዊ ሥነ ሥርዓት ለማብሰር ነው። ልጆቹ /ሙሽሮቹ/ ከቤተሰብ ከነበራቸው መልካም አስተዳደግ በተጨማሪ የማኅበረ ቅዱሳን ውጤት መሆናቸውን ተረድቻለሁ። ነገሩ እንዲህ ነው፦

የተመለከትኩት የሰርግ ሥነ ሥርዓት በአንድ ትንሽ የኢትዮጵያ የገጠር መንደር የተከናወነ እንጂ፣ በአንድ የአፍሪካ አገር ዋና ከተማ፣ ያውም የምዕራባውያን ባህል በተቀላቀለበት አዲስ አበባ የተከናወነ አይመስልም። ሥነ ሥርዓቱ የምዕራባውያን ባህል ትንሽ እንኳን በስህተት ያልገባበት ነበር። ሰርጉ የታጀበው ድሮ በሕፃንነቴ በተመለከትኳቸው ቀንደ መለከት /ጥሩንባ/ እና ከበሮ ብቻ ነበር። ሁላችንም የሰርጉ ታዳሚዎች እግዚአብሔርን በእልልታና በዝማሬ ስናመሰግን ዋልን። ሌላው ሁሉ ይቅርና ሙሽሮችና ሚዜዎች እንኳን መጠጫቸው የፈረንሳይ ብርጭቆ እና የቻይና ሴራሚክ ሳይሆን፣ የሚያማምሩ የኢትዮጵያ የቀንድ ዋንጫዎችና የቅል ሽክናዎች ነበሩ። ሙሽሮቹ በዚህች በአፍሪካ መዲና ውስጥ ተወልደው አድገው M.A (MSc.) ድረስ ተምረው ሳለ፣ በአውሮፓ ኬክ ምትክ የቀረሱት የሀበሻን /የኢትዮጵያን/ ድፎ ዳቦ ነበር። ከጤናም አንጻር ኬክም ሆነ ማናቸውም ጣፋጭ ነገሮች ለአላስፈላጊ ክብደት መጨመር፣ ለስኳር በሽታ፣ ለደም ግፊት ... ወዘተ እንደሚያጋልጥ እነዚህ ችግሮችም /በሽታዎች/ ካላደጉት አገሮች ይልቅ በአደጉት አገሮች በይበልጥ እንደሚታዩ ሳይንስ /ሲያንስ/ ያረጋገጠው ሀቅ ነው። በጣም የደነቀኝና የተደሰትኩበት የፈረንጆች ባህል የሆነው የሕፃናት ሻማ ያዦች እንኳ አለመኖራቸው ነው። ብቻ ምን አለፋችሁ በዝርዝር ከመጻፍ እንዲያው ብቻ፣ በድፍኑ የሰርጉ ሥነ ሥርዓት ፍጹም ኢትዮጵያዊ ነበር ማለቱ ይሻላል።

ሙሽሮች እንደዚህ ዓይነት ፍጹም ኢትዮጵያዊ በሆነ ሥርዓት ለመጋባታቸው የቤተሰብ አስተዋፅኦ ቢኖርበትም፣ በይበልጥ ግን በከፍተኛ ትምህርት ተቋም /ዩኒቨርስቲ/ በነበሩበት ወቅት በማኅበረ ቅዱሳን ግቢ ጉባኤ በሚሰጠው ትምህርት ኢትዮጵያዊነትን /ማንነታቸውን/ በጥልቅ የተረዱ መሆኑን ለመገንዘብ ችያለሁ። አበው «አሐደ ቀለመ ዘነገረከ ይኩን ከመ አቡከ፣ ክልኤተ ቀለመ ዘነገረከ ይኩን ከመ አምላክከ።» ያሉትም ለዚሁ ነው። ማኅበረ ቅዱሳን ለእነዚህና ለሌሎች ብዙ ሺሕ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች «ክልኤተ ቀለመ» የነገራቸው /ያስተማራቸው/ ነው ለማለት ይቻላል። በእርግጥ በዚህ ዘመን የእግዚአብሔርን ቃል የምንሰማው /የምንማረው/ ብዙ ሰዎች ብንሆንም፣ በተግባር የሚያውለውን አለማየቱ እና በተግባር ባለማዋሉ የሚፀፀተውን አለማየቱ ራሱ በጣም የሚያሳዝን ነው። በዚህች ነፍስና ሥጋ በመቀዋወም /በትግል/ በሚኖሩባት ዓለም /ሮሜ. ፯፥፲፰-፳፭/ በዚህ ዘመን እንደነዚህ ሙሽሮች ዓይነት ለነፍስ የማድላት ሁኔታ መመልከት ተስፋ ሰጪ ነው። ማኅበረ ቅዱሳንንም እግዚአብሔር ሥራችሁን ይባርክላችሁ። ሥራችሁም እንደዚህ ዓይነት ፍሬ እንዲያፈራ አምላከ ቅዱሳን ይርዳችሁ እላለሁ። ሙሽሮችም እኛ ታላላቆቻቸው ካለን ተሞክሮና አንድ የቤተ ክርስቲያናችን አባትም በሰርጉ ሥነ ሥርዓት ባደረጉት የማጠቃለያ ንግግር ላይ እንደገለጹት፣ ይህንን ቅዱስ ተግባር የሚፈታተን ሰይጣን ለወደፊቱ ብዙ ፈተና ሊያመጣባችሁ እንደሚችል ከወዲሁ በመረዳት የዲያብሎስን ውጊያ እንደ እናትና አባታችሁ በእግዚአብሔር ኃይልና በጸሎት እንደምታሸንፉት ተስፋ እናደርጋለን፣

*ዶ/ር ዘርፉ መልአኩ*
*ከአዲስ አበባ*

### በስም ኦርቶዶክስ፣ በምግባርስ?

እኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኞች እውነተኛ ሃይማኖት አለን። ምግባርስ አለን? ይህን ለማለት ያነሳሳኝ ነገር ቢኖር በተለያዩ በመጥፎ ቦታዎች ላይ ስማችን የሚነሳው እኛ ኦርቶዶክስ አማኞች ነን። አንዳንዶች እንደሚናገሩት ዝሙት እፈጽም ነበር። ቀማኛ ዱርዬ ነበርኩኝ ሃይማኖቴም ኦርቶዶክስ ወዘተ.. በማለት ሲናገሩ አደምጣለሁ። በሚዲያም የሚቀርቡ ሰዎች በተለይም ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ቫይረስ በደማቸው ያለባቸው ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ነን ሲሉ እሰማለሁኝ።

ለምሳሌ በFM 97.1 የሬዲዮ «ይበቃል» በሚል ፕሮግራም በሦስት ጉልቻ /ትዳር ፈላጊዎች/ በሚተዋወቁበት ክፍል በአብዛኛው ሃይማኖታቸውን ሲናገሩ የእኛ ሃይማኖት ተከታዮች ይበዛሉ። ታዲያ ይህ ነገር ምንድን ነው? እኛ ኦርቶዶክሶች ከሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች የበለጠ ኃጢአት /ዝሙት/ እንፈጽማለን ማለት ነው? /ምክንያቱም ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ከ፺ በመቶ በላይ የሚተላለፈው በዝሙት ነውና።/ ወይም የእኛ ሃይማኖት ተከታይ ስለሚበዛና በዛ ላይ የተያዘው ቁጥር ሲካፈል በዛ ስለሚል ነው? እኔ ግን አይመስለኝም።

የኛ ትውልድ ወደ ጥፋት ጐዳና እየተጓዘን ይመስለኛል። የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ማክበር እየቀረ ነው። አብዛኛዎቻችን በስም ኦርቶዶክስ ተብለን ብንጠራም ሥራችን ግን እግዚአብሔርን የማያስደስት ከፈቃደ ነፍሳችን ይልቅ ፈቃደ ሥጋችን የሠለጠነብን ነን። ይህን ስል ግን ሕገ እግዚአብሔርን የሚጠብቁ በምክረ ካህን የሚኖሩ መልካም ምግባር ያላቸው ብዙ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስቲያኖች እንዳሉ ዘንግቼ አይደለም። ታዲያ ይህ ትውልድ በአባቶች ጸሎትና ትምህርት ወደ ጥሩ ሥነ ምግባር የማንመልሰው ከሆነ ካለው የትምህርትና የስብከት አሰጣጥ በእጥፍ መጨመር ያስፈልጋል እላለሁኝ።

*ትክልቲ*
*መከላከያ ኢንጅነሪንግ ኮሌጅ*
*ደብረ ዘይት*

### ቤተ ክርስቲያንን ለማፍረስ ሩጫ

ዕለቱ ረቡዕ ከምሽቱ ለሁለት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ከንግድ ሥራ ኮሌጅ ትምህርቴን ተከታትዬ ወደ ቤቴ በመመለስ ላይ ነኝ። ከጎተራ ፒያሣ የሚለውን ታክሲ ይዤ ስጓዝ ... ለገሀር አካባቢ ሁለት ተሳፋሪዎች ታክሲ ውስጥ ገብተው ከኋላዬ ወንበር ተቀመጡ። ጨዋታቸው ይሰማኛል፣ የሚያወራው አንደኛው ነው። ከንግግራቸው እንደተረዳሁት ፍላጐታቸው ከኢትዮጵያ ውጪ ለመሄድ ከዶክተር እከሌና ከዶክተር እከሌ ጋር ሦስት ሆነን ልንሔድ ነው ይላል። ወደ ውጪ የሚሄዱት ታላቅ የወንጌል ሰባኪ ለማምጣት ነው። የሚመጣውም ፓስተር ቢያንስ ሁለት ከተሞች ላይ ጉባኤ ማዘጋጀት እንደሚፈልግ ሁለቱ ከተሞችም ጎንደርና መቀሌ እንደሆኑ አንድ ጉባኤ ይበቃል ከተባለም በመቀሌ ቢዘጋጅ ጥሩ መሆኑን ያስረዳዋል። ምክንያቱንም ሲያብራራ ጴንጤዎችን በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ ሀገር የሚቃወሟቸው ከሰሜን የሚሔዱ ናቸው። ሕዝቡም በጣም ድሀ አካባቢውም ረሐብ፣ ጦርነት የሚያጠቃው በመሆኑ፣ በአጠቃላይ ፓስተር ዶ/ር እከሌ እንዳለው ሌሎች አካባቢዎች በራቸውን ለወንጌል ክፍት አድርገው፣ ሰሜን ኢትዮጵያ ግን በሩን ለወንጌል ዝግ አድርጓል። ስለዚህም ጉባኤውን እዚያ በማካሄድ ይህንን ችግር መስበርና ሕዝቡን አማኝ ማድረግ እንዳለባቸው ይተርካል። የመጪው ሚሊኒየም በዓል የሚጀመረው ከሰኔ ፲፱፻፺፱ እስከ ሰኔ ፳፻ መሆኑን እንደሚያውቅና እነርሱም ጉባኤውን በሰኔ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም፣ ቀደም ብሎ በግንቦት በማዘጋጀት ከሚሊኒየሙ ጋር ለማገጣጠም እንደታሰበ ይነግረዋል።

ይህን ጨዋታ እየሰማሁ ታክሲው ፒያሣ ደርሶ ወረድኩኝ። በውስጤ በጣም ተበሳጨሁ፣ አዘንኩ። ሰው እንዴት በአጠቃላይ ሀገሩን፣ በተለይ ደግሞ ይህችን ሐዋርያዊ የሆነች የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለማፍረስ ይህንን ያህል ይደክማል። አያበሳጭም? አያሳዝንም ትላላችሁ? ለማንኛውም የታሰበውን ሴራ ዐውቀን እንድንጠነቀቅ አስፈላጊውን ዝግጅት እንድናደርግ እየጠቆምኩ፣ ልዑል አምላክ እግዚአብሔር ለሴረኞቹ ልብን እንዲሰጣቸው እመኛለሁ። ልዑል እግዚአብሔር አጽራረ ቤተ ክርስቲያንን ያስታግስልን። አሜን።

*ኃይለማርያም*
*ከአዲስ አበባ*

©ማኅበረ ቅዱሳን 

«... "ጰንጠቆስጤ" የሚለው ቃል የግሪክ ቃል ሲሆን ሃምሳኛ (ቀን) ማለት ነው። ከቂጣ በዓል በኋላ ካለው ቅዳሜ (ሰንበተ አይሁድ) ቀጥሎ ባለው ቀን (እሑድ) ከአዝመራው ካህኑ ትንሽ ነዶ ያጭድ ነበር። ይህ የታጨደ ነዶ ‹የሚ ወዘወዝ ነዶ› ይባል ነበር። ዘሌ.፳፫÷፲-፲፰። ...»

*በረከተ ወንጌል*

«...በአብዛኛው ጊዜ አክራሪዎች ወንጀል የሆነውን ጭፍጨፋ ፈጽመው እልቂትን ካስከተሉ በኋላ ለምን ይህን አደረጋችሁ ሲባሉ «ዐፄ ዮሐንስ እኛን እንዲሁ አድርጉብናል» የሚል መልስ ይሰጣሉ። ታሪኩን በደንብ ከተመለከትነው ግን በኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ላይ የተነሡት ዐፄዎች በሃይማኖት ማስለወጥ ጉዳይ አንድም ሰው እንዳላረዱና እንዳላቃጠሉ አያሌ ማስረጃዎች አሉ። ...»

*ወቅታዊ ጉዳዮች*

«...እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ገለጻ እመቤታችን ማድነቅና ማመስገን የተጀመረው ራእዩን /የአምላክን ሰው መሆን በትንቢት ከተመለከቱት/ ከነቢያት ጀምሮ ነው። «እምነ ጽዮን ይብል ሰብእ» የሚለውን የነቢዩ ዳዊትን ቃል ሲተረጉም ርቱዐ ሃይማኖት «ዘይቢሂ ማርያም ይእቲ ሰብአዊት ወእምነ ንሰምያ እስመ ተወለድነ ዳግመ በጥምቀት... ሰው እናታችን ጽዮን ይበል /ይላል/፣ ያላት ይህች ጽዮን ሰው ናት። ...»

*ትምህርተ ሃይማኖት*

ላማ ደብር ማርያም የተተከለችው በዐፄ ካሌብ ዘመነ መንግሥት በአምስተኛው ክፍለ ዘመን ነው። እንደ እነርሱ ገለጻ ደብሯንም የተ ከሏት «አባ ላማ» የተባሉ ቅዱስ ናቸው። ስለቅዱሱ የተጻፈ ገድልና የመሳሰሉትን ማየት ባልችልም ቦታው ወይም አካባቢው አባ ሰላማ ጵጵስናን ይዞ ከመጣ በኋላ ክር ስትናን ለማስፋፋት ከአክሱም ደቡብ አቅ ጣጫ ሲጓዙ ሰቆጣንና ላስታን አድርገው የሚደርሱበት አካባቢ ይኸው መቂት መሆኑ ግን ግልጽ ነው።

*እናስተዋውቃችሁ*


ዋና አዘጋጅ - ዲያቆን ብርሃኑ አድማስ
ም/ ዋና አዘጋጅ - ዲያቆን ያረጋል አበጋዝ
ሪፖርተሮች - መ/ር ደረጀ ጅማ
- ጌታቸው በቀለ
ኮምፒዩተር ዲዛይነር - ርብቃ ኀይለ ማርያም
የኮምፒዩተር ጸሐፊዎች - ጸዳሉ ሁንዴሳ
- ገነት ግርማ
- ይመኙሻል አበበ
E-mail: eoc-m-kidusan@ethionet.et
www.eotc-mkidusan.org
ስልክ 011-1-245135
መ.ሣ.ቁ 80078
አዲስ አበባ


«ማኅበረ ቅዱሳን»

እግዚአብሔር ያከበራቸው
የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃን፣ የሰማዕታት
በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ ትሩፋትና እማላጅነት
የሚዘከርበት በመሆኑ
ይህን ስያሜውን አግኝቷል።


ሐመር
፲፭ኛ ዓመት ቁጥር ፪
ሚያዝያ/ግንቦት ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.


# ይዘት


**የማኅበሩ መልእክት**
* የሁለት ሺሕ ዓመቱ ፍጻሜ የደግ ነገር ሁሉ ፍጻሜ እንዳይሆን ........ ፪

**ደብዳቤዎች** ........ ፬

**በረከተ ወንጌል**
* «መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው» ........ ፮

**የኢትዮጵያ ስምዓት /ስሥሬ ምዕት/**
* በማዕከለ ክልኤ አምኣት ር.ኢ.ኩ.ኪ. ........ ፱

**ወቅታዊ ጉዳዮች**
* «ቤተ ክርስቲያን ስትከፈል፣ ምእመናን ዝም ብለን ማየት የለብንም» ........ ፲፩
* የእስልምና እና የአክራሪ እስልምና ገጽታ በኢትዮጵያ ........ ፲፬
* ዜዋዌ መጻሕፍት ወሐተታ ምስጢራት ........ ፲፮

**ትምህርተ ሃይማኖት**
* በውኑ ዓለም ሳይፈጠር እመቤታችን አትታወቀምን? ........ ፲፰
* «በስመ ሥላሴ፣ እቀጠቅጥ ከይሴ» ........ ፳፩

**ምዕራፍ** ........ ፳፪

**ኪነ ጥበብ**
* ይድረስ ለባለ ዲግሪው ግያዝ ዘኢትዮጵያ ........ ፳፫

**እናስተዋውቃችሁ**
* የበረሐዋ ገነት ........ ፳፮

**ሐመረ ሕይወት**
* ራስን ማስቻል፣ እንዴት? ........ ፴

**ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ**
* ለራስ ጥቅም ሌሎችን ማስቀደም ........ ፴፪

**ስቡጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት**
* ቦዝ አንቀስ ........ ፴፰



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክር ስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የሚዲያና ሕዝብ ግንኙነት ዋና ክፍል በመጽሔት ዝግጅት ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስ ቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዐተ እምነ ትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ።

# የማኅበሩ መልእክት

*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፡፡*

## የሁለት ሺሕ ዓመቱ ፍጻሜ የደግ ነገር ሁሉ ፍጻሜ እንዳይሆን

ጠዋትም ሚሌኒዬም ማታም ሚሌኒዬም፡፡ የሚሊኒዬሙ ግቦች፣ የአዲስ ሺሕ ዓመት ስትራቴጂ፣ የዕሥራ ምዕቱ በዓልን ምክንያት በማድረግ፣... ሁሉም ይናገራል፡፡ ዕቅዱን፣ አሳቡን፣ ቅዠቱንም ይቀባጥራል፡፡ አንዳንዱ ደግሞ ክፋቱንም ጭምር ዐውቆም ይሁን ሳያውቅ ያገዛዋል፡፡ የእኛ አስተሳሰብ ለሀገር እድገት፣ የእኛ ሃይማኖትም ለዚህ ይጠቅማል፣... እያሉም የጥፋት አዋጃቸውን በመለፈፍ የሚያደነቁሩን አሁን እየበዙ መጥተዋል፡፡ «ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል» እንደሚባለው ሚሊኒዬሙ ብቅል ሆኖባቸው ዘንድሮ የለፈለፉት ብዙ ናቸው፡፡ አልፎ እናየው ይሆን?... ሚሊኒዬሙን፡፡

ፈዋሽ ነኝ ባዩ በሦስት በአራት አቅጣጫ ይሯሯጣል፡፡ አንዱ ጠበል አጥማቂ ነኝ ብሎ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ተጠግቶ በእግዚአብሔር ስም ይነግዳል፡፡ ቅዱስ ነኝ፣ የበቃሁ ነኝ፣ ለዚህ ዘመን እግዚአብሔር አዘጋጅቶ የላከኝ ነኝ፤ እኔን ብቻ ስሙ፡፡ እመቤታችን ልካኛለች፤ የሚሠራ ክህነት የለም፤ አታስቀድሱ ወደ እኔ ብቻ ኑ ይላል፡፡ ሰይጣን በእውነት በግልጽም ቢመጣ ከሰዎች ተከታይ እንደማያገኝ ያሳየው ሕዝባችንም ለዚህ ዓይነት አጭበርባሪዎች የሚገብረው ጊዜና ገንዘብ አላጣም፡፡ ከቤተ ክርስቲያን ሲያባርሩት ቤት እየተከራየ በተለያየ አጋንንታዊ ጥበብ ግልጽና ተራ በሆነ ማጭበርበር በእግዚአብሔር ስም የሚነግደው ነጋዴ በሥጋውና በኃጢአቱ ገበያ ያተረፈ ይመስላል፡፡ «የዔሊም ልጆች ምናምንቴዎች ነበሩ፤ እግዚአብሔርንም አያውቁም ነበር» ፩ሳሙ.፪፥፲፪፡፡ ተብሎ እንደተጻፈ እግዚአብሔርን የማያውቅ አዋቂ፣ እግዚአብሔርን የማያውቅ ካህን፣ እግዚአብሔርንም የማያውቅ መምህር፣ እግዚአብሔርን የማያውቅ ዘማሪና.... እንዳይበዛ የአሁኑ ወቅት ሁኔታ ያስፈራል፡፡ ሰዎች ከበሽታቸው የመዳንና መጻኢውን የማወቅ ፍላጐታቸው ሁልጊዜም ስለሚኖር ጥንቱንም እናድናለን፣ እንዲህ እናደርጋለን ወደሚሉ ሰዎች ሁልጊዜም ይሔዱ ነበር፡፡ ነገር ግን ሰዎቹ እናውቅልሃለን፣ እናድንሃለን ይላሉ እንጂ. እግዚአብሔር ልኳናል፤ ማርያም ልካኛለች፤ ገብርኤልም እንዲህ ብሎኛል ብለው አያውቁም፡፡ ለካስ ይህም ደግ ነገር ኑሮ ደግ ጠንቋይ ጠፋ ማለት ነው፡፡ ግሩም!!

የድሮውም ጴንጤ ለየት ያለ ነበር፤ ማለት ይቻላል፡፡ ራሱ ያመነ ቀን ሌሎቹ ያላመኑ ስለሚመስለው ና ኢየሱስን ተቀበል ቢልም ጥላቸውን አውጥቶ በይፋ አይደነፋም ነበር፡፡ አሁን ግን በሚሊኒዬሙ እድሜያቸው ሲያሰሉት እንኳን በኢትዮጵያ በዓለምአቀፍ ደረጃም ከአባታቸው ከሉተር ጀምረው ሲቆጥሩት ግማሽ ሚሊኒዬም አልሞላላቸው ሲል ሦስት ሺሕ ዓመታት ሕዝብን በፍቅር ሀገርን በአንድነት አጽንታ የመጣችው ቤተ ክርስቲያን ላይ መዛት ምን ይሉታል፡፡ ለዚህ እንደማስረጃ ሰኔ ፪ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም በመስቀል አደባባይ ላይ ለጠሩት ኮንፈረንስ ያሠራጩትን በራሪ ወረቀት እንደማስረጃ መጥቀስ ይችላል፡፡ «ሦስት ሺሕ ዘመን ከፍ ብለው የነበሩ ተራሮች በሚሊኒዬሙ «በእግዚአብሔር ክብር ይደነግጣሉ»!!» ይላሉ፡፡ በዓሉን የሚጠቀሙት የሦስት ሺሕ ዓመት ታሪክ ለማፍረስ ነው ማለት ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ተራሮች የተባሉ እነማን እንደሆኑ እንኳን ሳያውቁ እንዲህ የሚያቃዡቸው ከቶ ምን ይሆን? ቤት የሌለው ቤት በመሥራት ቤት ካለው ጋር ለመስተካከል ማሰብ ሲገባው ቤት ያለውን ቤቱን በማፍረስ ለመስተካከል ማሰብንስ ምን ይሉታል? መስቀል አደባባይ ላይ የጸረ መስቀል ኮንፈረንስ ማካሔድ ሚሊኒዬሙን ለግጭት፣ ለጥፋትና ጥንታዊ ቅርስነቱንም ለማጥፋት ካልሆነ በቀር ለምን አገልግሎት ሊባል ይችላል? እንግዲህ የጴንጤም ደግ ኑሮት አሁን ጠፋ ማለት ነው ወይስ የሚሊኒዬሙ ጣጣ?

ከዚህ ሁሉ በላይ የሚያሳዝነው ደግሞ ምድራችን ጽዮንነቷን እንድታጣ እየተባበሩ ያሉት የውስጥ ጠላቶቻችን መሆናቸው ነው፡፡ ከንግሥት ሳባ ጀምሮ በኢትዮጵያ የተጠጉትን ታቦተ ጽዮንን፣ መጻሕፍተ ኦሪቱን፣ ከቁስጥንጥንያ፣ ከሶርያና ከአርመን ከመጡት ቅዱሳን ጋር የመጡትን ንዋያተ ቅድሳት እና ሌሎቹንም ቅርሶች ለማጥፋት የሚካሔደው ዘመቻ አሳዛኝ ነው፡፡ በኦሪቱም፣ በዘመነ ክርስትናውም፣ ካህናት፣ ሊቃውንት፣ ቅዱሳንና መጻሕፍቶቻቸው ሁሉ ከዓለም ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ተጠጉ፡፡ እንኳን እነርሱ መሐመድ እንኳ ሰላም ያለበትን ጥግ የምትሰጠውን ኢትዮጵያን ያውቃታልና ዘመዶቹን ወደ ኢትዮጵያ ላካቸው፡፡ ኢትዮጵያም አማናዊት ጽዮን መሆኗን እንኳን ቅዱሳኑን መሐመድንም በማስጠጋት አስመሰከረች፡፡

በዚህ ያልተደሰተው ሰይጣን ደግሞ ብስጭቱን ሁሉ የገለጸባቸውን መከራዎች አዘነበብን፡፡ ዮዲትን አስነሥቶ ለዐርባ ዐመታት ብዙዎችን ቅርሶች አወደመ፡፡ በተለይም ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን የነበረውን ተጽፎ በአክሱም የተቀመጠውን የኢትዮጵያ የታሪክ መረጃ ሳይመለስ አጠፋው፡፡ ይህም ከዚያ የተረፈው ቁርጥራጭ ታሪክ ትንሽ ተገኝቶ ሲነገር እንኳ ለዛሬ ሰዎች የፈጠራ ታሪክ እንዲመስላቸው አደረገ፡፡ በኋላም በግራኝ አሕመድ ታላቅ ውድመትን አስከተለ፡፡ እንግሊዞች በመቅደስ ብዙ መጻሕፍትን አስዘረፈን፡፡ ጣልያኖችም የሚቻላቸውን ሁሉ ዘረፉ፤ መውሰድ ያቃታቸውንም አቃጠሉ፡፡ የሚመጡት ተጓዦችና ጐብኝዎችም ሲችሉ በነጻ፣ ሳይችሉ በገንዘብ፣ ሲችሉ እየዘረፉ፣ ሳይችሉ እየገዙ ብዙ መጻሕፍትንና ቅርሶችን ወሰዱአቸው፡፡ ይህ ሁሉ ሲፈጸም ግን የኢትዮጵያ ሊቃውንትና አባቶች ዝም ብለው አልሰጧቸውም፡፡ ሕይወታቸውን እየገበሩ፣ መሥዋዕትነቱን ሳይሰቀቁ የሞት ጽዋ እየጨለጡ፣ ተሸክመው በረሐ ለበረሐ እየዞሩ፣ በዋሻ ወስጥ እየቀበሩ፣ ጊዜው የሚጠይቃቸውን ዋጋ ሁሉ ከከፈሉ በኋላ ሳይቻላቸው ሲቀር በቻ ነበር፡፡

አሁን ያለው ሁኔታ ግን ፍጹም ሌላ ነው፡፡ በግራኝ አሕመድ ወረራ ወቅት ካህናት፣ መምህራንና ሊቃውንት በብዛት ተጨፍጭፈው፣ በአንዳንድ ቦታዎች ፍጹም የታረዱበትም ጊዜ ስለነበር ቤተ ክርስቲያንን ለማስከፈት ሲባል በቂ ትምህርት ሳይማር የሚሰጠው የክህነት አሠጣጥ እስካሁን ስለዘለቀ ለቤተ ክርስቲያን ሀብት ግድ የለሽ የሆኑ እንክርዳዶችም እየበዙ መጡ፡፡ በዚህ ምክንያት አንዳንድ ቅርሶቻችን በራሳችን ሰዎች እየተሸጡ ወደ ውጭ ተሻገሩ፡፡ ከዚህም በላይ ለታቦቴ እሞታለሁ፤ ከደብሬ ጋር እቃጠላለሁ እያለ ማተቡን ብቻ ሳይሆን ቅርሱን ጠብቆ ከኖረው ኩሩ ኢትዮጵያዊ የተወለዱት ልጆችም በአባቶቻቸው መንገድ ላይ የቆሙ አይመስሉም፡፡ ግማሾቹ ተደራጅተው ይዘርፋሉ፡፡ ደካሞቹን የዕቃ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ቤት ጠባቂዎች እያሠሩ፣ ጠንካሮቹን እየገደሉ ቤተ መቅደሳችንን መዘበሯት። ነቢዩ ዳዊት «እንደላይኛው መግቢያ ውስጥ፣ በዱር እንዳሉም እንጨቶች በመጥረቢያ በሮችዋን ሰበሩ። እንዲሁ በመጥረቢያና በመዶሻ ሰበሩአት። መቅደስህን በእሳት አቃጠሉ፤ የስምህንም ማደሪያ በምድር ውስጥ አረከሱ» እንዳለው በእውነት ታቦቶቻችን የተደራጀ የኮማንዶ ኃይል እንዳለ በማያስጠረጥር ሁኔታ ተዘረፉ። መዝ. ፸፫፥ ፭-፯፡ በዚህም ኢትዮጵያዊ መልክን ለመቀየር ደከሙ።

እነዚህ ወገኖቻችን ያሰለፉብን ጠላቶቻችንም ከሦስት አቅጣጫ የመጡ ይመስላሉ። አንደኛዎቹ ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት መባሏ የማያምቸው ናቸው። አፍሪካዊቷ ጽዮን እያሉም ጥርሳቸውን ይነክሱብናል። እንኳን ጌጣችን ድሪቶአችንም ያበሳጫቸዋል። እነዚህ አካላት ታቦቶቻችን፣ መጻሕፍቶቻችን፣ ቅርሶቻችን በሙሉ ጠፍተው ሌሎች የግራ ጽሑፎች በዝተው በነ ነጃሺ የፈጠራ የዘር ሐረግ ቢተካ ደስ ይላቸዋል። ለዚህም ተኝተው አያድሩም። ሲቻል በግራኝ ሰይፍ ሳይቻል በነጃሺ ድርሳን ታቦታችንና መጻሕፍቶቻችን እስከ ማደሪያዎቻቸው ቢጠፉ ይደሰታሉ። ይህም ቤተ ክርስቲያን ሲሰራ ገንዘብ ያወጣ የነበረው በፍቅር አብሮ የኖረው ደግ እስላም እየጠፋ መሄዱን ቁልጭ አድርጐ ያሳያል።

ሁለተኛዎቹ ደግሞ ለክርስትናው የተቆጩ ለሀገር ያሰቡ መስለው የሚናገሩት ናቸው። በውጭ ሆነው ኢትዮጵያን ወደኋላ ያስቀራት ይህ ጐታች ባሕል ነው ይላሉ። በውስጥ በአሰማሯቸው አካላትም ደግሞ የኢትዮጵያ ክርስትና ኦሪታዊት ነው በማለት ባሕልና ቅርሳችን ለማጥፋት ገንዘባቸውን ሁሉ ያፈስሳሉ። ሦስተኛዎቹና የመጨረሻዎቹ ደግሞ ጽዮንን መልሰው ሦስተኛውን ቤተ መቅደስ በኢየሩሳሌም ማነጽ የሚፈልጉት አይሁድ ናቸው። እነርሱም ታቦተ ጽዮንን ለመውሰድ ባላቸው ኅልም ብዙ እንደሚሠሩ ይገመታል። እንዲያውም እንደ አንዳንድ አስተዋይ ምእመናን ግምት በጣና ቂርቆስና በአካባቢው፣ በአክሱምና በአካባቢው ልዩ ፍለጋ ይደረጋል። ከዚህም የተነሣ ታቦታት ይዘረፋሉ፤ ንዋያተ ቅድሳቱ ይጋዛሉ፡ ሌሎችም ሥራዎች ሊሠሩ ይችላሉ። ሁሉም በዚች ቤተ ክርስቲያን ላይ የጥፋት አዋጁን የመጣሁብሽ ነጋሪቱን ሲጐስም ደግ ነገር ከየት እንስማ ያሰኛል።

እነዚህ ሁሉ በአንድነት የሚሠሩት ሥራ ምድራችን ከጽዮንነት ሕዝቡንም ከበረከት የሚለዩ ይመስላሉ። ታቦታቱ፣ ንዋያቱ፣ መጻሕፍቱ ከተጋዙ፣ አብያተ ክርስቲያናት ከተቃጠሉ፣ ክርስቲያኖችን ከተሰደዱ፣ ምድሪቱ ጽዮንነቷ፣ ቤተ ክርቲያንም የኖኅ መርከብነቷ ወዴት አለ? የምታድነው ከጠፋች፣ መጠጊያቱስ ከተሰደደች የሁለት ሺሕ ዓመት በዓል ማክበሩ ወዴት ላይ ሆኖ ነው? ለዚህ በጣልያን ወረራ ጊዜ አለቃ አፈወርቅ ዘውዴ ዘቦረና የተቀኙትና በዚህ መጽሔት በውስጥ ጽሑፎች የተገለጸው ቅኔ ምስክር ስለሚሆን የመጨረሻውን ክፍል ብቻ እንመልከተው።

«ወእስከ ኢክህለት ትትከበት
ንዋየ ቅድስት ሀገር እንተ መልዕልተ ደብር ተሐንፀት፣
ወእምላዕል ዘይዘንም ወዘይነቅህ እምታሕት
ማየ አይኅ አማዕበለነ በመዓልት ወበሌሊት፣
ወእማየ አይኅ ንድኅነ ኢትጹረነ ታቦት
ታቦትነ አራራተ ለርእሳ ኢረከበት።

ትርጉም፡ «ከላይ /ከውጭ/ የሚዘንመው፣ ከታች /ከውስጥ/ የሚመነጨው መከራ በቀንም በሌሊትም በወረደብን ጊዜ በተራራ ላይ የታነጸችው /ንዋያተ ቅድስት ሀገር/ ንዋያተ ቤተ ክርስቲያን ልትደበቅ /ልትሸሸግ/ እስካልቻለች ድረስ /አልተቻላትምና/። ከመከራው /ከጥፋት ውኃ/ እንድን ዘንድ ታቦት መርከባችን እንዳትሸከመን ታቦታችን ለራሷ ማረፊያ አራራትን አላገኘችም፤

ብሎ እንደገለጸው በርግጥም በዚህ ዘመን የውጭ ጠላቶቻችን ከውስጥ ባንዳዎቻችን ጋር ቤተ ክርስቲያናችን ላይ በሚያደርሱት መከራ ታቦቶቻችንና ንዋያተ ቅድሳት ማረፊያ አጥተው እስከ መንከራተት ደርሰዋል ቢባል የሚጋነን አይሆንም። በዚህም ከደረሰብን ቅጣትና መሳለቂያነት አንጻር በቅዱሱ ቃል «አቤቱ አሕዛብ ወደርስትህ ገቡ፣ የቅድስናህንም መቅደስ አረከሰሱ... ለጐረቤቶቻችን ስድብ ሆንን፤ በዙሪያችንም ላሉ ሳቅና ዘበት። አቤቱ እስከ መቼ ለዘላለም ትቆጣለህ? ... የቀደመውን በደላችንን አታስብብን ምሕረትህ በቶሎ ታግኘን እጅግ ተቸግረናል» ማለት ይጠበቅብናል። መዝ ፸፰፥ ፩-፲፫።

ይህ ሁሉ ካልሆነ ግን ዝጉሃኑን እንደኤርምያስ፣ መሬታችንን እንደ ኢየሩሳሌም የምስጢር ሥራ እንዲሠሩለን መለመኑ ሳይበጀን አይቀርም። የሚታመን ትውልድ ሲጠፋና መዓትና መቅሰፍት ሲበዛ፣ ፍርሃትና ሐፍረት ሲረሳ ካለዚህ ምን ሊታሰብ ይችላል። እስራኤል በበደሉና ተነግረው አልሰማ ባሉ ጊዜ ነቢየ እግዚአብሔር ኤርምያስ ስለንዋያተ ቅድሳቱ «ተሠውረን ስለምናገለግልበት ንዋየ ቅድሳት ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ በላያቸውስ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ።» ብሎ ጠየቀ። ጌታ እነሱን ወስደህ በምድር በውኖች ላይ የፈጠረሽ በሰገነት ክፍልም የከፈለሽ የፈጣሪሽ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተሽ ጌታሽን ተቀበዪ፣ ዘሩባቤል እስኪመጣ ድረስ ገንዘብሽንም ጠብቂ በላት አለው» ተብሎ እንደተጻፈ ሰው በጠፋ ጊዜ ምድር አደራ ተቀብላ ተወጣች። አሁንም በእኛ ዘመን ሁሉንም ካጠፋነው ሀገራችንንና ቤተ ክርቲያናችንን በማራቆት ከክብር እያሣነሥናት እንደሆነ ለትውልዳችን ማስረዳት ያስፈልጋል። ሁላችንም ለወገኖቻችን ቅርሶቻችን በመዝረፍና በማሻገር ሀገራችንን ከጽዮንነት አናውጣት እንበላቸው። ሰውም ካልሠማ አባቶች ሆይ እንደ ነቢዩ እንደ ኤርምያስ አደራውን ለምድራችን ስጡልን። ምድር ሆይ አንቺም እንደ ኢየሩሳሌም እባክሽን ንዋያተ ቅድሳቶቻችንን ከባቢሎን ምርኮ /ከአሕዛብና ከመናፍቃ ምዝበራ ከይሁዳም ስርቆት/ ሰውሪልን እንበላት።

ከዚህ ሁሉ በላይ እያሳሰበን ያለው ግን ከሁሉም አቅጣጫ የሚጐስመው የማንአለብኝነት ነጋሪት የመቻቻልንና አብሮ የመኖሩን ባሕል እየሸረሸረውና ትርጉም እያሳጣው መሔዱ ነው። በተለይ በአሁኑ ሰዓት ከላይ ቀደም ብለን ከጠቀስናቸው አካላት በመጀመሪያዎቹ በሁለቱ እየተፈጸመ ያለው ጉዳይ አስቸኳይ መፍትሔ የሚያሻው ነው። መስቀል አደባባይ ለጸረ መስቀል ኮንፈረንስ የሚፈለግበት ምክንያት መቻቻልን ለማጥፋት ካልሆነ ለምን ሊሆን ይችላል? ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ሆን ብሎ ሐዶ መጮኽና መረበሽስ ምን ዓይነት ነገር መሻት ነው? እነዚህንና ሌሎቹንም ሁኔታዎች ስናያቸው የሁለት ሺሕ ዓመቱ መጨረሻ የመቻቻልና አብሮ በሰላም የመኖር ባሕል መጨረሻም እንዳይሆን ያሰጋል። ለዚህ ደግሞ ሓላፊነት የሁሉም አካላት እንጂ የመንግሥት ብቻ ወይም የእምነት ተቋማቱ ብቻ አይመስልም። ለዚህ የሚያስፈልገውን ሁሉ በማድረግ የሁለተኛው ሺሕ ዓመት ፍጻሜ ችኩልነት፣ ጠብ አጫሪነት፣ እና ጸብና ግጭት የሚዘጉበት እንጂ መቻቻልና ተማምኖና ተከባብሮ መኖር የሚፈጸሙበት እንዳይሆን ሁሉም ወገን ሓላፊነቱን ሊወጣ ይገባዋል እንላለን።♦

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## ግዴታችንን እንወጣ

ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ለኢየሩሳሌም ሰላምን ለምኑ ያለው ለአማናዊቷ ጽዮን ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ነው። በአሁኑ ወቅት ቤተ ክርስቲያናችን በትልቅ ፈተና ውስጥ ገብታ እየታወከች ነው። በታሪክም ለመጀመሪያ ጊዜ በአባቶቻችን ጳጳሳት መካከል በተፈጠረው ያለ መግባባት በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ችግር ተፈጥሯል። ሕዝበ ክርስቲያኑ ተሰብስቦ ስለ ኢየሩሳሌም፣ ስለ ቤተ ክርስቲያናችን መጸለይና መለመን አለበት። መናፍቃን ይህን ክፍተት ተመልክተው ቀስታቸውን ወደ አማናዊት ቤተ ክርስቲያን እንዳይወረውሩ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። «ስለ እርስዋም ወደ እግዚአብሔር ጸልዩ» ኤር.፳፱፥፯-፰ እንደተባለ፣ በጾም በጸሎት ተወስነን ለሀገራችን፣ ለቤተ ክርስቲያናችን ሰላምን፣ ለሕዝባችን ፍቅር አንድነትን በመለመን ክርስቲያናዊ ግዴታችንን ልንወጣ ይገባናል።

*ደስታ በርኽ*
*ምክሃ ደናግል ተክለ ሃይማኖት*
*ሰንበት ት/ቤት*
*አዲስ አበባ*

## በሁሉም ቤተ ክርስቲያን ቢለመድ

በቤንች ማጂ ሀገረ ስብከት ከሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት የሸኮ ደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አንዱ ነው። ሐመር፣ ስምዐ ጽድቅ፣ መለከት እንዲሁም ሌሎች የቤተ ክርስቲያናችንን መጻሕፍት በማሰባሰብ ቤተ መጻሕፍት በመክፈት ለምእመናን አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። ቤተ መጻሕፍቱ ዘወትር ክፍት ነው። መጻሕፍቱ የተሰበሰቡት ከበጎ አድራጊዎች ምእመናንና ከማኅበረ ቅዱሳን ነው። ይህ መልካም አርአያነት ያለው በመሆኑ በሌሎችም የከተማ አብያተ ክርስቲያናት ቢለመድ መልካም ነው እንላለን።

*መ/ር እሸቱ ተክሌ እና*
*መ/ር አበራ ጉልማ*
*ከሸኮ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት*

## መድኀኒተ ሥጋ ወነፍስ

በጥር/የካቲት ፲፱፻፺ ዓ.ም ፲፫ኛ ዓመት ቁጥር ፩ እትም «በውኑ ዓለም ሳይፈጠር እመቤታችን አትታወቅምን?» በሚል ርእስ በትምህርተ ሃይማኖት ዐምድ የቀረበውን ጽሑፍ አንብቤዋለሁ። የብዙ ሰዎች ጥያቄ ትክክለኛ አቅጣጫና መልስ አግኝቷል። የአርዮስ ወገኖችንም አንገት የሚያስደፋ ጽሑፍ ሆኖ በማግኘቴ በጣም ተደስቻለሁ። «ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም መድኃኒትነት እና እኳን በእርሷ ይቅርና በጻድቃን በሰማዕታትም ልመና የለባቸውም» የሚሉትን ዝርዝር ነገሮችም በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረትነት በተገቢ ሁኔታ ተብራርቷል። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም መድኃኒተ ሥጋ ወነፍስ ትሁነን።

*ዲ/ን ተመስገን ዘገየ*
*ከምዕራብ እስቴ ግ/ገ/ል/ጽ/ቤት*
*አንዳቤት*

## ቀጣዩ ትውልድ እንዳይመክን

በጥር/የካቲት ፲፱፻፺ ዓ.ም እትም በወቅታዊ ጉዳዮች ዓምድ እንግዳ ሆነው የቀረቡትን የዶ/ር አየለ በከሪን ቃለ ምልልስ በጥሞና አንብቤ፣ ዶክተሩን ይበል እግዚአብሔር ያበርታዎ ብያለሁ። በተለይም ኢትዮጵያን ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ልዩ ከሚያደርጓት አንዱ የፊደል ጉዳይ ሲነሣ ነገሩ ውስጤን ይቆጨው ነበር። ዶ/ር እንዳሉት እያንዳንዱ ፊደል ያዘለችው ታሪክ፣ የያዘችው ጥበብ፣ ያቀፈችው ትውፊት አለ። በመሆኑም እነዚህ በፊደል ቀናሾቹ ጥቅም አልባ ተደርገው የሚታሰቡት ፊደላት የየራሳቸው የሆነ የት መጣና ፍቺ አላቸው ማለት ነው። እስከ አሁን ባለው ሁኔታ እንደሚታወቀውና ዶክተሩም እንዳሉት የኢትዮጵያ ታሪክ ከሚታወቀው የማይታወቀው ይሰፋል። ስለዚህ ከራሳችን አኳያ የጻፉልንን ወይም የጻፉብንን፣ እኛ ተቀብለን የወኔ መካኖች እንዳንሆን፣ ቀጣዩ ትውልድም እንዳይመክን ይልቁንም በወኔ ተዘርቶ በድል እንዲያብብና እንዲያፈራ የራሳችን ትክክለኛ ታሪክ ከራሳችን ቀዳማይ ምንጮች ቀድተን ልናጠጣው ይገባናል። እናም ፊደል ቀናሾቹ ለዘንለፈ ሥርየት ማስተካከያ ያዘጋጁ። ወለዘይመጽእ እቅበት ደግሞ የፊደላቱን ዋጋ እያወቁ ያደረጉት ከሆነ ስንፍናቸውን ወዲያ ይጣሉና ለዘላቂ ኢትዮጵያዊነት ብሩህ ትርጉም ይጣሩ።

*ዲ/ን መሐሪ ዘመልአክ ወርቁ*
*ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ*
*የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል*

## መፍትሔ ይፈለግበት

በሐመር ፲፫ኛ ዓመት ቁጥር ፩ በማኅበሩ መልእክት «ለዘንለፈ ሥርየት ወለዘይመጽእ እቅበት» በሚል ርእስ የተጻፈው ጽሑፍ፣ ላስተዋለው ሰው ትልቅ መልእክት አለው። አባቶቻችን መለያየትን አርቀው፣ አንድ ሆነው ቤተ ክርስቲያንን ሊያገለግሉ መንጋውን ሊጠብቁ ይገባል። በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ያሉት አባቶች ተገናኝተው ዕርቅን አንድነትን መመስረት አለባቸው። አለበለዚያ እኛ ልጆቻቸው ከእነርሱ ምን ልንማር ነው? ለዚህ ለተፈጠረው ችግር ጊዜ ሳይሰጡት መፍትሔ በመሻት ልጆቻቸውን ሊያስደስቱን፣ አጽራረ ቤተ ክርስቲያንን ደግሞ ሊያሳፍሩልን ይገባል።

*አዳነች አብዲ*
*ከተሰፋ ስዱዳን ሰ/ት/ቤት*
*አቡዳቢ*

## አርኪ ምላሽ

በተከታታይ በሐመር መጽሔት «የዳቪንቺ ኮድ» ልቦለድ መጽሐፍ በመንፈሳዊ ዓይን ሲገመገም፣» በሚል ርእስ በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ምላሽ ሲሰጥበት ቆይቷል። የተሰጠው ምላሽ በእጅጉ አርክቶኛል። የዘመኑ ትውልድ በዚህ ዓይነት አስጸያፊ የክህደት ትምህርት በያዘ መጽሐፍ ተስበው እንዳይሳሳቱ ግልጽ በሆነ መልኩ አርኪ ምላሽ ሰተተውበታል።ለወደፊቱም ትውልዱ ከእንደዚህ ዓይነት ከክህደት ትምህርቶች ራሱን እንዲጠብቅ፣ የሚያነባቸውንም መጻሕፍት እንዲያውቅ በቀጣይም ጠለቅ ያለ ትንታኔ በቤተ ክርስቲያን አባቶች ሊሰጥበት ይገባል።

*ዝማሽኝ ታደሰ*
*ወልቂጤ*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## መንጋውን ከኑፋቄ እንጠብቅ

«በውኑ እመቤታችን ዓለም ሳይፈጠር አትታወቅምን?» በሚል ርእስ በተከታታይ እየተጻፈ ያለው ጽሑፍ ለብዙዎች ትምህርት የሚሰጥ መናፍቃንንም አንገት ያስደፋ ነው:: የመናፍቃን ዘመቻ ከቀድሞ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያንን መፈታተኑ የማይታበል ሀቅ ነው፡ በመጽሐፍ ቅዱስም ስለእነርሱ ተነግሯል:: ሆኖም በእኛ አካባቢ በአሁኑ ወቅት ጠባያቸውን በመቀየር አንድነት ለመፍጠር «ብርሃነ ሕይወት» በሚል ስያሜ ጉባኤ በማካሔድ በየመንገዱ፣ የግለሰቦችን ቤት ሳይቀር በመቆርቆር ክሕደታቸውን እየነዙ ነው:: በይበልጥ ደግሞ በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ተስበው የአደጉበትን ማዕድ ረግጠው ከተዋሕዶ ጉያ ወጥተው የሔዱ የእናት ጡት ነካሾች በአሁኑ ወቅት በተአምረ ማርያምና በሌሎች አዋልድ መጻሕፍት የሚጽፏቸው የሐሰት ጽሑፎች በሃይማኖት ትምህርት ላልገፋ ያስበረግጋል:: ማኅበረ ቅዱሳንም በሚዲያዎቹ የመናፍቃንን ሤራ እየተከታተለ በማውጣት ምእመናንን ከተኩላ ለመጠበቅ የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ ነው:: ወደፊትም በዚሁ መቀጠል አለበት:: የመናፍቃንንም ብቻ ሳይሆን የሌሎችንም ተቃራኒ እምነቶች ባህርይ በየጊዜው በማጥናት ምእመኑን /መንጋውን/ ከኑፋቄ /የሐሰት ትምህርት/ መጠበቅ ይገባናል::✦

*ዲ/ን አሊየስ ዘራማ*
*ሰሜን ወሎ*

## አሁንም አንድ እንድንሆን

በሐመር መጽሔት ፲፫ኛ ዓመት ጥር/የካቲት ፲፱፻፺፱ ዓ.ም እትም «አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው» በሚል ርእስ በወቅታዊ ጉዳዮች ዓምድ ላይ የቀረበው ጽሑፍ በጣም የሚያስደስት ነው:: ቤተ ክርስቲያን በሚሊኒየም ዋዜማ ያጋጠማትን ፈተና ካለፈው የአብያተ ክርስቲያናት ታሪክ ጋር በማነጻጸር እንድናስታውስ ግድ ይለናል:: አሁን የተከሰተውን የመከፋፈልና የመወጋገዝ አደጋውን የሚያሳየን መስታወት ነው:: አሁንም አንድ እንድንሆን የቸርነት ባለቤት በስሙ እንዲጠብቀን ሁላችንም በጸሎታችን ልናሳስብ ይገባናል::✦

*ዝናቡ ሞላ*
*ማይጨው*

## ዝምታው አያዋጣም

ይህችን ደብዳቤ ለመጻፍ ያንሳሳኝ ምን መሰላችሁ:- ለራሳቸው ጥፋት መጻሕፍትን እንደገዛ ፈቃዳቸው ያጣምማሉ እንደተባለ፤ የሐሳዊው መሲሕ መንገድ ጠራጊዎች፤ አሁን ደግሞ ዓይናቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያናችን ገድላትና ተአምራት አዙረዋል:: ሐሳባቸው ምድራዊ የሆነ እነዚህ ሰዎች በቅዱሳን አበው የተደረጉትን ተአምራት በምድራዊ ጥበብ በመገምገምና በማጥላላት፤ ሲያስፈልጋቸውም ቅዱሳኑን ከእብድ ጋር በማነጻጸር ምእመናን ለቅዱሳን ያላቸውን ፍቅርና አክብሮት ጥላሸት ለመቀባት ዘምተዋል:: ለመሆኑ የሃይማኖት ነጻነት እስከምን ድረስ ነው? ለእነዚህ ሰዎችስ የእነርሱ ባልሆኑ የገድላትና የተአምራት መጻሕፍት ላይ እስከዚህ ድረስ ነጻነት የሰጣቸው ማነው? ዛሬ ጓዳችን ገብተው ቤታችንን ሲያንጐዳጉዱ ዝም ብለን ተመለከትን ነገስ...? ዝምታው አያዋጣም አንድ ነገር ቢደረግ መልካም ነው::✦

*ጌታቸው ሞገስ*
*መቀሌ ዩኒቨርስቲ*

## በመጽሐፍ ቢታተም

በሐመር መጽሔት ለአራት ተከታታይ እትም በፍሬምናጦስና በቀሲስ ስሎሞን ሙሉጌታ የዲቪንቺ ኮድን አስመልክቶ የቀረበው ጽሑፍ ምእመናንን ከክህደትና ከጥርጣሬ የታደገ ነው:: አባቶቻችን በየወቅቱ ለሚነሱ ክህደያን ተገቢውን መልስ በመስጠት አልፈዋል:: ዛሬም የቤተ ክርስቲያን ልጆች በዘመናችን ለተነሱ ለእነዚህ የክህደት ትምህርቶች ተገቢውን መልስ እየሰጡ በመሆናቸው በእውነቱ «በአባቶችሽ ፈንታ ልጆች ተወለዱልሽ» መዝ. ፵፬፥፲፮ የሚያሰኝ ነው:: አዘጋጆች ምስጋና ይድረሳቸው:: ይህ ጽሑፍ በአንድ ላይ ተሰባስቦ ብዙ መረጃዎች ታክለውበት በመጽሐፍ መልክ ቢታተም ብዙ ሰዎች ይማሩበታል::✦

*ሰሎሞን ጌታቸው*
*ከምሥራቅ ጎጃም*

## አርአያ ሆነውናል

የዘወትር የሐመርና የስምዐ ጽድቅ ተከታታይ ነኝ:: በጥር/የካቲት ፲፱፻፺፱ ዓ.ም እትም በሐመረ ሕይወት ዓምድ ላይ ያስፈራችሁት ጽሑፍ በእውነቱ በጣም ደስ ይላል:: በተረጂዎች «የምወድሽ» ተብለው የሚጠሩት ወ/ሮ አስገደች ለእኛ አርአያ ሆነውናል:: ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን በእውነት እያገለገሉ ያሉ ናቸው:: እግዚአብሔር አምላክ ቀሪውን የዕድሜ ዘመናቸውን ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ያርዝምልን:: እኛም የእርሳቸውን አርአያ ተከትለን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የምትጠብቅብንን ለማሟላት በርትተን እንነሣ::✦

*ዲ/ን ድረስ ረታ*
*ከናዝሬት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን*

## የሀገሪቱ ፓለቲካ በቤተ ክርስቲያን እንዳይደገም

ከጥቂት ወራት በፊት በአማርኛው የአሜሪካ ድምፅ «ፓትርያርኮች ተወጋገዙ» በቅርብ ቀን በጀርመን ሬዲዮ ደግሞ የለንደኑ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ሲኖዶስ አይታዘዝም የሚል ዘገባ ቀርቦ ነበር:: በጣም አዘንኩ:: በሐመር ፲፫ኛ ዓመት ቁጥር ፩ በማኅበሩ መልእክት ሥር ሰፋ ባለ ሁኔታ መፍትሔውንም በመጠቆም ያቀረባችሁት ነገሩን በሚገባ እንድንገነዘብ አድርጉናል:: የእኛ አባቶች አንድ ነገር መገንዘብ አለባቸው፡ ሥልጣንን ሳይሆን በምእመኑ ላይ እየተፈጸመብን ያለውን ፍጅት፣ ጉርፋን፣ ረሐቡን፣ ሽብሩን የተኩላዎች ወረራ ወዘተ ነው ሊያሳስባቸው የሚገባው:: እነዚህ ችግሮች የተፈ ራረቁብን በመካከላችን ፍቅር በመታጣቱ፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር በመራቁ ይመስለኛል:: አባቶች ተቻችለው፣ በፍቅር አንድ ሆነው ምእመኑን በተስፋ መንግሥቱን እንዲጠብቅ ማድረግ ሲገባቸው፡ ለሚያልፍ ነገር /ሥልጣን/ መወቃቀስ ምእመኑን ማስጨነቅ ምን ይባላል? በተለይም «በጉቼን ጠብቅ፡ ጠቦቶቼን አስማራ ....» የተባሉ አባቶቻችን በውግዘት መከፋፈልን ከሚያስነሣሩን ተስማምተው ለንስሐ ይጥሩን:: በሀገሪቱ ያለው የፓለቲካ አለመግባባት በቅድስት ቤተ ክርስቲያን መደገም የለበትም::

*ገብረ ሰንበት ወ/ጻድቅ*
*ባሕርዳር ዩኒቨርስቲ*

ከዚህ በታች ስማችሁ የተዘረዘረው አንባብያን ደብዳቤዎቻችሁ ደርሰውናል:: እናመሰግናለን:: መልእክቶቻችሁንና የጥቆማ ሐሳቦቻችሁን ወደፊት እንደ አስፈላጊነታቸው እንጠቀምባቸዋለን:: በተሳትፎአችሁ ቀጥሉበት::

ብዙአየሁ ንጉሤ- አዲስ አበባ፣ በላይ ተክሌ - ቤንች ማጂ ዞን፣ በላይ ዘነበ - ፍቼ፡ አቶ ስዩም ኃይየርጊስ - ደብረ ብርሃን፣ ብርሃኑ ታደሰ - ከሣቢልቻ፣ ሮማን አክሊሉ - ቆጵሮስ፣ ሕይወት ዓለማየሁ - ደሴ፣ አበበ ጥላሁን - አዲስ አበባ፣ ገብረ ማርያም - አምቦ፣ እሸቱ ጽጌ - ወልዲያ፣ ትዕግስት ታደሰ - ነቀምት፤ ሚሊዮን ታደሰ - ቦንጋ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# «መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው»

## የሐዋ. ፪ ፥ ፬

ዲ/ን ያረጋል አበጋዝ

እስራኤላውያን በኦሪቱ ሕግ እንዲያከብሩዋቸው የታዘዙ ሦስት ዋና ዋና በዓላት ነበሩ፡፡ እነዚህም የፋሲካ (የቂጣ) በዓል፣ የዳስ በዓልና የእሸት (የበኩራት) በዓል ነበሩ፡፡ እነዚህን በዓላት አይሁድ ከየተበታተኑበት አገር ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው ያከብሩዋቸው ነበር፡፡ በእነዚህ የኦሪት በዓላት በእያንዳንዳቸው የወንጌል (የክርስትና) በዓላት ተተክተውባቸዋል፡፡ በፋሲካ ዕለት አማናዊው ፋሲካችን ክርስቶስ ስለ እኛ ታርዶ ምሳሌውን በእውነተኛው፣ ጊዜያዊውን በዘለዓለማዊው ተክቶታል፡፡ ‹ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአልና› እንዳለ፡፡ ፩ቆሮ. ፭፥፯፡፡ እንዲሁም ከፋሲካ በዓል ቀጥሎ በሃምሳኛው ቀን ይከበር የነበረውን በዓል ምሳሌውን በአማናዊው ተክቶታል፡፡

ይህ በዓል በዕብራይስጥ «ሻቡት» ይባላል፡፡ "ጰንጠቆስጤ" የሚለው ቃል የግሪክ ቃል ሲሆን ሃምሳኛ (ቀን) ማለት ነው፡፡ ከቂጣ በዓል በኋላ ካለው ቅዳሜ (ሰንበተ አይሁድ) ቀጥሎ ባለው ቀን (እሑድ) ከአዝመራው ካህኑ ትንሽ ነዶ ያጭድ ነበር፡፡ ይህ የታጨደ ነዶ ‹የሚወዘወዝ ነዶ› ይባል ነበር፡፡ ዘሌ.፳፫፥፲-፲፭፡፡ ይህም ነዶ በእግዚአብሔር ፊት በመቅደሱ ይወዘወዝ ነበር፡፡ «የእናተን መከር በኩራት ነዶ ወደ ካህኑ አምጡ፤ እሱም ነዶውን በእግዚአብሔር ፊት እንዲሠምርላችሁ ይወዝውዘው፤ በማግሥቱ ከሰንበት በኋላ ይወዝውዘው፡፡» ዘሌ.፳፫፥፲-፲፩፡፡ ይህ የመኸር ነዶ መታጨድና በእግዚአብሔር ፊት መወዝወዝ ከዚያ በኋላ የደረሰው አዝመራ ሊታጨድ የሚችል መሆኑን አመልካች ነበር፡፡ አዝመራቸውን ለማጨድና ለመክተት ቀድሞ የደረሰውን የእህል በኩራት በእግዚአብሔር በማስባረክ ለቀጣዩ የአዝመራ መክተት ሥራ ፈቃድና ይሁንታ ማግኘታቸውን አመልካች ነበር፡፡

ከዚህ የሳምንቱ መጀመሪያ ከሆነው ከዚህ «የነዶ መወዝወዝ ቀን» ጀምሮ ሰባ ሳምንታትን ይቆጥሩ ነበር፡፡ ከሰባተኛው ሳምንት ቀጥሎ ያለው ቀን (አሁንም ይህም የሳምንቱ መጀመሪያ ቀን ማለትም እሑድ ነው) ታላቅ በዓል ሆኖ ይከበራል፡፡ ይህም በዓል «የሰባቱ ሱባኤ በዓል»፣ «የእሸት በዓል»፣ ‹የበኩራት በዓል› በሚሉ የተለያዩ ስያሜዎች ይጠራ ነበር፡፡ ዘዳ.፲፮፥፲፮፡፡ ነዶው በቤተ መቅደስ ከሚወዘወዝበት ቀን ጀምሮ እስከዚህ በዓል ድረስ ያለው ጊዜ ሃምሳ ቀናት በመሆኑ (ዘሌ.፳፫፥፲፭-፲፮) በሐዲስ ኪዳን ዘመን የሃምሳኛ ቀን በዓል፣ በግሪክ ቋንቋ በዓለ ጰንጠቆስጤ (በዓለ ሃምሳ) ተባለ፡፡

በኦሪቱ አይሁድ በዚህ በዓል ዕለት አዝመራቸውን ማጨድ (መሰብሰብ) የሚጀምሩበት ጊዜ ነበር፡፡ ይህ ምሳሌ ነበር፡፡ ከፋሲካ በዓል ባለው ሁለተኛ በሆነው ቀን፣ በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን (እሑድ) ታጭዶ በእግዚአብሔር ፊት ቀርቦ የሚወዘወዘው በኩራት ነዶ የክርስቶስ ምሳሌ ነበር፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ ሞትን በፈቃዱ ከተቀበለ በኋላ በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን (እሑድ) በመነሣት ስለ ሰው ልጅ ሁሉ በኩራት ሆኖ ራሱን ለአባቱ አቅርቧልና፡፡ (ዮሐ.፳፥፩-፲፰፤ ማቴ.፳፰፥፱)፡፡ ከመቃብር ለሚነሣው የሰው ልጅ ሁሉ እርሱ የትንሣኤ በኩር ሆነ፡፡ የሚወዘወዘው ነዶ ከሞት ወደ ሕይወት፣ ከመፍረስና መበስበስ ወደ አለመፍረስና አለመበስበስ ለሚሸጋገሩት የሰው ልጆች ሁሉ መጀመሪያ ሆኖ መፍረስንና መበስበስን፣ የመቃብርን ይዞ የማስቀረት ኃይልና የሞትን መውጊያ ኃጢአትን ድል አድርጎ ከሞት የተነሣውና ስለ እኛ በኩር (የመጀመሪያ፣ ጀማሪ፣ አንድን ነገር ጀምሮ፣ ሠርቶ የሚያሳይ) ሆነ፡፡ ቅዱስ ጳዉሎስ «አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቷል ... ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል፤ ክርስቶስ እንደ በኩራት ነው» በማለት የገለጸው ይህንን ነው፡፡ ፩ቆሮ.፲፭፥፳፤፳፫፡፡

ያን ጊዜ ከበዓለ ሃምሳ በኋላ የደረሰውን አዝመራቸውን እንደሚያጭዱ ሁሉ አሁን ደግሞ የአዝመራ ማጨጃ የሆነው ቅዱስ ቃሉ አዝመራ በሆነው ዓለም ላይ ተዘጋጅቷል፡፡ እንደ ስለታም ማጭድ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት ተሰጥቷልና፡፡ «የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፣ የሚሠራም፣ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነውና...» ዕብ.፬፥፲፪፡፡ መድኃኒታችን ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን አስቀድሞ እንዲህ ብሏቸው ነበርና፡- «እነሆ እላችኋለሁ፣ ዓይናችሁን አንሡ፣ አዝመራውም እንደ ደረሰ ተመልከቱ» ዮሐ.፬፥፴፭፡፡ እንዲሁም አዝመራው ይህ ዓለም (ማለትም ሰዎች)፣ አጫጆቹና ሰብሳቢዎቹ (ሠራተኞቹ) ደግሞ ሐዋርያት መሆናቸውን ሲናገር «በዚያን ቀን ደቀ መዛሙርቱ፡- መከሩስ ብዙ ነው፣ ሠራተኞቹ ግን ጥቂቶች ናቸው› ብሏል፡፡ ማቴ.፱፥፴፯፡፡ እንዲሁም «እኔም እናንተ ያልደከማችሁበትን ታጭዱ ዘንድ ሰደድኳችሁ» በማለት ሐዋርያት የወንጌልን አዝመራ የሚያጭዱ ሠራተኞች መሆናቸውን ተናግሯል፡፡ የሚታጨደው አዝመራ ንስሐ እየገቡ የሚጠመቁና የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ እተቀበሉ ወደ ዘለዓለማዊ መንግሥቱ የሚጠሩት የሰዎች መንፈሳዊ አዝመራ አመላካች (ተምሳሌት) ነበር፡፡

ከአዝመራው መጀመሪያ የደረሰው በእግዚአብሔር ፊት እንደሚቀርበው በኩራት (የሚወዘወዝ ነዶ) እርሱ ራሱ የእኛን ባሕርይ ተዋሕዶ በዕርገት ወስዶ በፊቱ በመንበሩ ላይ አስቀመጠው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ «ለፍጥረቱ በኩራት እንድንሆን በእውነት ቃል አስቦ ወለደን» በማለት የገለጸው ይህንን ምሥጢር ነው፡፡ ያዕ.፩፥፲፰፡፡ ባሕርያችንን በኩራት አድርጎ በእግዚአብሔር ፊት አቀረበው፡፡ በክርስቶስ ከሙታን በኩራት የሆነው የእኛ ባሕርይ ስለ ሰው ልጆች በአጠቃላይ የመጀመሪያ በኩር ሆኖ በእግዚአብሔር ፊት ይቀርብ ዘንድ ጌታችን በተነሣ በዐርባኛው ቀን ዐረገ፡፡ ከዚያም በዐረገ በዐሥረኛው ቀን፣ በተነሣ ደግሞ በሃምሳኛው ቀን መንፈስ ቅዱስን ላከ፡፡

ቅዱስ ሉቃስ በጻፈው የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በዚህ በዓል ዕለት የተደገረውን በተመለከተ እንዲህ ይላል፡- «በዓለ ሃምሳ የተባለው ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ በድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፣ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው፡፡ እንደ እሳት የተከፋፈሉ ልሳናት ታዩአቸው፤ በእያዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው፡፡ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው...»

**አንዱ በሌላው ላይ ለመሠልጠን ሳይሆን አንዱ ለሌላው ለመታዘዝና ሌላውን ለማገልገል የሚሽቀዳደሙ ሆኑ፡፡ ዓላማቸው ሁሉ የክርስቶስ ክብር፣ የሰዎች ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ብቻ ሆነ፡፡ የሚያስጨንቃቸው በዚህ ዓለም እንዴት ሀብት ንብረት እንደሚያገኙና እንደሚሾሙ ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን ነገር ብቻ ሆነ፡፡**



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ እንደሚልክላቸው አስቀድሞ ተስፋ የሰጣቸውን መንፈስ ቅዱስን የላከላቸው አይሁድ የአራቱን በዓላቸውን ለማክበር ተሰብስበው በነበረበት ዕለት ነው። ይህን ያደረገው በምሳሌ ይደረግ የነበረውን በእውነተኛው፣ ጥላውን በአካሉ ለመተካት ነው። እንዲሁም ጌታችን በፋሲካቸው በዓል ቀን በመሰቀሉ ከየአገሩ የተሰባሰቡት አይሁድ ስቀለቱንና ሞቱን እንዳዩና ለሞቱ ምስክር እንደሆኑ ሁሉ በመስቀል ላይ ለመሞቱ ምስክር የሆኑ እነዚያው ሰዎች ይህንን የእግዚአብሔርን ሥራ እንዲያዩና እንዲረዱ ለማድረግ ነው።

«ድንገትም እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ።» ለምን እንዲሁ በጸጥታ ሳሉ አላደረገውም? ይህን ያደረገው ስለማያምኑት ሰዎች ነው። እንዲህ የሚታይ ምልክት ተደርጎ እንኳ «አዲስ የወይን ጠጅ ጠጥተው ሰክረዋል» ካሉ እንዲህ ባይሆን ኖሮ ምን ባሉ ነበር? ይህ እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ባለ ሁኔታ መገለጹ የመንፈስ ቅዱስን ከሃሊነትና ኃያልነት የሚያሳይ ነው። ይህም «ተቀምጠው የነበሩበትን ቤት ሞላው።» በቤቱ ውስጥ የነበሩት ሁሉም ያመኑ ስለነበሩ ለጸጋው የተዘጋጁና የተገባቸው ሆነው በመገኘታቸው ነው።

ከዚህም ጋር እንደ እሳት የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው። በቁሙ እሳት ሳይሆን «እንደ እሳት» ነው ያለው። ነፋስ ሳይሆን «እንደ ዓውሎ ነፋስ» ሆኖ ከሰማይ እንደመጣ፣ እሳቱም እንዲሁ በቁሙ እሳት ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ የተገለጠበት ነው። መንፈስ ቅዱስ በጌታችን ጥምቀት ጊዜ በርግብ አምሳል እንደታየ አሁን ዓለሙ ሁሉ ሊለወጥ ባለበት ዕለት ዋዜማ (በአገዛሩ መክተቻው ዋዜማ) ደግሞ በአምሳለ እሳት ታየ። በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጠባቸው። ይህም ማለት በእነርሱ ኀደረ ላይለያቸው ቤቱ፣ ማደሪያው አደረጋቸው ማለት ነው። ተቀመጠባቸው የሚለው ማደርንና ከዚያው ሳይለዩ መቀጠልን (አለመለየትን) ያሳያልና። ከዚያም በሁሉም ላይ መንፈስ ቅዱስ አደረባቸው።

ደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን በመቀበላቸው ምን አገኙ? ያደረባቸው መንፈስ ቅዱስስ በእነርሱ ላይ በምን ተገለጠ? በሕይወታቸውስ ላይ ምን ለውጥ ታየባቸው?

## ኃይልን፣ ብርታትን፣ ቆራጥነትንና ጽናትን አገኙ

መንፈስ ቅዱስ ኃይልን ባይሰጣቸው ኖሮ መከራውን ሁሉ ሊሸከሙትና ሊጸኑ አይችሉም ነበር። በጸሎተ ሐሙስ ማታ ጌታችን በፍጹም ፈቃዱ በአይሁድ እጅ በተያዘ ጊዜ ከዮሐንስና ከጴጥሮስ በስተቀር ሁሉም ፈርተው ተበታትነው ነበር። «አልክድህም፣ ከአንተ ጋር እሞታለሁ» ሲል የነበረው ጴጥሮስም በአንድ ምሽት ውስጥ ሦስት ጊዜ ክዷል። ኋላ ቢሰባሰቡም ገና አይሁድን ይፈሩ ስለነበር ደጆችን ዘግተው ነበር የሚቀመጡት። ዮሐ.፳፥፲፱። ጌታችን የመነሣቱን ዜና መልአኩ ሲነግራቸውና ወጥተው ለደቀ መዛሙርቱ «ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል፤ እንደ ነገራችሁ በዚያ ታዩታላችሁ» ብላችሁ ንገሯቸው ሲላቸው እነርሱ ግን «መፍራትና መደንገጥ ይዞአቸው ነበርና ወጥተው ከመቃብሩ ሸሹ፣ ይፈሩ ነበርና ለማንም አንዳች አልተናገሩም።» ማር.፲፮፥፮-፰። ለዚህ ነበር ጌታችን «እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ» ያላቸው። ሉቃ.፳፬፥፵፱። ወደ አባቱ ሲያርግም «መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ» በማለት ተስፋውን አጽናናቸው። የሐዋ.፩፥፰። ያለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል ፈሪዎችና ድንጉጾች ነበሩና።

ተስፋ አድርጎ የተናገረውን ከመፈጸም ወደ ኋላ የማይል እግዚአብሔር በተስፋው መሠረት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ግን የሚያሸንፈው የሌለ ኃይልን፣ ምንም ነገር የማያሸብረው ጽናትንና የማይዝል ብርታትን አግኝተዋል። በገገርዎችና በነገሥታት ፊት እንኳ የማይፈሩ ሆነዋል። እንዲያውም ወንጌልን ማስተማራቸው ወንጀል ተደርጎ ወደ ሹማምንትና ገዢዎች ፊት መወሰዳቸውና ለፍርድ መቅረባቸው በሌላ መንገድ አይደርሱባቸውና አያገኟቸው ለነበሩት ለእነዚህ ወገኖች የክርስቶስን የመዳን ጥሪ የሚያደርሱበት ልዩ ዕድል ሰጣቸው። እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸው አንድ መንገድ ሆኖ አገኙት። ለምሳሌም ቅዱስ ጳውሎስ በአይሁድ ተከሶ ከታሰረ በኋላ ፊልክስ በሚባለው አገረ ገዢ ፊት ቀርቦ ስለ ጽድቅና ራስን ስለ መግዛት አስተማረው። የሐዋ.፳፬፥፳፬-፳፭። በዚሁ ሂደት አግሪጳ ወደሚባለው ንጉሥ ቀርቦ አሁን የተከሰሰበት ጉዳይ የሚያምነውና የሚያስተምረው የክርስቶስ የማዳን ጥሪ መሆኑን በመግለጽ ክርስትናን ሰበከ። በዚህ ጊዜ ንጉሡ ቅዱስ ጳውሎስን «በጥቂት ክርስቲያን ልታደርገኝ ትወዳለህ» እስኪለው ደረሰ። የሐዋ.፳፮፥፳፰። እየተከሰሱና እየተያዙ ከፍርድ ወደ ፍርድ መወሰዳቸው የሚያደናቅፋቸውና የሚያሰናክላቸው ሳይሆን እንዲህ መከራ እስከ መቀበል ደርሰው የቆሙለትን ዓላማ ለአይሁድም ለአሕዛብም ለማስረጨት መልካም አጋጣሚ ሆነላቸው።

አስቀድሞ ሐዋርያት ያልተማሩ ነበሩ። እንዲህ ማለት ነቀፌታ ሳይሆን ክብር ነው። ያልተማሩ ብቻ ሳይሆን ድሆች፣ የማያስተውሉ፣ የረቀቀ ነገር በቀላሉ የማይረዳቸው፣ ዝንጉአን ነበሩ። ነገር ግን እንዲህ የነበሩት እነዚህ ደቀ መዛሙርት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ በዚህ ዓለም አሉ በተባሉት ፈላስፎችና አዋቂዎች ትምህርት ተይዞና ተመልቶ የነበረውን ዓለም በትምህርታቸው አሳመኑት። እርሾ ሆነው ወደ እነርሱ ለወጡት። ጨው ሆነው አጣፈጡት። በፊት «መጽሐፍን የማያውቁና ያልተማሩ» እየተባሉ ይናቁ የነበሩት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ደግሞ እነዚያው በፊት የናቋቸው ሰዎች «ይህን ጥበብ ከየት አገኙት» እስከ ማለት ደርሰው ተደነቁባቸው። የሐዋ.፬፥፲፫። የፈላስፎችን ጥበብ፣ የሶፊስቶችን የክርክር ችሎታ፣ የተናጋሪዎችን የንግግር ክሂል፣ ከዚህ ሁሉ አንዱም የሌላቸው የነበሩት የገሊላ ዓሣ አጥማጆችና ገበሬዎች እነዚህን ከነተከታዮቻቸውና አስተሳሰባቸው ማረኩ።

በግሪኮችና በሮማውያን ፍልስፍናና አስተሳሰብ ተይዞ የነበረውን ሁሉ ወደ ክርስቶስ አቀረቡት። ድሆች ሲሆኑ በውጫዊ ሀብትና ክብር የታጀሉትን ማረኩ። በጎች ሆነው ተኩላዎችን ድል ነሱ። ይህ ሁሉ በእነርሱ ባደረው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተደረገ መሆኑ ግልጽ ሆነ። ስለዚህም ይህ ሥራ የእርሱ የራሱ ሥራ መሆኑ ግልጽ ይሆን ዘንድ ያልተማሩትን፣ ከገሊላ መንደር ውጭ ሌላ አገር የማያውቁትን፣ ድሆችና ምንም የሌላቸው የነበሩትን ለዚህ አገልግሎቱ መረጣቸው። ለወንጌል መስፋፋትና ለክርስትና በዓለም መዳረስ ምክንያቱ የእግዚአብሔር ኃይልና ፈቃድ ሳይሆን የሰዎች ጥበብና ፊሊጥ ነው ብሎ የሚያስብ እንዳይኖር ለማድረግ በሰዎች ዘንድ ጥበብ ከሚባለው ነገር ምንም የሌላቸውን መረጠ። ይህም በእነርሱ አድሮ የሠራው ሥራ የሰው ዕውቀት ወይንም የንግግር ጥበብ ወይንም የሀብትና የክብር ርዳታ የሌለበትና ይህ ሁሉ የማያስፈልገው፣ የፈለገውን ታላቅ ነገር እርሱ በወደደው በታናሹና በተናቀው ነገር መፈጸም የሚችል ከሃሊ አምላክ መሆኑ ይታወቅ ዘንድ ነው። ሐዋርያው እንዲህ በማለት እንደገለጸው፦ «እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ፤ ብርቱውንም ነገር እንዲያሳፍር እግዚአብሔር የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ፤ የሆነውን ነገር እንዲያጠፋ የዓለምን ምናምንቴ ነገር፣ የተናቀውንም ነገር ያልሆነውንም ነገር መረጠ፣ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እንዳይመካ።» ፩ቆሮ.፩፥፳፯-፳፱።

ባዶ እጃቸውን ወደ ዓለም የተሰማሩት በኃይል የታጠቁትን አሸነፉ። ይገረፉ የነበሩት የሚገርፏቸውን አስጨነቁ። የታሠሩት አሳሪዎቻቸውን አስፈሩቸው። የአይሁድ ሊቀ ካህናት እስሮ በሸንጎ ፊት አቅርቦአቸው እንዲህ ብሏልና፦ «በዚህ ስም እንዳታስተምሩ አጥብቀን አላዘዝናችሁምን? እነሆም ኢየሩሳሌምን በትምህርታችሁ ሞልታችኋል፤ የዚያን ሰው ደም በእኛ ታመጡብን ዘንድ ታስባላችሁ» ብሎ በምሬት ተናገራቸው። የሐዋ.፭፥፳፯-፳፰። ይህ አነጋገር የተጨነቀ ሰው አነጋገር ነውና። በኋላም ገርፈው በክርስቶስ ስም እንዳያስተምሩ

አስፈራርተው ፈቱአቸው። የታሰሩትና የተገረፉት ሐዋርያት ደስ እያላቸው ሲወጡ ያሰሯቸውና የገረፏቸው ግን በጭንቀት ላይ ነበሩ። በብዙ ተደብድበው ወደ እስር ቤት ተጥለው ሳሉ አሳሪዎቻቸውንና አስ ጨናቂዎቻቸውን የሕይወት ምርኮ ማረኳቸው። አሳሪዎቻቸው «ጌቶቼ ሆይ፣ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?» እስኪሉ ደረሱ። የሐዋ.፲፮፥፴። ክፉዎች ሰዎች መሰናክል አድርገው የሚያቀርቡላቸውን ነገር ባደረባቸው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያንኑ ወንጌልን የሚሰብኩ ያማሩ እግሮቻቸው የሚጓዙበት ደልዳላ ሜዳ አደረጉት። በሚፈተኑበት ነገር አንጻር በዚያው የእግዚአብሔርን ሥራ የሚሠሩ ሆኑ። በፈተናዎች የሚሰናከሉና የሚያጉረመርሙ ሳይሆን የበለጠ ለመሥራት የሚነሣሡበትና የሚተጉበት ምክንያት ሆኑ። የተቃዋሚዎች መብዛት የሚያስደነግጣቸውና ተስፋ የሚያስቆርጣቸው ሳይሆን ለበለጠ ሥራ የሚያነሳሳቸውና እንደ ሥራ መስክ የሚመለከቱት ሆኑ። «ሥራ የሞላበት ትልቅ በር ተከፍቶልኛልና፣ ተቃዋሚዎች ብዙ ናቸው።» የሚሉ ሆኑ። ፩ ቆሮ.፲፮፥፱።

የነገሥታት ማስፈራራትና የሠራዊታቸው መብዛት፣ የሰዎች ስር የሰደደ ወግና ልማድ፣ በዓለሙ ሁሉ ተስፋፍቶና ተንሰራፍቶ የነበረው የጣዖታት አምልኮ፣ እንደ ታላቅ ቁም ነገር ተይዞ የነበረው የፈላስፎች ንግግርና አስተሳሰብ፣ እንዲሁም እነዚህ የነበራቸው ዝናና ገናና ስም፤ ሌሎችም ነገሮች ሁሉ ዓሣ አጥማጆችና ድንኳን ሰፊዎች ለነበሩት ሰዎች ትምህርት እጁን ሰጠ። በአጠቃላይ እንዲህ የሚሉ ሆኑ፡- «በሰው ልማድ ምንም እንኳ የምንመላለስ ብን ሆን እንደ ሰው ልማድ አንዋጋም፤ የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና። ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፤ የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም ዕውቀት ላይ የሚነሳውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን፤ ለክርስቶም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን፣ መታዘዛችሁም በተፈጸመች ጊዜ አለመታዘዝን ሁሉ ልንቀበል ተዘጋጅተናል።» ፪ቆሮ.፲፥፫-፮። ይህ ድል አስደናቂ ነው። ይህ የኃይሉን ችሎታ ያሳይ ዘንድ ነው። ይህ ድል የተገኘው የመንፈስ ቅዱስን ኃይል በመታጠቃቸው ነበር።

ስለዚህ በዓለ ሃምሳ እግዚአብሔር አገልጋዮቹን ማንም ሊቃወመው የማይችል ሰማያዊ ኃይል ያስታጠቀበት ዕለት ነው። ቤተ ክርስቲያን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በየዘመኑ ከገዢዎች እስከ ተራው ግለሰብ ድረስ በተነሡ የተለያዩ ሰዎች በልዩ ልዩ ዓይነት ፈተና ስትፈተን ብትኖርም ሳትጠፋ ፈተናውን ሁሉ እያለፈች ከዛሬ የደረሰችው መሣሪያዋ ጠላት የማያከሽፈው፣ ዲያብሎስ የማይችለው፣ ዘመን የማይሽረው መንፈስ ቅዱስ ስለ ሆነ ነው። እያንዳንዳችንም የዚህን ዓለም ፈተና ለማለፍ በጥምቀት ያገኘነውን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በተቀደሰ ሕይወት በማበልጸግ ልንጠቀምበት ያስፈልጋል። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ካልሆነ በስተቀር ክርስቲያናዊ ፈተናዎችን ማለፍ ከባድ ነው።

### ዕውቀትንና ማስተዋልን አገኙ

ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን ብዙ ጊዜ ስለ አለማስተዋላቸው ገሥጾአቸዋል። ማቴ.፲፭፥፲፮፤፲፮፥፲፰። የደቀ መዛሙርቱ አለማስተዋል ወደ ኤማሁስ ሲጓዙ በነበሩት በሁለቱ መንገደኞች ግልጽ ሆኖ ይታያል። «እኛ ግን እስራኤልን እንዲቤዥ ያለው እርሱ እንደሆነ ተስፋ አድርገን ነበር።» ሉቃ.፳፬፥፳፩። እርሱ አስቀድሞ እንደሚሞትና እንደሚነሣ፣ ዓለምን የሚቤዥውም በዚህ መንገድ እንደ ሆነ ብዙ ጊዜ በምሳሌም በቀጥታም አስተምሮአቸው ነበር። ለምሳሌ ያህልም በራሱ ኃይል ከሙታን እንደሚነሣ ሲያስረዳቸው «ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፣ በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ» አለ። ዮሐ. ፪፥፲፱፤ ሞቱ ለሰው ሁሉ ድኅነት ሲል መሆኑን ሲገልጽ «የስንዴ ቅንጣት በምድር ጸድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤ ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች» ዮሐ.፲፪፥፳፬። በግልጽም «ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን፣ የሰው ልጅም ለካህናት አለቆችና ለጻፎች ይሰጣል፤ የሞት ፍርድም ይፈርዱበታል፣ ሊዘባበቱበትም ሊገርፉትም ሊሰቅሉትም ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታል፣ በሦስተኛውም ቀን ይነሣል አላቸው።» ማቴ.፳፥፲፯-፲፱።

በማርያም መግደላዊት በኩል የመጣላቸውን የትንሣኤውን ዜና የሰሙት አስቀድሞ ተነግሮት የሚሆንበትን ጊዜ እንደሚጠብቅ ሰው ባለ ኅሊና ሳይሆን ምንም ሳይነገራቸው በድንገት እንደሆነ ነገር ነበር የሆነባቸው። «ከእኛ ውስጥ ማልደው ከመቃብሩ ዘንድ የነበሩት አንዳንድ ሴቶች አስገረሙን፤ ሥጋውንም ባጡ ጊዜ፡- ሕያው ነው የሚሉ የመላእክትን ራእይ ደግሞ አየን ሲሉ መጥተው ነበር።» በማለት ተገረሙ። ሉቃ.፳፬፥፳፪-፳፫። ጌታችን ተላልፎ እንደሚሰጥና እንደሚሞት በተናገረ ቁጥር ያዝኑና ይተክዙ የነበረው፣ ከዚያም አልፎ ይህ ነገር አይሁንብህ እስከ ማለት ያደረሰቻው የክርስቶስን ዓላማና ትምህርት ባለማስተዋላቸውና ባለመረዳታቸው ነበር።

ለኤማሁስ መንገደኞች ከተገለጠላቸው በኋላ «እናንተ የማታስተውሉ፣ ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባችሁ ከማመን የዘገየ፣ ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና ወደ ክብሩ ይገባ ዘንድ ይገባው የለምን?» ያላቸው ለዚህ ነበር። ሉቃ.፳፬፥፳፮። በዚህ ዕለት መንፈስ ቅዱስን ከመቀበላቸው በፊት አእምሮአቸው ብዙ ምሥጢርና ከባድ ነገር ለመስማትና ለመሸከም እንደማይችል እንደ ሕፃን አእምሮ ነበር። ጌታችን እንዲህ ሲል እንደተናገራቸው፡- «የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ፣ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም። ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል።» ዮሐ.፲፮፥፲፪-፲፫። በተስፋ ቃሉ መሠረት መንፈስ ቅዱስን ሲልክላቸው ከእነርሱ ጋር በአካል ሳለ ያስተማራቸውና የነገራቸው ነገር ሁሉ ግልጽ ሆነላቸው፣ አእምሮአቸው የእግዚአብሔርን ድንቅና ረቂቅ ምሥጢር የሚረዳና የሚያስተውል ሆነ።

### በአስተሳሰባቸው ከምድራዊነት ወደ ሰማያዊነት ተሸጋገሩ

ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ከመቀበላቸው በፊት ደቀ መዛሙርቱ ብዙ ምድራዊ አስተሳሰቦችና ምኞቶች ነበሯቸው። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም የሚነግሥና መንግሥት የሚመሠርት መስሏቸው ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ ያዕቆብና ዮሐንስ ወደ እርሱ ቀርበው፡- «መምህር ሆይ፣ በክብርህ ጊዜ አንዳችን በቀኝ፣ አንዳችንም በግራህ መቀመጥን ስጠን» አሉት። ሌሎቹም ይህንን የሁለቱን ጥያቄ ሲሰሙ እነዚህ ሁለቱ ምድራዊ ሹመት በመፈለጋቸው ሳይሆን በእነርሱ ላይ ለመሰልጠንና እነርሱን

> ቤተ ክርስቲያን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በየዘመኑ ከገዢዎች እስከ ተራው ግለሰብ ድረስ በተነሡ የተለያዩ ሰዎች በልዩ ልዩ ዓይነት ፈተና ስትፈተን ብትኖርም ሳትጠፋ ፈተናውን ሁሉ እያለፈች ከዛሬ የደረሰችው መሣሪያዋ ጠላት የማያከሽፈው፣ ዲያብሎስ የማይችለው፣ ዘመን የማይሽረው መንፈስ ቅዱስ ስለ ሆነ ነው።

ወደ ገጽ ፴፫ ይዟል

# በማዕከለ ክልኤ አምኣት ርእኩኪ፤

## በሁለት ሺሕ ዓመት መካከል አየሁሽ

ጌታቸው በቀለ

*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሁለት ሺሕ ዘመኗ ታላላቅ ተግባራትን አከናውናለች:: ጥንታዊት፣ ታሪካዊትና ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ቅርሷን ጠብቃ አገራችንን በዓለም መድረክ እንድትታወቅ ከማድረጓም በላይ፣ ሀገራችንን ከሌላው ዓለም የተለየ የዘመን አቆጣጠር፣ የራሷ የሆነ ፊደልና ሥነ ጽሑፍ ባለቤት አድርጋለች:: ይህንኑ የቤተ ክርስቲያኒቱን አስተዋጽኦ ባለፈው ዕትም ያቀረብን ሲሆን ቀጣዩን እነሆ:: መልካም ንባብ::*

፫. አኀዝ ወይም የቁጥር ስልት:-

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለአገራችን ከአበረከተችው አስተዋጽኦ መካከል ዓለምን ያስደነቀው የዘመን አቆጣጠሯ ስልትና ሥፍረ ስዓት ነው:: የዘመን አቆጣጠሯም ልዩ የሆነና ጥንታዊውን ሀገሮችና አብያተ ክርስቲያናት ይሠሩበት እንደነበር ይታወቃል::

አብዛኛዎቹ የዓለም ሕዝቦች የሚጠቀሙበት አኀዝ ወይም የቁጥር ስልት የዓረብኛው የቁጥር ስልት መሆኑ ግልጽ ነው:: በኢትዮጵያም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በብዛት የሚሠራበት ይኸው የዓረብኛ ቁጥር ነው:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቁጥር መንገድ ወይም ስልት አሁንም ከዓረብኛው ቁጥር ጉን ለጉን በመሆን ይሠራበታል:: ለበለጠ መረጃ /ሐመር፡ መስከረም /ጥቅምት፡ ኀዳር/ ታኅሣሥ፡ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ይመልከቱ/

፬. ሥዕል

የኢትዮጵያ የሥዕል ታሪክ በጣም ጥንታዊ ነው:: የኢትዮጵያ ጥንታዊነት ከሚታወቅባቸው ባህሎች አንዱ ሥዕል ነው:: እንደማንኛውም ቅርስ ሁሉ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥዕል የተጀመረው ገና ጥንት ነው:: የኢትያጵያ ሥዕልና ያሳሳል ስልት እጅግ የተወደደና ከዘመን ወደ ዘመን እየተሻሻለ የሔደ ጥበብ ነው:: በታላላቅ ገዳማትና አድባራት የነበሩ መነኮሳትና ቀሳውስት የሥዕልን ሥራ ያስፋፉት የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት በመጀመሪያው ገጽና እንዲሁም አልፎ አልፎ በመካከልና በመጨረሻ ገጽ የተለዩ ሥዕሎችንና ሐረጎችን በመሳል ነው:: ቀጥሎም በቤተ መቅደሱና በመንበሩ ዙሪያ አንዳንድ ጊዜም በቅድስቱ ዙሪያ የተለዩ የጌታችንና የእመቤታችንን የመላእክትን፣ የጻድቃንና የሰማዕታትን ሥዕሎች በመሣል የሥዕሉ ጥበብ ከፍተኛ ተደናቂነትን እንዲያተርፍ አድርገውታል:: /ይህ የሥዕል ጥበብ ከሙሴ ጀምሮ የነበረ እንደነበር ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ::/

የጥንት መንፈሳውያን ሠዓሊዎች በቅዱሳት ሥዕሳት ብቻ ሳይወሰኑ፤ የኅብረተሰቡን ኑሮ በመከተል የሕዝቡን ደስታ፣ ኀዘን፣ እንዲሁም ጀግንነቱን የሚገልጹ ልዩ ልዩ ሥዕሎችን በየቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያና በየመጻሕፍቱ ገጽ ይሥሉ ነበር:: ለምሳሌ:- የአድዋው ጦርነትና በጠላት ላይ የተገኘው ድል፣ የማይጨው ጦርነት እና ፋሺስት ኢጣሊያ ድል ሆኖ ኢትዮጵያን ለቅቆ ሲሔድ እንዴት እንደነበር የሚያመላክቱ ሥዕሎች በአንዳንድ ታላላቅ አድባራት ቤተ መቅደሶች ዙሪያ ተሥለው እናገኛለን::

እነዚህ ሥዕላት በክብር ተጠብቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጡት፣ በመጀመሪያ የተሠሩትና የተዘጋጁት በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ነው:: ሠሪዎቹና አቀነባባሪዎቹ መነኮሳት፣ ቀሳውስትና ችሎታውና ተሰጥኦው ያላቸው ምእመናን ዲያቆናት ስለነበሩ ዕቃዎቹም ሆኑ መጻሕፍቱ ከሞላ ጎደል በክብር ተጠብቀው አሁን ላለው ትውልድ ሊደርሱ የቻሉት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ጥረት ነው:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ ውለታ ያደረገች ናት:: እነዚህ መጻሕፍት ዛሬ በአገር ውስጥና በውጪ ዓለም በተለያዩ ቤተ መጻሕፍቶች ይገኛሉ:: /በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የተዘጋጀ፤ አጭር የታሪክ የሃይ ማኖትና የሥርዓት መጽሐፍ፤ ፲፱፻፸፩ ዓ.ም፤ ገጽ ፫-፳፫/

፭. ለአገሪቱ ሕግ ቀረጻና ልማት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለአገሪቱ ሕግ ቀረጻና ልማት ያደረገችውን አስተዋጽኦ ፍትሐ ነገሥትን መነሻ በማድረግ የሕግ ባለሙያው አቶ አበበ ወርቄ ገልጸውታል:: እርሳቸው በአቀረቡት ጥናት እንደገለጹት፤ «ፍትሐ ነገሥት የብሉይ እና የሐዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች /Appostolic Origin/ እንዲሁም ፫፻፲፰ አባቶች በኒቅያ ከሰበሰቧቸው ሕጎች የተውጣጣ ነው:: ፍትሐ ነገሥት በቀደምት አባቶች፣ የቤተ ክርስቲያን ምሁራንና በቤተ መንግሥት አካባቢ ሰዎች እጅግ ከፍተኛ አክብሮት የተሰጠው በመሆኑ በቤተ መንግሥት የሚሠራበትና ቤተ ክርስቲያንም የምታስተምርበት ሕግ ሆኖ ቆይቷል:: ትምህርቱም የተስፋፋው በቤተ ክርስቲያኗ ምሁራን አማካኝነት ነው:: እንደ መንፈሳዊ ሕግነቱ፤ ሕገ አጽዋማትን፣ ሕገ ጸሎትን፣ ሕገ ምዕዋትን፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት የሚተዳደሩበትንም ወዘተ ይዟል:: እንደ ዓለማዊ ሕግነቱ፤ የንግድ ሕግን፣ የቤተሰብ ሕግን፣ የንብረት ሕግን፣ የብድር ሕግን፣ የወንጀል ሕግንና የመሳሰሉትን በሰፊው የያዘ ነው:: በየዘመኑ የተነሡ ነገሥታት ሕጉቹን በሥራ ላይ በሚያውሉበት ጊዜ ትርጉሙንና አንድምታውን የሚቀበሉት የግእዙ ዕውቀት ካላቸው የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ነበር::» በማለት ፍትሐ ነገሥት በቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ለቤተ መንግሥት እንዲሁም ለዘመናዊ ሕግ ቀረጻ አስተዋጽኦ እንዳደረገ ገልጸዋል::

**በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መነኮሳትና ቀሳውስት እጅ የተጻፉት ታላላቅ መንፈሳውያት የብራና መጻሕፍት በየገዳማቱና በየአድባራቱ የዕቃ ግምጃ ቤቶች ውስጥ ይገኛሉ:: እስከ ዛሬ ድረስ ጠብቃ በማቆየቷ በየጊዜው ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ አገር ጐብኚ /ቱሪስቶች/ እንዲጐበኙት በማድረግ ለአገሪቱ የኢኮኖሚ ግንባታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተች ትገኛለች::**

፮. በቱሪስት መስህብነት

ለአንድ አገር የኢኮኖሚ ዕድገት ቱሪዝም ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርግ መሆኑ ይታወቃል:: ወደ ሀገራችን የሚመጡ ቱሪስቶች በአብዛኛው የሚጐበኙት ጥንታውያኑን የኢትዮጵያ ቅዱሳት መካናት ገዳማትና አድባራትን፣ ጥንታዊ የብራና መጻሕፍት፣ ንዋየ ቅድሳት እንዲሁም እንደ ላሊበላ ያሉ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን ነው:: በተለይም በሌሎች ዓለም የማይገኙ ታላላቅ ቅርሶች የሚገኙት በቤተ ክርስቲያን በመሆኑ የታሪክ ባለቤት አድርጓታል:: በ፬ኛው፣ በ፭ኛው በ፲፪ኛውና በ፲፭ኛው ክፍለ ዘመናት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መነኮሳትና ቀሳውስት እጅ የተጻፉት ታላላቅ መንፈሳውያት የብራና መጻሕፍት በየገዳማቱና በየአድባራቱ የዕቃ ግምጃ ቤቶች ውስጥ ይገኛሉ:: እስከ ዛሬ ድረስ ጠብቃ በማቆየቷ በየጊዜው ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ ሀገር ጐብኚ /ቱሪስቶች/



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

እንዲጐበኙት በማድረግ ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ግንባታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተች ትገኛለች።

### ፯. የትምህርት ማዕከል /ሚኒስቴር/

በሀገራችን የዘመናዊውን ትምህርት በመምራት ላይ የሚገኘው የትምህርት ሚኒስቴር ከመቋቋሙ በፊት ለሦስት ሺሕ ዘመናት ያህል ትምህርቱ ይካሔድ የነበረው በቤተ ክህነት እንደነበር ታሪክ ይመሰክራል። ገዳማቱንና አድባራቱን የትምህርት ማዕከል በማድረግ ሊቃውንቱና ካህናቱ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ብቻ ሳይወሰኑ ከአገር መሪነት እስከ ተራ ሠራተኛነት ያለውን የመንግሥት ሥራ ያካሔዱ የነበሩት የቤተ ክርስቲያን ምሁራን እንደነበሩ የታወቀ ነው። ቤተ ክርስቲያኗ ለረጅም ዘመናት የትምህርት ማዕከል ሆና ኅብረተሰቡን ስታገለግል ከመኖሩዋ የተነሣ ለአገሪቱ ያተረፈችው የሥልጣኔ ውጤት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። ለምሳሌ፡- በአክሱም ሐውልቶች ላይ በሳባውያን፣ በግሪክና በግእዝ ቋንቋ የተጻፉት ጽሑፎች የዓይን ምስክሮች ናቸው።

### ከሣቴ ብርሃን ሰላማ

ክርስትና በኢትዮጵያ ከነሙሉ ሥርዓቱ የተሰበከው በፍሬምናጦስ ሐዋርያነት ጊዜ ነው። ነገሥታቱ አብርሃና አጽብሐ የክርስትና ሃይማኖት በአገራቸው እንዲስፋፋ በወቅቱ የክርስትና ማዕከል ወደ ነበረችው እስክንድርያ ደብዳቤ ጽፈው ጳጳስ ሹምልን ብለው ፓትርያርክ ወደነበረው ወደ ቅዱስ አትናቴዎስ ፍሬምናጦስን ላኩት።

ቅዱስ አትናቴዎስም የህገሩን ቋንቋና የሕዝቡን ልማድ የሚያውቅ ከቅዱስ ፍሬምናጦስ በቀር ሌላ ሰው አለመኖሩን ተገንዝቦ ሢመተ ጵጵስናን ሰጠውና ወደ ኢትዮጵያ ላከው። ፍሬምናጦስ ጵጵስናን ሲቀበል አባ ሰላማ በመባል ተሰይሟል። ከዚያም ወደ ኢትዮጵያ መጣ። አቡነ ሰላማ ቀደም ብሎ ወንጌል ያስተማራቸውን ነገሥታቱን አጠመቃቸው። የክርስትናን እምነት ለቤተ መንግሥት ልጆች ሁሉ አስተማረ፣ በአክሱም የነበሩ ካህናተ ኦሪትንም አስተምሯቸዋል።

አቡነ ሰላማ ከኦሪት ቀንበርና የተስፋ ሕይወት አውጥቶ ኃጢአት አጨልሟት በነበረችው ዓለም ያለችውን ኢትዮጵያን በብርሃነ ወንጌል ስለ አበራት፣ በብርሃን ትምህርቱ የተደሰቱ ኢትዮጵያውያን «ሰላማ ከሣቴ ብርሃን» /ሰላማ ብርሃንን ገላጭ ብርሃንን የገለጠ/ ሲሉ ሥራውን ጨምሮ የሚገልጥ የክብር ስም ሰጥተውታል።

### የአቡነ ሰላማ አስተዋጽኦ

፩. መካሪ /አበ ነፍስ/፡- በሕዝቡ የኑሮ አቀማመጥ ይዞታ አለመመቸት ያህል ውጤት ባያገኝም ብዙ ጥሩ ነገሮች ተደርገዋል። ከእነዚህም አንዱ በየቀበሌው አንዳንድ ቄስ መካሪ እንዲሆን መደረጉ ነው። ይሁን እንጂ በጊዜ ብዛት መካሪው ቄስ ስለ ነፍስ ጉዳይ የአባት ያህል ይመክራልና አበ ነፍስ /የነፍስ አባት/ ተብሎ ይጠራ ጀመር። በኋላም ስለ ኃጢአት ኑዛዜ በመቀበል ንስሐ ስለሚሰጥ የንስሐ አባት ተባለ። እስከ አሁንም ይህ አጠራር ተጠብቆ ይገኛል።

፪. አበ ልጅ /የክርስትና አባት/፡- አበ ልጅ ማለት የሚጠመቀውን ሕፃን በእግዚአብሔር መንገድ እየመራ እንዲያስተምረው እንደ ዋስ ወይም እንደ ተያዥ ሆኖ በቤተ ክርስቲያን ፊት መቀበሉን የሚያረጋግጥ ምእመን ነው። ይህም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እንዲሠራበት አድርጓል።

፫. ቅዱሳት መጻሕፍትን መተርጐም፡- በአቡነ ሰላማ ጊዜ ከጥንቱ ከዕብራይስጥ ከተተረጎመው ሌላ ቅዱሳት መጻሕፍት ከግሪክ /ከሰብዓ ሊቃናት/ መጽሐፍ ወደ ግእዝ ተተርጉመዋል።

፬. ቋንቋ፡- የጥንቱ ግእዝ ዛሬ እንደምናነበው ከካዕብ እስከ ሳብዕ ያለው ድምፅ በፊደል አልነበረም። ግን ግእዙን ብቻ አናጋሪ አድርጎ ይነበብ ነበር። ለምሳሌ «ሐወለተ አከሰመ» ሐውልተ አክሱም ማለት ነው። በዚህ ሁኔታ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመተርጎም አስቸጋሪ ስለሆነበት፣ አቡነ ሰላማ ከኢትዮጵያ ሊቃውንት ጋር ተመካክሮ በጥንታዊው የፊደል ቅርጽ መሠረት ከካዕብ እስከ ሳብዕ ያለውን ተእምርተ ድምፅ አዘጋጀ።

፭. ስብከተ ወንጌል ማስፋፋት፡- በሐዋርያት የተሰበከውና በ፫፻፲፰ ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት የጸናው ትምህርተ ሃይማኖት እንዲስፋፋ አድርጓል። ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ጋር በመወያየት ለትምህርተ ሃይማኖት ልዩ ልዩ ቃላትን አዘጋጅቷል።

ቤተ ክርስቲያኗ ለረጅም ዘመናት የትምህርት ማዕከል
ሆና ኅብረተሰቡን ስታገለግል ከመኖሯዋ የተነሣ
ለአገሪቱ ያተረፈችው የሥልጣኔ ውጤት መሆኑን
የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- በአክሱም ሐውልቶች
ላይ በሳባውያን፣ በግሪክና በግእዝ ቋንቋ የተጻፉት
ጽሑፎች የዓይን ምስክሮች ናቸው፡፡

* ከሣቴ ብርሃን ሰላማ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቀዳማዊ ሐዋርያ መሆኑ ይታወቃል። ስለዚህም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይህን ታላቅ መምህር፡- «አባ ሰላማ ከሡተ ለነ ብርሃነ ዜናሁ ለመድኃኒነ፣ አባ ሰላማ ብርሃን የሆነ የመድኃኒታችንን ዜና ገለጠልን።» እያለች የወንጌል መልእክተኛነቱን ትመሰክራለች። በስሙም ቤተ ክርስቲያን አንጻለች። ሐምሌ ፳፮ እና ታኅሣሥ ፲፰ ቀን ቅዱስ አባት ብላ ታከብረዋለች። /ትንሣኤ፣ ሐምሌ ፲፱፻፸፪ ዓ.ም፣ ገጽ ፳፱/

### አብርሃ ወአጽብሐ

በኢትዮጵያ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያን ነገሥታት አብርሃና አጽብሐ ሲሆኑ የነገሡበትም ዘመን በ፫፻፴፬ ዓ.ም አካባቢ መሆኑን ብዙ ታሪክ ጸሐፊዎች ይስማሙበታል። ነገሥታቱ ሥርዓተ ኦሪትን ከሊቀ ካህናቱ ከእንበረም፣ ትምህርተ ክርስትናን በቤተ መንግሥት ሞግዚታቸው ከነበረው ከፍሬምናጦስ ተምረዋል። የመጀመሪያ ስማቸው ኢዛናና ሳይዛና ሲሆን ከክርስትና በኋላ ግን አብርሃ /አበራ/፣ አጽብሐ /አነጋ/ የሚል ከክርስትና መሰበክ ጋር የተየያዘ ስም ተሰጥቷቸዋል።

ፍሬምናጦስ ለነገሥታቱ ስለ ነገረ ወንጌል ያስተምራቸው ስለነበር የክርስትናን እምነት የተቀበሉት ቀደም ብለው ነው። ክርስትና በቅድሚያ በቤተ መንግሥት መሰበኩ ወንጌል እንዲስፋፋ አስተዋጽኦ አድርጓል።

አብርሃና አጽብሐ ከሕንደኬዋ ጻን ደረባ ቀጥሎ የክርስትና እምነትን የተቀበሉና ያስፋፉ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በኩል በዓለም ውስጥ የነበሩ መናንያን ሆነው የኖሩ ቅዱሳን ነበሩ። በዘመናቸው የተነሣው የአርዮስ ኑፋቄ ወደ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንዳይገባ የተከላከሉና የተቃወሙ በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቁ ክርስቲያን ነገሥታት ነበሩ። የአርዮስ ኑፋቄ ደጋፊ የነበረው የታላቁ ቆስጠንጢኖስ ልጅ ኮንስታንቲንዮስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን የአርዮስ ኑፋቄ ደጋፊ ለማድረግ ለአብርሃና አጽብሐ የተማኅጽኖ ደብዳቤ ጽፎላቸው ነበር። ኢትዮጵያውያን ነገሥታቱ ግን ጥያቄውን አልተቀበሉትም። ነገሥታቱ በወሰዱት አቋም የተደሰተው ቅዱስ አትናቴዎስም የምስጋና ደብዳቤ ጽፎላቸዋል። /የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ፣ ፲፱፻፺ ዓ.ም፣ ገጽ ፴ -፴፩/

የነገሥታቱ አስተዋጽኦ ለኢትዮጵያ

* ኢትዮጵያውያን እንዲጠመቁ አደረጉ።
* የክርስትና ሃይማኖት እንዲስፋፋና ብሔራዊ ሃይማኖት እንዲሆን አድርገዋል።
* በተለያዩ ቦታዎች ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አሠርተዋል።
* በአክሱም ፲፪ ቤተ መቅደስ ያለው በአምስት ክፍሎች የተከፋፈለ ባለ ፮፻፸፪ አዕማድ ቤተ ክርስቲያን በጽዮን ማርያም ስም አሠርተዋል።
* ከድንጋይ ውቅር ተፈልፍለው የተሠሩትን ፩፻፵፬ የሚያስደንቁ አብያተ

ወደ ፴፮ ገጽ ዞሯል

# «ቤተ ክርስቲያን ስትከፈል፣ ምእመናን ዝም ብለን ማየት የለብንም»

ኢንጂነር ተረፈ ራስወርቅ

ጌታቸው በቀለ

ኢንጂነር ተረፈ ራስ ወርቅ በስዊዘርላንድ፣ ጄኔቭ ከተማ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊ ምሁር ናቸው:: የተወለዱት አንኮበር አፈር በዓይኔ ተክለ ሃይማኖት በሚባል ቦታ ነው:: የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በቀድሞ ተፈሪ መኮንን ት/ቤት አሁን እንጦጦ ቴክኒክ እና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ፣ የከፍተኛ ትምህርታቸውን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ተምረዋል:: ከዛም ወደ አሜሪካን አገር በመሔድ በኤሌትሪካል ኢንጅነሪንግ ተመርቀዋል::

ኢንጂነር ተረፈ ወደ አገራቸው መጥተው በኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን የትራንስሚሽንና በኋላም የኦፕሬሽን ሓላፊ በመሆን ለዐሥር ዓመት ከአገለገሉ በኋላ /የዓለም አቀፍ ቴሌኮሚዩኒኬሽን ማኅበር International Telecommunication Union/ ባወጣው ክፍት የሥራ ቦታ ተወዳድረው በማሸነፍ በዚህ ድርጅት ተቀጥረው ወደ ጄኔቭ ስዊዘርላንድ ሔዱ:: በዛም ለረጅም ዓመታት ሠር ተዋል:: ይህ ክፍል በአህጉሪቱ በሚገኙ አገሮች ያሉትን የቴሌኮሚዩኒኬሽን ማሠልጠኛ ት/ቤቶች የሚያደራጅ፣ ዕቅድ የሚያወጣና ኔትወርክ የሚዘረጋ ነው:: እርሳቸውም ለአፍሪካ ቴሌኮሚዩኒኬሽን ዕድገት እና መስፋፋት ትምህርት ቤት በማቋቋም፣ ዕቅድ በማውጣት፣ መስመሮችን በመዘርጋትም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል:: በዚሁ መሥሪያ ቤት በመጀመሪያ የአፍሪካ ክፍል ዋና ሓላፊ ከዚያም ለዋና ጸሐፊው በአማካሪነት ዓለም አቀፍ ሥራ ሲሠሩ ቆይተዋል:: በኋላም ይህንን ሥራ በመልቀቅ የቴሌኮሚዩኒኬሽን ኢንቨስትመንት ኩባንያ /World Tel./ የተባለ የግል ኢንቨስትመንት ሲቋቋም ከአቋቋሚዎቹ አንዱ ሆኑ:: በአሁኑ ወቅትም በዚህ ኩባንያ በዋና ጸሐፊነት በመሥራት ላይ ይገኛሉ::

ኢንጂነር ተረፈ ከአለባቸው ታላቅ የሥራ ሓላፊነት በተጨማሪ ጊዜያቸውን መሥዋዕት በማድረግ በቤተክርስቲያን አገልግሎት ንቁ ተሳታፊ ናቸው:: በጄኔቭ፣ ስዊዘርላንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ሰብሳቢ ናቸው:: በአሁኑ ወቅት ደግሞ «በዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ምእመናን አንድነት ጉባኤ» ሰብሳቢ በመሆን እየገለገሉ ያሉ ምሁር ናቸው:: ኢንጂነር ተረፈን ስለውጩ አገር የቤተክርስቲያን እንቅስቃሴ እና ወቅታዊውን የቤተክርስቲያን ጉዳይ በተመለከተ አዲስ አበባ ለሥራ በመጡበት ወቅት አግኝተን ቃለ መጠይቅ አድርገንላቸው ነበር:: ወቅታዊና ጠቃሚ በመሆኑ በጽሑፍ አቅርበንላችኋል:: መልካም ንባብ::



«የቤተክርስቲያን መሪዎች ክፍተት ሲፈጥሩ የምእመኑ አንድነት ላይ ክፍተት መፈጠር የለበትም::» ኢንጂነር ተረፈ ራስወርቅ

ሐመር፦ በውጪ ዓለም በተለይም በአውሮፓ ያለው የሰበካ ጉባኤ እንቅስቃሴ ምን ይመስላል?

ኢንጂኒየር ተረፈ፦ ዛሬ ከመቼውም ይልቅ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በእግዚአብሔር ፈቃድ ወደ ዓለም እየወጣች ወንጌል እያስተማረች ያለችበት ጊዜ ነው:: ይኸም ተገቢ ሁኔታ ነው:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ብቸኛዋ የጽላተ ሙሴ ባለ አደራ እንደ መሆኗ እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ነች:: ስለዚህም ቤተክርስቲያኗ ትምህርተ ወንጌልን ለዓለም ማስፋፋት ያለባት ወቅት ዛሬ ነው:: የዓለም ምጽአት እየተቃረበ ሲሔድ ቤተክርስቲያን እውነተኛውን የሃይማኖት ትምህርት ለዓለም የማዳረስ ሓላፊነት አለባት:: ይኸንን መርሕ በመከተል በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታቦቷን፣ ወንጌሏን ይዛ በዓለም ላይ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ መንቀሳቀስ ጀምራለች:: ቤተ ክርስቲያኒቱ ከኢትዮጵያ ውጪ በምትሔድበት ጊዜ አገልግሎቷ በውጭ ላሉት ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን፤ ለዓለም ሕዝቦች በሙሉ መሆን አለበት:: በቅርቡ ከአዲስ ከአበባ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሲዊዘርላንድ ታቦት አምጥተን ነበር:: ይኸን ታቦት ስናመጣ ያደረግ ነው ነገር ቢኖር በቅድሚያ ለስዊዝ ባለ ሥልጣናት ማስታወቅ ነበር:: ይህ የሚመጣው ጽላት ለስዊዝ አገር ሕዝብ በረከትና ቡራኬ ያመጣል፤ በማለታችንና አሳባችንም ተቀባይነት በማግኘቱ ታቦቱ በVIP ላውንጅ (በልዩ መዓርግ በሆነ እልፍኝ) ነበር እንዲያልፍ የተደረገው:: ከዚህም በኋላ በከፍተኛ ክብር ተቀብለውን መንገድ ተዘግቶ በፓሊስ ጸጥታው ተከብሮ ምእመናኑ ታቦቱን አጅበው፣ መዘምራኑ በከበሮ፣ በጸናጽል እየዘመሩ ነበር ወደ ቤተ ክርስቲያን ያደረሱት:: ይሄ አንድ ነገር ያሳየናል፤ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ለዓለም ሕዝብ ያለባትን ሓላፊነት መወጣት ጀምራለች ማለት ነው:: ስለዚህ ነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ወደ ውጭ መውጣቷ ተገቢ ነው የሚያበረታታም ነው፤ ያልኩት::

ሐመር፦ እርስዎ ሲመለከቱት ቤተ ክርስቲያን በውጩ ዓለም ተገቢውን እንቅስቃሴ እያደረገች ነው ማለት ይቻላል?

ኢንጂኒየር ተረፈ፦ ቤተክርስቲያን ሙሉ በሙሉ በቂ የሆነ እንቅስቃሴ አድርጋለች ለማለት አይቻልም:: ቤተክርስቲያን ከኢትዮጵያ ውጭ አገልግሎቷን በተጠናከረ መልክ ማካሄድ ከጀመረች ከ፳-፴ ዓመት ቢሆናት ነው:: ቤተክርስቲያኒቷ አሁንም በውጩ ዓለም የምታተኩረው በኢትዮጵያውያን ምእመናን ላይ ብቻ መሆን የለበትም:: ከኢትዮጵያውያን አልፎ ለዓለም ሕዝብ መሆን አለበት:: ቅዳሴውም፣ ትምህርቱም ወዘተ በልዩ ልዩ ቋንቋ ተተርጉሞ ለዓለም ሕዝብ በየቋንቋቸው እንዲቀርብ የማድረግ ሓላፊነት አለብን:: ስለዚህ ቤተክርስቲያኗ ብዙ እንቅስቃሴ አድርጋለች ባልልም ጅምሩ ግን አለ:: መጀመሩም ጥሩ ነው ለወደፊቱ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የቤተ ክርስቲያኒቱ አካላት ምእመናን፣ ካህናቱ



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

እንዲሁም ቅዱስ ሲኖዶሱም በጥልቀት ሊያስቡበት ያስፈልጋል::

*ሐመር:- ቤተ ክርስቲያን ዓለምአቀፋዊት እንድትሆንና በሀገር ወስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ላሉት ልጆች ጠንካራ ተቋም እንድትሆን የሚያደርጉት አስተዋጽኦ ምንድን ነው?*

ኢንጂኒየር ተረፈ:- በአለሁበት ሀገር በስዊዘርላንድ ካለኝ ተሳትፎ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዓለም አቀፍ የምእመናን ጉባኤ ላይም በሓላፊነት በማገልገል ላይ እገኛለሁ::

*ሐመር:- እርስዎ የሚኖሩት ሲውዘርላንድ ጀኔቭ ነው፣ በዓለም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን አንድነት ጉባኤ ስትመሠርቱ ከተለያዩ ቦታ ተሰብስባችሁ ነው:: አሜሪካን አገር እንዴት ለመመሥረት ቻላችሁ? የእርስዎ ሓላፊነትስ ምንድን ነው?*

ኢንጂኒየር ተረፈ:- አሜሪካን አገር ውስጥ ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እድገትና ህልውና ተቆርቋሪ የሆን ቡድን በዓለም ውስጥ ለሚገኙት የቤተ ክርስቲያናችን ተከታይ ምእመናን በአንድነት ተገናኝተው እንዲወያዩ ጥሪ አስተላለፈ:: እኔም በጀኔቫ ስዊዘርላንድ

**ቤተክርስቲያኒቱ አሁንም በውጪ ዓለም የምታተኩረው በኢትዮጵያውያን ምእመናን ላይ ብቻ መሆን የለበትም:: ከኢትዮጵያውያን አልፎ ለዓለም ሕዝብ መሆን አለበት:: ቅዳሴውም፣ ትምህርቱም ወዘተ በልዩ ልዩ ቋንቋ ተተርጉሞ ለዓለም ሕዝብ በየቋንቋቸው እንዲቀርብ የማድረግ ሓላፊነት አለብን::**

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ሰብሳቢ በመሆኔ ጥሪው ደርሶኝ ወደ ስብሰባው አመራሁ:: በዛ ምክንያት አንድነት ጉባኤው ተመሠረተ:: በዚያም የጉባኤው ሰብሳቢ እንድሆን ተመረጥኩ::

*ሐመር:- የዚህ ዓለምአቀፍ የምእመናን አንድነት ጉባኤ ዓላማው ምንድን ነው?*

ኢንጂኒየር ተረፈ:- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሦስት አካላት ወይም መዋቅሮች አሏት:: አንደኛው በፓትርያርኩ የሚመራው የሊቃነ ጳጳሳት ጉባኤ ቅዱስ ሲኖዶስ ሲሆን ሁለተኛው የካህናቱ ጉባኤ ወይም ማኅበረ ካህናቱ ነው:: ሦስተኛው ክፍል ደግሞ ምእመናኑ ናቸው:: በአጠቃላይ መዋቅሩ ውስጥ የመጀመሪያው ደረጃ ቅዱስ ሲኖዶስ ሲሆን የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ በመሆን በቤተ ክርስቲያኗ በተለይ በመንፈሳዊ ከዚያም ቀጥሎ በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የሚመሥጥበት አካል ነው:: ማኅበረ ካህናቱም ከላይ የሚወርድ ትእዛዝና አሠራር በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲኖር የክህነት ደረጃውን የጠበቀ ሠራተኞች የሚተዳደሩበት አካል ሲሆን በምእመናኑ በኩል ግን የተጠናከረ መዋቅር የለም:: እነዚህ ሦስቱ አውታሮች ተደጋግፈው ነው ቤተ ክርስቲያኒቷን ሊረዱ፣ ሊያጠነክሩ የሚችሉት:: በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ውስጥ የምእመኑ የሥራ ድርሻና ሓላፊነት ግልጽ ያለ የአወቃቀር ስልት ያለው አይመስልም:: በቀድሞው ጊዜ ማለትም በነገሥታቱ ዘመን ንጉሠ ነገሥቱ የቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ ጠባቂ በመሆን ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አንሥቶ እስከ ዋናው ቤተ ክህነት ደረስ በተዋረድ የምእመናን ሓላፊነትና አስተዋጽኦ የታወቀ ነበር:: ከአጥቢያ ቤተክርስቲያን ጀምሮ እያንዳንዱ ቤተክርስቲያን ምእመናኑን ያሳተፍ ነበር:: ምእመናን ሁነኛ ቦታ ነበራቸው:: በንጉሠ ነገሥቱ ጊዜ እንደ ቅዱስ ሲኖዶስና ካህናቱ መዋቅር አንዳንድ የምእመናን ተጠሪ የነበረ ሲሆን በመሬት በንብረትና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ ይሠራል:: እርሱም «ገበዝ» በሚል ስያሜ ይታወቃል:: ይህም በቅደም ተከተል ተዋቅሮ እስከ ቤተ ክስርቲያን የበላይ ጠባቂ የሆኑት ንጉሠ ነገሥቱ ድረስ ይደርስ ነበር::

ይኼ አሠራር የሚታወቀው በእኛ ቤተ ክርስቲያን ብቻ አይደለም:: ለምሳሌ የአንግሊካን ቤተክስርቲያንን ብንወስድ የዚህ ቤተክርስቲያን ዋና ቁንጮ ንግሥት ኤልሳቤጥ ናቸው:: እንግዲህ ንግሥቲቱ ክሀነት የላቸውም፤ ከምእመናኑ አንዷ ናቸው እንጂ:: ስለዚህ በእኛም ቤተክርስቲያን ሲሠራበት የቆየውና አሁን የሌለው የምእመናን ጠንካራ መዋቅር አለመኖር በራሱ ብዙ ችግሮች አስከትሏል:: ለምሳሌ በየቦታው አስደናቂና ታላላቅ አብያተ ክርስቲያናት ይታነጻሉ፤ በአንጻሩ ገጠር የሚገኙና ጥንታውያን አብያተክርስቲያናት መቀደሻ መሠለሻ አጥተው እየተዘጉ ናቸው:: የአብነት ትምህርት ቤቶችም በተማሪዎችና በአስተማሪዎች አለመኖር እየተዳከሙ ናቸው:: የገበዙ ሓላፊነት ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን የሚያሠራ፣ ለካህናቱ መሬት የሚሰጥ፣ የሚሰበስብ ጧፍ ዕጣን የሚያዘጋጅ ነበር:: እነኚህ ሓላፊነቶች ከታች ጀምሮ በዛው እየተዋቀረ ሔዶ በመጨረሻ ንጉሠ ነገሥቱ ጋር ይደርስ ነበር:: ንጉሠ ነገሥቱ የቤተክርስቲያኒቱ የበላይ ጠባቂ በመሆናቸው አስተዳዳሩን የሚመሩት እርሳቸው ነበሩ:: በርግጥ መንፈሳዊውን አገልግሎት የሚመሩት ጳጳሳት ናቸው:: ባለፈው ሃምሳ ዓመት ቤተክርስቲያን ራሷን ከቻለች በኋላ የመንፈሳዊ ሓላፊነት የሚመሩት ፓትርያርኩ ናቸው:: ይሄ እንግዲህ ቤተክርስቲያን እና ቤተመንግሥት ተደጋግፈው በአንድነት የሚኖሩበት ሥርዓት እንደ ነበር ያሳየናል:: በደርግ ጊዜ ግን ይሄ አቋም ተለወጠ::

ከዚህ በኋላ ገዳማቱ አድባራቱ ንብረታቸውን አጡና ተቸገሩ:: ማስቀደሻም ቸገራቸው:: ለሀገርና ለሕዝብ ይጸልዩ የነበሩት አባቶችም በረሀብና በችግሩ ምክንያት ወደ ከተማ ወጡ:: ንጉሠ ነገሥቱ በነበራቸው ሓላፊነት ዲፕሎማታቸውን ልከው የሚከራከሩለት በኢየሩሳሌም ያለው የገዳማችንና የአባቶቻችን ሁኔታም እንዲሁ ችግር ላይ ወደቀ:: ሁኔታው ከመንፈሳውያኑ አባቶቻችን በተጨማሪ በአስተዳደር ጉዳይ የምእመናንና የባለሙያዎችን ድጋፍ የሚጠይቅ ነው:: ለኢትዮጵያ ባሕል፣ ትምህርትና ሥልጣኔ መሠረት የነበሩት የአብነት ት/ቤቶችም ተዘጉ:: ስለዚህ እነዚህን ሁሉ በማሰብ ገዳማት አድባራቱን ለመርዳት፣ የአብነት ትምህርት ቤቶችን ለማስፋፋት ምእመናን ወሳኝ ድርሻ አላቸው:: ሊቃነ ጳጳሳትንና ካህናትንም በገንዘብ በዕውቀት በአመራር ሊደግፏቸው ይችላል ተብሎ የምእመናን ጉባኤ እንዲመሠረት ተወሰነ:: ርግጥ በቃለ አዋዲው መሠረት በተዋቀረው በሰበካ ጉባኤ ምእመናኑ ይሳተፋሉ:: እዛ ላይ ግን የምእመናን በቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደር ውስጥ የአገልግሎት ድርሻቸው ምን መሥራት እንደሚገባቸው የሚያሳይ ግልጽ የሆነ መመሪያ የለም:: ስለዚህ ምእመናኑ ትልቅ ሓላፊነት እንዳላቸው መዘንጋት የለበትም:: ዛሬ እንደሚታየው ትላልቅ አብያተ ክርስቲያናትን የሚያሳንጹት ምእመናን ናቸው:: ነገር ግን ቤተክርስቲያኑን አሠርተው አስተዳደር ውስጥ ግልጽ የሆነ የሥራ ድርሻ የላቸውም:: በመሆኑም የቤተ ክርስቲያኗን ችግሮች ለይቶ በማወቅ ስለ ሃይማኖትና ስለ አገር ፍቅር ለመሥራት ይህን የምእመናን የአንድነት ጉባኤ ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል:: በተለይ በውጪ ዓለም የሚገኙ ምእመናን በአንድነት መዋቀራቸው ቤተክርስቲያኒቱን ሊቃነ ጳጳሳቱንና ካህናቱን በገንዘብ በዕውቀት ሊደግፏቸው ይችላል ተብሎ የምእመናን ጉባኤ እንዲመሠረት ተወሰነ::

የጉባኤውን ዓላማዎች በአጭሩ እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል::

፩) ከሲኖዶሱና ከካህናቱ ጋር በቅርብ እየተባበረ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስብከተ ወንጌልን በሀገራችን ውስጥ እንዲስፋፋ በሕዝባችንም መካከል ሰላምና ፍቅር መተባበርም እንዲዳብር ማገዝ፤

፪) ቤተ ክርስቲያናችን የጀመረችውን ዓለም አቀፍ ሐዋርያዊ ጉዞ ማስፋፋትና ማጠናከር፤

፫) ቤተ ክርስቲያናችን በኢኮኖሚና በማኅበራዊ ልማት ረገድ ያላትን እንቅስቃሴ መደገፍ፤

፬) የቤተ ክርስቲያናችን ትምህርትና ቅዳሴ ወዘተ በልዩ ልዩ ቋንቋ እንዲስፋፋ ማገዝ፣

፭) በሀገራችን ውስጥ የሚገኙት ጥንታዊና ታሪካዊ አድባራትና የአብነት ት/ቤቶች እንዲደገፉና እንዲስፋፉ ማገዝ፣

፮) በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ውስጥ የሚገኘውን ጥንታዊ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይዞታና ቅርስ እንዲጠበቅና እንዲስፋፋ መረባረብ፣

፯) ከልዩ ልዩ እምነት ተከታዮች ጋር በሀገር ውስጥ መከባበርና መግባባት እንዲሰፍን መርዳት እና

፰) በቅርቡ በአባቶች መካከል የተከሰተውን አለመግባባት ብፁዓን ጳጳሳት በአንክሮ ተመልክተው ወደ ዕርቅና መተሳሰብ ጉዳይ እንዲያመሩ መማፀን ናቸው።

ስለዚህም ይህ የምእመናን ጉባኤ እንዲቋቋም ያደረግነው የምእመናን ሓላፊነት የምእመናን የሥራ ደርሻ በማሳየት ቤተ ክርስቲያኒቱን ለማበልጸግ፣ ሲኖዶስንና ካህናቱን ለማገዝ እምነታችንን ለማዳበር ይበጃል ይረዳል ብለን ነው።

*ሐመር፡- ዓለም አቀፍ የምእመናን አንድነት ጉባኤ ከተቋቋመ ስንት ጊዜው ነው? ወደፊትስ ሊሠራቸው ያቀዳቸው ሥራዎች አሉት? በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ተቀባይነቱስ ምን ያህል ነው?*

ኢንጂኒየር ተረፈ፡- ይህ ጉባኤ የተቋቋመው ኅዳር ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ነው። ከተዋቀረ ሦስት ወር ቢሆነው ነው። ጉባኤው ዳላስ ቢካሄድም ተሳታፊዎቹ ግን ከኢትዮጵያ፣ አሜሪካና አውሮፓ በተገኙ ምእመናን የተካሄደ ነው። ጉባኤው አንድ መሪ ውሳኔ አሳልፏል። የጉባኤውን ውሳኔ በሀገር ውስጥና በውጭም ለሚገኙ ምእመናንና ካህናት በትነናል። አሁን ያለንበት ወቅት የምእመናኑ፣ የቤተክህነቱን ድርሻ ምን እንደሚሆን ይጠቅሳል። አሁን እየሠራን ያለነው ዓለም አቀፉ የምእመናን አንድነት ጉባኤ መዋቅሩን በሀገር ውስጥም በውጭም ለሚመለከታቸው ሁሉ ማሳወቅ ነው። በውጭ ለሚገኙት ጳጳሳትም ለሁሉም አቅርበናል። ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስም የምእመናኑን አንድነት መዋቀር እንዲያውቁልን፣ ቡራኬያቸውን እንዲሰጡን የቤተክርስቲያኒቱ ደጋፊ መሆናችንን እንዲያውቁልን ውሳኔውን በአክብሮት ሰጥተናቸዋል። ይህንን ጉዳይ ምእመናኑ፣ ካህናቱ፣ ጳጳሳቱ በያሉበት እንዲያውቁ አድርገናል። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስም ጉዳዩን ለሲኖዶስ አቀርባለሁ ብለውናል።

*ሐመር፡- አሁን በአባቶች ዘንድ በተፈጠረው መወጋገዝ /መለያየት/ በግልዎ ምን ተሰማዎት? እርስዎ ሚመሩትስ ጉባኤ ያለው አመለካከት ምንድን ነው?*

ኢንጂኒየር ተረፈ፡- በግሌ በጣም በጣም ነው ያሳዘነኝ። መደረግ የማይገባው ነገር ነው የተደረገው። ጉባኤው ሲሰበሰብ ከወሰናቸው ውሳኔዎች አንዱ አባቶች በመካከላቸው በተፈጠረው ችግር ዙሪያ እንዲወያዩ ተማፅኖ ማቅረብ ነበር። እንዲያውም መነሻ ያደረግነው በቅርብ ጊዜ በቤተ ክርስቲያንና በክርስቲያኖች ላይ በደረሰው የአክራሪ እስላሞች ጥቃት ጉባኤው አንሥቶ ሲወያይ ይህንንም ጉዳይ አንስተነው ነበር። አገር ውስጥም ውጭም ያሉ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ልዩነታቸውን አስወግደው ምእመናንና ቤተ ክርስቲያን የሚያቃጥል የአክራሪ እስላሞች ጥቃት ዙሪያ እንዲወያዩና እንዲመክሩ የሚል በጽሑፍም በቃልም ለሁለቱም ወገኖች አቅርበን ነበር። በዚህ ሁኔታ እንዳለን አሜሪካን የሚኖሩ ጳጳሳት ተጨማሪ ጳጳሳት ሊሾሙ ነው የሚል ወሬ ስንሰማ፣ ይህ መሠረታዊ የቤተ ክርስቲያን ህልውና ጉዳይ ነው፤ በቅድሚያ ውይይት ይደረግ ከዛ በኋላ ወደ ውሳኔ ብትሔዱ ይሻላል፤ ብለን አሳስበን ነበር። እኛ እናስታርቅ አይደለም ያል ነው፤ እኛ አባቶች የመንጋው መሪ እንደመሆናችሁ መጠን ጉዳዩን አስቡበት፤ ተነጋገሩበት ነበር ያል ነው። በዚህ ስንማፀን /ስንለምን/ ከዛ አልፎ ተርፎ የተፈጠረው ክስተት በጣም የሚያሳዝን ነው። አባቶች በመልካም ምሳሌ ልጆቻቸውን እንዲመሩ ሐዋርያዊ ሓላፊነት ተጥሎባቸዋል የሐ.ሥራ.፳+፳፰። በተቃራኒው መንገድ መሔዳቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂ ያደርጋቸዋል። ምእመናን መከተል ያለባቸው እምነታቸውን ብቻ ነው። ሁኔታው ጉባኤውን አስጨንቋል፤ ጠቅላላውንም ምእመናን እጅግ አሳዝኗል። ምእመናን ጉዳዩን መመዘን ያለባቸው ከራሳቸው ከሰዎቹ ድክመት እንጂ ከእምነቱ እንዳልሆነ መረዳት አለባቸው። እኛ ምእመናን መመልከት የሚገባን ትምህርተ ወንጌልን ነው እንጂ በየጊዜው ያሉ የቤተክርስርቲያን መሪዎች ክፍተት ሲፈጥሩ የምእመኑ አንድነት ላይ ክፍተት መፈጠር የለበትም። መታመናችን በልዑል እግዚአብሔር እንጂ በሰዎች አይደለምና። አሁንም ቢሆን በእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ሰላም ወደ ጽድቅ ለመምጣት ጳጳሳቱ የግል ልዩነታቸውን ትተው ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን ብለው እንዲወያዩ አጥብቀን አደራ እንላለን። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ለሁለት ሺሕ ዓመት አንድ ሁና ስትኖር ዛሬ በዚህ አጋጣሚ መከፋፈል የመጣ እንደሆነ ለታሪካችንም ለቤተ ክርስቲያናችንም በጣም የሚያሳስብ ነው። ስለዚህ ያለውን አደጋ፣ የሚያስከትለውን ችግር ተገንዝበው አባቶች ቢወያዩ፣ ቢነጋገሩበት አንድ መፍትሔ ይገኛል ብዬ አምናለሁ።

*ሐመር፡- በውጬ ዓለም የሚኖሩ የምእመናን አስተያየት ምንድን ነው? የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት እና ቤተ ክርስቲያንም አንድ እንድትሆን ምን መደረግ አለበት?*

ኢንጂኒየር ተረፈ፡- በውጭ ሁሉም ምእመናን ተጨንቀዋል፣ በጣም ደንግጠዋል፤ አዝነዋል። ይህ ሁናቴ ሊቀጥል አይችልም። ስለዚህ የችግሩ ዋነኛ ባለጉዳዮቹ ጳጳሳቱ ናቸው። ጥናትም እንደሆን ይጠና፤ አማላጅ ያስፈልግም ከሆን ይላክ፤ ሰላም እንዲወርድ ሁሉም ምእመናን ይፈልጋሉ። በአሁኑ ጊዜ ሱባኤ የሚገባበት፣ የሚጸለይበት ወቅት ነው። ይሄ የኮንፍረንስ ጉዳይ አይደለም፤ ተጠራርቶ ተሰባስቦ ውሳኔ የማሳለፍ ጉዳይ አይደለም። አሁን የሚያስፈልጋው ይህን ችግር ከመንፈሳዊ ዕይታ አንጻር ለቤተ ክርስቲያን፣ ለምእመናኑ ስንል ወደ ሰላም መምጣት ከሁሉም ወገን ይጠበቃል። በአሁኑ ወቅትም በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ለተከሰተው ችግር ምእመኑ ሁሉም ማዘን፣ ማልቀስ፣ አለበት።

*ሐመር፡- በጳጳሳቱ መካከል ተቀራርቦ የመነጋገሩ እድል ጠባብ ይመስላል። ሦስተኛ አካል መግባት እንዳለበት የሚያሳይ ነገርም አለ። የምእመናን አንድነት ጉባኤ ለዚህ ችግር መፈታት በመሸምገልም በኩል ድርሻው ምንድን ነው?*

ኢንጂኒየር ተረፈ፡- አዎ አስጨንቆናል አስበንቢታል። አሁንም ቢሆን ሁለቱንም ወገን ከማነጋገር ወደ ኋላ አንልም። እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው የእኛ ወይም የሌሎች ጥረት ስምረት የሚኖረው ባለጉዳዮቹ ጳጳሳቱ ተነሣሽነት ሲኖራቸው ነው። ጥንትም እኮ ቤተ ክርስቲያንን በችግር ጊዜ የሚጠብቋት ምእመናን ናቸው። ስለዚህ ዝም ማለት የለባቸውም ለተፈጠረው ችግር መፍትሔ መፈለግ ይጠበቅባቸዋል። ስለዚህ እኛ ደጋግመን የምንለው ጉዳዩ ለሚመለከታቸው በውጪም በአገር ውስጥም ላሉት የምናቀርበው ጥሪ ችግሩን በሰላም ለመፍታት በጠረጴዛ ዙሪያ ቁጭ ብሎ ለመወያየት እና ችግሩን ለመፍታት ረጅም ጊዜ መስጠት የለበትም ነው። ይህቺ በብዙ ዘመን አልፋ ለዛሬ የበቃችው ጥንታዊት ቤተ ክርስርቲያን ማነህ በማነህ እንደትከፋፈል መሞከር በጣም አሳዛኝ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ እነዚህን አባቶች ሥልጣን ላይ የምናውቃቸው ከሃያ፣ ከሃያ አምስት ዓመታት ወዲህ ነው። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ግን በክርስቶስ መሠረትነት ብሉይ ኪዳንን ከሐዲስ አስተባብራ ለመላው የሰው ልጆች ደኅንነት የቆመችው ከሁለት ሺሕ ዓመታት ጀምሮ ነው። ታዲያ በሰዎች ልዩነት የቤተክርስቲያናን አንድነት መፈታተን ተገቢ ነው? እኔ ተገቢ ነው አልልም። አሁንም ይወያዩ። ካልተወያዩ ክፍተቱ ሥር ይሰዳል። አደጋም ይኖረዋል።

*ሐመር፡- እርስዎ እንዳሉት የምእመናኑ ድርሻ ትልቅ ነው። ምእመናኑን ስለ ጉዳዩ ያላቸው መረዳት እርስ በርስ የሚያደርጉት የመረጃ መለዋወጥ ችግሩን ለማስፋትም ለማጥበብም የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አለው። ከዚህ አንጻር ምእመናኑ ሊከተሉት የሚገባው አቅጣጫ ምንድን ነው? የአንድነት ጉባኤውስ በዚህ ዙሪያ ምን እያደረገ ነው?*

ኢንጂኒየር ተረፈ፡- ምእመኑ ላይ በርግጥ አስጨናቂ፣ ጉዳይ ፍርጅብኝ ነው የደረሰበት። ሆኖም በተፈጠረው ክስተት እምነታቸውን መተውና መደናገጥ የለባቸውም። ለቤተ ክስርቲያኗ አንድነት ምእመናኑ ከፍተኛ ሓላፊነት አለባቸው። የቅድስት ቤተ ክርስቲያኗን ተቆርቋሪ የሆኑ ወገኖች ሁሉ በተለይም ምእመናን ካህናቱም አሁንም ቤተ ክርስቲያኗ እንዳትከፈል ብዙ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋቸዋል። እንደ እውነቱ ከሆነ አንድነት ነው እንጂ የሚያስቸግራቸው መከፋፈል በጣም ቀላል ነገር ነው። የኢትዮጵያ

ወደ ፴፮ ገጽ ዞሯል



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የእስልምና እና የአክራሪ እስልምና ገጽታ በኢትዮጵያ

## ኢትዮጵያውያን ነገሥታትና ክርስቲያን ምእመናን በእሰላሞች ላይ የፈጸሙት ግፍ ይኖር ይሆን?

*በንፋይ ስሜ*

*ባለፈው እትማችን የአክራሪ እስልምና እንቅስቃሴ ምንጩ ሁልጊዜም የውጪ ኃይል መሆኑንና በኢትዮጵያም በተነሡባቸው ዘመናት ሁሉ የደረሱባቸው [illegible]ቶች በግራኝ ጊዜ ደግሞ እነርሱ ያደረሱትን ጥፋትና ውድመት ተመልክተን ነበር:: በዚህ ዕትም ደግሞ የኢትዮጵያ ክርስቲያን ነገሥታት በሃይማኖትም ምክንያት ምንም ጫና አድርገው የማያውቁ መሆናቸውን አይተን እንፈጽለን::*

### የባሕር ማዶዎቹ አክራሪዎች በይፋ ጥቃት የከፈቱበት ዘመን

ብዙም ሳይቆይ በወኪላቸው በኩል ሐሳባቸው ያልተከናወንላቸው ቱርኮች በዐፄ ሠርፀ ድንግል ጊዜ በምፅዋ ስተት ብለው በመግባት ከሐዲውን ባሕረ ነጋሽ ይስሐቅን በመጠቀም የለመዱትን የግዛት ማስፋፋትና የባህል ወረራን በደም ማፍሰስ ለማሳካት ተጣጣሩ:: ሕዝቡን በጦር ጨፈጨፉ አሰለሙ /ላጺስ ዴሌቦ፣ የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና መንግሥት ታሪክ ፩ኛ መጽሐፍ /አዲስ አበባ፣ ፲፱፻፹፪/ ገጽ ፩፻፹፪፣ ፩፻፺፩/ በዚህ ጊዜ ነበር ለኦርቶዶክስ ሃይማኖት ሲሉ ታሪክ ሊረሳቸው የማይችል የቁርባን፣ የጊዮርጊስ ኃይሌ፣ የአቄትዝር፣ የኮከብ እና አፍሮ አይገባ ሃይማኖታዊና ወታደራዊ ቡድኖች ወይም ጨዋዎች /Templars/ በመነሣት ከቀይ ባሕር ዳርቻ ሆኖ በኢትዮጵያውን ደጅ ሲያደባ የነበረውን የቱርኮችን ምዕአታዊ እቅድ እንደ አውሎ ነፋስ በኃይል ወደ ኋላ ገፍተው የመለሱት:: /Ibid, pp.182,186,188,192,194/ በዚያም ሰዓት ከቁርባኖችና ከጊዮርጊስ ኃይሌዎቹ ጋር ሆነው በቱርኮች ላይ የተሰለፉት መለሳይ በመባል የሚጠሩ የእስላም ተቀጣሪ /Mercenary/ የአዳል ወታደሮች ናቸው Ibid, pp 121,189

ይህ በጠቅላላው ብዙ መቶ ዓመታትን የፈጀው የጠላት ሴራ ኢትዮጵያን አድክሞ ከመታት በኋላ ሥልጣኔ፣ ሥርዓት፣ ማእከላዊ መንግሥት፣ የሃይማኖት ኅብረት እንዲሁም የአገር አንድነት የመሰለው ሁሉ አንድ በአንድ እየወደቀ ለዘመነ መሳፍንት ጨለማ አሳልፎ ሰጣት:: ጊዜው እንዲያ እንዲያ እያለ ሄዶ የዐፄ ቴዎድሮስ ዘመን ደረሰ:: በደባርቅ ጦርነት ከግብፆች ጋር ተዋግቶ በመሸነፉ /፲፰፻፵፰/ የቆሰለው ቴዎድሮስ ለቱርኮችና ግብጾች ያለውን ፅኑ ምሬት እያብሰለሰለ በድሉም ጊዜ «የኢትዮጵያ ባል የኢየሩሳሌም አጮኛ» ብሎ ሲፎክር ቆይቶ አንድ ቀን ባሕር ተሻግሮ ደሙን ሊመልስ ሲያልም ቆይቶ አረፈ:: /Bahru Zewde, A History of modern Ethiopia: 1855-1991 (Oxford, 1991) P.28

### ኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ውስጥ አክራሪነት ያለው እውነታ ምንድን ነው?

በዐፄ ዮሐንስ ዘመን የግብጽ የሦስት አቅጣጫ ወራሪ ኀይል በጉንደትና /፲፰፻፷፰/ ጉርአ /፲፰፻፷፰/ ጦርነት ተዋርዶ ድል ሲነሣ የቅኝ ግዛት ሕልምዋን በአክራሪ እስልምና ስም ለጥፋ መፍጨርጨርዋን ከነበሩት መካከል የአፋር /የደንከል/ ሕዝቦች ይገኙበታል:: በሙዚንገር የሚመራውን የግብጽ ጦር ከታጁራ ተነሥቶ አፋር በረሃ ውስጥ እንዳለ ለወሬ ነጋሪ ሳያተርፍ የፈጁት እስላሞቹ አፋሮች ነበሩ:: /Bahiru Zewde:pp.50-53)/ ይህ ሁሉ መረጃ ኢትዮጵያዊው የእስልምና ማኅበረሰብ በኢትዮጵያ ያለውን እስልምና ኢትዮጵያዊ መልክ እንደሰጠውና ጠላት በመጣም ጊዜ ሀገሩን የሚያስቀድም መሆኑን የሚያሳይ ነው:: በአንጻሩ ደግሞ ከውጭ የሚመጣው የእስልምና እንቅስቅሴ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊ መልክን ለመለወጥ እስከ መጨረሻ ሲታገል ኑሯል::

የሱዳኖቹም መሐዲዎች ግብጽ ያልተሳካላትን አክራሪነት አንግተው በሳር ውሃ ጦርነት /፲፰፻፹፩/ አልፎ ተርፎም ጎንደር ድረስ ብዙ እልቂት ማስከተላቸው ለዚህ ምስክር ሊሆን ይችላል:: በዚህም ሰበብ በመተማው ጦርነት ዐፄ ዮሐንስ ሰማዕትነት መቀበላቸው ይታወሳል:: Ibid,p.59

### በእስልምናው ላይ የተፈጸመ ጥቃት ይኖር ይሆንን?

በአብዛኛው ጊዜ አክራሪዎች ወንጀል የሆነውን ጭፍጨፋ ፈጽመው እልቂትን ካስከተሉ በኋላ ለምን ይህን አደረጋችሁ ሲባሉ «ዐፄ ዮሐንስ እኛን እንዲሁ አድርጉብናል» የሚል መልስ ይሰጣሉ:: ታሪኩን በደንብ ከተመለከትነው ግን በኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ላይ የተነሡት ዐፄዎች በሃይማኖት ማስለወጥ ጉዳይ አንድም ሰው እንዳላረዱና እንዳላቃጠሉ አያሌ ማስረጃዎች አሉ::

በእርግጥ ከቦሩ ሜዳ ጉባኤ በኋላ ዐፄ ዮሐንስ በሁለት ወገን አዋጆችን አውጥተዋል:: አንደኛው «የጸጋና የቅባት» ኑፋቄ የሚከተሉ ይህንን ትምህርት እንዳያስተምሩ ሲሆን፤ እስላሞቹ ደግሞ ወደ ክርስትና ዞረው እንዲጠመቁ አዘዋል:: ይህ ድርጊት በይዘቱ ፖለቲካዊ ቢሆንም ሳይፈጽሙ የተገኙ ቢኖሩ እንኳን ከእርስት በመነቀልና በንብረት ውርስ ብቻ እንዲቀጡ እንጂ ይጨፍጨፉ ያሉበት ምንም አዋጅ የለም፤ ድርጊቱም አልተፈጸመም:: /Bahru Zewde,p.48/

እንዲያውም በቦሩ ሜዳ ክርክር ወቅት ንጉሡንና ሊጋባውን የተሳደቡትን በአካል ሲቀጡ ያዩ ሌሎች ነገሩ ስላልገባቸው ሁሉም ተይዘው በተመሳሳይ መንገድ ይሙቱ ቢሉዋቸው «ለዶግማዬ ብዬ ሰዎችን አልገድልም:: ነገር ግን ሃይማኖቴን በመከላከል እሞትላታለሁ.» እንዳሉ ታሪክ ስለሚመሰክር ምን ያህል ያለ ሥራቸው የታመኑ ንጉሥ መሆናቸውን ያረጋግጣል:: R.A. Caulk, Religion and State in Nineteenth century Ethiopia. (Journal of Ethiopian studies)Vol.x, No.1./Addis Ababa, 1972/ p.25.

አልፎ ተርፎም ዛሬ «ዮሐንስ ጨቁኖናል» ብለው የሚናገሩ ነገሩን ያልጠነቀቁና ለርካሽ ዓላማ ባልተጻፈ ታሪክ የሚያራግቡትም ቢሆኑ ሊያውቁት የሚገባ ነገር አለ:: ዐፄ ዮሐንስ ለንጉሥ ምኒልክና ለያኔው ራስ አዳል በላኩት መልእክት ሁለቱም በግዛቶቻቸው ባሉት እስላሞች ላይ ጠንካራ የሆነ እርምጃዎች እንዳይወስዱና በወሎ እኔ <መሐመድ አሊን> ራስ ሚካኤል እንዳልኩት ሁሉ መሪዎቻቸውን ብቻ ክርስትና አንስታችሁ ሌሎቹ እነርሱን እንዲመስሉ ሥሩ በማለት ለማዘዛቸው ግልጽ የታሪክ ማስረጃ አለ:: Ibid, p26; Zawde Gabra seelase The Process of Re-unification of the Ethiopia Empire, 1886-1989 PHD dissertation (oxford, 1971) p.221 ይሁን እንጂ በዚያ ዘመን የዐፄ ዮሐንስን የሃይማኖት አንድ ወጥነት ፖሊሲ ዙሪያ «እስላሞች ተጨፈጨፉ» ብለው ወሬ ሲያራግቡና የፕሮፖጋንዳ ሥራ ሲሠሩ የነበሩት የግብጽ ጋዜጠኞችና መሪዎች ነበሩ:: ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፤ ዐፄ ዮሐንስ እና የኢትዮጵያ አንድነት /አዲስ አበባ፤ ፲፱፻፹፪ እ.ኤ.አ/ ገጽ ፪፻-፪፻፷ሕ፭/

የግብጽ ጋዜጠኞችና መሪዎች ይህን ያሉበትን ምክንያት በደንብ ስንመረምረው ደግሞ ከጀርባው ሌላ ታሪክና ገጽታ እናገኛለን:: ብዙ ምሁራን እንደሚስማሙበት ቀናተኛው ዐፄ ዮሐንስ የሃይማኖት አንድ ወጥነት ፖሊሲ ያወጡት አክራሪ ክርስቲያን ስለነበሩ እና እስላምም በሀገሬ መኖር የለበትም ብለው ሳይሆን በዘመኑ የነበረውን የሱዳን መሐዲስቶችና የግብጽ ወራሪ እስላሞችን ለመከላከል ያደረጉት ዘዴ ነበር:: እንደ እርሳቸው እምነት ኢትዮጵያን ቅኝ ለማድረግ የሚመኙት ሁሉ ከአገር ውስጥ ባለው የሃይማኖት ክፍተት ይጠቀማሉ ብለው በመስጋታቸው በፖለቲካዊ ብስለት ችግሩን ለመመለስ ያደረጉት ጥረት መሆኑ ግልጽ ነው:: ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ ገጽ ፩፻፲፪-፩፻፲፫፤ M.Abir; Ethiopia the Era of the princes: The challenge of Islam and the Re-unification of the Christian Empire 1769-1855 (London, 1968), pp.112-116; R.A. Caulk, pp.25,30-31

ይህም ጉዳዮ የሃይማኖት አክራሪነት ሳይሆን የፖለቲካና የተጢያቂነት እንደሆነ ግልጽ አድርጎ ያሳየናል:: በእውነትም አክራሪ እስልምና ክርስት መፈናቀልን በእርሱ ሲደርስ እንደሞት ቆጥሮት ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን በዘመኑ የአሁኑ ዓይነት አክራሪነት ሰፍኖ ቢሆን ኖሮ ነገሥታቱ ቸል

ብለው ሊያዩት እንደማይችሉ የታወቀ ነው:: ይህ ቢሆን ኖሮ ደግሞ ባላቸው የጦር ኃይል ብቃት እንኳን በወሎ ብቻ ያለው ይቅርና በመላው ኢትዮጵያ ያለው እስላም መትረፉ ያጠራጥራል:: በግራኝና በሌሎች የእስ ላም መሪዎች የተፈጸመው ግፍ ግን አገ ራቱን ምድረ በዳ የማድረግ ሥራ ነበር:: «ካስታንሆዞ»፣ ዶ/ር ካሚል ሙራድና አቶ ዮና ቦጋለ፣ ገጽ ፳::

ዐፄ ዮሐንስ እንዲህ ዓይነት ድርጊት ሳለመፈጸማቸው ግን ሌላም ተጨማሪ ማስረጃ አለ:: ዐፄ ዮሐንስ ራሳቸው በጻፉአቸው ደብዳቤዎች ከአሕመድ ግራኝ ወዲህ የኢትዮጵያ ነገሥታት እየተዳከሙ በመሔዳቸው እስላሞቹ /ቱርኮች/ እያየሉ መሔዳቸውን ጠቅሰው እንዲህ ይላሉ:: «የግብጽ መንግሥት በያለበት ከቦኛል ... አሁንም የግብጾች ሐሳብ በእጃቸው ያለውን የኢትዮጵያን ግዛት በሙሉ ለመውሰድ መሆኑን አመለከቱ::» ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ ገጽ. ፩፻፲፪-፩፻፲፫ የንጉሡን ሥጋት እውነታ የሚያሳይ ተጨማሪ ማስረጃ ደግሞ በወሎ ከነበሩት የእስልምና መሪዎች መካከል መሐመድ ካኒኪ ከውጭ ሙስሊሞች ጋር የጦር መሣሪያና የንግድ እርዳታና ትብብር እንደነበራቸው በታሪክ የተመዘገበ ሐቅ ነው:: R.A. caulk p.35 see Foot notes and notes 75. ንጉሡ ደጋግመው ስለ ግራኝ መናገራቸውና የቦሩ ሜዳም ጉባኤ ከሌላም ልምድ የተማሩትን እውነታ ያሳያል:: ዐፄ ቴዎድሮስ ሲሞቱ በመቅደላ አንባ የተረፈውን የወሰደችው ሙስሊምዋ መስታወት ክርስቲያኑን ሕዝብ የወጋች መሆንዋን የሚያውቁት ዐፄ ዮሐንስ በግራኝ ዘመን እንደተፈጸመው ሁሉ እንኝህም ከግብጽ በሚደረግ እርዳታ ሊነሡ ይችላሉ የሚል ሥጋት ነበራቸው:: ስለዚህ ይህን ፖለቲካዊና ሀገራዊ ሁኔታ በአስተማማኝ ሁኔታ ለመጠበቅና ወሎንም ለባዕድ አሳልፎ ላለመ ስጠት በነበራቸው ሐሳብ የታወጀ የፀጥ ታና የብሔራዊ አንድነት /Nationalism/ ግንባታ ፖሊሲ ነው:: ተክለ ጻድቅ፣ ገፅ ፰፱ /see: letter of king Menilek/ ይህ ደግሞ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታን እየቃኘ ከሚሔድ መሪ ሁሉ የሚጠበቅ ነው:: እንዲያውም ሊያስገርመን የሚገባው ይህን ባያደርጉ ነበር::

አክራሪዎች ወንጀል የሆነውን ጭፍጨፋ
ፈጽመው አብቂትን ካስ ከተሱ በኋላ
ስምን ይህን አደረጋችሁ ሲባሉ «ዐፄ
ዮሐንስ እኛን እንዲሁ አድርጉብናል»
የሚል መልስ ይሰጣሉ:: ታሪኩን
በደንብ ከተመለከትነው ግን በኢትዮጵያ
ዘመናዊ ታሪክ ላይ የተነሡት ዐፄዎች
በሃይማኖት ማስለወጥ ጉዳይ አንድም
ሰው እንዳሳረፉና እንዳሳቃጠሉ አያሴ
ማስረጃዎች አሉ::

ሌላውና አስገራሚው እውነታ ደግሞ ከእስልምና ወደ ክርስትና የመጡት አብዛኛዎቹ በፈቃዳቸው መሆኑ ነው:: ይህንንም ሁኔታ በንጉሡ ደብዳቤ ላይ ማየት ይቻላል::

«ሸዋ ዘምቼ ሳለሁ እኛ ክርስቲያኖቹ በሃይማኖት ተከራክረን እረተን ወደ እስክንድርያ ሃይማኖት አገባናቸው:: እስላሞቹም ይህንን አይተው ለኛስ አባት የለንምን?» ስለዚህ ያጥምቁን ክርስትና ያስነሱን ብለው ለመኑኝ:: እሺ ከፈቀድክ ከወደድህስ ክርስትና ግባ ብዬው የኢትዮጵያ እስላም ሁሉ ወዶ በፈቃዱ ክርስቲያን ሆነ:: አንድም ነገር በኀይል ያደረግሁት ነገር የለም ወዶ በፈቃዱ ነው እንጂ የገባው:: ጌታ በወንጌል ሲጽፍ በኀይል አድርጉ አላለም አላዘዘም» ሲሉ ከአስመራ ከተማ ኅዳር ፲፩ ቀን ፲፰፻፸፪ ዓም ጽፈዋል:: Public Records office london F095-7 38-12-99

ቅሉ ይህ ማስተባበያ ነው የሚል ክፍል ስለማይጠፋ ከአክራሪ እስልምና ማጠናከሪያ እንዲሰጥበት ሌላ እማኝ እንጥራ:: በጎንደር ዘምቶ የነበረው የመሐዲስቶች መሪ ከተማዋን ካቃጠለ በኋላ አንዳንድ እስላሞች ሊቀበሉት ወጡ:: ከእነርሱም መካከል የተጠመቁትን ተመልክቶ «እናንተ ሰዎች ዮሐንስ በግዛ ፈቃዳችሁ ብትወድዱ እንድትጠመቁ ባትወዱ እንዳሻችሁ ሁኑ ብሎ ነበር:: እናንተ ግን ተጠመቃችሁ:: ስለዚህ ለሰዎቼ መጥፎ ምሳሌ /አርአያ/ ትሆናላችሁና ከኔ ሂዱ» እንዳላቸው ታሪክ ሕያው ምስክር ነው:: R.A Caulk, /p.28/

በቦሩ ሜዳ አዋጅም በፈቃዳቸው ወደው ክርስትና ከተነሡት መካከል ራስ ሚካኤል አንዱ እንደነበሩ በዘመኑ ሚሲዮናውያን የማጣራት ጥያቄ ተረጋግጦአል:: ሚስዮናውያኑ ራስ ኀይለ ማርያም ግን ለሥልጣናቸው ሲሉ ነው እንጂ ለሃይማኖት ደንታ የላቸውም ብለዋል:: Ibid. p.24

በዐፄ ምኒልክም ዘመን ሐረርጌን፣ ጅማን፣ አርሲን፣ ባሌን፣ በያዙበት ወራትም ሆነ በሌላ ጊዜ አንድንም ሰው አስገድደው ሃይማኖት የማስለወጥ ሥራዎችን አልሠሩም:: በርሳቸው ዘመን ግን በላስታ የተወለዱት ሼህ ዘከርያ መጻሕፍትን በመመርመርና በፈቃደ እግዚአብሔር ወደ ክርስትና ተመልሰው ወገኖቻቸውን በማስተማር ብዙ እስላሞችን በወንጌል በማሳመንና በማስጠመቅ ራሳቸውን እንዲመስሉ አድርገዋል:: በዚህ ሥራ የተበሳጩት ሌሎች እስላሞች ደግሞ ሃይማኖታችንን አጠፋ፣ ብለው ዐፄው ድረስ በመሔድ ከሰሱዋቸው:: ንጉሡም የተማሩት እስላሞች ቀርበው ተከራክረው እንዲያሳምኑት ፈቀዱላቸው:: የተባሉት የእስልምና ምሁራን በመጡ ጊዜ ግን ሼሕ ዘከርያን ሊያሳምኑ ቀርቶ በሚያስደንቅ ሁኔታ ተረቱ:: እስላሞቹ ግን ከአንዴም ሦስት ጊዜ ይግባኝ እያሉና ከግብጽ፣ ከዐረብ፣ ከኢራንና ሕንድ ድረስ ሊቃውንት እንጥራ እያሉ በእስልምና ሃይማኖት ቢከራከሩ ሼህ ዘከርያ አሁንም ረቱዋቸው:: ወዲያውም አባ ዘካርያስ ተብለው የአለቅነት ማዕረግ ተሰጣቸው:: ተሸናፊዎቹም በጉባኤ አንድን ሰው ማስተማር አትችልም ከምትሉት ርቱት ስትባሉ ከዓለም ላይ ሁሉ መጥታችሁ ከተረታችሁ የማስተማር ሥልጣን ይገባዋል ብለው ፈረዱ:: /ገብረ ዕድ ኤርምያስ ከበደ፣ ኢትዮጵያ የዓለሙ መፋረጃ /፲፱፻፺፫/ ገጽ ፪፻፺፯ -፫፻፯/ እውነታው ይህ ነው:: ክርስቲያን ነገሥታቱ አስገድደው ያሰለሙት የለም:: ቁርዓንን መርምረው ሐሰተኛ ናት ብለው ወደ ወንጌል የገቡት ግን ብዙ እስላም ወገኖቻቸውን አስተምረው አሳምነው አጥምቀዋል::

በተገላቢጦሹ ግን አባ ጅፋር በጅማ ለንግድ የመጡትን ክርስቲያን ነጋዴዎች ሁሉ አስገድዶ ያሰልም ነበር:: ዐፄ ምንሊክም ለአባ ጅፋር ከዚህ እንዲታቀብ አዝዘው አስቆሙት እንጂ አንዳችም የአጸፋ እርምጃ አልወሰዱም:: ጳውሎስ ኞኞ፣ ዐፄ ሚኒልክ /አዲስ አበባ ፲፱፻፹፩/ ገፅ ፴፪::

ዐፄ ኀይለ ሥላሴ ጋርም ስንደርስ ታዋቂ ከሆኑበት ንግግር መካከል «ሀገር የጋራ ነው ሃይማኖት የግል ነው» የሚለው ነው:: በዘመናቸው ከላይ ያየነውን ዐይነት ፕሮፓጋንዳ ስለ ተስፋፋ ያንን አስመልክቶ እስላሞች ራሳቸው ስለ ሃይማኖት መብታቸው እንዲመሰክሩ ተጠይቀው አርባ ዘጠኝ የሚሆኑ የእስላም ዲፕሎማቶች፣ ወረዳ አስተዳዳሪዎች፣ የአፋርና የመሳሰሉት ብሔር መሪዎችና ባላባቶች፣ የእስልምና ሃይማኖት መሪዎች፣ የየመን የንግድ ሰዎች የእስልምና ትምህርት ቤት ዳይሬክተር ሌሎችም ሙሉ ነጻነትና መብት ውስጥ እንዳሉ የመሰከሩበት ግልጽ መረጃ አለ:: በኢትዮጵያ ላይ የእስላሞች ነጻነት በዐፄው ተደፍሮአል ብሎ አለባልታውን የነዛው አካል ግን የመላው ዓለም አቀፋ ስድስተኛው የሙስሊሞች ኮንግረስ ተብሎ የሚታወቀውና በሞቃዲሾ ስብሰባው ወቅት ሲአድባሬን መሪ ተናጋሪ አድርጉ የተሰበሰበው ድርጅት ነበር:: ታዲያ ይህን መሰሉ ወሬ ለምን እንደተሰነዘረ የሰዎቹ ማንነትና በኋለኛው ጊዜ የሠሩት ሥራቸው ሁላችን በምናውቀው መልኩ የበለጠ ያብራራዋል:: *Ministry of Information. Religious Freedom in Ethiopia (Addis Ababa, 1965) pp.7,17,49-91.* ታሪካዊ እውነታው ይሄ ሆኖና ይህም እውነት ከእነርሱ ሳይሰወር የአሁኖችን አክራሪዎች ምን ቀሰቀሳቸው? ትናንት በጅማ የፈጸሙትስ ጉዳይ እውነተኛ ዓላማው ምንድን ነው? የወደፊት ዕቅዳቸውስ?

## ትናንት የፈሰሰው ደም በዳር አገር ያለ የክርስቲያን ወገን ነው:: ነገስ?

እንዲህም እንዲያም እያልን ወደ ዘመናችን ስንመጣ የአክራሪነት አባዜ የተጠናወታቸው ጥቂት ቅጥረኞች እንደ ቦይውኃ ሌላውንም እስላም ወደ እልቂት ለመምራት እየባዘኑ በሰላም የመኖር ሕልም ያለውን ሕዝበ ክርስቲያን ሲያውኩ ይታያሉ:: እነዚህ ግለሰቦች በከሚሴ፣ በአፋር፣ በአርሲ /ኮፈሌ፣ ቆሬ/ በሐረር፣ በጉራጌ ዞን፣ በአሰቦት ገዳም እንዲሁም አሁን በጅማና በኢሉባቦር ዞን ለዐሥራ ሦስት ዓመታት ያደረሱትን ጭፍጨፋ ፈጽመን አንረሳውም::

ወደ ፴፰ ገጽ ዞሯል

# ዜዋዌ መጻሕፍት ወሐተታ ምስጢራት

## በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የደረሰው ስደት፣ ዘረፋና ቅሰጣ ምስጢረ መጻሕፍትን በመመርመር ሲታይ

መ/ር ደሴ ቀለብ

ሀገራችን ኢትዮጵያ የራሷን ፊደል፣ አኀዝ ያደላደለች እመቤት እንደመሆኗ በሥነ ጽሑፍ ያደገና የበለጸገ ሀብት እንዳላት መዛግብት ያስረዳሉ። ለዚህ ሥልጣኔ ደግሞ ግንባር ቀደሙን ሚና የምትጫወተው ቤተ ክርስቲያኗ መሆኗ ለማንም ያልተሰወረ ነው። ሊቃውንቱ፣ ነገሥታቱ፣ እቴጌዎቹ፣ መኳንንቱ፣ አበው፣ እማቱ፣ መምህራኑ፣ አርድእቱ፣ ወራዙቱ፣ ወይዛዝርቱ ኹሉም የየበኩላቸውን በባህል ማኅሌታ ያበረከቱት ድርሻ ላቅ ያለ በመሆኑ ለአፍሪካውያን ኩራት ሊሆን የሚችለው ሁለገብ የዕውቀት ዕሴት በየትውልዱ እና በየአዝማኑ ሳይቋረጥ ሲተላለፍ ነው።

ይሁን እንጂ እንደሚታወቀው በሀገራችን ኢትዮጵያ ያሉ መዛግብቱ፣ ዜናተ መዋዕላቱ፣ የሃይማኖት መጻሕፍቱ፣ የፍልስፍና መጻሕፍቱ... በየዘመናቱ ከሀገራቸው ሲፈልሱ፣ ሲሰደዱ ቆይተዋል። የሀብታቱ በቅሰጣ፣ በዝርፊያ መወሰድ ቤታችንን ለባዶነት ከመዳረጉም በላይ ታሪካችን፣ ትምህርተ ነገረ ሃይማኖታችን፣ ባህላችን ለማወቅ፣ ለመመርመር አልፎ አልፎም ሙሉ በሙሉ በአውሮፓውያኑ ጥገኛ የምንሆንባቸው ጉዳዮች እንዲኖሩን አስገድዶናል። ይህም የሆነው ከግራኝ ዘመን በፊት፣ ጊዜ፣ እና በኋላ ባሉ ዘመናት ካለን ውጫዊ ግንኙነት ተከትሎ ሲሆን ለእኛ ጥቅም ብቻ ወይም የጋራ ጥቅም ለመመሥረት የተደረገ ባለመሆኑና በአመዛኙ አውሮፓውያኑ ወይም ሌሎቹ ወዳጆቻችን ከእኛ የሚያገኙት ጥቅም ይበልጥባቸው ስለነበረ ብቻ ነው። በመሆኑም እንደ በወዳጅነት የመሠረቱት ግንኙነት ወደኋላ መልኩን ለውጦ በራሳቸው ያለው የበላይነት ስሜት አይሎ ስለበረታ ወደ አልተፈለገ ክርክር፣ ጦርነት፣... ሀገራችን በመግባቷ ለበለጠ ኪሳራና ጉስቁልና ዳርጐናል። ለምሳሌ፡- በዐፄ ቴዎድሮስና በእንግሊዞቹ፣ በዐፄ ዮሐንስና በግብጾቹ፣ በመሐዲስቶቹ ... በዐፄ ሚኒልክ ወይም ኃይለ ሥላሴና በጣሊያኖቹ የነበረን «ጤናማ» ግንኙነት ተለውጦ አብያተ ክርስቲያናት እንዲቃጠሉ፣ የተዘረፉት ንዋያተ ቅድሳትም ደግሞ በበቅሎ፣ በአህያ፣ በሰው ወዘተ እየተቀባበሉ ወደ ምዕራባውያኑ ጓዳ እንዲገቡ አድርጓል።

ቀድሞ ዐፄ ገላውዴዎስን /በ፲፮ ክ.ዘ/ ለመርዳት የፈለጉት አንዳንድ ፖርቱጋሎችም ቢሆን ከኢኮኖሚያዊ የጥቅም ግንኙነት ይልቅ ያላቸውን የኢየሱሳውያን ተልዕኳዊ ዕቅድ /Jesuits misssinories/ ለማከናወን በተቀነባበረ ስልት ባህላችን፣ ቋንቋችን... አጥንተው ውስጥ ውስጡን የታሪክ፣ የሃይማኖት ብረዛ ሲያደርጉ ቆይተዋል። ይህ እኩይ ተግባራቸውም በዐፄ ዘድንግልና በዐፄ ሱስንዮስ ዘመን አይሎ ለእነዚያ ሁሉ ሊቃውንት፣ አባቶች፣ እናቶች፣ ወንድሞች፣ እኅቶች የነገሥታት ቤተሰቦችንም ጨምሮ ለእልፈት መዳረግ ዐቢይ ምክንያት ነበር።

በእጅጉ የባሰው ደግሞ በዘመነ መሳፍንት /፲፯፻፷ዎቹ- ፲፰፻ዎቹ/ ወቅት ነበር። ይኸው ቁስል እንደገና አገርሽቶ ሊቃውንቱን በቅኔ፣ በመጽሐፍ ሲያነታርክ በምስጢረ ሥላሴ ሲያጣላ አቀያቸውና እነርሱ የደረሱዋቸውን ቅኔያት፣ የጻፏቸውን መጻሕፍት መልእክታቸውን ለማወቅ እና ሃይማኖትን ለመለየት የቤተ ክርስቲያኗን ልሳን ግእዙን ማወቅ የግድ አስባለ። በቁንጽል ዕውቀት የተነሡት ግን የጸጋውን፣ የቅባቱን፣ የተዋሕዶውን ለመለየት የሚቸገሩ ሆኑና የተደረሰው ድርሰት፣ የተጻፈው መጽሐፍ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን መስሎ ታያቸው። የኋላ ኋላ ግን የቅባቱ ከጸጋው የጸጋው ከቅባቱ እየተቀላቀለ፣ እየተመሳሰለ ማስቸገሩ የሊቃውንትን ውድነት ማመላከት ጀመረ።

ከዚህም ጋር ተያይዞ የሚያሳዝነውና መፍቀርያነ ዕውቀትን የሚያስቆጨው አብዛኞዎቹና ዋና ዋና የእንድምታ፣ የታሪክ... ዕውቀት የተቀመመባቸው ማጣቀሻ መጻሕፍት ባሕር ማዶ ባሉ የሮም፣ የቫቲካን፣ የብሪታንያ፣ የፓሪስ፣ የአሜሪካ፣ የሃምቡርግ... አብያተ መጻሕፍት፣ አብያተ መዘክር ... መገኘታቸውና ለባለቤቶቹ እና ለተመራማሪዎች የመራቃቸውና በቀላሉ ያለመገኘታቸው ሁኔታ ነው። በእርግጥ ዛሬም ቢሆን የሚመለሱ ሀብቶቻችንን ዜና አንዳንዴ በመገናኛ ብዙኀን ብንሰማም ንዋያተ ቅድሳቱ በልዩ ልዩ መንገድ በእኛው የይሁዳ ግብረ አበሮች ዘመቻም ቤታቸውን፣ ሀገረ ሙላዳቸውን ለቀው መሰደዳቸውን እና መራቃቸውን እና ዝርዋን መሆናቸውን ቀጥለውበታል።

እኛም መጻሕፍቶቻችን እንዴት እንደሆኑ፣ ምን እንደደረሰባቸው በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ያሉ መጽሐፎቻችን ምን ይመስላሉ? እንዴት እንጠቀምባቸው ብለን ጽሑፋችን ለመዳሰስ አለመሞከራችን የተፈጠረውን ክፍተት አስፍቶታል። ይህንን ክፍተት ደግሞ እኛው ራሳችን እስካልሞላነው ድረስ የእንጀራ ብቻ ሳይሆን የዕውቀትና የማንነታችን ዜና ጠባቂዎች ያደርገናል። ይህም በመሆኑ ፈረንጆቹ ያሉት ስሙር፣ ትክክል፣ በጥራዝ ነጠቅ ዕውቀት የተበየነባቸው መጻሕፍት ገለጻ፣ አስተያየት ሁሉ አግባብ እየመሰላቸው በመቀበል ወደ አልተጠና ድምዳሜ የደረሱ ራሳቸውንም በጥራዝ ነጠቅነት ወደኑፋቄው ዓለም ያስኮበለሉ ወገኖች ብዙዎች ናቸው። በትንሽ መረጃ የተሠራው ሥራ ትክክል ሊመስለው የሚችል አልያም በዚያ ጉዳይ ከኔ በላይ ዐዋቂ ላሳር ብሎ የሚያምን ቢኖር መጻሕፍትን በግርድፉ በመጻፍ ኑፋቄን እና የኑፋቄ መንገድን የሚመራበት እንዲሁም ጉዳናውን የሚያሰፋበት ሥርጥ ቢኖር ይኸው መሆኑ ነው። መመራመሩ፣ መጠራጠሩ፣ ለማወቅ መነሣሣቱ ባይከፋም ገና በመቅድሙ፣ በአርእስቱ ቆንጽሎ የተሳሳተ ትርጓሜን ከትርጓም፣ መጻሕፍትን ከመጻሕፍት፣ ቃልን ከቃል፣ ገጸ ንባብን ከገጸ ንባብ ሳያስተውል ሳያመሳክር የሚነጉደው ሰው ዱኳው ብዙ ነው። ከዚህ ችግር አንጻር በመጠኑም ቢሆን በዚህ ጽሑፍ ስለመጻሕፍቶቻችን አጠቃላይ መልክዕ፣ ጠባይ፣ ልዩነት፣ ሁኔታ፣ አንድነት እና አጠቃቀም ለመመልከት እንሞክር ዘንድ አስፈላጊ ስለመሰለን ልናቀርብላችሁ ወደድን።

### መጻሕፍትን የማሰባሰብ ታሪክ

መጻሕፍትን መሰብሰብና መለየት ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በዋናነት ታላቁ ቆስጠንጢኖስ ሮማዊ መጻሕፍትን በመሰብሰብ፣ በማደራጀት እና አብያተ ክርስቲያናትን በማሳነጽ ከዚህም አልፎ ልንቀበላቸው ከሚገባን መጻሕፍት ከውስጣቸው ማንም በፈቃዱ እንዳይጨምር እንዳይቀንስ ማስወሰኑ ይታወሳል።

ወዓዲ ፈነዋ ለእሙ እሌኒ ንግሥት መፍቀሪተ እግዚአብሔር ከመ ትኅሥሥ ዕፀ መስቀል ክቡር ዘተሰቅለ ቦቱ እግዚእነ ወመድኀኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ ስብሐት። በሀገረ ኢየሩሳሌም ቅድስት በመዋዕሊሁ ለብፁዕ አባ አይሊሙን ጳጳስ ዘኢየሩሳሌም። ወሐነፀት ዓዲ መካነ እምቀዳሚ ወሀሎ እስከ ይእዜ። ወቆስጠንጢኖስኒ ንጉሥ ዓዲ ሐነፀ ቤተ ክርስቲያን በሀገረ ብራንጥያ መአድምተ ሥን ወሠናይተ ራእይ ወኢኮነት ይእቲ ንእስተ አምጣነ አላ መልዕልተ ጥቀ። ወእምድኅረ ፈጸመ ሐኒፆታ /ለሀገር/ ቈስጥንጥንያ ሰመያ በስሙ እስመ ይእቲ ኮነት ቅድመ ትሰመይ ብራንጥያ። ወአፍቀረ ኪሪ ኀቢሃ ወረሰያ ማኅደረ ለክርስቶስ ወዳዲ አስተጋብአ መጻሕፍተ ቅዱስ ወአንበሮን ውስተ አብያተ ክርስቲያናት። ወእምዝ አስተጋብኦሙ ለቅዱሳን ፫፻፲፰ ወ፰ ርቱዓነ ሃይማኖት በሀገረ ኒቅያ ወአቀመ ሃይማኖተ ኦርቶዶክሳዊት፡- ዳግመኛም እግዚአብሔርን የምትወድ እናቱን እሌኒ ንግሥትን ምስጋና የባሕርዩ የሆነ ጌታችን እና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትን የክብረ ዕፀ መስቀልን ትፈልግ ዘንድ ላካት። በኢየሩሳሌም ሀገር ብፁዕ አባ አይሊሙን የኢየሩሳሌም ጳጳስ በሆነበት ዘመን ዳግመኛም ቤተ ክርስቲያንን አሳነፀች። ይህም እስከአሁን ድረስ አለ። ንጉሥ ቆስጠንጢኖስም ያሸበረቀች ለዐይን የምታስደስት ቤተ ክርስቲያንን በብራንጥያ ሀገር አነፀ። ይህቺውም በጣም ግዝፍት እንጂ በመጠን ያነሰች አይደለችም። ሥራዋን /ኩተማዋን/ ካጠናቀቀ በኋላም ቁስጥንጥንያ ብሎ በስሙ ጠራት። ቀድሞ ብራንጥያ ትባል ነበርና። በእርሷ ዘንድ ይኖር ዘንድ ወደደ፣ ለክርስቶስም ማደሪያ አደረጋት። ዳግመኛም የቅዱስ መጽሐፍን ክፍላት አሰባስቦ በአብያተ ክርስቲያናት አስቀመጣቸው። ከዚህ በኋላም ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንቱን ቅዱሳን በኒቅያ አሰባስቦ ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖትን አቆመ። /አጸና/። እንዲል ዮሐንስ መደብር።

ሠለስቱ ምዕት ይሄንን ሲያደርጉ መጻሕፍትን ሲወስኑ ምስጢር እንዳይብራራ አንድምታ እንዳይሠራ ሳይሆን ዓምዱ እና መሠረቱ አንድ ሆኖ ኑፋቄን ለመከላከል፣ በራስ ፈቃድ ያለመንፈስ ቅዱስ ንባብ ቅኝት፣ ሐተታ እንዳይኖር እና አንዲት ሃይማኖትን ለመጠበቅ፣ ለማጽናት ነው እንጂ ምስጢር ተቀድቶ እንደማያልቅ፣ ተሰብኮ የማይፈጸም ምሉዕ መሆኑን ሳይረዱት ቀርተው አይደለም:: ነገር ግን ሥርዐቱ መሠረታዊ ሥራን እንድንሠራ በአንድ ዓምድ እንድንቆም አስችሎናል:::

ይሁን እንጂ በየዘመናቱ የሚነሡ የቤተ ክርስቲያኒ መሪዎች ግን የመጻሕፍትን ሐሳብ ለመቀየርና ለመቀነስ ታግለው ነበር::

ንጉሥ አንስጣስዮስ ንጉሥ ዘይኑን በጻፈው መጽሐፍ በተስማማ ጊዜ የሦስቱ ጉባኤያትን ውሳኔ የኒቅያ፣ የቁስጥንጥንያ እና የኤፌሶንን ውሳኔ በግዛቱ እንዲጸና አዝዟል:: ነገር ግን በዘመኑ የነበረው የቁስጥንጥንያ ጳጳስ አውፍምዮስ ክርስቶስን ሁለት ባሕርይ /፪ ጠባይዕ/ አለው ብሎ በማስተማሩና በመለየቱ ቃለ አምላክ ታምራትን ሲያደርግ ትስብእት ግን ያነሰ የተለየ ነው ብሏል:: ይህንን ባስተማረበት ጊዜ እኛ በቅዳሴያችን «ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኀያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ዘተሰቅለ በእንቲአነ ተሣሃለነ» የምንለውን እሱ «ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኀያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ተሣሃለነ» ብሎ «ዘተሰቅለ በእንቲአነ /ስለኛ ተሰቀለ/» የሚለውን በማውጣት ታላቅ ስሕተት ማምጣቱ ይታወሳል:: በዘመነ መቅደንዮስም የፍልስጤም አርቶዶክሳውያን የንጉሡን መጽሐፍ አንቀበልም ማለታቸው መጻሕፍት መቆነጻጸላቸውን፣ መበጣጠሳቸውን የሚያመለክት ነው:: በንስጥሮስ፣ በሳባልዮስ... በሁሉም ዘንድ የታየው ነገርም ይኸው ነው:::

ይህ በመጻሕፍት ላይ የተከሰተው ችግር ደግሞ ከዚህ አልፎ ለባሱ መለያየቶችም ታላቅ በር ከፋች ነበር:: በእርስ በእርስ የነገረ መለኮት ክርክሩ ምክንያት በኋላም ብዙም ሳይቆይ የእስልምና መነሣት እና በኦቶማን ቱርኮች ሥር የምሥራቁ ሮማውያን ግዛት በተለይም በሴልጁክ ዐረቦች መውደቅ እና የመሐመድ ተከታዮች /ካሊፎች/ መካከለኛውን ምሥራቅ፣ ደቡባዊውን ምሥራቅ አውሮፓ እንዲሁም በሰሜን አፍሪካ አልፈው ከኮርዶቫ የጦር ሜዳ ድል በኋላ እስከ ፈረንሳይ መዝለቃቸው በመጻሕፍት ላይ ጉዳት ታላቅ ጉዳት አድርጓል:: ከዚህም ባሻገር የሮማ ካቶሊክን ከሁለት በመከፈል ለተደረገው ዋዜማ ድልድይ ነበር ማለት ይቻላል:: በዚያው ቀጥሎ የጥንቱን መጻሕፍት /የላቲኑን፣ የግሪኩን/ በማዘከርና በማጥናት የሥልጣኔው ርእዮት ተደምሮበት በእነ ኢራስሙስ እና ሊእ በማዕከለ አውሮፓ የተቀሰቀሰው የመጻሕፍትን /የጥንታዊ ጽሑፎችን/ ማወዳደር፣ ማስተያየት፣ መገምገም፣ ብሎም በመጻሕፍት ላይ ቅንሳን፣ ድማሬን፣ ለውጥን፣ ኑፋቄን ወዘተ ማስከተሉ ለብዙ መጻሕፍት መቃጠል እና ለባሰ ክርክር እንዲሁም ለብዙ ሰዎች ሕይወት መጥፋት መሠረት ሆኖ ነበር:: ይህ የመጻሕፍት ጉዳይ በዚህ ሳያበቃ ጭራሹን መንበረ ካርዲናሉንና ፓፓውን ከፋፈላቸው:: የሁለቱ ጐራም ሀገራቱን በሁለት ርእዮት ከማስቀመጡም በላይ ፓለቲካዊ ይዘት እና ፋይዳ እንደ ነበረውና ዛሬም አሻራ ሳይሆን ቀጣይ ሆኖ ይስተዋላል:: በመሆኑም መጻሕፍት ጥንታዊውን ፈር ሲለቁ እና የእምነት ተቋማት እንደ ማኅበራት ሲበራከቱ፣ ሲባዙ ማየት ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ለሚገዳቸው ወገኖች አሳባቢ የሆነ ጉዳይ ከሆነ ሰነባብቷል:: በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ የቤዛንታይን ነገሥታት ለሥልጣን የሚያደርጉት ሹኩቻ፣ እርስ በርስ በመርገዝ፣ በሌላም መንገድ የሚያደርጉት መገዳደል ድክመቱን ያበረታታ ተግባር ነበር:: በአንጻሩም ቅጆችን? እየፈለጉ፣ እያጠኑ ዕብራይስጡ፣ ግሪኩ፣ ላቲኑ አረማይኩ፣ ግእዙ እንዲህ ይላል:: ይኸ ከዚህ የተቀዳ ይመስላል በማለት አወንታዊውን የሚደግፉና ለአዎንታዊው አሉታዊ አዎንታ እየሰጡ መከራከሩ፣ መመራመሩ ዛሬም ድረስ በየጐራው እና በየክፍሉ የቀጠለ ሙግት ነው:::

በመሆኑም ቅኔንና ጥንታዊ በመጻሕፍትን ለመመርመር ያላቸውን ልዩነት ለማወቅ፣ ለማሳወቅ... መጻሕፍትን ማሰባሰቡና ለጥናት በየቤተ መዘክሩ፣ በቤተ መጻሕፍቶች እና በየሃይማኖት ተቋማቱ ማስቀመጡ የምርምር ማእከላትን ማደራጀቱ እና ጥንታውያኑን የግሪክ እና የላቲን ልሳናት መሠረት አድርጎ መመራመሩን ዛሬ በይፋ በስፋት እየተካሄደበት መሆኑም እንደመ ፍትሔ የሚታይ ጉዳይ ነው:: ይህም ሃይማኖታዊውን እና ሳይንሳዊውን ጥናት ያስተሳሰረ ምርምር ማድረግ ተገቢ መሆኑን የሚጠቁም ይመስለናል::

በኛም ሀገር ሀገራችን ክርስትናን ከተቀበለችበት ጊዜ ጀምሮ መጻሕፍትን በመተርጐም፣ በመድረስ፣ አብያተ ክርስቲያናትን በማስፋት፣ ክርስትናን በማስፋፋት የሀገር ውስጡ አበው እና የሀገር ውጩ አበው በጋራ ባደረጉት ተጋድሎ ቤተ ክርስቲያኗ ተስፋፍታለች:: የመጻሕፍትን ጉዳይም ገና ከነ ኢዛና /አብርሃ/ ጀምሮ በመለየት ጉዞዋን ጀምራለች:: እንደሚታወሰው ለአርዮሳውያን የትርጉም አቀባበል የነበረው የነገሥታቱ ግፊት ለእኛም ተርፎናል:: ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያን በማንኛውም ዓለም ዐቀፍ ተጽዕኖ ውስጥ እና የሀገር ውስጥ ፈተናዎች እያለፈች መጻሕፍትን እየጻፈች እየደጐሰች እስከ ዘመነ ኢትዮጵያዊው ቆስጠንጢኖስ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ አድርሳለች:: በእርሱ ዘመን ደግሞ ገድላት መጻፋቸው፣ ወጥ ድርሰቶች መደረሳቸው ሀገራዊ ጽሑፎች እየበዙ እና ቅጅዎች ከዕለት ወደ ዕለት እየበረከቱ መጥተው በሺዎች ሊቆጠሩ ችለዋል::

መጻሕፍቱም የሚደረሱት መሠረታዊውን ትምህርተ ሃይማኖት ለማስተማር ሲሆን ለዚህ ደግሞ ዋናው ተጠቃሽ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ነው:: ይህ አባት በሊቅነትና በቅድስና በቅቶ በዘመኑ ከአንድ ፈረንጅ ጋር በነበረው ክርክር እና ለውጪ መናፍቃን ለነአርዮስ፣ አርጌንስ፣ ሰባልዮስ... ወዘተ መልስ ይሆን ዘንድ መጽሐፈ ምስጢር በሚል ባዘጋጀው እና በሌሎቹም ሥራዎቹ የሚታወቅ አባት ነው:: የጊዜውን ክርክርም የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዜናመዋዕል እንዲህ ያስነብባል::

*«ዘርዐያዕቆብ ራብዕ ወልዱ ለዳዊት ነግሠ ፴ ወ፬ ወር አውራኅ ወተሰምየ ስመ መንግሥቱ ቆስጠንጢኖስ ወበመዋዕሊሁ ኮነ ተቃሕዎ በእንተ ሃይማኖት ወተዋሥኦ አባ ጊዮርጊስ ምስለ ፩ አፍርንጅ እስከ ከሠተ ወደረሰ መጽሐፈ ምስጢር ወካዕበ በ፲ ዓመተ መንግሥቱ አዕረፈ አባ ዮሐንስ ዘዊፋት:: ዕረፍቱኒ ለዐፄ ዘርዐያዕቆብ ኮነ አመ፫ ለጳጒሜን ወመቃብሪሁ በደሴተ ዳጋ፦* የዳዊት አራተኛ ልጅ ዘርዐያዕቆብም ሠላሳ ዓመት ከአራት ወር ነገሠ:: ስመ መንግሥቱም ቆስጠንጢኖስ ተባለ:: በዘመኑም ስለ ሃይማኖት ክርክር ሆኖ አባ ጊዮርጊስ መጽሐፈ ምስጢርን እስኪደርስ ድረስ ከአንድ ፈረንጅ ጋር ተከራከረ:: በዐሥረኛው የመንግሥቱ ዘመንም የዊፋቱ አባ ዮሐንስ ዐረፈ:: የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብም ዕረፍቱ ጳጉሜ ሦስት ሆነ እና መቃብሩም በደሴተ ዳጋ ሆነ::»

ራሳቸው ንጉሡ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብም ብዙ መጻሕፍትን የደረሱ ሲሆን ታናሽ ወንድማቸው መርቆሬዎስም /በኋላ አቡነ ዮሴፍ/ የተወለዱበትን አካባቢ ደብረ ታቦርን ትተው ሹመት ሽልማቱን፣ ተስፋ እና ክብረ ሥልጣኑን፣ ፍቅረ ሲመትን ንቀው መጻሕፍተ ቤተ ክርስቲያንን በመጻፍ ከገዳም ወደ ዓለም ሳይሆን ከዓለም ወደ ገዳም በመሔድ ዘመናቸውን አሳልፈዋል:: በእንደዚህ ዓይነቱ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት አባ ኖብ ዘሬማ /የዐፄ ይስሐቅ ወንድም/ እና አባ ሂሩተ አምላክም /የዐፄ ይኩኖ አምላክ ወንድም/ ሊታወሱ ይገባቸዋል::

ልጁ በዕደማርያም በነገሠ ጊዜም ሕዝቡ ለሃይማኖቱ፣ ለባህሉ ቀናዒ በመሆኑ ንጉሡ በፈረንጂ እጅ ሥዕለ ማርያምን በማሣላቸው እንዴት በፈረንጅ እጅ ሥዕለ ማርያም ይሣላል? በማለት አንጐራጉረዋል:: ዜና መዋዕል ዘበእደ ማርያም፦

*በእደ ማርያም ወልዱ ነግሠ ፲ ዓመተ ውእቱኒ አሥዓለ ሥዕለ ማርያም ወሥዕለ ኢየሱስ ክርስቶስ በእደ አፍርንጅ ወበእንተዝ አንጐርጐሩ ሕዝበ ኢትዮጵያ ወሥዕሉኒ ነበረ በአትሮንሰ ማርያም እስከ አመ ፫ ዓመተ መንግሥቱ ለዐፄ ቴዎፍሎስ ሲል አስፍሯል::*

ልጁ በዕደ ማርያምም ዐሥር ዓመት ነገሠ:: እሱም የማርያምን እና የኢየሱስ ክርስቶስን ሥዕል በፈረንጅ እጅ በማሰቡ ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንጐራጐሩ ሥዕሉም ዐፄ ተዎፍሎስ እስከነገሠበት እና እስከ ሦስተኛ ዘመነ መንግሥቱ ድረስ በአትሮንስ ማርያም ነበር::

*ይቆየን*

የማኅበረ ቅዱሳንን ገጸ ድር ይጎብኙ
www.eotc-mkidusan.org

ሐመር መጽሔትን እና
ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣን ያንብቡ::

# በውኑ ዓለም ሳይፈጠር እመቤታችን አትታወቅምን?

በኀይለ ጊዮርጊስ ዘደብረ ሃይማኖት

*ባለፉት ሁለት ተከታታይ ዕትሞቻችን በተአምረ ማርያም መቅድምና በሌሎችም መጻሕፍት ላይ የዘመኑ የቤተ ክርስቲያናችን የውስጥ መናፍቃን ከሚያነሷቸው ጥያቄዎች መካከል ዋና ዋናዎቹን በማንሣት የቃላቱን ምንነትና በዘመኑ የነበሩትም አባቶች ከምን መልእክት ወይም ትርጓሜ አንጻር ሊጠቀሙባቸው እንደሚችሉ አሁን ቤተ ክርስቲያናችን ከምትጠቀምበት አንጻር መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ ለመስጠት ሞክረናል። በዚህ ዕትም ደግሞ እመቤታችንን ማመስገንና ለእመቤታችን ድርሰ*
*መጻፍ መቼ ተጀመረ? በምን ምክንያት የሚሉትን ከአየን በኋ*
*በእኛስ ሀገር ከዘርዐ ያዕቆብ በፊት የእመቤታችን ምስጋና ም*
*ዓይነት ነው? የሚለውንም ለማየት እንሞክራለን። በመጨረሻ*
*ተሐድሶዎቹ ለምን ይህን ስልት ተጠቀሙ የሚለውን በማየ*
*በዚህ ዕትም ጽሑፉን እንደመድማለን።*

## እመቤታችን ማመስገን መቼ ተጀመረ?

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ገለጻ እመቤታችን ማድነቅና ማመስገን የተጀመረው ራእዩን /የአምላክን ሰው መሆን በትንቢት ከተመለከቱት/ ከነቢያት ጀምሮ ነው። «እምነ ጽዮን ይብል ሰብእ» የሚለውን የነቢዩ ዳዊትን ቃል ሲተረጉም ርቱዐ ሃይማኖት «ዘይቢሂ ማርያም ይእቲ ሰብአዊት ወእምነ ን ሰምያ እስመ ተወለድነ ዳግመ በጥምቀት... ሰው እናታችን ጽዮን ይበል /ይላል/፤ ያላት ይህች ጽዮን ሰው ናት። እናታችን እንላታለን፤ በጥምቀት ዳግመኛ ተወልደናልና» ብሎ ሊቁ እንደተረጐመው ነቢያቱ ቀድመው እናታችን እመቤታችንን እያሉ አመስግነዋታል።

ነቢያት በሩቅ አይተው አመስግነዋታል። «የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆንን፤ ገሞራንም በመሰልን» እያሉ የመመኪያችን ዘውድ የደኅነታች ንንም አክሊል እንደሆነች ገልጸዋል። ሙሴ ያያት ዕፀ እርሷ ናት። ሕዝቅኤል ያያት መቅደስም እርሷ ናት።

እርሷም ለዚህ የተመረጠች መሆኗንና ፍጥረት ሊያመሰግናት እንደሚችል ገልጻለች። የመላእክት አለቃ ቅዱስ ገብርኤል «ሰላምታ ይገባሻል፤ ከሴቶች ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ፤» ካላት በኋላ ኤልሳቤጥም በተመሳሳይ መንገድ «የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንደምን ይሆንልኛል» ከሚል ትሕትና ጋር ከአመሰገነቻት በኋላ ራሷም «ከእንግዲህስ በኋላ ነቢያትና መላእክት ብቻ ሳይሆኑ/ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል» ብላለች። ሉቃ. ፩፥፵፰።

ለመሆኑ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እመቤታችንን ማመስገንና ለእርሷም መከራከር የእርሷንም ምስጋና የያዘ ድርሰት መቼ ተጀመረ?

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደተገለጸው እነ ጠርጡለስ፣ ሐሬኔዎስና የመሳሰሉት የሁለተኛው ክፍለ ዘመን ሊቃውንት እመቤታችንን በአግባቡና በድርሰት አመስግነዋል፤ ስለ እርሷም ጽፈዋል። በኋላም አርዮስ «ወልድ ፍጡር» ብሎ በተነሣ ጊዜ ቅዱስ አትናቴዎስ አምላክነቱን /የጌታን/ ለማስረዳት መሠረት አድርጎ አጠንክሮ ያስተማረው ነገረ ማርያምን ነው። እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሆኖ ተወልዷል። እመቤታችን ማርያምም ወላዲተ አምላክ ናት እያለ አጠንክሮና አስፋፍቶ አስተማረ። (The Oxford dictionary of he Christan Church, P.1047፣ በዓላት፣ ምን፣ ለምን፣ እንዴት፣ ገጽ ፩፻፲)

ከቅዱስ አትናቴዎስ በኋላ ለነገረ ማርያም ትምህርት መስፋፋት ዋናው ምክንያት



የንስጥሮስ መነሣት ነበር። የንስጥሮስን ትምህርት እንደ ሰማ ቅዱስ ቄርሎስ የጻፈለት ደብዳቤ መነሻው የእመቤታችን ጉዳይ ነበር። ቅዱስ ቄርሎስ «ወላዲተ አምላክ (Theotokos) የሚለው ቃል በራሱ በቤተ ክርስቲያን እምነት /ለሥጋዌ/ ትልቅ መሠረት እንደሆነ ነበር የገለጸለት። (V.C. Samuel, The council of Chalcedon Re-examined, P.6)

ይህን ታሪክ በሰፊው የዘገበው ዮሐንስ መደብርም በወቅቱ ስለነበረው በሰፊው ተርኳል። ዮሐንስ እንደ መዘገበው በዚህ ዘመን ንስጥሮስ ኑፋቄውን ማስፋፋት የጀመረው እመቤታችንን በማቃለልና ወላዲተ አምላክ አይደለችም እያለ በማስተማር ነበር። ከዚህ የተነሣ እርሱ ይህን ያስፋፋባቸው ቦታዎች ሁሉ የተዋሕዶዎችን ጳጳሳት እስካለመቀበል ደርሰው ነበር። ለምሳሌ ለቁስጥንጥንያ አቅራቢያ በነበረችው በከስከስ የተሾመው አብሩክሊስ ከሀገረ ስብከቱ የወጣው በዚሁ ምክንያት ነበር። እርሱን የሾመው ሲስኑስ ነበር። «ወሲስኑ ሊቀ ጳጳሳት ዘተ ሠይመ እምድኅረ አዲደንኮስ ሜሞ ጳጳሰ ላዕለ መንበረ ከስከስ ወወሀቦሙ ዘንተ ሀብተ ዐቢየ፤ ባሕቱ ኢተወክፍዎ ሰብአ ይእቲ ሀገር እስመ ኢኮኑ ድልዋነ ለተወክፎ ዝንቱ ንዋይ ኄሩይ ዘእግዚአብሔር፡- ከአዲደንኮስ በኋላ ሊቀ ጳጳስ ሆኖ የተሾመው ሲስኑ ለሀገረ ከስከስ ጳጳስ አድርጎ ሾመው። የሀገሪቱ ሰዎች ግን ይህ የእግዚአብሔር ምርጥ የተገባቸው አልነበሩምና አልተቀበሉትም» ምክንያቱንም የንስጥሮስ ጉዳይ እንደሆነ እንደሚከተለው ገልጾታል።

«ወነበረ በብሕታዌ በሀገረ ብራንጥያ እንዘ ሀሎ ንስጥሮስ የሀውኮሙ ለአብያተ ክርስቲያናት ጊዜ ኮነ ሊቀ ጳጳሳት በእንተ ዘገብረ ጽልአ ላዕለ እግዝእትነ

ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አም
ላክ፡- ንስጥሮስ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳ
ሆኖ በእመቤታችን ላይ የጥላቻ ትም
ርትን ሲያስተምር አብሩክሊስ በብራንጥ
/ቁስጥንጥንያ/ በብቸኝነት ይኖር ነበር»
ይላል። በዚህ ጊዜ ቅዱስ አብሩክሊስ ስ
እመቤታችን አንድ ድርሠት ደርሶ ለሕ
ዝቡ አነበበላቸው። «ወቅዱስሰ አብርክሊ
ደረሰ ድርሳነ በእንተ እግዝእትነ ቅድስት
ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ወአንበ
ወስተ ቤተ ክርስቲያን ዘቁስ ጥንጥን
እንዘ ሀለው ሕዝብ ጉቡአን ውስተ ቤተ
ክርስቲያን፤ ወለንስጥሮስሰ ብዙኀ ዘለ
በድርሳኑ በእንተ ዘኮነ ልቡ ለኀጉል። ወ
ጽሑፍ በጥንተ ድርሳኑ ዘይብል፤ ናብዕ
በዓለ ድንግልናዌ ወንጸርኀ በልሳንነ እን
ንብል፤ ዮም ንወድሳ ለማርያም ወላዲ
አምላክ። ወሶበ ሰምዑ ዘንተ ኩሎሙ ሕዝ
ሰብሕዋ ለእግዝዕትነ ወአእኩትዋ ወአንከ
ጥቀ፡- ቅዱስ አብርክ ሊስም አምላክን ስ
ወለደች ስለ እመቤታችን ድርሰትን ደረሰ።
ሕዝቡ ተሰባስበው ሳሉም አነበበላቸው።
በድርሰቱም ልቡናው ለጥፋት ተላልፎ የተ
ጠውን ንስጥሮስንም ብዙ ዘለፈው። በእርስ
ድርሳንም እንዲህ የሚል ጽሑፍ አለ፡- በድ
ንግልና የከበረችውን እመቤታችንን እና
ክብራት፤ በአንደበታችንም ዛሬ የአምላ
ክን እናት ማርያምን እናመስናግት እ
ልን እንጩህ። ሕዝቡም ይህን በሰሙ ጊዜ
እመቤታችንን አመሰገኗት፤ አወደሷት፤
እጅግም አደነቋት።» /ዮሐንስ መደብር
የብራና መጽሐፍ/ በዚህ ታሪክ በሰፊው
እንደተገለጸው አጽራረ ማርያም የሆኑ
ሰዎች በሚነሡበት ጊዜ ሊቃውንትና አባ
ቶች ሁሉ ለርሷ የምስጋና ድርሰት ደርሰ
ዋል፤ እምቤታችንን አመስግነው ሕዝቡም
እንዲያመሰግኗት አድርገዋል። ከዚህ ከንስጥ
ሮስ በኋላ በአንጾኪያና በቁስጥንጥንያ የተ
ነሡ ቅዱሳን አበው ደግሞ ድንቅ ድንቅ
ድርሰቶችን በመድረስ እመቤታችንን አመ
ስግነዋታል። ከእነዚህም መካከል የመን
ፈስ ቅዱስ ዕንዚራ የሚባለው ቅዱስ ኤፍ
ሬምና የቀድሞው የአንጾኪያው የኋላው
የቁስጥንጥንያው ፓትርያርክ ቅዱስ ዮሐ
ንስ አፈወርቅ ተጠቃሾች ናቸው። ከቅዱስ
ኤፍሬም ድርሰቶች ውስጥ አሁን ለጸሎት
የምንጠቀምበት ውዳሴ ማርያም በሀገራችን
ከመታወቅ በላይ ነው። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወ
ርቅም ሃይማኖተ አበው ላይ «ተፈስሒ አ
እግዝእተየ ማርያም፡- እመቤቴ ማርያም
ሆይ ደስ ይበልሽ» በሚለው ድርሰቱ ይታ
ወቃል። ይህ ድርሰት በእኛ ሀገር ከተአ
ምረ ማርያም መቅደም ጋር ተካትቶ ሁል
ጊዜ ከተአምሯ በፊት የሚነበበው ነው።

ወደ -እኛ ሀገርም ስንመጣ በዚያው በስድስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እመቤታችን በድርሰት መመስገኗ የታወቀ ነው። ለዚህም መሠረታዊና መነሻ የሚሆነን የቅዱስ ያሬድ ድጓ ነው። ሊቀ ቅዱስ ያሬድ በግንቦት ልደታ ለማርያም ድጓ ላይ «አዳም ወሠናይት ዕዕዱት ወብርሀት እንቶሙ ለመላእክት ማርያምስ ተሐቱ ወስተ ከርሡ ለአዳም ከመ ባሕርይ ፀዓዳ እንተ ሠረፀት እምሥርወ ዕሤይ፡ ፍጹም ወብ፣ ፍጽምት ብርሀት የመላእክት እኅታቸው ናት። ከዕሤይ አባትነት የተለወለደችው ማርያምማ ከጥንት ጀምሮ በአዳም አብራክ እንደሚያበራ ኑጭ ባሕርየ ዕንቁ ታብራ ነበር» በማለት ከጥንተ አብሶ ንጽሕት መሆኗን በመግለጽ አመስግኗታል። በአንቀጸ ብርሃን ድርሰቱም «ዘኮንኪ» ላይ ስለጌታ ልደት በተናገረበት አንቀጽ «ወበህየ በካልዕ ስብሐት ወደሱኪ ኪሩቤል ወሱራፌል ዘኢኮነ እምስብሐቲሆሙ ዘውስተ ሰማያት ወኢ እምስቢሐቲሆሙ ዘትካት፡- ሱራፌልና ኪሩቤል በሰማያት ካለው ምስጋናቸው ወይም ከቀድሞ ምስጋናቸው ባልሆነ በሌላ በአዲስ ምስጋና አመሰገኑሽ» በማለትም በልዩ ምስጋና እንደምትመሰገን ገልጿል።

. ከእርሱም በኋላ ያሉ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አመስግነዋታል። በጣም ከቀደሙት ሊቃውንት የሚጠቀሰው ርቱዐ ሃይማኖት የስብከት ድርሳኑ /ብርሃን፣ ኖላዊ፣ ስብከት/ ላይ ቅዱስ ገብርኤል ለእመቤታችን የአበሰረውን ቃል በተረጐመበት አንቀጹ «ወይቤላ ስምዒ እፌክርለኪ ወጠይቂ በለብዎ ወተወክፊ በአሚን፤ እስመ በእንቲአኪ ተፈጥረ ዓለም ወአንቲኒ ተፈጠርኪ በእንተ ሕይወተ ዓለም፡-. ስሚ፥ እተረጉምልሻለሁ፤ በማስተዋል ጠይቂ፤ በእምነትም፤ ዓለም ስለአንቺ ተፈጠረ፤ አንቺም ስለ ዐለም ሕይወት ተፈጠርሽ» ብሎ አመስግኗታል። ሊቁ በልደት ድርሳኑ ላይም ጌታችን ከእመቤታችን እንደሚወለድ የተነገሩትን ትንቢቶች እያነሣ ስለእመቤታችን ክብር በሰፊው ይዘረዝራል። በመጨረሻ ላይም ራሱን አስችሎ ስለእመቤታችን አንድ ድርሰት አለው። የዚህ ድርሰቱ መነሻው የእመቤታችን ዕርገት ነው። በዚህ ድርሰቱ ደግሞ ክብሯን፣ ልዕልናዋን፣ መገለጧን ትንሣኤዋንና ዕርገቷን በሰፊው ገልጾበታል። ሊቁ ስለ እርሷ ብዙ ከተናገረ በኋላ ለማጠቃለል «ወበእንተዝ ይብልዋ ኩሉ መጻሕፍት ሰላም ለኪ ኦ ደብረ መቅደሱ ለእግዚአብሔር እንተ መልዕለተ ኵሎሙ ቅዱሳን፡- ስለዚህም መጻሕፍት ሁሉ ከቅዱሳን ሁሉ በላይ የሆንሽ የእግዚአብሔር የመመስገኛው ተራራ ሆይ ሰላምታ ይገባሻል ይላሉ» በማለት ከእርሱ በፊት ስለነበሩ መጻሕፍትም ገልጿል። ርቱዐ ሃይማኖት ከእርሱ በፊት ስለተነሡትና ስለዘመኑ ብቻ ሳይሆን ስለወደፊቱም ጭምር «ወበእንተዝ ይቤ ኤፍሬም፡- ለእመ ሰማይ ክርታሰ ውማይ ዘባሕር ቀለመ፤ ለእመ ኮኑ ዕፀ ገዳም ብርዐ እም ኢክህሉ ፈጽሞ ጽሒፈ ወዳሴሃ ለዘወለደት አምላክ፡- ስለዚህ ነገር ሰማይ ክርታስ /ወረቀት/፣ የባሕር ውኃ ቀለም፤ የዱር ዕፅዋትም ብርዕ /መጻፊያዎች/ ቢሆን አምላክን የወለደች /የእመቤታችንን/ ምስጋና ጽፎ መጨረስ አይቻላቸውም . አባ ኤፍሬም ተናገረ» ብሎአል። አብ ብንያሚም የእመቤታችን ሥጋ አልተነሣ ለሚሉት ትንሣኤዋን ከመሰከረ በኋላ «ወባሕቱ ማርያምሰ ተዓቢ እምኵሉ ፍጥረት በከመ የዓቢ ቤተ ማኅደሩ ለንጉሥ ሥርግው በወርቅ እም ቅጽራት በአፍአ እለ ተነድቁ በጽቡር፡- በወርቅ የተለበጠው የንጉሥ ቤት በውጭ ካሉትና በጭቃ ከተሠሩት ቤቶች እንዲበልጥ ማርያምም ከፍጥረት ሁሉ ትበልጣለች።» ብሏል። ርቱዐ ሃይማኖት በሌላም ቦታ» የእመቤታችንን ዕበየ ልዕልናዋን ማወቅ ከፈለግህ በረድ ላይ ተቀመጠ ዐርባዕቱ እንስሳ የሚሸከሙትን፣ ጉልበት ሁሉ የሚሰግዱለትን ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከት፤ የሚታየው ሥጋ የእርሷ ነውና» ይላል። ከእርሱ ድርሰት አንዱን አንቀጽ ብቻ ጠቅሼ ወደሚቀጥለው ልሸ ጋገር «አኮ ሰብእ ባሕቲቶሙ ዘያስተበፅዑኪ ኦ ድንግል አላ መላእክተ ሰማይኒ ያስተበፅዑኪ ወይገንዩ ለመድምም ዘኮነ ላዕሌኪ ኦ ማርያም ወአኀዘ ይንግራ ወሰበ ርእዩ ለምስጢረ መድኀኒትነ ላዕሌኪ ይቤ አልቦ ነገር ዘይስአኖ ለእግዚአብሔር። አማን ኢተስእኖ ለአምላክ ሶበ ኮነ ባዕደ ዘእንበለ ኢይት በዓድ እም ሀላዌ ዘትካት ዝ ግብር ዘኮነ በላዕሌኪ ኦ ታቦት ዘኖኅ ዕፁት ዘኢ ይቀርባ ወኢይሰቁራ አይኀ ኃጢአት። አኮ መላእክት ባሕቲቶሙ ዘያስተበፅዑኪ አላ ነቢያትኒ ይብሉኪ ነኪር ነገሩ በእንቲአኪ ሀገረ እግዚአብሔር አማን ነኪር ወመድምም ዝ ነገር ድንግልና ከመ ወለት ወሐሊብ ከመ ውስብት ተረክበ በላዕሌኪ፡- ድንግል ሆይ ሰዎች ብቻ የሚያመሰግኑሽ አይደለሽም፤ ይልቁንም የሰማይ መላእክት ያመሰግኑሻል፤ በአንቺ ስለተደረገው ድንቅ ነገርም ይገዛሉ እንጂ። ማርያም ሆይ በአንቺ ላይ የሚደረ ገውን የድኅነታችን ምስጢር ባየ ጊዜ ያነጋግራት ጀመረ፤ ማርያም ሆይ አለ፡ ለእግዚአብሔር የሚሣነው ነገር የለም። ባዕድ ሥጋን በንሣ /ሰው በሆነ ጊዜ/ ከቀደመ ባሕርይ ክብሩ/ አልተናወጸም፤ በእውነት ለአምላክ አልተሣነውም። ይህ ነገር በአንቺ ላይ የተፈጸመ የኃጢአት ውኃ ያልቀረባትና ያልገባባት የተዘጋች የኖኅ ታቦት ነሽ። መላእክትም ብቻቸውን የሚያመሰግኑሽ አይደለም፤ ነቢያትም የእግዚአብሔር ሀገር ሆይ በአንቺ የተደረገው ነገር ግሩም ነው ይሉሻል። በእውነትም ይህ ነገር ፍጹም ድንቅ ነው። ድንግልና እንደ ልጃገረድ፣ ወተትም እንደ አገባች ሴት በአንቺ አለና» ብሏታል።

ከእርሱም በኋላ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ በመጽሐፈ ምስጢርና በሌሎቹም ድርሰቶቹ ከደረሰው ውጭ ራሱን የቻለ «አርጋኖን» የተባለ ድርሰት ደርሶላታል። አባ ጽጌ ድንግልም ማኅሌተ ጽጌን ደርሶላታል። በእነዚህ ሊቃውንት ሥራዎች ወደፊት ስለምንመለስ ዛሬ አንጠቅስም። ታዲያ ከጥንት እስካሁን ከውጪ እስከ ሀገር ውስጥ በቅዱሳን ሊቃውንት አበው እንዲህ ከተመሰገነች ከዘርዐ ያዕቆብ በኋላ የተጨመረው አዲስ ድርሰት የቱ ነው? በተአምረ ማርያም መቅድም ላይ ከተገለጹትና ባለፉት እትሞቻችን ከተሰናገዱት ውስጥ በእነዚህ ሊቃውንት ያልተገለጸው አዲሱ ቃል የቱ ነው? ፍርዱን ለአንባብያን ትተን ወደሚቀጥለው ጉዳይ እንመለስ።

## ዘርዐ ያዕቆብንና ከእርሱ በኋላ ያለውን ማንሣት ለምን አስፈለገ?

የተሐድሶ አራማጆችን ነን ባዮች በመጀመሪያ «ከቤተ ክርስቲናችን ምኑ ለውጥ ያስፈልገዋል?» ተብለው እንኳን ቢጠየቁ በጥናት የተደገፈ እውነተኛ ገጽታን ማሳየት እንደማይችሉ የታወቀ ነው። የዚህ ዋናው ምክንያቱ ደግሞ ጥንቱንም ለቤተ ክርስቲያኒቱ ዕድገትና ቀና መንገድ ያልተነሡ መሆናቸው ነው። እንዲያውም እውነተኛ ነን በሚል ሰበብ የጥንቱ እንዲህ ነበር፤ አሁን ግን እንዲህ ሆነ እያሉ የሰውን ልብ ወደ ተነሡለት ዓላማ ለማሸፈት እንዲመቻቸው ነው። የግድ አንድ ቦታ ላይ ተብሳሽ ካላሉ የአሁኑን ስህተት ነው ለማለት አይመቻቸውም። እንግዲህ ይህ ገዜና ቦታ ሲፈለግ ነው ዘርዐ ያዕቆብ የተመረጠው።

ለመሆኑ ዘርዐ ያዕቆብ ለምን ተመረጠ? የሚለውን ጠቀሞ ማለፍ ያስፈልጋል። በመጀመሪያ ደረጃ ለዚህ ተጠያቂዎቹ እነርሱ ቢሆኑም ዘርዐ ያዕቆብን ለማንሣት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ግን ከዚህ እንደሚከተለው እና ቀርባለን።

ሀ/ ስም ለማጥፋት፡- መናፍቃን ከጥንት ጀምሮ ይሔ ተቀዳድሞ ስም የማጥፋት አባዜ አለባቸው። አርዮስ በዚህ ተንኰል የብዙዎችን ስም ለማጥፋት ብቻ ሳይሆን አትናቴዎስንም እስከማስጋዝ ደርሷል። ሌላው ቀርቶ የለየለቱ ሁለተኛው የሥጋዌ መናፍቅ ንስጥሮስ የራሱን ቡድን ሰብስቦ ቄርሎስን ለማውገዝና ስሙን ለማጥፋት ጥሯል። ልዮንና ግብረ አበሮቹም በዲዮስቆሮስና በተዋሕዶዎች ላይ የሠሩት ሥራ ተመሳሳይ ነው። ወደ ሀገራችንም ስንመለስ ብዙ ተመሳሳይ ታሪኮችን እናገኛለን። ቅባቶችና ጸጋዎች የተዋሕዶዎችን ስም ለማጥፋት ያልጣሩት ጥረት የለም። አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ «ሃይማኖተ አበው» በሚል ስም ባሳባሰቡት እስትግቡእ ሁለተኛው ምዕራፍ ላይ «ተዋሕዶ በሊቃውንት አዋጅ ቃልና ሥጋን ፩ አካል ፩ ልጅ ወልድ ዋሕድ ታሠኛለች እንጂ እንደ ሐራጥቃ ባሕርያትንና ግብራትን ቀላቅላ ደባልቃ ፩ ባሕርይ ፩ ግብር አታሠኝም፤ ተዓቅቦ ይከለክላታል። ወልድ የኛን ባሕርይ ነሥቶ ሰው የሆነ በተለየ ስሙ፣ በተለየ አካሉ፣ በተለየ ሕላዌው ነው እንጂ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ሊለይ ሊከፈል በማይችል በመለኮታዊ ባሕርዩ ሰው የኾነ አይደለም። የቢዘንና የተንቤን ምዕላድ መምህር አካለ ወልድ እንደሚሉት አካሉ ሰው ሲሆን ባሕርዩም ሰው ሆኗል ቢባል ግን ምስጢረ ሥላሴ ይፈርሳል፤ ... ካራና ቅባትም እንደ አውጣኬ የሰውነቱን ግብር አጥፍተው ቃልን በሰውነቱ አምላክ የአብ የባሕርይ ልጅ ይላሉና፤ በዚህ አንጻር የባሕርይ ልጆች ሊባሉ ይገባል። በተዋሕዶ ወልድ ዋሕድ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው፤ በቅብዐተ መንፈስ መሲሕ ወበኵር ዳግማይ አዳም ካሉ በኋላ ግን እንደ ዐቃቤ ሰዓት ከብቴ ፩ ባሕርይ ፩ ግብር የሚሉ መናፍቅ ካሮች ወይም መንፈቅ ኦርቶዶክሶች ናቸው እንጂ ፍጹማን አይደሉም፤ ፩ ባሕርይ ማለት

ያውጣኬ ነውና::» በማለት ጽፈዋል:: አለቃ በዚህ ጽሑፋቸውና በሌሎቹ አንቀጾቻቸው ላይም ብዙ ዘለፋ ተዋሕዶና ስም ማጥፋት ጽፈዋል:: ከላይ በተገለጸው ላይ ማየት እንደሚቻለው ከሊቃውንቱ የእርሳቸውን ሃይማኖት በግልጽ ማወቅ ለሚፈልግ በዚህ ጽሑፋቸው ላይ «የተዋሕዶ ባህል ባጭር ቃል ይህ ነው:: ቃልና ሥጋ በተዋሕዶ ወልድ ዋሕድ ፩ አካል ፩ ልጅ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው፥ በተፀቅቦ ፪ ባሕርይ፣ ፪ ግብራት፥ ፪ የባሕርይ ልደታት ወልደ አብ በመለኮቱ፣ ወልደ ማርያም በትስብእቱ፣ አብ ቀባዒ ወልድ ተቀባዒ፥ መንፈስ ቅዱስ ቅብዕ ...» በማለት ጸጋ መሆናቸውን በግልጽ አስቀምጠዋል:: ይህም አንድ አካል ሁለት ባሕርይ ግልጽ የሆነ የካቶሊክ ትምህርት እንደሆነ እየታወቀ እርሳቸው ግን ሳያፍሩና ሳይፈሩ የራሳቸውን ተዋሕዶ ብለው ተዋሕዶን ግን ካራ ብለዋል:: እኔን የጸጋ ልደት ካላችሁኝም እናንተም የባሕርይ ልደት ልትባሉ ይገባችኋልም ብለውናል:: ከዚህም በላይ በተአቅቦ የሚገለጸውን ተዋሕዶ ስም ለማጥፋት ሲሉ ወስደው ከአውጣኬ ጋር ደምረውታል:: በጣም የሚገርመው ብዙ ታሪኮች ላይ ተሐድሶዎች የሚጠቅሷቸው ታሪኮች ምንጫቸው ይህ የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በብራና ላይ የተጻፈ የእጅ ጽሑፍ ነው::

ከላይ የተገለጸውን ሰፊ ታሪክ ማስቀመጥ የተፈለገው መናፍቃን በሀገራችን ስም ለማጥፋት ቦዝነው የማያውቁ መሆናቸውን በተጨባጭ ለማሳየት ነው:: ልክ እንደዚህ በየቦታው ከተቀመጡት በላይ በየምዕላዱ የተጻፉና የተፋቁ፣ የተቀነሱ ወይም የተጨመሩ እንደሚኖሩ የታወቀ ነው:: እነዚህን ጉዳዮች በሌላ ዕትም የምናያቸው ቢሆንም በዚህ ጽሑፍ ያነሣነውን የመናፍቃን የስም ማጥፋት ዘመቻ አብቅተን ወደሚቀጥለው ነጥብ እንሸጋገር::

### ለ. ከዘርዐ ያዕቆብ በፊት ለሀሳባቸው ድጋፍ የሚሰጥ አሻራ ባለመገኘቱ

ከዚያ በፊት የነበረ አንዳች ተራ ነገር እንኳ ቢኖር ዝም እንደማይሉ የታወቀ ነው:: ታዲያ ዘርዐ ያዕቆብስ ላይ ስንል፥ በእርሱ ዘመን ለተሠሩት ሥራዎች ለጠማማ አስተሳሰባቸው ምክንያት የሚያደርጉትን በማግኘታቸው ነው:: ዘርዐ ያዕቆብ ላይ ለነቀፌታቸው እንደ መነሻ ምክንያት የሚጠቅሱት በንጉሥነቱ የሠራቸውን ሥራዎች ነው:: ዘርዐ ያዕቆብ በዚህ ሥራው ሊፈረድበት ከተገባም ከሌሎቹ ነገሥታት ጋር በማነጻጸር መሆን ይኖርበታል እንጂ ሃይማኖታዊ ሥራው ላይ በመጫን መሆን የለበትም:: ምክንያቱም በሃይማኖቱ ርቱዕ በዕውቀቱም ደግሞ የተመሰከረለት ሊቅ በመሆኑ ነው:: «በእውነት ለመናገር ዘርዐ ያዕቆብ ቅዱስ አይደለም:: ነገር ግን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የማይረሣ /ሲታወስ የሚኖር/ አሻራ ትተው ካለፉት በጣም ጥቂት ሊቃውንት ውስጥ አንዱ ነው::» ተብሎ የተመሰከረለት ሊቅ ነው:: (በዓላት ምን? ለምን? እንዴት፣ ገጽ. ፩፻፳፪፣ The Coptic Encyclopedia, P.484). ከዚህም የተነሣ በቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት መካከል የነበሩትን አንዳንድ አለመግባባቶች በጉባኤ እንዲወሰኑና ሰላም እንዲወርድ ካደረገ በኋላ መናፍቃንንም አግባብቶ ለመመለስ ጥረት አድርጎ ነበር:: ይህ አልሳካ ሲለው ደግሞ በነበረው ንጉሣዊ ሥልጣንና ሓላፊነት አስፈላጊውን ሁሉ ፈጽሞአል:: እነዚህ ሰዎች እንደ ምክንያት የሚያነሡት ይህን በእነ አባ እስጢፋኖስ ላይ የተወሰደውን እርምጃ ሲሆን እስጢፋኖሳውያንንም እንደ ትክክል በመውሰድ ይጠቅሷቸዋል:: በርግጥ በዚህ ዙሪያም ማለትም በእነ አባ እስጢፋኖስ ትምህርት ላይና በጊዜው በነበሩት ሁኔታዎች ዙሪያ ራሱን የቻለ ጥናት ቢያስፈልግም ተሐድሶዎቹ ግን ለኑፋቄያቸው እንደመነሻ በማቅረብ ይጠቀሙባቸዋል:: ዘርዐ ያዕቆብ ላይ የተፈጠረውም ስም ማጥፋት መሠረቱ ይኸው ጉዳይ ነው:: ከዚህ በፊት ግን ቀደም ብለን እንዳየነው ሊቃውንቱ በጻፏቸው ጽሑፎችና በኖሩት ሕይወት የኑፋቄን አፍ ዘግተው አልፈዋል::

### ሐ. የሰውን ድካም ለመጠቀም

ተሐድሶዎች የሚሔዱበት አካሔድ ፍጹም ሰይጣናዊና የሰውን ድካም ለመጠቀም ሆን ተብሎ የተቀየሰ ይመስላል:: ሰይጣን በመጀመሪያ አዳምንና ሔዋንን የፈተናቸው ድካማቸውንና ክፍተት የሚሰጠውን /አትብሉ የተባሉትን ነገር/ መርምሮ ካወቀ በኋላ ነበር:: አዳምና ሔዋንን «እግዚአብሔር ዕፀ በለስን አትብሉ ያላችሁ አምላክ እንዳትሆኑ ነው» ብሎ ሰይጣን አምላካቸውን ሲያማላቸው ሐሜቱን ሰምተው ለሥልጣንም ጓጉተው ዕፀ በለስን ለመብላት ሔዱ:: ይህ የሰው ድካም አሁንም አለ:: ብዙ ሰዎች አንተም ካህን መሆን ትችላለህ፣ አንተም ቅዱስ ነህ፣ አንቺም እንደ ማርያም ነሽ፥ የእነ እገሌ ትምህርት አምልኮ ቅዱሳን ነው ሲላቸው ልቡናቸው እኩብር ባይ ስለሆን እንደ አዳምና እንደ ሔዋን የሚጠቅማቸውን የአትሕቶ ሕይወት ትተው በራሳቸው መንገድ ለመጓዝ ይሻሉ:: ይህን የሰውን ድካም የሚያውቀውና ሁልጊዜም በዚህ መንገድ በማሳት ደስታ የሚሰጠው ሰይጣን አሁንም ሰዎችን በድካማችን ተጠቅሞ ለመጣል አላንቀላፋም:: ለእንርሱ ለሚቀበሉት ደግሞ ራሱን የብርሃን መልአክ እንኳን እያስመሰለ ይገልጽላቸዋል:: እነርሱም ቅሩባነ እግዚአብሔር የሆኑ እየመሰላቸው እንደ እንስሳ «እምቧ» ብለው ይከተሉታል::

ተሐድሶዎችም የእርሱ የግብር ልጆች በመሆናቸው ማናናቅና ማጥላላት የሚወደውን ደካማ ጐናችን በመጠቀም ለመሥራት የሚፈልጉ ይመስላሉ:: ምክንያቱም ሰዎች ከሚያሳምን ነገር ይልቅ የሚያጠራጥር ነገርን ለመቀበል የመቅደም ጠባይና ዝንባሌ ስላላቸው ነው:: ከአዳምና ከሔዋን ጀምሮ እንዳየነው ሰው እንኳን በቅዱሳን ላይ በእግዚአብሔር ላይ ሐሜታና ነቀፌታ ሲያቀርቡለት መቼ ቸል ይላል? እነዚያ ቅዱሳንን እየነቀፉ ወደ ፕሮቴስታንቱ ዓለም የገቡት አውሮፓውያን አሁን ጭራሹን እግዚአብሔር የለም ለምን አሉ? ክርስቶስ እንደ እኛ አግብቷል /ሉቱ ስብሐት/ አሉት እንጂ መቼ አማላጅ ነው ብለው ብቻ ቀሩ፥ በአዋልድ ላይ የጀመሩትንም ዘመቻ ወደ ወንጌልም በማሳደግ ወንጌልንም አጥጥለው ለማጎብል ደከሙ:: የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትንም እንደሞያ እንጂ እንደ ሃይማኖት መቼ ኖሩበት:: ይህ ሁሉ የሚያሳየው ከጥንት ጀምሮ ያለውን የሰውን ድካም ተጠቅሞ በእምነትም በምግባርም ለመጣል ነውና መጠንቀቅና መጠበቅ ያስፈልጋል::

### ተሐድሶዎች ተአምረ ማርያምና ሌሎች አዋልድ ላይ ለምን ዘመቱ?

የተሐድሶው መሥራች መሠረት ስብሐት ለአብ «በዘመናችንም የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ትልቅ ርእስ እየሆነ ነው» በማለት በታሪክ መጽሐፋቸው ላይ ከገለጹ በኋላ የመጽሐፋቸውም ዓላማ የቱ ይታደስ? የትኛው ይቀጥል? የሚለውን ለማሳየት እንደሆነ ራሳቸው ገልጸውታል:: መሠረት ስብሐት ለአብ በዚሁ የታሪክ ጽሑፋቸው ስለ አባ እስጢፋኖስ ሲናገሩም ጸረ ማርያምና ጸረ መስቀል እንደ ነበሩ ተቀብለው እንዲያውም ሉተርን ቀድመው በመነሣታቸውም በተዘዋዋሪ አድንቀዋቸዋል:: ቃሉም የሚከተለው ነው:: «እነሆም በኢትዮጵያ ምድር አግዓዚ እስጢፋኖስ በፈጠረው ኀሳብና እንቅስቃሴ ተከሰሶበት የሞትን ጽዋዕ የተቀበለበት ሲሆን፣ እስጢፋኖስ ከሞተ ከ፺፮ ዓመታት በኋላ ማርቲን ሉተር የሚባል ጀርመናዊ በዚሁ ሀሳብና እንቅስቃሴ ከአውሮፓ ተነሥቶ ጊዜና ቦታ ዕድል ረድቶት ፕሮቴስታንት የሚባለውን ባህል ፈጥሮ በአውሮፓውያን ዘኮነ ከዊና ዓለምን ለመግዛት አብቅቶአቸዋል» የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአስተዋጽኦ፣ በታይፕ ተመትቶ በመጽሐፍ መልክ የተጠረዘ፣ ገጽ. ፳፱/ ታዲያ እንግዲህ በመጀመሪያ ስለተሐድሶ ገልጸውልን የተሐድሶ መሥራች ያሉአቸውን አባ እስጢፋኖስን እስከ እምነታቸውና ተጋድሎአቸው ካስተዋወቁን በኋላ የእርሳቸው ባይሳካም ይህንኑ አሳብ ይዞ የተነሣው ሉተር ተሣክለት የሚሉን ከሆነ ተሐድሶን ኢትዮጵያዊ ፕሮቴስታንት ከምንለው በቀር ማን ልንለው እንችላለን? ኢትዮጵያዊ ፕሮቴስታንት የሚያሰኘውም ምን አልባት ሌሎቹም የተሐድሶ አራማጆች ስለ ምስጢረ ሥጋዌና ምስጢረ ሥላሴ ያላቸው እምነት የእኛን ቤተ ክርስቲያን ትምህርት የያዘ የመሠረት ስብሐት ለአብ ዓይነት ከሆነ ነው:: ከዚህ በቀር ፕሮቴስታንት ከሚያራምደው ነገር የተለየ አንድም ነጥብ እንደሌለው ራሳቸው መስክረውልናል::

የተሐድሶዎችን ማንነት በአጭሩ በላይኛው አንቀጽ ማይት ያስፈለገው ተሐድሶዎች አዋልድ ላይ የሚዘምቱበትን ምስጢር ለመረዳት ሩቅ መጓዝ ስለማያስፈልግ ነው:: እነዚህ ሰዎች ፕሮቴስታንቶች ከሆኑ በአጭር ቃል አዋልድን አይቀበሉም ማለት ነው:: (ስለ አዋልድ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ በጥሩ ሁኔታ ለመረዳት በቅርቡ የታተመው ሐመረ ተዋሕዶ መጽሐፍ ላይ አዋልድ መጻሕፍት የሚለውን ርእስ መመልከት ይቻላል::) ተሐድሶዎች ኢትዮጵያዊ ፕሮቴስታንቶች መሆናቸው ግልጽ

ወደ ገጽ ፴፬ ይዞራል

# «በስመ ሥላሴ፣ እቀጠቅጥ ከይሴ»

## የበስመ አብ ትርጓሜ

*መምህር ተፈሪ መንግሥቱ*

*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ የሚለው ጸሎት ለአንድ ክርስቲያን የማንኛውም ተግባሩ መቅድም ወይም መጀመሪያ ነው:: የጸሎትም መጀመሪያው ይህ ነው:: ይህንን የጸሎት ክፍል ንባቡን ከነትርጓሜው ለክርስቲያን ሁሉ መማር ይገባል:: ይህንን ያልተማረና ለማናቸውም ጉዳይ ሁሉ መነሻ ያላደረገ ፍጹም ክርስቲያን ሊባል አይገባውም ይላሉ ሊቃውንት:: በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ በማለት የሚያስፈልገው ስለ ብዙ ምክንያት ነው:: እነዚህም:-*

### ፩ኛ. ሥላሴ የሚመሰገኑበት ስም በመሆኑ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ የሚለው የሥላሴ ስም በመሆኑ ነው:: ሥላሴ እምቅድመ ዓለም ሲጠሩበት የነበረ አሁንም በዚህ ዓለም የሚጠሩበት ኋላም ይኽንን ዓለም አሳልፈው በአንድንተ በአፈ መላእክትና በሰው ለዘለዓለም የሚመሰገኑበት ስማቸው ነው:: ሥላሴ ማለትም ሦስትነት ማለት ነው:: እግዚአብሔር አምላካችን አንድ አምላክ ነው:: ይህ አንድ የሆነ እግዚአብሔር የስም፣ የግብርና የአካል ሦስትነት ያለው በመሆኑ ሥላሴ ይህንን ሦስትነት የሚያመለክት ስም ነው:: «አንሰ ሶበ እቤ እግዚአብሔር እብል በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ:- እኔ እግዚአብሔር ስል አብ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን ማለቴ ነው» እንዳለ ቅዱስ ባስልዮስ:: ስለዚህም አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስንል እግዚአብሔር ማለታችን ነው:: ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ፀባዖት ፍጹም ምሉዕ ስማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ - ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብርህ ተሞልታለች::» እያሉ ቅዱሳን መላእክት ሲያመሰግኑ አይቷል ሰምቷል:: ኢሳ.፮÷፫ ይኽም ሥላሴ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ተብለው እንደሚመሰገኑ ይነግረናል:: «ቅዱስ» የሚለው ቃል ሦስት ጊዜ መደጋገሙ ስመ አብን ስመ ወልድን ስመ መንፈስ ቅዱስን ይወክላልና:: ይህንንም በመጽሐፈ ቅዳሴ ተብርሬቶ እናገኘዋለን:: በቅዳሴ ወቅት ካህኑ በዓቢይ ቃል «አሐዱ አብ ቅዱስ፣ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፣ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ፡ አብ በእውነት ቅዱስ ነው፣ ወልድም በእውነት ቅዱስ፣ መንፈስ ቅዱስም በእውነት ቅዱስ ነው::» እያለ የሚያመሰግነው ሕዝቡም «በአማን አብ ቅዱስ በአማን ወልድ ቅዱስ በአማን ውእቱ መንፈስ ቅዱስ» እያሉ የካህኑን ምስክርነት እውነት መሆኑን ያረጋግጣሉ:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫም በሰዓታት ድርሰቱ «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘበሠለስቱ ግጻዌ ወዘ በአሐዱ ህላዌ - እግዚአብሔር አንድ በሆነ ህልውናወና በሦስት አካላቱ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ነው::» በማለት አመስግኗል::

### ፪ኛ. ጌታ ያስተማረው ትምህርት በመሆኑ

ጌታችን በዚህ ምድር ሲመላለስ ለሕዝቡም ሆነ ለደቀመዛሙርቱ አያሌ ትምህርቶችን አስተምሯቸዋል:: ደቀመዛሙርቱም ከእግሩ ሥር ተቀምጠው ተምረዋል:: እርሱም ካስተማረው እነርሱም ከተማሩት ትምህርት አንዱ ወደዚህ ዓለም ለስብከት ሲያሰማራቸው በማን ስም ማጥመቅ እንደሚገባቸው የሚገልጸው ነበር:: ይኸውም በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲያጠምቁ አስተምሯቸዋል:: ማቴ.፳፰+፲፱:: ስለዚህ እኛ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ልንል የሚገባን ጌታ ለሐዋርያቱ ጠቅሶ ያስተማረው ዐቢይ ትምህርት በመሆኑ ነው፤ የሥላሴን ልጅነት በምእመናን ዘንድ እንዲያጸኑ ያስተማረውም በዚህ ስም ነው::

ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታችን በወንጌል «አነ ወአብ አሐዱ ንሕነ - እኔና አብ አንድ ነን» (ዮሐ.፲+፴) ያለውን መሠረት በማድረግ የረቀቀ ምሥጢር አምልቶ አጉልቶ «አሐዱ አምላክ» የሚለውን ተናግሯል:: ለጌታችን ሰዎች የተለያየ ስምና ስያሜ ይሰጡት ነበር:: በዚህ ወቅት ጌታችን ደቀመዛሙርቱን «እናንተስ እኔ ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ?» አላቸው:: ቅዱስ ጴጥሮስ «አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ::» (ማቴ.፲፮+፲፮) በማለት ከአብ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ መሆኑን ገልጿል:: ቅዱስ ጴጥሮስ ከጌታ ተምሮ በምስጢር የተናገረው በመሆኑ እኛም እንዲሁ እንላለን:: ይኸም ብቻ አይደለም፤ በመጀመሪያዪቱ መልእክቱም እንዲህ በማለት ስመ ሥላሴን ገልጿል:: «እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ እንዳወቃቸው በመንፈስም እንደሚቀደሱ ይታዘዙና በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጩ ዘንድ ለተመረጡት...» በማለት ጴጥ.፩+፩-፪ ስመ አብን፣ ስመ ወልድን ስመ መንፈስ ቅዱስን ገልጿል::

### ፫ኛ. ትውፊት ስለሆን

ትውፊት ውርስ ቅብብል ማለት ነው:: ይኸውም አንድ ትውልድ ከርሱ በፊት ከነበሩት የሚወርሰው የሚያገኘው የሚቀበለው ነገር ነው:: ሂደቱም በተቀበለው የሚያበቃ ሳይሆን እርሱም በተራው ለሚቀጥለው የሚያስተላልፈው ነው:: ይኽም ጸሎት ከቀደሙ አበው ሲወርድ ሲወራረድ ወደ እኛ የደረሰ ነው:: ይህንም አስመልክቶ በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው ጠርጡለስ «እውነተኛ ክርስቲያን ከቤቱ ሲወጣና ወደቤቱ ሲገባ ሲተኛና ከእንቅልፍ ሲነቃ፥ ልብሱን ሲለብስ፥ ምግቡን ለመመገብ ሲቀመጥ፥ እንዲሁም በሥራው ሁሉ ያማትባል:: የማማተብ መሠረቱ ከየት ነው ብሎ ሰው ቢጠይቃችሁ መሠረቱ ትውፊት ነው፤ ሥርዓት አጸናው፤ እምነት ደግሞ አረጋገጠው በሉት» በማለት ትውፊታዊ ቅብብል መኖሩን አብራርቶ ነግሮናል:: እኛም የአበውን ትውፊት መሠረት አድርገን ስንወጣ ስንገባ፣ ስንነሣ፣ ስንቀመጥ፣ ስንበላ እና ስንጠጣ በስመ ሥላሴ እናማትባለን::

### ፬ኛ. የቅዱሳን አበው ድንጋጌ በመሆኑ

በየዘመኑ የተነሡ ሊቃውንት የክርስቶስን ትምህርት መሠረት በማድረግ ጉባኤ ሠርተው ዘመኑን ሊዋጅ የሚችሉ ድንጋጌዎችን ደንግገዋል:: እነዚህ ድንጋጌዎች የሚወስኑት አዲስ ነገር ለማምጣት ሳይሆን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያት ጀምሮ የምታምነውን ትምህርቷን ለመጠበቅና ለማጽናት ነው:: ቅዱስ አትናቴዎስ «ስለ ሃይማኖት በኒቅያ የተሰበሰቡት አባቶች ‹እንደዚህ ተወስኗል› ብለው አልጻፉም፤ ዓለምአቀፋዊነትና ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ‹እንዲህ ታምናለች› በማለት የቤተ ክርስቲያንን እምነት ገለጹ እንጂ» ያለው ለዚህ ነው:: ከደነገጉት አንዱ ማንኛውም ክርስቲያን ተግባሩን ከመጀመሩ አስቀድሞ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ብሎ እንዲያማትብ ነው:: ይህም የራሱ የሆነ መነሻ አለው:: በዲዮቅልጥያኖስ ዘመነ መንግሥት ከ፪፻፹፬-፫፻፭ ዓ.ም. በዓይነትም ሆነ በብዛት ተመሳሳይና ተወዳዳሪ የሌለው የክርስቲያኖች እልቂት ተፈጽሟል:: አብያተ ክርስቲያናት እንዲደመሰሱ አብያተ ጣዖታት እንዲከፈቱ «አብያተ ክርስቲያናት ይትዐፀዋ አብያተ ጣዖታት ይትረኀዋ» ብሎ አዋጅ አስነግሮ ለአርባ /፵/ ዘመናት መጻሕፍት እንዲቃጠሉ ክርስቲያኖች እንዲሰደዱ አደረገ:: ለቸርነቱ ወሰን የሌለው ልዑል እግዚአብሔር ከመከራው ዘመን ቆይታ በኋላ ደገኛውን ንጉሥ ቆስጠንጢኖስን አስነሣ:: በዚህን ጊዜ የከሐዲውን የዲዮቅልጥያኖስ አዋጅ በአዋጅ ሽሮ «አብያተ ጣኦታት ይትዐፀዋ አብያተ ክርስቲያናት ይትረኀዋ - አብያተ ጣኦታት ይዘጉ፣ አብያተ ክርስቲያናት ይከፈቱ/» ብሎ አሳወጀ:: ይህን አዋጅ የሰሙ ምእመናን ከተሰደዱበት ተመልሰው ለአርባ ዘመናት የወደቁ መጽሐፍትን ሰበሰቡ:: የቤተ ክርስቲያን አባቶችም ጉባኤ ሠርተው፣ ሕግ ደንግገው «ዖተግባር ሁሉ መቅድም /መጀመሪያ/ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ይሁን» ብለው ወስነው ጽፈውልናል:: እኛም ይህንን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ እንጠቀምበታለን:: ፍትሐ ነገሥታም በስመ ሥላሴ እንድናማትብ ደንግጓል /ፍ.ነ. አንቀጽ ፲፬/፭፻፴፪፣ ገጽ ፩፻፵፪/፣ ረስጣ ፵፱

አበው ሊቃውንት የነገሮች ሁሉ መጀመሪያ ይሁን ብለው እንደ ሥርዓት ደንግገው በመቅድምነት መጻፋቸው:- ለሁሉ መጀመሪያ በመሆኑ የሥራ መጀ መሪያነቱን ለማረጋገጥና ለተግባር አጽንዖት ለመስጠት ነው:: እንዲሁም በአራቱም ማዕዘነ ዓለም የሚገኙ ክርስቲያኖች ከአረማውያን የሚለዩበት ትእምርት /ምልክት/ ይሁን ብለው ጽፈዋል:: ይህንንም የደማስቆው ቅዱስ ዮሐንስ እንዲህ በማለት ገልጾታል «ግዝረት የእስራኤል ልጆች መታወቂያ እንደ ነበረ በፊታችን መስቀለኛ ማማተብ የተሰጠን እኛ ምእመናን ከሌሎች ተለይተን የምንታወቅበት ምልክት

ወደ ፴፮ ገጽ ዞሯል





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## አምስቱ ዕለታት በደብረ ምጥማቅ

የድንግል ማርያም በዓላት አምስቱ ከግንቦት ፳፩-፳፭ ቀን ያሉት ናቸው። ደብረ ምጥማቅ የምትገኘው በምድረ ግብጽ ስትሆን፣ በዚያች ቦታ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዓበይት ተአምራትን ፈጽማለች። ለአምስት ቀናት ሴት፣ ወንድ፣ ትንሽ፣ ትልቅ ሳትለይ ለሁሉ ስትታይ መስንበቷ በተአምሯ ተብራርቶ ተጽፏል። ሕዝቡም ድንግል ማርያምን ለመመልከት ከምሥራቅ፣ ከምዕራብ፣ ከሰሜን ከደቡብ ተሰብስበው እኩሉ ድንኳን ተክለው፣ እኩሉ ጊዚያዊ ሠቀላ ሠርተው ለአምስት ቀናት ቆይተዋል። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከዚያችው ቦታ ላይ በስሟ በታነጸችው ቤተ ክርስቲያን በሐመረ ብርሃን ላይ ተቀምጣ ለሁሉም ትታያቸው ነበር።

*/ትንሣኤ፣ ግንቦት ፲፱፻፸፫ ዓ.ም፣ ገጽ. ፬/*

*/ስንክሳር ዘወርሃ ግንቦት/*

## ጉባኤ ቃና

ደመናት ካህናት እለ ሞተ ወልድ ሰምዑ፣
አርብዐ ዕለተ እንዘ ይጌልቁ መጽኡ

### ትርጉም

*የወልድን ሞት የሰሙ ደመናት /ካህናት፣*
*አርባ ቀን ቆጥረው መጡ*

### ምስጢር፡-

አንድ ክርስቲያን የሆነ ሰው በሞተ በአርባ ቀኑ ካህናት ተሰብስበው ጸሎት ያደርሳሉ። ደመናትም ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ ከሞተ በኋላ አርባ ቀን ቆጥረው መጡ፤ ማለት ክርስቶስ ሞቶ በተነሣ በአርባ ቀኑ በደመና ወደ ሰማይ ዐረገ ማለት ነው።

*ወ/ሰንበት ተሰፋ ሕይወት*

*/የግእዝ ቅኔያት፣ ፫ኛ መጽሐፍ፣ ገጽ ፻፷፪-፻፷፫/*

## ጨረስኩ ሳልጀምረው

ከፊደላት ተራ ከሆሄ ገብቼ፣
ኩብርሽን ለመግለጽ እምዐቼ አስፍቼ፣
አበው ሲናገሩ ለሳንቺ ሰምቼ፣
ቃላትን ከቃላት መርጬ ለሳኩቼ።
«ሀ» ብዬ ጀመርኩኝ ልናገር ፀጋሽን፣
መጽሐፍ ከሚለው በልቤ ያለውን፣
አባቶች ቀዱሳን ያስተሳሰፉትን፣
በሕይወት ከእነርሱ የተቀበልኩትን።
ከነ «ሀ» ጎረቤት ከነ «ለ» አዝማዳት፣
በሰባት በሰባት ከተከፋፈሉት፣
ከሳይ አስከታች ከተደረደሩት፣
እስከነ «ፐ» ድረስ ከተሰበሰቡት።
ያንንም ሳመጣው ይህንም ስመዘው፣
ጥንት የመረጥኩትን መልሼ ስተወው፣
ፊት ያስገባሁትን ኋላ ስመልሰው፣
አንዱን አስገብቼ ሌላውን ሳወጣው፣
ፈጽሚአለሁ ብዬ የጻፍኩትን ሳየው፣
ድንግል ውዳሴሽን ጨረስኩ ሳልጀምረው።

*ለሜሣ አባተ*
*አዲስ አበባ*

## ብሂለ አበው

* «ሰማያዊን ነገር ለማሰብ ሰውነትህን ሁልጊዜ አነቃቃት» /ማር ይስሐቅ/
* «ስለ አንተ ድክመት የሚነግርህን ሰው ጥሩ ባልንጀራ አድርገህ ያዘው» /ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ/
* «በአንድ ሰው በተተቸህ ጊዜ አንተም ራስህን በውስጥህ ውቀሰው፤ በውስጥና በአፍአ ሚዛናዊነትን መጠበቅ እንድትችል» /ቅዱስ እንጦንስ/
* «ጠዋት ከመኝታህ በምትነቃበት ጊዜ በዕለቱ ለምትሠራው ለእያንዳንዱ ሥራ ለእግዚአብሔር መልስ እንደም ትሰጥ አስታውሰህ አትበድል፤ ፈሪሃ እግዚአብሔርም በአንተ ያድራል» /ባሕታዊ ቅዱስ ኢሳይያስ/
* «ማለዳ ማለዳ በዕለቱ ስለምትፈጽመው ማንኛውም ድርጊት ለእግዚአብሔር መልስ መስጠት እንዲገባ አስታውስ፡- ይህንንም ካሰብህ ፈሪሃ እግዚአብሔር በልቡናህ መዝገብ ይቀረጻል» /ቅዱስ ሙሴ ጸሊም/



©

# ይድረስ ለባለ ዲግሪው ግያዝ ዘኢትዮጵያ

ወዳጄ ግያዝ ዘኢትዮጵያ ሆይ ሰላም ለአንተ ይሁን:: ደብዳቤው የምጽፍልህ ከብሔረ ሕያዋን ነቢየ እግዚአብሔር ኤልያስ ነኝ:: በሰብአ ዓለም ላላችሁት ሰዎች ስጽፍ ይህ ሁለተኛዬ ነው::

አሁን በብሔረ ሕያዋን ብኖርም በምድር ላይ የምትሠሩትን ሥራ ግን አውቃለሁ:: የትኛውም ቦታ የሚሠራውን ሥራ፣ በተለይም እግዚአብሔርን እናገለግላለን ብላችሁ የምትደክሙትን የአንተንና የወንድሞችህን ውጣ ውረድ፣ ደካማና ጠንካራ ጐን፣ ሌላውንም ነገር ሁሉ እናውቃለን:: ወንድሜ ሆይ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ አምነው ድል የነሡት የጻድቃን፣ በምድር በተጋድሎ ላይ ያሉት ምእምናን፣ በብሔረ ሕያዋን ያለን የእኛ፣ በብሔረ ብፁዓን ያሉ ቅዱሳን እና የቅዱሳን መላእክት አንድነት መገለጫ መሆኗን አምናለሁ እንደምትል ዐውቃለሁ:: ነገር ግን በተአምራት የሚገለጸውን የቅዱሳን ዕውቀት በተግባር ለመቀበል ስለሚቸግርህ ደግሞም ቅዱሳን ደብዳቤ ይጽፋሉን የሚል ውሳጣዊ ጸር እንዳለብህም እረዳለሁ:: ወንድሜ ሆይ የምጽፈው ልፈርድብህና ልከስህ እንዳልሆነ አንተም ልትረዳው ትችላለህ:: ከዚህ በፊት ስለ ጻፍኩት ደብዳቤዬና ስለ ዕውቀታችን ግን ከጉዳዬ ፊት መንገር ሳያስፈልገኝ አልቀረም::

ወዳጄ ሆይ የምታነበውንና የምትሰብከበትን መጽሐፍ ቅዱስ በደንብ ካስተዋልከው ከዚህ በፊት ከእኔ ስለተጻፈው ደብዳቤም ይነግርሃል:: ኢዮራም በአባቱ በኢዮሳፍጥ ተተክቶ ከነገሠ በኋላ ወንድሞቹንና የእስራኤልን መሳፍንት ገድሎ በይሁዳ ተራራዎች ላይ መስገጃዎችን ሠራ:: እጅግ ብዙ ክፋትንም በእግዚአብሔር ፊት አደረገ:: ከዚህም በላይ ሕዝቡንም ሁሉ ባሳተ ጊዜ እግዚአብሔር እንዳዘዘኝ «የአባትህ የዳዊት አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- በአባትህ በኢዮሣፍጥ መንገድ በይሁዳም ንጉሥ በአሳ መንገድ አልሔድህምና፥ በእስራኤል ነገሥታት መንገድ ግን ሔደሃልና፥ የአክዓብም ቤት እንዳደረገ ይሁዳንና በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን እንዲያመነዝሩ አድርገሃልና፥ እነሆ እግዚአብሔር ሕዝብህንና ልጆችህን ሚስቶችህንም ያለህንም ሁሉ በታላቅ መቅሰፍት ይቀሥፋል:: አንተም ከደዌው ጽናት የተነሣ አንጀትህ በየዕለቱ እስኪወጣ ድረስ በክፉ የአንጀት ደዌ ትታመማለህ» የሚል ደብዳቤ ጽፌለት ነበር:: ይህንኑ ደብዳቤ ማረጋገጥ ከፈልግህ በዜና መዋዕል ካልዕ ሃያ አንደኛው ምዕራፍ ላይ ቁጥር አሥራ ሁለቱ ጀምሮ ብታነብብ ታገኘዋለህ:: ስለ ዚህ ወዳጄ ሆይ ደብዳቤ ከአንተ በፊት ለነበረ ሰው ጽፌ እንደነበር ላስታውስህ የፈለግሁት በዘመኑ ተጠራጣሪያን የጥቅስ ጥያቄ ተወናብደህ ግራ እንዳትጋባ ነው::

ቅዱሳን በሰማይ ሆነው እያንዳንዱን የምድር እንቅስቃሴ እንዴት ሊያውቁ ደቻላሉም አትበል:: የእግዚአብሔር ጸጋ በእኛ አለና እንድናውቀው ከማይፈቀደው በቀር ሁሉን እናውቃለን:: የምናውቀው ደግሞ በመንፈስ እግዚአብሔር ነው:: በርግጥ አንተም «አይሳነውም» እንደምትል ዐውቃለሁ:: ኤልሣዕ የንጉሥ ሶርያን ምስጢር፥ ጋራ ተራራ ሳይከለክለው እያየ ንጉሡ እስራኤልን እንደረዳው እየገለጽህ እንደምታስተምር ዐውቃለሁ:: በአንተ ዘመን ያሉ የአሁኑ መናፍቃን «ቅዱሳን በምድር ላይ እያሉ ያውቃሉ፤ በሰማይ ግን ስንት ጊዜ ከሞት እየተነሡ ይማልዳሉ? እንዲያውም በውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ላይ እማቤታችን «እንኳን በእርሷ በጻድቃን በሰማዕታትም ልመና የለባቸውም» የሚለውን ሲጠቅሱብህ ግን ልቡናህ መታወኩ አልቀረም::

እንደምናውቅ በመጀመሪያ ልገልጽልህ ያስፈለገኝም ይህን መታወክህን ስለማውቅ ነው:: አንተ የዋህ እስኪ ረጋ ብለህ አስተውል:: የጥንቱ አባቶችህ፥ አሁን የአንተ ዘመን ሰዎች የሚጠቀሙበት ዘመናዊ የመገናኛ መሣሪያ አንዱም ሳይኖር የእግዚአብሔርን ሥራ ያለ ምንታዌ ልብ /ልቡናቸው ሳይከፈል/ ይቀበሉት ነበር:: የእናንተ ዘመን ጥርጣሬ የሠለጠነበት በመሆኑ ተቸገራችሁ እንጂ ማስረጃው የሚበልጠው ግን በእናንተ ዘመን ነው:: አንተ የምትጠቀምበት ተንቀሳቃሽ ስልክ፣ በኮምፒዩተር የምትላላኳቸው ደብዳቤዎች /e-mail/፣ ፋክሶችና ሌሎችም የአንዱ መልእክት ከሌላው ጋር ሳይምታታ በያለበት ዓለም ለምን ይደርሰዋል? ብዬ ብጠይቅህ የተማርኸውን ሳይንስ በመጥቀስ በሞገድ /electro magnetic wave/ ምክንያት እንደሆነ ገልጸህ አሳምረህ እንደምትመልስልኝ አልጠራጠርም:: አንተ ተምረህ የምታውቀውን እግዚአብሔር ለእኔ በጸጋ ይገልጸዋልና ስለ እኔ መማርና አለመማር አትጨነቅ:: ታዲያ አንተ ሞኝ እግዚአብሔር የፈጠረውን የኤሌክትሮኒክስ መግነጢሳዊ ሞገድ ተጠቅማችሁ የሰው ልጆች በሠራችው ዕቃዎች እንዲህ መገናኘት ከቻላችሁ፤ ሞገዱን በፈጠረው በእግዚአብሔር መንፈስማ የበለጠ ልናውቅ እንደምንችል ለምን አትረዳም? አንተ የዋሕ:- «ኢትዮጵያዊው በአማርኛ ሶርያውያን በዐረብኛ፣ እንግሊዞች በእንግሊዝኛ፣ ሌሎቹም በሌላ ቋንቋ ሲጸልዩ ቅዱሳኑ እንዴት ይሰማሉ?» ብለው ሲጠይቁህ ለምን ትረበሻለህ? እስኪ ልጠይቅህ ሁልጊዜ የምትሰብከውን ቅዱስ ጴጥሮስ በአንድ ጊዜ ሦስት ሺሕ ሰዎችን ያጠመቀበትን ታሪክ ለምን አታስታውሰውም? እነዚያ ሁሉ ሰዎች ያመኑት በአንድ ቋንቋ ተሰብኮላቸው ይመስልሃል? ወይስ ቅዱስ ጴጥሮስ አንድ ጊዜ በብዙ ቋንቋ የተናገረ ይመስልሃል? ይህን እንኳ ለምን አትመረምርም:: ይህን ብትመረምር መንፈስ ቅዱስ በመምህርና በደቀመዝሙር አድሮ እንዲረዱ እንዳደረገ በእኛና በእናንተ መካከል አድሮም ሊሠራ የሚችለውን በሙሉ ልብህ ትናገር ነበር:: አንተ ላይ ተጽእኖ ያመጣውን ግን ሳልነግርህ ልሔድ አልፈልግም:: ስማ ግያዝ ዘኢትዮጵያ «ግያዝ ዘእስራኤልን» ስለምን ትመስለዋለህ? እርሱ

*ኤልያስ ዘቴስቢ*

መምህሩና አባቱ ኤልሳዕ የሰጠውን በትረ ድኅነት «ይሄ በትር ምን ኃይል አለው?» ይል ነበር:: አንተ ደግሞ ስለኮምፒዩተር ትንሽ በመማርህ ያለ ሶፍትዌር እንዴት ያውቃል ትላለህ? ራስህን ብትጠይቅማ የሰው ልጅ ሶፍትዌርን ሠርቶ ይህን ያህል መግባባት ከቻለ ከሁሉ በላይ የሆነው መንፈስ እግዚአብሔርማ ስንቱን ረቂቅ ነገር አጉልቶ ያሳይ ይሆን ትል ነበር? አንተ ግን ከጥንቱ ግያዝ መንፈስ ስላል ተላቀቅህ አሁንም አንድ አባት ምን ያውቃል ትለናለህ?

ቢታስተውልማ አንተ የምትጠቀምበት ኮምፒዩተር ብዙ ነገር ያስተምርህ ነበር:: እንዲያውም በዚህ አጋጣሚ አንተ ስለማታውቀው አንድ ሶፍትዌር እኔ ልንገርህ:: በአሁኑ ጊዜ ከኮምፒዩተርህ ሙሉ በሙሉ የደመሰስካቸውን ፋይሎች ፋይሎቹን አስቀምጠህበት የነበረው ስም /file name/ ብቻ ካለህ እነዚያን ከብዙ ዓመታት በፊት ያጠፋሃቸውን እንደገና ማምጣት ተችሏል:: ይህን የምገልጽልህ ስለዚህ ሁኔታ እንኳ ቅዱሳኑ የሚያውቁ መሆናቸውን ልነግርህ አይደለም:: ነገር ግን የምታምን ከሆነ ከዚህ መማር የምትችል መሆንህን ልጠቁምህ ነው:: ከብዙ ዓመት በፊት ንስሐ ገብተህ የተውኸውን ኃጢአትህን አሁን ከአንዱ የቀድሞ ባልንጀራህ ጋር ሆነህ እያስታውስክ ማድነቅ ከጀመርህ ለሰይጣን የፋይሎችን ስም ነገረህ እነዚያን ነገሮች መልስልኝ እያልከው እንደሆነ መረዳት አለብህ:: ኃጢአትህን ማስታወስ ያለብህ እግዚአብሔር ይተውልህ ዘንድ ለመናዘዝ ብቻ መሆን አለበት:: አሁን እንደ ጀማመረህ «ላይፍን ኑረናት ነበር» እያልክ ኃጢአትህን እንደገና አትጥራት:: ሰይጣን በድሮው ብቻ አይተውህም:: ጌታ በወንጌል እንደተናገረ ከእርሱ የከፉ ሌሎች ሰባት አጋንንትን ይዞ ይመጣብሃልና:: አንተ አሁን እንዴት ለዚህ ደረጃ በቁ? እንደዚያ ትጉሃን የነበሩ ሰዎች እያልክ የምታዝንላቸው መንፈሳዊ ወንድሞችህም በዚህ እንደተሰናከሉ ዕወቅ:: ትዳር ውስጥ ከገቡ በኋላ ትተውት በቆዩት የድሮ አኗኗር ለመኖር የሚጀምሩ ካሉ እንዳይሞክሩት ንገራቸው:: እንደገለጽኩልህ ከቀድሞ የከፉ ሌሎች ሰባት አጋንንት ይጨመሩባቸውና ምግባራቸው ፈጽሞ ይለወጣል፤ እንደ አንዳንዶቹም ለፍች ሁሉ ሊደርሱ ይችላሉ:: ስለዚህች ሶፍትዌር ይህን ያህል ከነገርኩህ ወደ ጥንተ ነገሬ ልመለስ::

ስማኝ ግያዝ ቀደም ብዬ እንደ ገለጽኩልህ እኛ በምድር የምትሠሩትን ሁሉንም ስለምናውቅ ነው የጻፍኩልህ:: ለኢዮራምም የጻፍኩለት የእኔን መነጠቅ ዐውቆ እንደ አክዓብ በግምባር መናገር ባለመቻሌ አሁን ባለሁበት ቦታ ሆኜ የማውቅ ስላልመሰለው ነበር:: አሁንም ለሌሎቹ ንገርልን:: በዚህ ዓይነት ደካማ አሳብ መያዝ ኢዮራምን መምሰል እንደ ሆነ ሊያውቁት ይገባሉ:: አሁንም የሚሉህን ዐውቃለሁ::




©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ኤልያስ በብሔረ ሕያዋን ካለ ደብዳቤ የሚጽፍልህ ወረቀትና እስክሪፕቶ የት አገኝቶ ነው? ይልሃል:: አንተ ግን እባክህ ለዚህ ዓይነት ጥያቄ አትደናገጥ:: ከዚህ በፊት ለኢዮራም ሲጽፍ ታዲያ ከየት አመጣው? ብለህ ጠይቃቸው:: ስማ ከዚህ በፊት የላሊበላን መስቀል ከሰማይ አልወረደም ለማለት በተማሯት የሥነ ምድር /Geography/ ትምህርት ተመሥርተው፣ በሰማይ ወርቅና ብር ሥሪ ሳይኖር ማን ሠራው? ደግሞስ በሕዋ እንኳን ወርቅና ብር ኦክስጂን እንኳን የት አለ? ሲሉህም ደንግጠህ ነበር:: ለአብርሃም የወረደው በግ ከየት መጣ? አትላቸውምን:: እነዚህን ሰነፎች አትስማቸው:: ትንሽ ስነባብተው ደግሞ እግዚአብሔር ፍጥረትንም ሁሉ ለመፍጠር ቅርጽ ያወጣለት /ዲዛይነሩ/ ማን ነው እንኳ ቢሉህ አትደነቅ:: ስለዚህ ስለደብዳቤው አትጨነቅ::

ዛሬ ግን የምጽፍልህ በምትወደው ልበወለድ መጽሐፍ በፍቅር እስከ መቃብር ውስጥ የተገለጸውን ፊረጃን መሆንህን ሳታውቀው በእርሱ አብዝተህ የምትስቅ መሆንህ ስላሳዘነኝ ነው:: ጽሑፉን አንብበህ ምን ስትል እንደነበር ታስታውሳለህ? «እንዴት «ዕዝራን» የመሰለ ስም እያለው ደኅናው የቄስ ተማሪ ፊዘኞች «ፊረጃ» ሲሉት ዝም ብሎ ለምን አቤት ይላል» ትላለህ:: አንተስ እንደ እርሱ ያለ ስምህ ስም ሲሰጡህ፣ ግብርህን ለውጠው ሲናገሩ መች ማንነትህን ገለጥክ::

ስማኝ ግያዝ በምንድን ነው ዝም ያልኩት? መቼስ ነው ማንነቴን ያልገለጽኩት? ልትል ትችላለህ:: አንተ መድረክ ላይ ቆመህ መጽሐፍ ቅዱስ በማስተማርህ ብቻ ሥራህን የፈጸምክ፣ ስለሃይማኖትህም የመሰከርክ ይመስልሃል:: ግን እውነት ተጥሎ የፈጠራ ታሪክ ሲነገር መቼ መለስክ? እውነተኛውና ጻድቁ ንጉሥ አርማህ» እንኳን ወዳጅህን ጠላትህን ቢራብ አብላው፣ ቢጠማ አጠጣው» የሚለውን ቃለ ወንጌል ለመፈጸም ምንም የማያውቃቸውን ሰዎች ተቀብሎ በማስተናገዱ «ስለመ» ሲባል ምን መለስክ? ስማኝ እንጂ ግያዝ ደግሞ ባለዲግሪ ነኝ እያልህ ራስህን አዋቂ ታደርጋለህ:: ባለ ዲግሪ መሆንህ መማርህና ማወቅህ እውነተኛውን ታሪክ ለማወቅ ለሌላውም ለማስረዳት ካልጠቀመህ ለመቼ ይጠቅምሃል? በኢትዮጵያ በሀገርህ ታሪክ እንደተገለጸው እንኳን በጥንቱ በአክሱም ዘመነ መንግሥት «ንጉሡ ስለመ» ተብሎ በዐፄ ሱስንዮስ ዘመን ንጉሡ ካቶሊክ ሆኑ» በመባሉ የተነሣውን ጦረነት አታስታውስምን? በአንድ ቀን ስምንት ሺሕ ገበሬዎች የተሰውት፣ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ምእመናን ሰማዕትነት የተቀበሉበትን ታሪክ ዘንግተህ ንጉሡ «ሰልሞ ሞተ» ሲሉህ ዝም የምትል ከሆነ ከአንተ በላይ «ፊረጃ» መባል የሚገባው ያለ ይመስል ሃልን?

ስማ እንጂ ግያዝ እግዚአብሔር የሚያውቃቸውና ሰዎችም እንኳን የሚያውቋቸው ቅዱሳን መናኞች ሳይቆጠሩ ከምግሽ በላይ የሚሆኑትን ምእመናንና ከሃያ አምስት በመቶ በላይ የሆኑት ሌሎቹን አማኞች ሁሉ ዘንግተውና ጨፍልቀው ከሕዝቡ ከሃምሳ በመቶ በላይ ሰልሟል ሲሉህስ ምን መለስህ? ክርስቲያኖቹ ሰልመው ነው? ወይስ አልቀው? ወይስ ምን ተአምራት ተፈጥሮ? ስማኝ እንጂ ባለዲግሪው ግያዝ:- ለመሆኑ በዐሥር ዓመት ውስጥ አንድ ሃይማኖት ያለው ብቻ እየተባዛ ሌላው ያቆማል? ወይስ የአንድ አካባቢ ያሉ ሕዝብ ብቻውን በተአምራት ተባዝቶ የሚበልጥበት ነገር ተገኝቶአል? ወይስ ዓላማ ያለው የቅስቀሳና የፕሮፓጋንዳ ሥራ? ወይስ ያለቦታው ስታቲስቲክስ እያልክ የምትጠቅሰው የትምህርት ስሌትና ቀመር /Formula/ ለዚህ አይሠራም? የምጣኔ ሀብት ባለሞያዎች ስለሕዝቡ እድገት በሠሩት ሞያዊ ትንበያ በማየት እያንዳንዱ እንዴት እንደሚጨምር መረዳት ይገባህ ነበር:: አንተ ግን እንዲህ ዓይነት ጽሑፎችን ማየት እንደ ሥራ ፈትነት ስለምትቆጥራቸው እውነትን ሳትረዳ ዝም አልህ:: ታዲያ አንተ ባለ ዲግሪው እንኳን ይህን ሳትመረምር ያልሆንከውን ሆንህ እየተባለ ሲነገር ከተቀበልክ ከአንተ በላይ «ፊረጃ» መባል የሚገባው የት አለ? ስማኝ ግያዝ ወደ መረጃ መረብ /Internet/ ገብተህ እንኳን ብታይ ብዙ መረጃዎችን ልታገኝ ትችል ነበር:: አንተ ግን እርሱን ተመልክተህ ለመሥራት እንኳን አልተዘጋጀህም:: ለመሆኑ ገብተህ አይተኸው ታውቃለህ? ታዲያ ከአንተ በላይ ፊረጃ ማን አለ:: እውነተኛ ማንነቱን ትቶ ሌሎች በሰጡት ማንነት መኖር ከጀመርክ ሰነበትህ:: ክርስትናን ማስፋፋት ቅኝ ግዛት ነው ሲሉህ ዝም ብለህ ትቀበላለህ:: ጥንት ክርስትና እስከየት እንደተሰበከ ባለማወቅህ ታሪክህም ላይ እንደጌታ መስቀል የታሪክ ቆሻሻ አብዝተው በመድፋት ሲደብቁብህ አንተ ዝም አልክ:: ክርስትናህን ለዘመኑ የሚመች የፖለቲካ ጥላሸት ቀብተው ሲናገሩህ እውነትን ለማስረዳትና እውነተኛ ገጽታውን ለማሳየት መቼ ልቡናህ ከጀለ?

ስማኝ ግያዝ አንተ ከመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፈ አስቴርን በመጥቀስ ስለሐማ ክፋትና ሕዝብን ለማስተዳደር የተሰጠውን ሥልጣን አላግባብ በመጠቀም ንጉሡን አርጤ ክስስንም የሚያሳምን የሐሰት ነገር አቅርቦ እርሱ የሚጠላቸውን አይሁድን በአንድ ቀን ሊያጠፋ፣ የሠራውን አንሥተህ ታስተምራለህ:: ታዲያ በአሁኑ የአንተ ዘመን ያሉ ሐማዎችስ ሓላፊነታቸውን ዘንግተው ድህነትን፣ ኋላቀርነትንም፣ ሌላውንም ሀገራዊ የጋራ ፈተና በኦርቶዶክስ እያመካኙ ሲናገሩና መንግሥትንም ለማሳሳት ሲጮኹ እውነቱን ለማስተረዳት መቼ ደፈርክ? በራሳቸው ሃይማኖት ያላመኑትን ለማንገላታት የፈጠራ ፖለቲካዊ ክሶችን ሲደረድሩ ሐማ አይሁድነትን ለማጥፋት እንደጠራው እነርሱ ክርስትናን ለማጥፋት ሲነሡ መቼ መለስክ? እንዲያውም እውነት ይሆን ይሆናል በማለት አሁንም እየተጠራጠርክ ብዙ ሰዎችን ጎዳህ::

ግያዝ ሆይ ስማኝ ልንገርህ:: አንተ መጽሐፍ ቅዱስን ለመግለጥ የምትደፍረውን ያህል እውነትን ለመረዳትና ለማስረዳት ለምን አትደፍርም? እውነትን እነግርሃለሁ:: ራስህን ካላስተካከልክ በቀር ከእግዚአብሔር የሚጠብቅህ ፍርድ የሚቀርልህ አይምሰልህ? አንተ አልዋሽሁም፣ ክፉም አልተናገርኩም፤ ሕዝቡንም አላሳሳትኩምና ተጠያቂ አልሆንም ብለህ አታስብ:: ጌታ በትያጥሮን ላለችው የቤተ ክርስቲያን አለቃ የተናገረውንና በዮሐንስ ራእይ ላይ የተጻፈውን ትዘነጋለህን? «ነቢይ ነኝ የምትለውን፣ ባሪያዎቼንም እንዲሴስኑና ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉ የምታስተምረውንና የምታስተውን ያችን ሴት ኤልዛቤልን ስለምትተዋት የምነቅፍብህ ነገር አለኝ» እንዳለው አንተም እንደ ዕዝራ ፊረጃነትህን ተቀብለህ ዝም በማለትህ የሚያስነቅፍ ነገር አለብህ:: ግያዝ ሆይ በፍጥነት ራስህን አስተካክል:: የቤተ ክርስቲያንህንም እውነተኛ መልስ ግለጥ:: በፍርሃት ተውጠህ በቸልተኝነትም ተይዘህ እውነትን አትቅበር:: የብዙዎች ጩኸትም አያስደንግጥህ:: እንኳን ዛሬ የጥንት ሰዎችም የክርስቶስን ትንሣኤ ውሸት ነው ብለው አውርተው ነበር:: ጌታንም አይሁድን ሊያፈናቅል፣ በንጉሡ ሔሮድስ ሊያሳምጽ የመጣ ነው ብለውት ነበር:: ስለዚህ አንተም ያሻቸውን ቢያወሩብህ አትደንግጥ:: ብቻ ክፉውን ሥራ ሁልጊዜም ተጸየፈው:: ክፉ እስካልሠራህ ድረስ ግን እውነቱን ለመናገር ስለ ክርስቶስ ለመመስከርም አትፍራ:: ማንነትህን ገልጠህ እውነቱን መናገር ካልቻልክ ኤልያስን «ሸምሱ» ባሮክን «ሁሴን» እያሉ ስማችሁን ለውጠው ይነግሯችኋል፤ እናንተም ማን ይሰማናል እያላችሁ ትቀበሉትና ተረቱ ታሪክ ሆኖ ሲነገር መስማት ትጀምራላችሁ:: በርግጥ እናንተ አትደንግጡም:: ዋሻ አኖሬዎስ የኑር ሁሴን ዋሻ ሲባል ምን አላችሁና? ለጊዜው በእዚህ አሳቤ ልሠናበትህ:: በል ግያዝ ሠርተህ ለመለወጥ እግዚአብሔር አምላካችን እንዲረዳህ እየተመኘሁ ብለይህም ወደፊት ግን የምጽፍልህ መሆኔን በመግለጥ ጭምር ነው:: ደኅና ሁን ግያዝ::ቀ

ብታስተውልማ አንተ የምትጠቀምበት ኮምፒዩተር ብዙ ነገር ያስተምርህ ነበር:: አንተ ስለማታውቀው አንድ ሶፍትዌር እኔ ልንገርህ:: በአሁኑ ጊዜ ከኮምፒዩተርህ ውስጥ በውስጥ የደመሰስካቸውን ፋይሎች ፋይሎቹን አስቀምጠህበት የነበረው ስም /file name/ ብቻ ካስህ እነዚያን ከብዙ ዓመታት በፊት ያጠፋሃቸውን እንደገና ማምጣት ተችሏል:: ይህን የምገልጽልህ ስለዚህ ሁኔታ እንኳ ቅዱሳኑ የሚያውቁ መሆናቸውን ልነግርህ አይደለም:: ነገር ግን የምታምን ከሆነ ከዚህ መማር የምትችል መሆንህን ልጠቁምህ ነው::

# የበረሐዋ ገነት

## ላማ ደብር ማርያም ዘመቄት

ዲ/ን ብርሃኑ አድማስ

ከአዲስ አበባ ፭፻ ኪ.ሜ ርቀት ላይ ወዳለችው ገዳም ለመጓዝ የተነሣሁት ረቡዕ ጥር ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ከሰዓት በኋላ ነበር:: የተለመደውን የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዝግጅታ ከሚጠበቀው የደኅንነት ጥያቄያቸው ጋር ተቀብለን ሦስት ሰዓት ያህል በቦሌ ደጅ ጠናን:: ከዚህ ሁሉ ደጅ ጥናት ፀኋላ ዐሥር ሰዓት ላይ የበረረው አውሮፕላን ተፈጥሮን ከአዲስ አቅጣጫ እን ድናያት እያጋበዘንና የጉም መልክአ ምድ ርን እያስጐበኘን ከሃምሳ አምስት ደቂቃ በኋላ ባሕርዳር ከተማ አድርሶን ተመለሰ::

ከቀኑ ዐሥራ አንድ ሰዓት ላይ የተቀ በለችን ባሕርዳር ከቀኑ ሙቀቷ በነፋሻ ማው የጣና አየር እየቀዘቀዘች ነበር:: ብዙ ዎች በብስክሌት ይከንፋሉ፣ ወጣቶች በጉ ርድና በሸሚዝ ቀለል ባሉ ልብሶች ከመ ንገዶቿ ግራና ቀኝ በተሰለፉት ዘንባባ ዎቿ መካከል ይጓዛሉ:: ሠራተኞችና ተማ ሪዎች ወደ ቤት የተለቀቁበት ሰዓት በመ ሆኑ መንገዶች በሰው ተጨናንቀዋል:: በተ ፈጥሮአዊ ውበቷ የምትወደደው የባሕ ርዳር ከተማን እንደማናውቃት ሁሉ አፍ ጥጠን እያየን ወደተዘጋጀልን ማረፊያ አመራን::

ሐሙስ ረፋዱ ላይ በተዘጋጀልን መኪና ተሳፍረን ከባሕርዳር ሰሜን ምሥራቅ አቅ ጣጫ ወደሚገኘው የሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ጉዞ ጀመርን:: ከባሕርዳር ሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ለመድረስ ደቡብ ጎን ደርን ሙሉ በሙሉ ማቋረጥ ስለሚጠይቅ ከባሕርዳር ጎንደር የሚወስደውን መንገድ ይዞ ስልሣ ኪሎ ሜትር ያህል ከተጓዙ በኋላ የወረታን ከተማ ወጣ እንዳሉ ወደ ቀኝ የሚታጠፈውን መንገድ መያዝ ያስፈል ጋል:: እኛ ግን በእስቴ ወረዳ ደብረ ሃይ ማኖት መካነ ኢየሱስ የሚገኘውን የብሉ ያትና የሐዲሳት የትርጓሜ ቤት ለማየ ትና ከመምህሩም ጸሎት ተቀብሎ ለመሔድ ስለተስማማን ሐሙሲት ከተማ እንደ ደረ ስን ሾፌራችንን ወደ እስቴ እንዲወስደን ጠየቅነው:: ሾፌሩ ሁለት መቶ ብር እንደ ሚያስጨምር ነግሮን ጉዞውን ቀጠለ:: ከሐሙሲት እስቴ የሚወስደውን መንገድ እንደ ጀመርን በግራ በኩል የግብጻዊት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ልምላሜው በሚ ማርክ ደን ተከባ ብቅ አለች:: /ግብጻዊት ማርያም እመቤታችንና ጌታችን በስደት ወቅት ካረፉባቸው ቦታዎች አንዷ በመ ሆኗና እመቤታችንን የመጣችው ከግብጽ መሆኑን ለመናገር ነበር ግብጻዊት የተባ ለችው::/ እርሷን ተሳልመን የእነ ቅድስት እማ ሸንኩሮን ሀገር አልፈን ሰኔ ማርያም ተራራ ላይ ደረስን:: መኪናችን ይፈጥናል:: ለምን ሰኔ ማርያም እንደተባለች ተነጋግረን ሳንጨርስ ጥንታዊቷ ደብር ሸሜ ማርያም ላይ ደረስን:: አሁን ደግሞ መነጋገሪያችን እርሷ ሆነች:: የእርሷን ሳንጨርሰው ግራኝ ድል የተደረገበትና ኢትዮጵያ ዊው ዐፄ ገላውዴዎስ ያሠሩት የሰማዕቱ የገላውዴዎስ ቤተ ክርስቲያን ደረስን::



ላማ ደብር ማርያም ዘትክልት በመዋዕሊሁ ለካሌብ ጻድቅ

«ጊፋራ» ተብሎ በሚጠራው ስፈ የተፈጥሮ ደን የተከበበውንና ደብሩ ከተተከለ ጀምሮ እንዳለች በሚነገርላት ነጭ ነብ ጭምር የሚታወቀውን መካነ ሰማዕት ገላውዴዎስ ንና የቦታውን ታላቅ መምህር መልአከ ሕይወት አስናቀ ጸጋውን ሰላም ለማለት ጊዜ አላገኘንም:: ሾፌራችን በጊዜ መግባት አለብን እያለ ይፈጥናል::

የጉማራን ወንዝ እንደተሻገርን ልጫ መስ ቀልን አልፈን ግንድ አጠመም ሚካኤል ደረስን:: ቦታውን ቀደም ብዬ ባውቀ ውም አሁን ግን ልዩ ትዝታ በደንብ እን ድመከለተው ጋበዘኝ:: ከሁለት ወራት በፊት በሰሜን ኢትዮጵያ እየተዘዋዋሩ ገዳማትና አድባራትን ከችግር ለማላቀቅ የሚያስችሏቸውን የልማት ሥራዎች /ፕሮ ጀክቶች/ ለመቅረጽ የወጡ የማኅበሩ መደ በኛ አገልጋዮች ነበሩ:: ባለሞያዎቹ በሰሜን ሸዋ ወጥተው ወሎ፣ ትግራይና ጎንደርን ሠር ተው በጎጃም ፈጸመው ከሁለት ወራት በኋላ ነበር የተመለሱት:: ከእነዚህ የማኅበረ ቅዱሳን የቅዳሴት መሐናትና የአብነት ትምህርት ዐቶች መርጃና ማቋቋሚያ ክፍል ባለሙያዎች አንዱ ጌታ ባሕሩ ለሥራው ሲፋጠን የጠፋው እዚህ አካባቢ ነበር:: ጌቱ ማኅደረ ማርያም ሔዶ ለማጥናት ሲጓዝ ነበር ከእስቴ መጥቶ ግንድ አጠመም ሲደርስ መንገድ ጠፍቶት ወደ ግራሪያ በርሃ የተጓዘው:: ጌቱ ሪፓርቱን ሲያቀርብ በዓይኑ ጎሊና ያየሁትን አሁን በአካል ሳገኘው እኛንም የሚያደናግረን ይመስል አፈጠጠከብኝ:: ለማንኛውም ጌቱ ስለተገኘና አዲስ አበባ ስለተመለሰ የሌሎቹንም ድካምና የሚደ ርሳባቸውን እንግልት የእነርሱንም ቆራጥነትና መንፈሳዊነት ያልተለየው አግ ልግሎት እያወጣሁ እያወረዳሁ መካነ ኢየሱስ ገባን::

ደብረ ሃይማኖት መካነ ኢየሱስ የእስቴ ወረዳ ከተማን መካነ ኢየሱስን አቋርጠ ው በግምት ሰባት ኪሎ ሜትር ያህል ወደ ሰሜን (ወደ ደብረ ታቦር) እንደተ ጓዙ የሚገኝ በዐፄ አድያም ሰገድ ኢያሱ የተተከለ ደብር ነው:: ከደብሩ ጀርባ ያለውና የተቀመጠ አንበሳ የሚመስለው የእስቴ ዴንሳ ተራራ ልዩ ግርማ ሰጥቶ ታል:: በነጋታው የሚከበረውን የሰማዕቱ የቅዱስ መርቆሬዎስን በዓል ለማክበር በአካባቢው ትውፊት መሠረት ታቦት ሊያወርዱ ይዘጋጃሉ:: ለዚሁ በዓል የሔዱ ከአዲስ አበባና ከካናዳ እንዲሁም ከሌሎች ከተሞች የመጡትን እንግዶች ሰላም ብለን ወደ ጉባኤ ቤቱ አመራን:: ከየኔታ ኃይለ ሚካኤል መስቀል ለመሳለም ወደ ጸሎት ቤታቸው ብቅ ስንል የኔታ ትንሽ አሟቸው ስለነበር ቶሎ ብቅ አላሉም:: ጸሎታቸውን በአቡነ ዘበሰማያት አሥረው ወደ እኛ ቀስ ብለው ብቅ አሉ:: በተለመደው አባታዊ ፍቅር ተቀብለው ወደ እንግዳ ቤት ወሰ ዱን:: ከዐርባ ዓመት በላይ በረድነት ያገ ለግሏቸው አባ ኪዳነ ማርያም /የኔታ አባ/ ለክብረ በዓል በተዘጋጀው ድግስ አስተና ገዱን:: በእርሳቸው የተጠመቀውን ጠላም ቀማምሰን ደስ እያለን ጉዞ ወደ ወሎ::

### የእግዚአብሔር ድልድይ

በጋሳኝ ወጥተን ክምር ድንጋይን አቋ ርጠን እነዙርአምባ ጽርሐ አርያም አቡነ አረጋዊ ገዳምን እያየን ነፋስ መውጫ

ወደ ፀሥር ሰዓት ተኩል አካባቢ ገባን:: ከድካማችን ለመንቃት ሻይ ቡና አልንና የደቡብ ጎንደርን የመጨረሻዋን ከተማ ንፋስ መውጫን ተሰናብተን የጨጨሆ በረሐን ተያያዝነው:: የጨጨሆ በረሐ በግራ በኩል የተከዜ ወንዝ ገባሮችንና የዕብናትና የበለሳ ገጠራማ ቀበሌዎችን አሻግሮ ያሳያል:: በቀኝ በኩል ደግሞ የበሽሎ ወንዝ መነሻዎችንና የደቡብ ወሎ አቅጥጣጫን የሚያሳይ ነው:: ጨጨሆ እንደ ባሕረ እሳት በቀኝም በግራም ገደል እያዩ የሚያልፉበት አስደናቂ ተፈጥሮአዊ ገጽታ ያለው ቦታ ነው::

ከላይ የመጣንበት ገደላማ ገጽታ ከግራም ከቀኝም ገደልና በርሐ ቢሆንም የደቡብ ጎንደርና የሰሜን ወሎ መገናኛ ላይ ያለው ሁኔታ ግን ይለያል:: ገደላማ ገጽታው ከግራም ከቀኝም እየሳሳ ይመጣና እዚህች ቦታ ሲደርስ ከመኪና መንገዱ በቀር በግራም በቀኝም ጭው ያለና ማረፊያው የማይታይ ገደል ነው:: በዚህ ምክንያት የአካባቢው ነዋሪዎች የእግዚአብሔር ድልድይ ይሉታል:: እውነትም የእግዚአብሔር ደልድይ:: ስፋቷ በጣም ጠባብ ባለመሆኑና ርቀቷም አጭር ባይሆን ድንጋጤውን አይጣለው::

የእግዚአቤሔር ደልድይን ተሻግረን ጠመዝማዛውንና ገደላማውን ቀሪውን የጨጨሆ ክፍል አቋርጠን ደጋማውና ነፋሻው መቄት ገባን:: የመንገዱ ግራና ቀኝ በባሕር ዛፎች የተዘጋ አጥር ነው:: በባሕር ዛፉ እያሾለክን ሜዳውን እያማተርን አሥራ አንድ ከሩብ አካባቢ የፍላቂት ከተማ ደረስን:: ተጓዦቻችን ለአካባቢው አድባራትና አብያተ ክርስቲያናት እንዲሰጥ የያዙትን ጧፍና ዕጣን አስቀምጠው ልንሔድበት ወደ መጣነው ደብር ለመጓዝ መንገዷን ማጠያየቅ ያስፈልገን ነበር::

*ከፍላቂት ወደ ላማ ደብር ማርያም*

ወደ ላማ ደብር ማርያም ለመሔድ ከዋናው መንገድ ቢያንስ ሃያ ኪሎ ሜትሩ በምግብ ለሥራ የተሠራ መንገድ አለው:: ከፍላቂት ከተማ ወደ ነፋስ መውጫ አቅጣጫ ሰባት ኪሎ ሜትር የሚሆን ከተመለስን በኋላ ወደ ቀኝ እንደታጠፍን እጅግ የሚያስደነግጥ ገደል ገጠመን:: መኪናችን አቁመን ወርደን ተመለከትነው:: በዚያ ያሉት ገበሬዎችን ጠየቅን:: አሻግረው በእጃቸው እየጠቆሙ አመለከቱን:: ሁላችንም የመሰለንን የተለያየ ቦታ ተረድተን አድራችሁ ብትሔዱ ይሻላል የሚለውን ምክራቸውን ትተን ለመጓዝ ወሰንን:: ባለመኪናችን ደግሞ ይህን አስፈሪ ገደልና በእጅ የተሠራ መንገድ ደኅና ገንዘብ ካልተጨመረኝ አልሔድም አለ:: አቢሎ ሹፌራችን መጀመሪያ ገጠር ሒዶ ማደሩንም አልወደደውም ነበር:: መካነ ኢየሱስ ከበላነው ውጭም ምግብ ሌላ ቦታ ስላልበላን የራቱም ነገር አሳስቦታል:: በኋላ ግን በጉዞአችን ከተሳተፉት በለንደን ነዋሪ የሆነችው ዊይንታና ለመሔድ ያላትን ፍላጐት ሲያይ እንዴት ከእርሷ አንሳለሁ በማለት ቆረጠ::

**የጨለማው ጉዞ**

እጅግ የሚያሳቀቅቀውን ገደል በዝምታ መውረድ ተጀመረ:: ቀኑ እየመሸ ነው:: በእጅ የተነጠፉ ድንጋዮችንና



*አፈ መምህር መልአክ ንጋቱ*

የተቆፋፈሩ መንገድ መሰል መሬቶችን እየረገጠ መኪናችን በሰዓት አሥር ኪሎ ሜትር በሚያደርስ ፍጥነት ጉዞውን ተያያዘው:: ያ በሰዓት መቶ እስከ መቶ ሃያ ኪሎ ሜትር ይፈጥን የነበረ መኪና /Toyota Land cruser/ አሁን እንደ ዔሊ ይንቀራፈፍ ጀመር:: እያነሣ እያፈረጠን፤ ከጐኑም እያላተመን ገና ዐሥር ኪሎ ሜትሩን እንደተጓዝን ፀሐይ ደብዛዋ ብቻ ሳይሆን የብርሃን ጭላንጭሏ ተሟጥጦ በጨለማ ተዋጥን::

የበረሐው ጉዞ ግን እንደቀጠለ ነው:: አካባቢው ተራራማና ገደላማ በመሆኑ መንገዱ ጠመዝማዛ ነው:: ስለዚህ ወደ ዳገት ሲወጣ የት እንደሚሔድ የምናውቀው ከወጣ በኋላ ነው:: ሜዳ ነው ብሎ መሮጥ ሲጀምር ገደል አፋፍ ሔዶ ይቆማል:: ወደ ግራ እየዞረ እንዳለ እንደገና ወደቀኝ ይጠመዘዛል:: መንገዱ አሳልቅ አለን:: እፊታችን ገደል ይሆን ተራራ አይታወቅም:: እኔና ሊቀ ጠበብት አርአያ አላስቻለንም:: «ኦ ክርስቶስ ቀስ በል፤» አንዳንዴ ደግሞ በጩኸት ጭምር «ቀና! ቀና!» እንላለን:: የልብ ትርታችን ይመታል:: ሜዳ ላይ ስንደርስ ተንፈስ እንልና ቀደም ብለን በተናገርነው መሳቅ እንደጀመርን እንደገና ሌላ ገደል! እንደገና ድንጋጤ:: ለመሆኑ የት ነው የምንሔደው? መቼ ነው የምንደርሰው? መጠየቅ ጀመርሁ:: ደግነቱ በዚያ ጊዜና ቦታ ጐማ እንኳን አለመተንፈሱ:: አስቃቂውንና አስደንጋጩን የአንድ ሰዓት ተኩል መንገድ ከተጓዝን በኋላ በመኪናው መብራት ድንገት ጫማ ተመለከትንና ደነገጥን:: በሌላ በኩል ደግሞ ከተማ ደረስን ማለት ነው? የሚል የተስፋ ጥያቄም አደረብን:: ትንሽ ቆይቶ ደግሞ ወደ መኪናችን የሚሯሯጡ ሰዎች መጡ:: ባንነጋገርም ምንነቱ ስላልገባን ተደናግጠናል:: እነርሱን እያየን ዘወር ስንል ግን የቆርቆሮ ቤቶችን ተመለከትን:: እፎይ!

**እፎይታ**

ሻሽ የጠመጠሙ አባትና ሦስት የሚሆኑ ገበሬዎች ቀስ እያሉ ወደ እኛ ይጠጋሉ፤ ጨለማ ስለሆነ ልንለያቸው አልቻልንም:: ዊይንታና አፈ መምህር ናቸው፣ ትላለች፤ እኛ ደግሞ አይደሉም እያልን፤ እነርሱ ሲጠጉ እኛም በጥርጣሬ ስንመለከት ወደ መብራቱ በደንብ ተጠጉልን:: ያን ጊዜ መልካቸውን አይተን ማንነታቸውን ለየንና በደስታ ከመኪናችን ወርደን ተቃቅፈን ተሳሳምን:: እግዚአብሔርን አመስግነን ወደ ተዘጋጀልን ማረፊያ አመራን::

እኔ በነጋታው ስለምመለስ ገዳሙ ካደርንበት ምን ያህል እንደሚርቅ መጠየቅ ጀመርሁ:: በእግር የሁለት ሰዓት የሚወስድ መንገድ ነው አሉኝ:: ስለዚህ ቃለ መጠይቁን ማታውን መሥራት እንዳለብኝ ወሰንኩ:: ዕቃዎቼን ካዘጋጀሁ በኋላ አፈ መምህርን ጠይቅኋቸው:: «ስምዎትን? ከማን እና መቼ ተወለዱ?»

«ንጉሥ ሰሎሞን ምኒልክ ቀዳማዊን ይወልዳል፣ ምኒልክ...» አሉና ንግሥተ ሳባ ከእስራኤል ንጉሥ ከሰሎሞን ከወለደችው ጀምረው መጓዝ ጀመሩ:: መካከል ላይ እየተገረምኩ አንዳንዴም ሳቄ እየመጣ በግምት ከሃያ ደቂቃ በኋላ የእርሳቸው ወላጆች ላይ ደርሰው የእርሳቸውን ትውልድ መግለጽ ቻሉ:: በዚህ መንገድ ቃለ መጠየቁን አጠናቅቄ በፍቅርና በአክብሮት የተዘጋጀልንን ማዕድ ተቋድሰን ለማረፍ ተዘጋጀን:: ቁንጫውን የፈራነው ሦስታችን ወደ መኪናው ገባን:: ሌሎቹ እቤት ውስጥ ዐረፉ፤ ነገር ግን እንደተፈራው አንዴ በቀኝ በጎን ሌላ ጊዜ በግራ እየተገላበጡ ቁንጫ ጋር ሲሯሯጡ አደሩ እንጂ ዕረፍት አላገኙም:: እኛም እግራችንን አጣጥፈን ስንነቃ እየተዛዘን፤ ዕንቅልፍ ሲወስደን እየተጋፋን አደርን::

**የእግር ጉዞ ወደ ላማ ደብር ማርያም**

ከሌሊቱ ዐሥራ አንድ ሠዓት ላይ ከእኔ ጋር እንዲሔዱ ከተመደቡልኝ ሰዎች ጋር አስገራሚው የእግር ጉዞ ተጀመረ:: እንድሔድባት የተዘጋጀችልኝ በቅሎ ቀመቷ በማጠሩ ምክንያት ርካቡ እግሬን ከማጠፉ በቀር ጸባይ አላት:: ሊነጋጋ ሲል ዐሥራ ሁለት ሰዓት አካባቢ የሰማይ ባላ የመሰለው ረጅም ተራራ ጋር ተፋጠጥን:: ዳገቱ ለኔ በእግር የሚታሰብ አይደለም:: በቅሎዋ ላይ ሆኜ በእነዚያ ፈጣን ገበሬዎች እየተመራሁ ተራራውን ተያያዝኩት:: ከአንድ ሰዓት በኋላ ተራራው አናት ላይ ደረስን:: አሻግሮ የላሊበላና የዐይና ተራራዎች /ቡግና ውስጥ ያለ አሁን ራሱን ችሎ ወረዳ የሆነ/ ይታያሉ::

**ድርብርብ ግርምታ**

ከተራራው ወጥቼ ቀልቁለቱን ለመውረድ እንደጀመርን ድንገት በግራ ጭኔ በኩል ንዝረት ተሰማኝ፤ ትንሽ ቆይቶ ደግሞ ድምፅ ተሰማኝ:: በድንጋጤ ሰውነቴን ጨበጥኩ፤ በኪሴ ውስጥ የነበረው ተንቀሳቃሽ ስልክ ነበር:: ማመን አልቻልኩም፤ ስልካችን ከኔትወርክ ውጭ ከሆን ሁለት መቶ ኪ.ሜትር አካባቢ ሆኖታል:: ጥሪው ከባሕር ዳር ነበር:: የምመለስበትን የአውሮፕላን ትኬት ሊያረጋግጡ (Ok ሊያስብሉ) የሰጧቸው እስክንድርና ሰላማዊት ነበሩ:: ስልኩን ባልመለስ ኖሮ የመመለሻዬ ነገር አስቸጋሪ ሊሆን ይችል የነበረ መሆኑን ስረዳ እንደገና ተአምራት ሆኖብኝ:: ኔትወርክ ከየት መጣ? እየተገረምሁ መልስ ሳላገኝለት እንደገና ወደ ሲኦል የመውረድ ያህል የሚያንደረ ደረውን ቁልቁለት ተያየዝነው:: ሁለት ሰዓት ይወስዳል የተባለው መንገድ ሁለት ሰዓት ከተጓዝኩ በኋላ ግማሽ ላይ እንደ ደረስኩ ተነገረኝ:: ልመለስ አልችል ይሆን በሚል ስሜት እያዘንኩ ከበቅሎዬ

ወርጄ ቁልቁለቱን በእግሬ መንደርደሩን ተያያዝኩት። አብረውን ያሉት ሰዎች ተጨነቁ «እጠክምትን ይውጡ» አለኝ አንደኛው ወንድም። «ቁልቁለቱ በጣም ኃይለኛ በመሆኑ በበቅሎይቱ አንገት ሾልኬ እወድቃለሁ» ስላቸው በጸጸት «እንዲህ መሆኑን እኮ ብናውቅ አልጋ አዘጋጅተን፣ እዚያ ላይ ወንበር አድርገን፣ በሸክም እና ወርድዎት ነበር» አሉኝ። እንደገና ሌላ ግርምታ፤ እነርሱ መንገድ እንዳይመታኝ ይህን ያህል ይንሰፈሰፉልኛል፤ እኔ ግን ከተማ ውስጥ ባገኛቸውና አንድ ታክሲ ውስጥ ብንሳፈር እጉናቸው እቀመጥ ይሆን? እያልኩ በአግራሞት ጉዞዬን ቀጠልኩ።

### አቀባበል

ከአንድ ሰዓት ተኩል በኋላ ገዳሟን አምስት ኪሎ ሜትር ላይ ሆኜ ገደል ውስጥ መመልከት ቻልኩ። ገና ተራራው ላይ ብቅ ስንል እገዳሟ መግቢያ ላይ ድባብ ተተክሎ ጃንጥላዎች ተይዘው ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ካህናት እያጠኑ መዘምራኑ ለወረብ ይዘጋጃሉ። ምንድን ነው ስል ጠየቅሁኝ። «እናንተ ከአዲስ አበባ እንደምትመጡ አፈ መምህር ስለተናገሩ ሊቀበሉ ወጥተው ነው።» አሁን ጥሩምባ የሚነፋው እኛን ስላዩ ለመቀበል እየተዘጋጁ ነው አሉኝ። እኔም አንዳችሁ ሒዱና ዋናዎቹ እንግዳዎች ከኋላ ናቸው ብላችሁ አስቁሙ ብዬ በልመና ልኬ በብዙ ድርድር አቆሙ። ስደርስ ግን ሁሉም ከዚህ በፊት እንደሚያውቁኝ እየተጠመጠሙ ይስሙኛል። እንዳንዶቹ በአግራሞት ያዩኛል። እነርሱ እንደሆኑ አሁንም ወረቡን ሊወርቡት ያምራቸዋል። እኔ ግን ጊዜ አልነበረኝምና ቶሎ ወደ ጸበሉ ውሰዱኝ፤ ዛሬውኑ እመለሳለሁ አልኩኝ። የለበሱት ካህናት ፊት ለፊት እየመሩ ጉዞው ተጀመረ።

### ጥንታዊቷ ገዳም ላማ ደብር ማርያም

ላማ ደብር ማርያም የሁሉ ቀደምት፣
አባ ገብረ ኢየሱስ የጸለዩበት፣
ለምልሞ ይታያል ዙሪያው በአታክልት፣
ጠበሉ ዐርባ ሁለት የዓለም መድኃኒት፣
ድምፁን እያሰማ ቀንና ሌሊት፣
ዘበኛው ዘንዶ ነው የሚጠብቃት፣
የኢጣሊያ መንግሥት ያልተረገጣት፣
ስሟ የሚጣፍጠው እንደ ማር ወተት፣
ዋድላና ደላንታ ሲቀበርባት፣
ይመስክር የለ ሽድሆ መቄት፣
በጌምድር ነገላ ጨጭሆ ጋይንት
ላስታ ላሊበላ ግዳን ደንጐባት።

አፈ መምህር መልአከ ንጋቱ ስለ ላማ ደብር ማርያም ታሪክ ሲጠየቁ መጀመሪያ የሚያቀርቡት እምሃ ይህ ከላይ የተገለጸው ግጥም ነው።

እንደ አፈ መምህር ገለጻ ላማ ደብር ማርያም የተተከለችው በዐፄ ካሌብ ዘመነ መንግሥት በአምስተኛው ክፍለ ዘመን ነው። እንደ እነርሱ ገለጻ ደብሯንም የተከሏት «አባ ላማ» የተባሉ ቅዱስ ናቸው። ስለቅዱሱ የተጻፈ ገድልና የመሳሰሉትን ማየት ባልችልም ቦታው ወይም አካባቢው አባ ሰላማ ጽጽስናን ይዞ ከመጣ በኋላ ክርስትናን ለማስፋፋት ከአክሱም ደቡብ አቅጣጫ ሲጓዙ ሰቆጣንና ላስታን አድርገው የሚደርሱበት አካባቢ ይኸው መቄት መሆኑ ግን ግልጽ ነው። ላሊበላን ለመሳለም የወረደ ሰው ወደ ይምርሃነ ክርስቶስ ከሔደ በዚያ አካባቢ ያሉት የእነ ብልባላ ቅዱስ ጊዮርጊስ ዋሻዎች በዐፄ ካሌብና በዐፄ ገብረ ማስቀል ዘመን የተሠሩ ፍልፍል ሥራ ዎች መሆናቸውን ሲያይ በዚህ አካባቢም ይህች ደብር በዚያ ዘመን ተተከለች ቢባል ለመቀበል አይቸገርም። ከዚህም አልፎ «ኮን» ውስጥ የአባ ሙሴን ገዳም ጭራ መድኃኔዓለም ወርዶ የቅዱሱን ገድል ለተመለከተ እርሳቸውንም ገድላቸው ከሰላማ በኋላ የመጡ ጳጳስ አድርጎ ስለሚገልጻቸው በተባለው ዘመን በዚህ አካባቢ የመጡ ቅዱሳን እንዳሉና ታሪካቸውንና ሥራቸውን ገና በውል እንዳልተረዳነው ለመረዳት አያዳግትም።

የላማ ደብር ማርያም ትክል ገና ጥንት ቀደም ብሎ በዐፄ ካሌብ ዘመነ መንግሥት ይሁን እንጂ የተደበረችው ወይም ደብር የሆነችው ግን በኋላ በጎንደር ዘመነ መንግሥት እንደሆነ አፈ መምህር ይገልጻሉ። ያስደበራት ዐፄ ፋሲል ሲሆን ለዚህም ምክንያት የሆነው በጸበሏ የሚደረገው ዝሪ ተአምራት ነው ይላሉ አፈ መምህር መልአክ።

ወደዚህች ታሪካዊት ቦታ እኔም በአካል ደርሼ የተቀበሉኝን ካህናት መጀመሪያ እንዲወስዱኝ የጠየቅኋቸው ወደ ጸበሉ ነበር። እዚያ በረሃ ውስጥ የገነት ቀበሌ መስላ ለብቻዋ ለምልማ የተቀመጠችው ላማ ደብር ማርያም ከቤተ ክርስቲያኗ በግምት አንድ መቶ ሜትር ወረድ እንዳሉ ጸበሉ ከሩቅ እየተንሿሿ ይሰሙታል። ካህናቱ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ያጥኑታል። ገና ወንዝ ወደ መሰለው ቦታ እንደገባሁ ቅዝቃዜው፣ ጸጥታው፣ አትክልቱና ሰላሙ ልቤን አስሸፈተው። ቀና ስል ብዙ ሠልጣኝ ያለባቸው የሥልጠና ቦታዎች ላይ የተሠሩ መታጠቢያዎች መስለው ጸበሎቹ እንደ ሻንዳ ይወርዳሉ። «እነዚህ ናቸው ጸበሎቹ?» አልኳቸው ከፊት ለፊቴ እያጠኑ ያሉትን ካህናት። አዎን ናቸው፤ ግን ይህ መጀመሪያው ነው እንጂ ገና ብዙ አሉ፤ አርባ ሁለት ጸበል ነው ያለው» አሉኝ በርጋታ። ሁሉንም ልታሳዩኝ ትችላላችሁ? አዎን እንዴታ። ጥሩንባ ይነፋል። ከኋላ ከኋላ ሕዝብ ይከተላል። ካህናት ከፊት ከፊት እያጠኑ ዐርባ ሁለቱን ጸበል ለማየት አሐዱ ብለን ጀመርን።

«ጌታው ጠጋ እያሉ ይመልከቱ! ብየ ጠበሉ አካባቢ የማን ጠበል እንደሆነ የሚገልጽ የተጻፈ ጽሑፍ አለ» አሉኝ አንደኛው ካህን። እኔም ጠጋ ብዬ ለማንበብ ጀመርኩኝ። የመጀመሪያው የእግዚአብሔር አብ ጸበል ነው። ሁለተኛው የሥላሴ ሦስተኛው የዐማኑኤል፣ እያለ ቀጠለ። የአቡነ አረጋዊ፣ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፣ የመድኃኔዓለም፣ የአቡነ አቢብ፣ የነአኩቶ ለአብ፣ የራጉኤል፣ የሚካኤል፣ የገብረ ማርያም፣ የሩፋኤል፣ የገብረ ክርስቶስ፣ የገብርኤል /ሁለት ጸበል/፣ የኪዳነ ምሕረት፣ የጊዮርጊስ፣ የማርያም፣ የአቡነ ኪሮስ፤ የመርቆሬዎስ፣ የተክለ ሃይማኖት፣ የመድኃኔዓለም /ሁለተኛ/፣ የቅዱስ እስጢፋኖስ፣ የቅድስት ክርስቶስ ሠምራ፣ የቅዱስ ቂርቆስ፣ የበዓታ፣ ልደታ... እነዚህን



ስውራኑ የሚወጡበት ከባሕሩ ጀርባ ያለው ዋሻ

ሁሉ ጸበሎች በቅደም ተከተል እያየሁ የዐሥራ አምስት ደቂቃ የሚሆን መንገድ ወንዝ ለወንዝ ከተጓዝኩ በኋላ አንድ ትልቅ ገደል ደረስን። እነዚህ ሁሉ ጸበሎች በአንድነት ሔደው እንደፏፏቴ ሠርተው እዚህ ላይ ይወርዳሉ። ፏፏቴው ከሚያርፍበት ከባሕሩ ጎን ትልቅ ዋሻ አለ። እንደካህናቱ ገለጻ በዋና ቀረብ ተብሎ ቢታይም ወደ ውስጥ አይገባም። ቦታው የቅዱሳን በዓት ነውና። ይሁን እንጂ የእሳት ማንደጃና መቋሚያቸውን አይተው ያውቃሉ። ይህን ቦታ አሻግሬ ካየሁ በኋላ ወደታች ያሉትን ቀሪ የጸበል ቦታዎች አላየኋቸውም። ከዚህ በኋላ ያለው መንገድ አስቸጋሪ ነበርና። ወንዙን በመሐል እንዲሔድ የፈቀዱለት በግራና በቀኝ በጥሩ አርክቴክት ተነድፈው በውድ እምነ በረድ የተገነቡ የሚመስሉት ጥርብ ዓለቶች ጉንና ጉናቸው ላይ መስኮት በሚመስል ሁኔታ የተበሳሱ ናቸው። ዋሻዎቹ የመናኞች መኖሪያዎች ነበሩ።

ሕዝቡም ካህናቱም ከስውራኑ ውጭ የሚያውቋቸው መናኞች እስከ ቅርብ ጊዜ ነበሩ። በተለይም ለሰማንያ ስምንት ዓመት ከእነዚህ ዋሻዎች በአንዱ ዘግተው የኖሩትን አባ ገብረ ኢየሱስን ሁሉም ካህናት ደጋግመው ያነሷቸዋል። አባ ገብረ ኢየሱስንም ሆነ ሌሎቹን ተራው ምእመን ቀርቦ አይጠይቃቸውም ነበር። ለበረከት የሚሆን ነገር አዘጋጅቶ መስጠት የፈለገ ሰው ካለ ከካህናቱ ሁለቱ ወደ በዓታቸው ሰዓት ጠብቀው ወርደው ይላላኩ ስለነበር፤ በእነርሱ በኩል ይልካሉ እንጂ ወደ በዓታቸው አይቀርቡም። አባ ገብረ ኢየሱስ ያረፉት ሐምሌ ፯ ቀን ፲፱፻፴፯ ዓ.ም ነበር። አባ ገብረኢየሱስ ባረፉ ጊዜ ማንም ሳይጠራቸው እጅግ ብዙ ቅዱሳንን ተሰባስበው ተገኝተዋል። እንደ ካህናቱ ገለጻ አባ ገብረኢየሱስ ድምፀ አንስትን መስማት ቀርቶ አዘጋጅተው የላኩትን እንኳ ቀምሰው አያውቁም። ክብራቸውና ጸጋቸውም የተገለጸው በዕረፍታቸው ወቅት ነው። በብዙ ሀገሮች ያሉ ምእመናንንና ሊቃውንትም ከበረከታቸው ለመሳተፍ ተዝካራቸውን አውጥተዋል። እርሳቸው ዘግተው የነበሩበት ዋሻ ዐጽማቸውን ለማሳረፍ የገቡት አባቶችም በጊዜው ሁለት ጽላቶችን ከባዕታቸው ውስጥ አውጥተው ለቤተ ክርስቲያኑ ሰጥተዋል።

አሁን ያሉት ካህናት እርሳቸውን የሚያ ሲታውሱበት ዋናው ትምህርታቸውም «ለመ ነኩሴ አንድ ብር ማስቀመጥ አንድ ሰይ ጣን ማስቀመጥ ነው:: ሁለት ብር ማስ ቀመጥም ሁለት ሰይጣን ማስቀመጥ ነው፤... ዐሥር ሲሞላ ደግሞ ፈጽሞ ክዶ ጣዖት ማምለክ ነው» የሚለው የጸሊአ ንዋይ ትምህርታቸው ነው::

### ድውይ ማስጫና ጠበል ጠባቂው ዘንዶ

ስለአባ ገብረኢየሱስ እየነገሩኝ ቀሪዎቹን ጸበሎች ለማየት ጊዜ አጣሁኝ:: አሻግሬ ካማተርኳቸው በኋላ መመለስ ጀመርኩኝ:: መመለሻችን እንደ ቀድሞው ውስጥ ለው ስጥ ወይም ጸበል ለጸበል አልነበረም:: በየ ብስ መመለስ እንደጀመርን አሁንም ባለ ሞያ ያነጠፉቸው የሚመስሉ ድርብርብ ዐለ ቶችን አገኘን:: «ይህች ቦታ ድውይ ማስጫ» ትባላለች አሉኝ ካህኑ:: ቦታዋ ስያሜዋን ያገኘችው ጠበልተኛው በየጠ በሉ ከተጠመቀ በኋላ ወጥቶ ፀሐይ የሚ ሞቀው፤ ልብሱንም አጥቦ የሚያሰጣው በዚህች ቦታ ስለሆነ ነው:: ትርጉሙም እንደታሪኩ /በሽተኞች/ የሚሰጡበት፤ ፀሐይ የሚሞቁበት ማለት ነው:: ይህን ጠበል ብዙ የገጠር ሰዎች ከትግራይና ከጎንደር ድረስ እየመጡ ይጠመቁና ከደዌያቸው ይፈወሱበታል:: በዚህ ቦታ ከተፈጸሙት ተአምራትም ለአንዲት እስ ላም የተፈጸመው ተጠቃሽ ነው:: «ማሰው ሱዋሊህ የሚባል እስላም ሚስቱ ለሞት ቀርባበት ተጨንቆ ይዟት ሊያስጠምቅ መጣ:: አንዳንድ ሰዎች በወቅቱ ባይደሰቱም ተፈ ቀደለትና ገብቶ አስጠመቃት:: በሦስት ቀን ብቻ ድና ወደ ሀገሩ ይዟት ተመልሳለች ይላሉ አፈ መምህር መልአክ::

ለመሆኑ ጸበሉን የሚጠብቀው አለ? አልኳቸው:: እንዴታ አሉኝ አፈ መምህር:: ስማኝ ወዳጄ አንተም ዛሬ እዚች ቦታ ብታድር ታየዋለህ:: የሚጠብቀው ዘንዶ ነው:: የተዳደፉ ሰዎች /በሩካቤ፣ .../ ከመጡ ዘንዶው ብቅ ይላል፤ ወይም ድምፁን ያሰ ማል፤ ያን ጊዜ ሰዎቹ ይመለሳሉ:: አፈ መምህር እንደገለጹት ከእኔ ተለይተው በቤተ ክርስቲያኗ ዙሪያ የሰነበቱትና ከእኔ ጋር ከአዲስ አበባ የሔዱት እነ ወ/ሮ ሳቤላ ዘንዶውን ሰምተውታል:: ሌሊት ሌሊት ከጠበሉ ቦታ ወጥቶ ቤተ ክር ስቲያኗ ጋር መጥቶ ጮኸ ድምፁን አሰ ምቶ ይመለስ እንደነበር ገልጸውልኛል::



*የዝንጆሮ መኖሪያ ዋሻዎች ያሉበት ጥርብ ዓለት*

አፈ መምህር መልአክን «ሰዎችን አይጣ ላም ወይ?» ብዬ ስጠይቃቸው ዘንዶ ውም ነብሩም ለመጠበቅና፣ ቦታውም እን ዲፈራና እንዲከበር ይገለጻሉ እንጂ ተጣ ልተውን አያውቁም፤ እስካሁን ማንንም ነክተው አያውቁም ሲሉ ይላሉ::

### ስውራኑና ላማ ደብር ማርያም

በደብሯ ስለነበረው የስውራን ሁኔታ ስጠይቃቸው እነ አፈ መምህር መልአክ ብዙ ጊዜ ዝም ካሉ በኋላ በልጅነታቸ ውና በማዕከላዊነታቸው የሚያውቋቸው ብዙ ተአምራት እንዳሉ ገልጸው ጥቂቶቹን ብቻ ተረኩልኝ::

በዚህች ቤተ ክርስቲያን ከሚሰጠው አገልግሎት ዋናው የግሑሳኑ አባቶች አገ ልግሎት ነው:: ሌሊት ሌሊት ምስጋና ቸው ይሰማል:: ብዙ ነገሮችም ይደመ ጣሉ:: «እኔ ዲያቆን ሳለሁ» ይላሉ አፈ መምህር:: የፍልሰታ ጾምን ሰዓታት ደወል ደውዬ የማስጀምረው እኔ ነበርኩ:: ታዲያ ለካ ታላላቆቹ አባቶች የግሑሳኑን ጸሎት /ሰዓታቱን ሌላውንም/ እየሰሙ አይነግሩ ኝም ነበር:: በዐሥራ ዐራተኛው ቀን ከእን ቅልፌ ስነቃ እኔ ሳልደውል «ቅዱስ ቅዱስ.. እያሉ ሰዓታቱን ሲያሔዱት ሰማሁ:: እኔ ስለፋና ስደውል ከርሜ እንዴት ዛሬ በሱ ባኤው መጨረሻ ቀን እንቅልፍ ይጥለኛል በማለት እያዘንኩ ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሮጥኩ ሔድኩኝ:: እየተጣደፍኩ ወደ ቤተ ክርስቲያን እገባለሁ ስል መብራቱ ድንገት ጠፋ:: እኔም ደንግጬ በግምባሬ ተደፋሁ:: ለካ ገና እንደተኛን በምሽት እያደረሱ ነበር ያሉት:: ወዲያው አባ ቴን ስነግረው በጣም ተቆጣኝ:: እባክህን ረጋ በል፤ ይህ ቦታ የቅዱሳን ቦታ ነው:: እንዳትቀሰፍ እግርህን ጠብቀህ ተራመድ አለኝ:: እኔም ከዚያ በኋላ እያስተዋ ልሁና እየተረዳሁ መጣሁ::

### ከእኔ ነው እንዴ ነገርህ

ከዚህስ በኋላ ያዩት ምንድን ነው ሳል ኳቸውም ሲያመነቱ ከቆዩ በኋላ ሁለት ነገሮችን ብቻ እነግርሃለሁ አሉኝ:: አንዱ እንደነገርኩህ በዲቁና እያለሁ ተዝካር ወጥቶ ተናጽቼ /ተጸዳድቼ/ ለመመለስ እንደወጣሁ አንድ ትልቅ ጽሕማም አረ ጋዊ ሽማግሌ አገኘሁ:: እኔም «የመጣ ተዝ ካር አለ፤ ገባ ብለው አርፈው ይሒዱ» ብዬ ለመንኳቸው:: እርሳቸውም አንዳንድ ነገር እየነገሩኝ፤ የማላውቃቸውንም ምስ ጢራት እየገለጡልኝ ደጀ ሰላሙ ደረስን:: አስገብቼ አስቀምጫቸው ጠላ ልቀዳላ ቸው ጽዋ ላመጣ ሔደት ብዬ ስመለስ አጣኋቸው:: በኋላ ትልልቆቹን ስነግራ ቸው ደግ /ጻድቅ/ ቢሆኑ ነው አሉኝ:: እስካሁን ድረስ ጊዜውን እየጠበቀ የነገ ሩኝ ሁሉ ሲፈጸም አየዋለሁ::

ከዚህ በኋላ ቅስና ተቀበልኩና የደብሯ አለቃ ከሆ ንኩ በኋላ ወማኮ ጊዮርጊስ ላይ ጉብኘና ተሾምኩ:: ጊዜው በ፲፱፻፹፪ ዓም ነው:: በደንቡ መሠረት ለክብረ በዓል የሚመጡትን ሊቃውንት ደግሶ የሚያ በላ ገበዝ ስለነበረ እኔም ለሚያዝያ ጊዮርጊስ ክብረ በዓል ድፍድፉንና ሌላውን እስ ጭኜ ሔጄ ዐሥር ጋን ጠላ አስጥዬ ድግ ሱን እየተ መለከትኩ እንጀራ ቤት ሳለሁ በዚያ በቅኔ ማኅሌቱ የደብረ አሮን ሊቃውንት ካህናት እያገለገሉ ባሉበት:-

*«ቅዱስ ጊዮርጊስ ሶበ ተከለለ*
*ደም ወማይ ወሐሊብ እምን ክሳዱ ፈልፈለ»*
*የሚለውን ወርበው*
*«ይጥዕም ስምከ፣ ይጥዕም ስምከ*
*ጊዮርጊስ ይጥዕም ስምከ»*

የሚለውን ሲያቸበችቡ ቅዱስ ጊዮርጊስ በግልጽ ወርዶ ሲባርክ አየሁት:: ያን ጊዜ እየሮጥኩ ሔጄ እቅኔ ማኅሌቱ ዘልዬ ስገባ ወደ ኋላ ሸሸት ሸሸት ብሎ እልም አይ ልም:: እኔም አዝኜ «ከእኔ ነው እንዴ ነገርህ» አልኩት:: እርሱ ግን ሳይመልስ ልኝ ሔደ:: ከዚያ ወዲህ ግን እንዲህ ዐይ ነት ነገር አይቼ አላውቅም:: ጥንት ንጽ ሕና ነበር:: አሁን ግን ኃጢአት ስለበዛ እኔም በጣም ብስጬ /ተናዳጅ/ በመሆ ኔና በኃጢአትም ስለተዳደፍን እንዲህ ያለው ጸጋ ፈጽሞ ርቆናል:: ይገርምሃል ይህ አካባቢ የቅዱሳን አገር ነው:: በዚ ያው አካባቢ አቡሻሮ ሚካኤል እንዲሁ የቅዱሳን አገር ነው::

በቦታው እስከ ቅርብ ጊዜ ስለነበሩት አባቶችም በማዘን ያነሣሉ:: እነ አባ ወልደ ሃና፣ አባ ወልደ ሙሴ፣ አባ አባተ፣ አባ ሽበሺ በጣም ታዋቂዎች ናቸው:: ከቦታው ወጥቶ ከተማ የገባ የለም:: እንዲያውም ይላሉ አፈ መምህር እንኳን መናኞቹ ከእኔ በቀር ከአሁን በፊት አዲስ አበባን ያየ ካህን እንኳን አልነበረም:: አሁን ይህ ብቻ አይቶብኛል ይላሉ፤ ከጐናቸው ያሉትን አሁን አዲስ የተተከለውን የመ ድኃኔዓለም ቤተ ክርቲያን ገበዝ የሆኑ ትን ቄስ::

ከላማ ደብር ማርያም ጋር አብረው በአንድ አለቃ የሚመሩ ሌሎች ሁለት አብያተ ክርስቲያናት አሉ:: የመጀመ ሪያዋ ዐፄ ፋሲል ላማ ደብር ማርያምን ባስደበሩ ጊዜ አቶ ክፍፍሩ /ክፍፍረ ክርስቶስ/ ያስተከላት አዛና ኪዳነ ምሕረት ስትሆን ሁለተኛው ደግሞ አሁን በ፲፱፻፹፬ ዓ.ም በጣም ሩቅ ሳሉት ሠፈሮች የተተከለው የመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ነው::

በ፲፱፻፹፯ ዓ.ም የአዛና ኪዳነ ምሕረ ትን ታቦቷ ትንሽ ስለነበረች እንድትቀ የር አዲስ አበባ መጥቼ ለአቡነ እንድር ያስ ነገርኳቸው:: አቡነ እንድርያስም ለመ ሆኑ የመጀመሪያው የጥንቱ ታቦት አለ ወይ? አሉኝ:: እኔም አዝኜ በእርስዎ አገር ታቦት ይሸጣልን? አልኳቸው:: እር ሳቸውም እስኪ ና መስቀሌን ምታ አሉኝ:: እኔም መስቀላቸውን ልመታ ስነሣ ተወው ተወው አሉኝና አለቀሱ:: የዲያቆን ሚስት የነበረች እኅታቸው ባሏ ሲሞትባት መንና ወደ ላማ ደብር መጥታ ሃያ ስምንት ዓመት ተጋድላ ስላረፈች ቦታውን በደንብ ያው ቁታል:: እርሳቸውም ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ተቀብለውና ከጃንሆይ አስፈቅደው እርሳቸው ጋር ሰኔ ፲፩ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ.ም ታቦቱን ይዘን ወደ ሀገራ ችን ሔድን:: ሕዝቡም «አይ! ነገር ተበ ላሽ፤ አፈ መምህር በአውሮፕላን ሔደ» ያለኝ ያን ጊዜ ነው:: በዚህ መልክ ታቦ ታችን ሔዶ ገባ::

ከዚያ ወዲህ ምን አደረጋችሁ? አሁን ቤተ ክርስቲያኑ በዚህ መልክ የተሠራውና ቆርቆሮ የለበሰው መቼ ነው ሳልኳቸ ውም ሲመልሱ የአሁኑ መቅደስ በዚህ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

መልክ የተሠራው ኢሕአዴግ ከገባ በኋላ
ነው::--በ፲፱፻፹፯ ዓ.ም ተጀምሮ በዐራ
ተኛው ዓመት በ፲፱፻፹፬ ዓ.ም ተፈ
ጽሟል:: ድንጋዩን ገበሬው እየፈለፈለ
ሊቀ ጠበብት ኃይሉ የሚባሉ ጥበበኛ
ሰው ናቸው የሠሯት:: ቀለባቸውን ገበሬ
ችሉ ለእጃቸው የሚያስፈልገውንም ገንዘብ
እዚያው እኛው ቻልን:: ቆርቆሮውን ደግሞ
የደጃች ክፍሌ ባለቤት ወ/ሮ አጥናፍና
ልጆቻቸው ስምንት ሺሕ ብር ሰጥተውን
ገዛን:: የጐደለውን ደግሞ ባሕታዊ ገብረ
መስቀል አሟልተውልን ሠርተን ፈጽመ
ናል:: ከዚህም በኋላ ዕቃ ቤቷን ማኅበረ
ቅዱሳን አንድ ሺሕ አምስት መቶ ብር
ሰጥቶን አሠርተን ቆርቆሮ አልብሠናል::
አሁን እየሠራን ያለነው የመድኃኔ
ዓለምን ቤተ ክርስቲያን ነው:: ለሥራው
ሕዝቡ እየተረባረበ ነው:: ለሥራው ዋና
አንቀሳቃሽ የሆነው ከወ/ሮ ሳቤላ ያገኘ
ነው የገንዘብ ርዳታ ነው:: እርሷ አምና
ሁለት ሺሕ ብር ሰጠችን:: ለእኔም ለመ
ሳፈሪያ ብላ የሰጠችኝ አንድ ሺሕ ብር
ለሥራው መስጠቴን ለሕዝቡ ስገልጽ ሕዝ
ቡም እንደ አቅሙ አዋጣና ሥራው ተጀ
ምሮ አሁን በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል::
አሁን የቀረን የቆርቆሮው ወጭ ብቻ
ነው:: በርግጥ እኛ ለምንንም ስለማናውቅ
አላገኘንም:: አሁን ግን ዝናቡ መጣሁ
መጣሁ ሲል የምንወድደውን ዝናብም
ለመሳቀቅ ደርሰናል:: እንግዲህ እሱ የፈ
ቀደለት ቢረዳንና ብናለብሰው እንመኛለን::

ቤተ ክርስቲያኑን የማይሠራውን ደግሞ
ገበሬው

*«ወይ አገሬ በሽሎ ወይ አገሬ ጂማ፣*
*የሚያገላብጠው ወደል በክትክታ፣*
*ደብሩን አፈረሰው ማተቡን የፈታ፣*
*አንት ወደል አሀያ ና ውጣ ና ውጣ::»*

እያለ በግጥምና በፉከራ ስለሚጐሽመው
ለደብር ያለው አመለካከት ከፍተኛ ነው
ይላሉ:: እንዳሉትም እነዚህን ትሑታንና
ትጉሐን ገበሬዎች በትንሽ ገንዘብ በመ
ርዳት ማስደሰት ቢቻል እንዴት መልካም
ነው፤ እኛም እግዚአብሔር የፈቀደለት
ፈጥኖ ቢደርስላቸው እግዚአብሔርም በበ
ረከት እንደሚደርስለት ተስፋ እናደርጋለን::

«ንጉሥ ሰሎሞን ምኒልክ
ቀዳማዊን ይወልዳል፣
ምኒልክ...» ሰሉና ንግሥተ ሳባ
ከእስራኤል ንጉሥ ከሰሎሞን
ከወለደችው ጀምረው መንዝ
ጀመሩ:: መካከል ላይ
እየተገረምኩ አንዳንዴም ሳቄ
እየመጣ በግምት ከሃያ ደቂቃ
በኋላ የእርሳቸው ወላጆች ላይ
ደርሰው የእርሳቸውን ትውልድ
መግለጽ ቻሉ::

### የሚገርመው ግብዣ

ቃለ መጠይቁንና ጉብኝቴን ጨርሼ ዕለ
ቱን ባሕርዳር ለመግባት ወደ ሚጠብ
ቀኝ መኪና ለመድረስ መጣደፌን ተያያ
ዝኩት:: ከብዙ ግልግልና ማስረዳት በኋላ
ሁለት ባለመሣሪያ የቀበሌው ሚሊሻዎች
ተመድበውልኝ የመልስ ጉዞዬን ከበቅሎ
መሪዬ ጋር ተያየዝኩት:: ደብሯን ለቅቀን
ወደ መንደሩ እንደደረስን ወደ አፈ መም
ሀር ቤት ይዘውኝ ገቡ:: በዚያ ያሉት ሁሉ
ተነሥተው ተቀበሉኝ:: «እንግዳው ስለማ
ያድሩ አሁኑኑ በፍጥነት ምሳ አቅርቡ»
ተባለ:: ሴትየዋ እየተጣደፉ ለእኔ ብቻ
ሰባቱን እንጀራ ደርበው ደራርበው ይዘ
ውልኝ መጡ:: «እኔ እኮ አንድ ሰው ነኝ፤
አንድ እንጀራ ይበቃኛል፤ እምቢም ካሉ
ሁለት ያደርጉት» አልኳቸው:: እርሳቸው
ግን አይሞከርም አሉ:: በግድ ለምኜ
ሁለቱ እንጀራ ተነሥቶ አምስቱ ቀረ::
እኔም ከዚህ በላይ መከራከር ከባድ መሆ
ኑን አይቼ አምስቱን እንጀራ መመገብ
ጀመርኩ:: ሰው መውደዳቸውና አክብሮ
ታቸው እያስገረመኝ ስበላ በማቴዎስ ወን
ጌል የተጠቀሱት አምስት እንጀራዎች
ትዝ አሉኝ:: ሴቶችንና ሕፃናት ሳይቆጠሩ
ለአምስት ሺሕ ሕዝብ የቀረቡት እነዚያ
እንጀራዎች ዛሬ ለእኔ ብቻ ቀረቡ፤ እያልኩ
እያሰብኩ ጉረስ ሳደርግ «ከለመለመው»
አሉና እመይቴ ሁለቱን አምጥተው ቆራ
ረሱና ፊቴ ላይ ደረደሩት:: ምን ይባላል
«ሁለቱ ዓሣ መሆኑ ነው» ለራሴ ገለጽ
ኩት:: ወዲያው ሁለት ወንዶች በሁለት
ማንቆርቆሪያዎች ሁለት ጠላ ይዘው መጡ::
አንዱ በማር የታሸ ፍርንዱስ፤ ሁለተ
ኛው ጥሬ ጠላ:: በማር ከታሸው አንድ
ጽዋ ጠላ ጠጥቼ በላማ ደብር ማርያም
ይዣችኋለሁ ብዬ እንደምንም ማዕዱ
ተነሣልኝ:: በዚህ «Thank You» በለመደ
አፌ የአቅሜን መራርቄ በነበሩት ካህን
አቡነ ዘበሰማያት ተቀብዬ ጉዞ ወደ አዲስ
አበባ::

### ነገረኛው ተራራ

ጠላዬን ጠጥቼ ስወጣ የበረሐው ግለ
ትና የፀሐዩ ትኩሳት እየለበለቡኝ ስጓዝ
ስመጣ በእግሬ የወረድሁት አስቸጋሪ
ቁልቁለት አሁን ጥርሱን ያገጠጠ አንበሳ
መስሎ ጠበቀኝ:: በቅሎ ላይ ወጥቼ ጃን
ጥላዬን ዘርግቼ ስጓዝ ግራ ጭኔን ከነዘ
ረኝ በኋላ ድምፅ ሲሰማ፤ አብረውኝ ያሉት
ባለመሣሪያዎች «የምን ድምፅ ነው? አሉ::
አሁንም ስልኬ ነበር:: በቅሎዋን የሚመ
ራልኝና ሟት እዚህ አካባቢ መደወሉን
ያስታወሰው ወንድሜ ይህ ተራራ ነገረኛ
ነው:: እዚህ ስንደርስ ብቻ ለምን ያስ
ጮኻታል? አለ:: ስልኩ እንደ አጋጣሚ
ከጎንደር ነበር የተደወለው:: የቀረችኝን
የአሥራ አምስት ቀቂቃ መንገድ ከጎን
ደሩ ዲያቆን መልአኩ እዘዘው ጋር እየ
ተነጋገርኩ ስሔድ አብረውኝ የነበሩት
ይገረሙ ነበር:: ስልኩ ከቆመ በኋላ እዚህ
ረጅም ተራራ ላይ ኔትወርክ ከየት እን
ደሚመጣ ለማወቅ በርቀት የሚያዩትንና
ጉም የለበሱትን ረጃጅም ተራራዎች እነ
ማን ናቸው እያልኩ ሳጠያይቅ ሰሜን
ምሥራቅ ላይ የላሊበላ ከተማና የአሽተን
ማርያም ተራራዎችን አሳዩኝ፤ ለካስ እዛ

ከፍተኛ ቦታ ላይ የሚደርሰው የላሊበላ
ኔትወርክ ኖሯል:: ከዚህ በኃላ በወን
ድሜ ነገረኛ የተባለውን ተራራ ቁልቁለ
ቱን እንደገና በእግሬ ከተጓዝኩ በኋላ
የሚጠብቀኝን መኪና አገኘሁት:: ከቀኑ
ስምንት ሰዓት ላይ መኪና ውስጥ ከጠ
በቀኝ እሽግ የአቢሲኒያ ውኃ ጋር ተሳ
ስሜ ጉዞ ወደ መቄት ከተማ:: ያንን አስ
ቸጋሪ መንገድ ሁለት ሰዓት ተጉዘን መቄት
ገባን:: ትንሽ የጾም ምግብ ቀማምሰን
ዐሥር ሰዓት ተኩል ላይ ወደ ባሕርዳር
ተነሣን::
ዕለቱ ጥር ሃያ አምስት የመርቆሬ
ዎስ ዕለት በመሆኑ ብንችል መካነ ኢየ
ሱስ ቃል አስገብተውን ስለነበር እዚያው
ለመድረስ መኪናችንን በክንፍ የምትበር
እስክትመስል ድረስ አቢሎ ያስሮጣት
ጀመረ:: ለደብረታቦር አሥራ ስምንት
ኪሎ ሜትር ሲቀረን ወደ እስቴ መካነ
ኢየሱስ መገንጠያው ጋሳኝ ላይ ታጥፈን
ከመርቆሬዎስ በረከት ለመሳተፍ ስንፈጥን
ከምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ጉማራ
በርሐ ውስጥ የመኪናችን ጐማ ተነፈሰ::
አቢሎ ክሪኩን አውጥቶ ጐማውን ሊቀ
ይር ሲዘጋጅ በመንገድ ተንጦ ዘይት ያፈ
ሰሰው ክሪክ አላነሣም አለን:: ለሠላሳ
ደቂቃ ያህል በጭንቀት ቆየን:: የፀሐይ
ደብዛዋ ጠፍቷል:: አቤሎ መበሳጨት
ጀመረ:: ከአውራ መንገድ አስወጥተህ
መኪና የማይሔድበት በረሐ ላይ ጉድ
አደረግኸን ማለት ጀምሯል:: እኔ ምን
ላድርግ «እባክህ ቅዱስ መርቆሬዎስ አን
ተን ብለን መጥተን እዚህ በርሐ አታስ
ቀረን እያልኩ አማጽንኩና የአቅሜን ጸሎት
ለማድረግ ሞከርኩ:: ከዚህ በኋላ ክሪኩ ለምን
እንደማያነሣ ስጠይቀው ዘይት በማፍሰ
ሱና እርሱ ደግሞ ዘይት ባለመያዙ እን
ደሆነ ነገረኝ:: በትንሹም ቢሆን የተማር
ኳትንም ያስተማርኳትንም የፊዚክስን የግ
ፊት (Pressure) መርሕ አስታወሰኝና የሚ
ፈለገው ቦታውን በፈሳሽ ይዞ ግፊቱን
መጨመር ስለነበር የያዝነውን ውኃ በአሞ
በጥብጠን ክሪኩን ሞላንና በል እንግዲህ
መርቆሬዎስ የቀረውን አንተ ሙላልን
አልነው:: ክሪኩም የታዘዘ ይመስል ቀጥ
አድርጎ አነሣልንና ጐማችን ቀይረን አንድ
ሰዓት ከሩብ ላይ መካነ ኢየሱስ ገባን::
እነ ይኄታ ጋር ስናመራ እንግዳው ተሽ
ኝቶ አዳራሽ ተዘግቶ ይኄታ ጸሎት ቤታ
ቸው ገብተው አገኘን:: መጡ ተብሎ ሲነ
ገራቸው ወጡ:: ምንም ያልቀመሰው አቢሉ
እና እኔ በአንድነት የሰማዕቱን ድግስ በፍ
ጥነት በላነው:: ጠላውን አቀረቡልን መጠ
ጣት አቃተን:: እንደማናድር ስንነግራ
ቸው ውኃውን በጨረስነው የውኃ እቃ
ጠላውን ሞሉልንና ጉዞአችንን በየኔታ
ጸሎትና ምረቃት ጀመርነው:: የቀረ
ችንን መቶ ኪሎ ሜትር በአንድ ሰዓት
ተኩል ተጉዘን ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ተኩል
ላይ ባሕርዳር ገባን:: እኔም የገዳም ጠላ
ዬን ይገዬ ሳላስነካ ለአዲስ አበባ ጠበቅ
ኋት:: ከብዙ ድካም በኋላ አቦራዬን አራ
ግፌ ወደ ከተማው ኑሮ ተቀላቀልኩ::
በሟት ተነሥቼ የእነ አባ ኪዳን ጠላ
ይገፄ አዲስ አበባ ለመድረስ ባሕርዳር
አውሮፕላን ማረፊያ ገሠገሥኩ:: አሁን
እዚያው ነኝ:: ጠላዋን የምትፈልጉ ቦሌ
ጠብቁኝ::✤

# ራስን ማስቻል፤ እንዴት?



ጌታቸው በቀለ

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በዘመናችን ለብዙ ሰዎች ሕይወት መጥፋት፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መንስኤ በመሆኑ፤ ይህን ችግር ለመቅረፍ በርካታ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (NGO) የተለያዩ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ይገኛሉ። ድርጅቶቹ ቫይረሱ በደማቸው ያለባቸውን ሰዎች በቁሳቁስ፣ በገንዘብ ወዘተ ይረዳሉ። በተጨማሪም ራሳቸውን ለማስቻል በአነስተኛ ንግድ እንዲሰማሩ፣ በተናጠልም በማደራጀት እንዲሠሩ የሚደረግበትም ሁኔታ አለ። ድርጅቶቹ ከሚረዷቸውም መካከል ጥሩ ደረጃ ደርሰው ራሳቸውን ችለው ቤተሰብ የሚያስተዳድሩና ድርጅቱ ባደረገልኝ ድጋፍ ከፍተኛ ደረጃ ደርሻለሁ የሚሉ አሉ። በተለያዩ ምክንያቶች በዕድሉ ሳይጠቀሙም የቀሩ አሉ።

በአንጻሩ የሚሰሙ የተለያዩ ብሶቶችም አሉ። በተለያየ ቦታ የሚኖሩ ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝባቸው ሰዎች እንደሚናገሩት ከርዳታ ድርጅቶች በቂ ገንዘብ አናገኝም፣ ለሕሙማኑ ተብሎ የሚመጣውን ገንዘብ የሌሎች መጠቀሚያ ሆኗል፤ ገንዘቡ በቂ አይደለም፣ በማለት በምሬት የሚናገሩ አሉ።

ለመሆኑ ርዳታ ምንድን ነው? ዓላማውስ? ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝባቸው ወገኖቻችን ምን ይላሉ? የርዳታ ድርጅቶቹስ ራስን ከማስቻል አንጻር ምን እየሠሩ ነው። ብዙ ጥያቄዎችን ማንሳት ይቻላል። በዚህ ዕትም እነዚህን እና ሌሎች ተዛማች ጉዳዮችን በተመለከተ፤ ቫይረሱ በደማቸው ያለባቸውን ሰዎች፣ ኤች አይ ቪ/ኤድስ በመከላከል ረገድ እየሠሩ ካሉ ድርጅቶች እና ባለሙያዎች ጥቂቶቹን አነጋግረን አቅርበንላችኋል።

አንዲት በመኖሪያ ቤቷ የአገኘኋት ወጣት ለሁለት ዓመት ያህል በእንጦጦ ማርያም በጠበል ቆይታለች። ሕፃን ልጅ አላት፤ ቫይረሱ በደሟ አለ፤ እርሷ ግን ምንም መተዳደሪያ የላትም። ባለቤቷ ሞቷል። ኑሮዋ እንዴት እንደሆነ ጠይቄአት ነበር። እንዲህ ትመልሳለች፡- «የምተዳደረው እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው በሚሰጠኝ ገንዘብ ነበር። አሁን ደግሞ አንዳንድ ሰዎች ርዳታ ድርጅቶች ጋር ለምን አትሔጂም ሲሉኝ ምክራቸውን ተቀብዬ ርዳታ ወደ ሚሰጥበት ቦታ ሔጄ አሁን እየተረዳሁ ነው። አሁን የምኖረው በእርሱ ነው። የምተዳደረው በየወሩ በማገኘው ርዳታ ነው፤ አሁን ምንም ሥራ አልሠራም። ቀድሞ በየሰው ቤት ልብስ አጥቤ እንጀራ እጋግር ነበር።»

በርዳታ አሰጣጡ ዙሪያ ቅሬታቸውን የገለጹም ነበሩ። በአሁኑ ወቅት ቫይረሱ ያለበትም ሆነ የሌለበት ርዳታ ለምዷል ያሉኝ እናት «ርዳታ የሚሰጡ ድርጅቶችም ጋር፣ እኛም ጋር ችግር አለ። በተገቢው መንገድ እየተሰጠ አይደለም በማለት ችግሩን ይገልጻሉ።

በጠበል አካባቢ የአገኘሁት ቫይረሱ በደሙ ውስጥ የሚገኝ አንድ ወጣት በሰጠው አስተያየት ደግሞ «እኔ ጠበል እየተጠመቅኩ ነው፤ ከአንድ ቦታም እየተረዳሁ ነው፤ እግዚአብሔር ይመስገን! አብቃቅቼ እጠቀማለሁ፤ ሰዎችን ከመለመን ድኛለሁ፤ ነገር ግን በጠበል ቦታ ብዙ ነገር ትመለከታለህ፤ ትሰማለህ አንዳንዶች መጠመቁን እየተው ርዳታ አለ የተባለበት የተለያየ ቦታ የሚሔዱ ሁለትና ሦስት ቦታ የሚረዱ አሉ። የእኔ አባባል ለምን ተረዱ ሳይሆን ለሁሉም ሥርዓት አለው። ወደ ጠበል የሄድነው ለመዳን፣ በረከት፣ ድኅነት ለማግኘት ነው። አንድ ሰው ከአንድ ቦታ ከአገኘ ሌላ ቦታ ደግሞ ሌሎች ወገኖቻችን እንዲጠቀሙበት መሻማቱን መተው አለበት። እርስ በርስ ልንተሳሰብ ይገባል፣ ቫይረሱ በደሜ አለብኝ ብሎ ርዳታ ማሳደድ ተገቢም አይደለም። ብቻ በአጠቃላይ ስትመለከተው የርዳታ ሁኔታ በጠበል አካባቢ ያሉ የአንዳንድ ተጠማቂዎችን አመለካከት ቀይሮታል።» ነበር ያለኝ። ለአብነት ያህል እነዚህን አነሳን እንጂ ሌሎችም በርካታ አስተያየቶች አሉ።

## ጥገኝነትን የመቀነስ ሥራ እየሠራን ነው

ሕይወት ኢትዮጵያ ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለማስተማር ከተቋቋሙት መንግሥታዊ ያልሆኑ አገር በቀል ድርጅቶች መካከል አንዱ ነው። ድርጅቱ በ፲፱፻፺፪ ዓ.ም ሕጋዊ ዕውቅና አግኝቶ በአዲስ አበባ እና በሰሜን ሸዋ አገልግሎቱን እያካሔደ ነው። የድርጅቱ ዳይሬክተር አቶ ጌታለም ካሣ ቫይረሱ በደማቸው ያለባቸውን ሰዎች ራስን ከማስቻል አንጻር ምን እየሠሩ እንደሆነ አነጋግሬያቸው ነበር።

ድርጅቱ ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች ራስን የማስቻል ፕሮግራም ነድፎ በአነስተኛና ጥቃቅን ንግድ እንዲሰማሩ እያደረገ ነው። በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ሕፃናት እገዛና ድጋፍ ያደርጋል። ከእነዚህ ውስጥ ሴቶች ራሳቸውን እንዲችሉ /ራስን የማስቻል/ የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ከቀበሌ ጋር በመነጋገር ቦታ እንዲያገኙ በማድረግ፤ በአነስተኛና ጥቃቅን ሱቅ በመክፈት ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን እንዲያስተዳድሩ አድርገዋል። በኮተቤ አንቆርጫ፣ በእንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን አካባቢ እና በሽሮ ሜዳ ሱቅ ከፍተው በመሥራት ላይ ይገኛሉ። ድርጅቱም በቅርብ በመሆን ድጋፍና ክትትል ያደርግላቸዋል። ሠራተኞቹም ከሚያገኙት ትርፍ ውስጥ ቀንሰው ባንክ አካውንት በመክፈት የባንክ ደብተራቸውንም በዚህ ድርጅት በማስቀመጥ እየተጠቀሙ ነው።

ርዳታ ስንል ሁልጊዜ የውጭ ሰዎችን ለምንን ነው ብር የምናመጣው የሚሉት ዳይሬክተሩ፤ «መለመኑ ራሱ ትልቅ ውጣ ውረድ አለው። ፕሮጀክቶች ተነድፈው ተጠንተው ታይተው ነው ርዳታው የሚሳካው። ፕሮጀክት ሲባል ደግሞ የሚያበቃበት ጊዜ አለው። የፕሮጀክቱ ጊዜ ሲያልቅ ሰዎቹ እንዳይጎዱ፣ እንዳይበተኑ፣ ችግር እንዳይደርስባቸው፣ ራሳቸውን ችለው መቀጠል እንዲችሉ የማድረግ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል። ከዚህ አንጻር ነው ከቫይረሱ ጋር ላሉ ሴቶች የመጀመሪያውን ራስን የማስቻል ፕሮግራም የሠራነው። እነዚህ በፕሮጀክቱ የታቀፉት ራሳቸውን ሲችሉ፤ በእነርሱ የሚተዳደሩት የቤተሰብ አባላት የዕለት ጉርስ ያገኛሉ፣ ሥራም ሊይዙ ይችላሉ። ለሌሎች አዲስ ለሚመጡ ደግሞ በፕሮራሙም ውስጥ እንዲገቡ ይደረጋል። ትልቁ ሥራም እነዚህን የሚደግፋቸው የሌላቸውን ሰዎች ከልመና ተላቅቀው ራሳቸውን ማስቻል ነው። ነገሩ ጥገኝነት የመቀነስ ሥራ መሥራት ነው።» ይላሉ።

በበጎ ጐኑ ካየነው፤ ርዳታ ድጋፍ ነው። የእኛ ዋናው ዓላማ ለተቸገሩ ዜጎቻችንን ድጋፍ አድርገን ወደሚቀጥለው ደረጃ እንዲሄዱ ማድረግ ነው። መማር ፈልጐ አቅም ለሌለው ወጣት እንዲማር ብትረዳው፣ ሲማር መብላት ይፈልጋል። መብላት እንዲችል ደግሞ ትደግፈዋለህ፤ ሠርቶ መብላት እንዲችል ከዛም ቀስ በቀስ ራሱን እየቻለ እንዲሄድ ለማድረግ ነው። ነገር ግን ርዳታ ለዘላለም የሚደረግ ስጦታ ማለት አይደለም። ድርጅቶቹም የዘላለም አይደሉም። የተወሰነ ጊዜ አላቸው፤ በዚያች ወቅት ግን ፍሬያማ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል። ብዙ ሰዎች ርዳታን ዘላቂነት ያለው ነገር አድርገው ስለሚወስዱት ከሥራ ይልቅ ርዳታን ይጠብቃሉ።

ዳይሬክተሩ በርዳታ ዙሪያ ያጋጠማቸውንም ሲያስረዱ «በአንድ ወቅት ገንዘብ በየወሩ እንከፍል ነበር፤ ካሊጋሾቻችን በወቅቱ ገንዘብ ሳይመጣ ሲቀር ሰዎቹ እንዳይቸገሩ በማሰብ ከሌላው በጀት አንሥተን እንሰጣለን። በዚህ ወቅት ታዲያ ብዙ ነገሮች ገጥመውናል። በተለይ አንዳንዶቹ ተረጂዎች ባለሙያዎቻችን የሚረብሹ ነበሩ። በዚህ ክፍል ተመድባ ትሠራ የነበረች ባለሙያ ከራሷ ከኪሷ የምትሰጥበት ጊዜ ነበር። ከቫይረሱ ጋር በሚኖሩ ሰዎች ስም የሚመጣውን ብር እኛ በልተን የምንኖር ስለሚመስላቸው፤ በደሜ የመጣ ብር ነው ዛሬ የሚዝናኑበት፤ የሚሉህ አሉ። እንደዚህ የሚሉ ሰዎች ከሦስት፣ ከአራት ቦታ ርዳታ የሚያገኙ ናቸው። ከቫይረሱ ጋር እስካሉ ድረስ በነጻ ገንዘብ ማግኘት ያለባቸው የሚመስላቸው አንዳንድ ሰዎች አሉ። ይህ ትክክለኛ አመለካከት አይደለም።

ዳይሬክተሩ እንደነዚህ ዓይነት ችግሮችን ለማስወገድ የሚከተሉት ነገሮች መደረግ እንዳለባቸው ይመክራሉ።





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

* በርዳታ ድርጅቶች መካከል በግልጽነትና በመናበብ መሥራት
* በዚህ ዙሪያ የሚሠሩ ድርጅቶች ከውጡ በሚመጣ ብር ብቻ አይደለም የሚሠሩት፣ ከተለያየ ቦታ ያገኛሉ:: ካለው ችግር ስፋት አንጻር ድርጅቶቹ እንዴት እኩል ክፍፍል ሊያደርጉ እንደሚችሉ በቅርበት መወያየት አለባቸው::
* ከቫይረሱ ጋር ያሉት ደግሞ፣ በአልጋ ላይ ላሉት ወገኖቻቸው ሊያስቡ ይገባል:: ምናልባት ከአንድ ቦታ የሚረዱት ሰባ ወይም አንድ መቶ ብር ለመተዳደሪያ ላይበቃ ይችላል:: ነገር ግን ዐሥር ሳንቲም ደግሞ ያጣ ሌላ ወገን አለ:: እኔ ከዚህ የማገኝ ከሆነ እኔ እከሌ ደግሞ ከዛኛው ቢያገኙ በማለት መተሳሰብ ይገባል::

አንዳንድ ጊዜ የሚመጣው ርዳታና ተጠቃሚው የማይገናኙበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል:: ድርጅቶችም ራሳችን ልንፈትሽ ይገባል፣ ከእኛም ችግር ሊኖር ይችላል:: በእውነት ለተረጂዎች የምናቀርበው ነገር ወደ ተጠቃሚው በትክክል እየደረሰ ነው ወይ? ስርጭቱስ በተገቢው መንገድ ነው ወይ? ያላገኙት ሰዎች አግኝተዋል ወይስ ያገኙት ሰዎች ላይ ብቻ ነው እየሠራን ያለነው? የሚለውን ለይተን ማወቅና መሥራት መቻል ያለብን ይመስለኛል::

## ርዳታ ጊዜያዊ ችግር ማቃለያ ነው

ቫይረሱ በደማቸው ያለባቸውን ሰዎች ራስን ከማስቻል አንጻር የተለያዩ ድርጅቶች ምን እየሠሩ እንደሆነ፣ ወደፊትም መደረግ ያለበትን በተመለከተ ሙያዊ አስተያየት የሰጡን ደግሞ አቶ ዘላለም ናቸው:: አቶ ዘላለም በተለያዩ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ በጤና ዘርፍ ላይ የሠሩ ባለሙያ ናቸው:: በአሁኑ ወቅት በጐል ኢትዮጵያ ለችግር የተጋለጡ ሕፃናት ፕሮግራም ውስጥ የማኅበራዊ አገልግሎት ሠራተኛ ናቸው::

አንድ ሰው በዕቅድ ቢኖርም በተፈጥሮ እና በሰው ሠራሽ አደጋ በግለሰብ ወይም በአገር ደረጃ ችግር ሊደርስ ይችላል:: ችግሩ ከቁጥጥርህ ውጭ ሲሆን፣ መቋቋም ሲያቅትህ የሌላ ሰዎች ርዳታ ያስፈልግሃል:: ይህን ችግር የደረሰበትን ሰው በገንዘብ፣ በምክር በተለያዩ ነገሮች፣ በቁሳቁስ መርዳት ያስፈልጋል:: የተለያዩ ድርጅቶች በራሳቸው መመዘኛ፣ ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ምንም ገቢ ለሌላቸው ሰዎች ርዳታ ይሰጣሉ::

የርዳታ ዋናው ዓላማ ሰዎች ለዘላለም ርዳታ እየተረዱ እንዲኖሩ አይደለም:: ለዚያ ቤተሰብ በሁለት እግሩ እንዲሄድ ድጋፍ መስጠት ነው:: ርዳታ ጊዜያዊ ችግር መፍቻ ነው:: ከዚህ ይልቅ የሙያ ሥልጠና ብታሰለጥናቸው የተሻለ ነው:: ለምሳሌ:- ወላጆቻቸውን ካጡት ቤተሰብ መካከል አንዱን በሙያ ስናሠለጥነው፣ እኅት ወንድሞቹ መተዳደሪያ አጥተው፣ ከት/ቤት ሊቀሩ ይችላሉ:: እንደዚህ እንዳይሆኑ ልጅ ሠልጥኖ ሙያ እስኪይዝ ድረስ:: የቤት ኪራይ መስጠት፣ አልባሳታቸውን ማቅረብ ተገቢ ነው:: ያ በአዋቂዎችም ዘንድ እንደ ዚሁ ነው:: መሥራት ከቻሉ፣ በተለያየ ሙያ በማሠልጠን እንዲሠሩ ድጋፍ ማድረግ፣ አቅማቸው እየደከመ መሥራት ሳይችሉ ሲቀር ደግሞ እንደ ሁኔታው መርዳት ነው::

የተለያዩ ድርጅቶች ቫይረሱ በደማቸው ላለባቸው ሰዎች የአነስተኛ ንግድ ሥልጠናዎች ይሰጣሉ:: ሠልጥነው የተሰማሩበት የሥራ መስክ አነስተኛ ገቢ ኖሮት ቤተሰብን ለማስተዳደር በቂ ሳይሆን ሲቀር የተሰማሩበትን የሥራ መስክ የሚተው አሉ:: ለምሳሌ:- በርዳታ ያገኙት የነበረው ገንዘብ በወር መቶ ብር ከሆነ አሁን በአነስተኛ ንግድ ተሰማርተው ከዚያ በታች ካገኙ፣ ሥራውን ይተውታል:: ዛሬ እዚህ ደርሻለሁ ነገ ደግሞ የበለጠ ይሳካልኛል ብለው ጥረት የሚያደርጉ ጥቂቶች ናቸው:: በዚህም የተነሣ ሳንሠራ እየተረዳን እንኑር የሚሉ አሉ:: ሁለተኛው ደግሞ (Dependency Syndrom) በርዳታው ላይ ጥገኛ የመሆን ዓይነት ነገር ይታያል:: በብዙዎች ሰዎች የሚታየው የመሥራት ፍላጐት መቀነስ ነው:: ድርጅቶች የሙያ መሣሪያውን አቅርበውላቸው፣ በቡድን ሁለት

> ርዳታ በፕሮጀክት የሚመጣ ነው::
> ፕሮጀክት ሲባል ደግሞ የተወሰነ የሚያል
> ቅበት ጊዜ አለው:: በዚያች ጊዜ
> ተፍጨርጭረህ ራስህን ቻል ስትለው፣
> በአብዛኛው ሰው ራሱን ከመቻል ወደ ኋላ
> የሚልበት ሁኔታ አለ::

ሦስት አድርገው አቋቁመዋቸው እንኳ
የሚሳነፉበት ሁኔታ አለ:: የሙያ ሥል
ጠና ተሰጥቷቸው ጥሩ ደረጃ ደርሰው ውጤ
ታማ የሆኑ እንዳሉ ሁሉ በአንዳንድ
ቦታዎችም ሥልጠናዎቹ ኖረው ውጤ
ታማነቱ ግን የተጠበቀውን ያህል ያልሆ
ነላቸው አሉ::

መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር
ስትሠራ በርዳታ ዙሪያ ብዙ ገጠመኞች
ይኖራሉ:: በአንዳንድ ቦታ ስትመለከተው
ማኅበረሰቡ በእውነቱ ስለ መያድ /NGO/
ትክክለኛ አመለካከት ያለው አይመስልም::
ድርጅቶቹ ከለጋሾቻቸው ጫና አለባቸው::
ለኅብረተሰቡ ገንዘብ ሰጥተናቸዋል፣ የታለ
የተለወጡት ይላሉ፣ ኅብረተሰቡን ደግሞ
በሠለጠናችሁበት ሙያ ሥሩ፣ ውጤታማ
ሁኑ፣ ካለበለዚያ ገንዘቡ ይቆማል በሚባ
ልበት ጊዜ ሰዎቹ አያምኑም:: እንዲያውም
የመጣው ገንዘብ ይህ ብቻ አይደለም የሚል
ጥርጣሬ አላቸው:: ሌላም ምሳሌ ማንሳት
ይቻላል:: ለጋሹ የሚሠለጥኑትን ልጆች
እስቲ አምጧቸው ይልሃል፣ የሚሠለጥኑት
ልጆች ግን ፎቶ ለመነሣት እንኳ ፈቃ
ደኞች አይደሉም:: እንደውም በእኛ ፎቶ
ልትለምኑ ነው ይሉሃል:: ስለዚህ መያዶች
በለጋሾችና በኅብረተሰቡ መሐል ሆነው
በጣም ተጣብቀው ነው ያሉት:: በአ ንድ
በኩል ቀበሌው ድረስ ያለው የመን
ግሥት መዋቅር ውጤት አላመጣችሁም
እያለ ይቆጣጠራቸዋል:: እንዲህ እንዲህ
ዓይነት ችግሮች አሉባቸው:: ኅብረተሰቡ
የርዳታ ድርጅትን ዝም ብሎ ገንዘብ አም
ጥቶ ለግለሰቦች ለእያንዳንዳቸው ያድላቸው
የሚል ዓይነት አመለካከት ነው ያላቸው::
እውነታው ግን ይህ አይደለም::

ርዳታ በፕሮጀክት የሚመጣ ነው:: ፕሮ
ጀክት ሲባል ደግሞ የተወሰነ የሚያል
ቅበት ጊዜ አለው:: በዚያች ጊዜ ተፍጨ
ርጭረህ ራስህን ቻል ስትለው፣ በአብዛ
ኛው ሰው ራሱን ከመቻል ወደ ኋላ የሚ
ልበት ሁኔታ አለ::

በአጠቃላይ ሲታይ ግን ኅብረተሰቡ ከቫ
ይረሱ ጋር የሚኖሩት ዝም ብላችሁ ብር
ስጡን ነው የሚሉት፣ የነገን ራእያቸውን
ለማሳካት ጥረት የሚያደርጉት የተወሰኑ
ናቸው:: ዐሥር ሰው ብታሰለጥን ከዚያ
ውስጥ ራሱን የሚችለው ከሁለት አይበ
ልጥም::

በፕሮጀክት ታቅፈው ርዳታ ለሚደረ
ግላቸው፣ በትክክል ይደርሳቸዋል:: ቢያ
ንስ ሁለት፣ ሦስት ጊዜ የሙያ ሥልጠና
ያላገኘ ሰው የለም:: ይሠራበታል ወይ?
ትልቁ ጥያቄ ነው:: በተሰጠው ሥልጠና
ራሱን ችሏል ወይ? ስትል አልቻለም:: በተ
ወሰነ ደረጃ ግን ለውጥ አለ:: ራሳቸውን
ችለው ቤተሰቦቻቸውን የሚያስተዳደሩ
ትልቅ ደረጃ የደረሱ አሉ:: ለሌሎች
አርአያ የሆኑም ብዙ ልጆች አሉ:: በዚህ
ዙሪያ ያለው ችግር መጠነ ሰፊ ነው ረጂ
ዎችም ተረጂዎችም ሊገነዘቡና የጋራ
ችግራችንን በአንድነት ማሸነፍ ይጠበ
ቅብናል:: ካለበለዚያ ገንዘብ መውጣቱም
ሳይቀር ራሱንም የሚችል ሳይኖር በጊዜ
ያዊ ርዳታ ብቻ የተወሰነና የሥራ ልቡና
ውን ለዘለለም የሚያጣ አካል የምናፈራ
እንዳይሆን ያስጋል:: ♦

*ይቆየን:*
*ወስብሐት ለእግዚአብሔ*

# ለራስ ጥቅም ሌሎችን ማስቀደም

ዲ/ን ያረጋል አበጋዝ

*ባለው እትማችን እያንዳንዳችንን በሚያገናኘን ማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ተጠቃሚ መሆን የሚቻለው እንዴት ነው? ከሌሎች ጋር በሚኖረን የጥቅማ ጥቅምና ሌሎች የአብሮአዊነት ጉዳዮች ላይ እንዴት ተጠቃሚ መሆን እንችላለን? አንድ ሰው ራሱን ለመጥቀም ምን ማድረግ አለበት የሚሉትን ነጥቦች በአብርሃምና በሎጥ፣ በሙሴ እንዲሁም በመበልተ ሰራፕታዋ ሕይወት አንጻር ተመልክተን ነበር። ዛሬ ደግሞ የነቢዩ ዮናስንና የቅዱስ ጳዉሎስን ሕይወት በመዳሰስ የመጨረሻውን ክፍል አቅርበንላችኋል።*

ሠ/ ነቢዩ ዮናስ - የነነዌ ሰዎች ኃጢአት በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ በሆነ ጊዜ የኃጥኡን መመለስ እንጂ ሞቱን የማይወድ መሐሪና ይቅር ባይ አባታችን እግዚአብሔር ወደ ዮናስ ቃሉን እንዲህ ሲል ላከ፡- «ተነሥተህ ወደዚያች ወደ ታላቂቱ ከተማ ወደ ነነዌ ሂድ፣ ክፋታቸውም ወደ ፊቴ ወጥቶአልና በእርስዋ ላይ ስበክ።» ዮና. ፩፥፪-፫ ዮናስ ግን እግዚአብሔር እንዳዘዘው ወደ ነነዌ ሄዶ መስበኩን ትቶ እግዚአብሔር ቸርና ይቅር ባይ ነው፤ አሁን እኔ ሄጄ ትጠፋላችሁ ብዬ ከተናገርኩ በኋላ እርሱ ይምራቸዋል፤ እኔም ይህ ነቢየ ሐሰት እየተባልኩ መዘባበቻ እሆናለሁ በማለት ከነነዌ ሕዝብ መዳን ይልቅ ለራሱ ክብርና ዝና ብቻ በመጨነቅ ከኢየሩሳሌም ወጥቶ ራቅ ወዳለ ወደ ሌላ ሀገር ቢሄድ ከእግዚአብሔር ፊት መራቅ የሚችል መስሎት ወደ ተርሴስ ለመሄድ በመርከብ ተሳፈረ።

ወደ ተርሴስ ሔዶ ከእግዚአብሔር ፊት በመራቅ ወደ ነነዌ ሳይሄድ ውሸታም የመባልን አደጋ በማራቅ ክብሩን ለመጠበቅ በማሰብ በመርከብ በተሳፈረ ጊዜ የተሳፈረባት መርከብ ልትሰበር እስክትደርስ ድረስ በባሕሩ ታላቅ ማዕበል ሆነ። ጥፋት የተነገረባት ነነዌ ሳትናወጥ እርሱ በባሕር ማዕበል ተጨነቀ። ወደ ባሕር የሚጣለው ሰው ዕጣ በእርሱ ላይ ስለ ወጣበት ወደ ባሕር ተጣለ፤ በዚያም በዓሣ ነባሪ ተውጦ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በዓሳው ሆድ ውስጥ ኖረ። «ኩሉ ማዕበልከ ወሞገድከ እንተ ላዕሌየ ኅለፈ -ማዕበልህና ሞገድህ ሁሉ በላዬ አለፈ» እስኪል ድረስ ለሞት በቀረበ መከራ ውስጥ ወደቀ። ዮና.፫፥፬። በእግዚአብሔር ትእዛዝ ዓሣው በነነዌ የብስ ላይ ከተፋው በኋላ ግን የነነዌ ሰዎችን ድኅነትና ጥቅም በመፈለግ ንስሐ ይገቡ ዘንድ በሰበከ ጊዜ የራሱንም ደኅንነት አገኘ። የዮናስ ጥቅምና ሕይወት ለነነዌ ሰዎች በሚያደርገው ነገር የተመሠረተና የሚወሰን ሆኖ እናያለን። የሌሎችን ትቶ ለራሱ ሲያስብ የራሱን ደኅንነት የሚያጣ፣ ለእነርሱ ሲያስብ ደግሞ የእርሱ ሕይወትና ደኅንነት የሚጠበቅ ሆኖ እናያለን።

ረ/ ቅዱስ ጳዉሎስ - ይኽ ሐዋርያ በኑሮውም በትምህርቱም ከራሱ ይልቅ ሌሎችን ያስቀድም እንደነበር በብዙ ሁኔታ ይታያል። በትምህርቱ «እያንዳንዱ የባልንጀራውን ጥቅም እንጂ አንድ እንኳ የራሱን ጥቅም አይፈልግ ... እኔ ብዙዎች ይድኑ ዘንድ ለጥቅማቸው እንጂ በሁሉ ነገር የራሴን ጥቅም ሳልፈልግ ብዙዎች የሚጠቀሙበትን እንደማደርግ» ይላል። ፩ቆሮ.፲፥፳፬-፴፫። እንዲሁም ለሮሜ ክርስቲያኖች በላከው መልእክቱ እንዲህ ይላል፡- «እኛም ኃይለኞች የሆንን የደካሞችን ድካም እንድንሸከም፣ ራሳችንንም ደስ እንድናሰኝ ይገባናል። እያንዳንዳችን እንድናንጸው እርሱን ለመጥቀም ባልንጀራችንን ደስ እናሰኝ። ክርስቶስ ራሱን ደስ አላሰኘምና።» ሮሜ ፲፭፥ ፩-፪።

የክርስትና ሕግ ይህ ነው - ራሳችንን ሳይሆን ሌሎችን ለመጥቀምና ለማስደሰት ቅድሚያ መስጠት። ክርስቶስ በተግባር ያሳየን ይህን ነውና። እርሱ መከራ ተቀብሎ እኛን ከመከራ አዳነን፤ እሱ በጲላጦስ ፊት ተከሶ ለፍርድ በመቆሙ በኀጢአታችን ምክንያት በእግዚአብሔር ፊት መቆም አንችል የነበርን እኛ በእርሱ ቸርነት እንቆም ዘንድ አደረገን፤ እርሱ ራሱን አሳልፎ በመስጠት ደቀ መዛሙርቱን «እኔን ትፈልጉ እንደሆናችሁ እነዚህ ይሂዱ፣ ተዉአቸው» (ዮሐ.፲፰፥፰) በማለት እርሱ ተይዞ ሁላችንንም ነጻ አወጣን። እርሱ መራራና የውርደት ሞትን በመሞቱ እኛ ለክብር በቃን። በአጠቃላይ የክርስቶስ ሰው የመሆን ዓላማና ሰው ሆኖም የፈጸማቸው ነገሮች በሙሉ ለእኛ ሲል ራሱን ያዋረደበትና ለመከራ አሳልፎ የሰጠበት፣ በእነዚህም መከራዎቹ እኛ የከበርንባቸው ናቸው።

ለዚህ ነው ቅዱስ ጳዉሎስም «እኔ ክርስቶስን እንደ መሰልኩ እናንተም እኔን ምሰሉ» ብሎ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በመልእክቱ የጻፈው። ፩ ቆሮ. ፲፩፥፩። ለሌሎች እንደ ማሰብና የሌሎችን መልካም ነገር እንደ ማስቀደም ክርስቶስን የሚያስመስል ነገር የለምና። አንድ ሰው ብዙ ቢጾም፣ መሬት ላይ ቢተኛ፣ ብዙ ፀዋትወ መከራ ቢቀበል፣ ብዙ ተጋድሎ ቢፈጽም፣ ነገር ግን ስለሌላው ሰው ጥቅምና ድኅነት የማያስብና ግድ የሌለው ከሆነ ክርስቶስን ከመምሰል ብዙ ርቆ ይገኛል።

ቅዱስ ጳዉሎስ ስለሌሎች ጥቅም ሲል ብዙ ነገሮችን አድርጓል። መብቱ የሆነውን ነገር ከመተው ጀምሮ ለሰውነትም ሆነ ለሕሊና የሚከብዱና የማይመቹ፣ ነገር ግን ስለሌሎች ጥቅም ሲል ያደረጋቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ለምሳሌም የሚከተሉትን እንመልከት።

፩. ግዝረት - ደርቤንና ልስጥራን በሚባል ቦታ በግሪክ አገር ከሲላስ ጋር በደረሰ ጊዜ ወደ ፊት ታማኝና ተወዳጅ ልጁ የሚሆነውን ጢሞቴዎስን አገኘና ከእርሱ ጋር ይወስደው ዘንድ ወደደ። ነገር ግን በዚያ ስፍራ አይሁድ ስለ ነበሩ እነርሱ ደግሞ ያልተገዘረን ሰው ደቀ መዝሙሩ አድርጎ ሲወስድ ቢያዩ የኦሪቱ ግዝረት በጥምቀት የተተካና በክርስትና ግዝረት ምንም ዋጋ የሌለው መሆኑን ተምረው እስኪያውቁ ድረስ እንዳይሰናከሉና በዚህም ምክንያት ወንጌልን ከመስማትና ስምተውም ከማመንና ከመዳን ራሳቸውን እንዳያርቁ ለእነርሱ ሲል ገዘረው። «በዚያም ስለነበሩ አይሁድ ጢሞቴዎስን ይዞ ገዘረው» የሐዋ. ፲፮፥ ፩-፬።

ቅዱሳን ሐዋርያት በኢየሩሳሌም ጉባኤ አድርገው በወሰኑት ውሳኔ «ለጣዖት ከተሰዋ፣ ከደምም፣ ከታነቀም፣ ከዝሙትም ትርቁ ዘንድ ከዚህ ከሚያስፈልገው በቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናልና፤ ከዚህም ሁሉ ራሳችሁን ብትጠብቁ በመልካም ትኖራላችሁ» ብለው ወስነዋል። በዚህም ውሳኔያቸው ከአሕዛብና ከአይሁድ ወደ ክርስትና የሚመጡትን ወገኖች ሲያወዛግቡ የነበሩትን ግዝረትን፣ በኦሪቱ የታዘዘውን - ይህን ብሉ፣ ይህን አትብሉ - የሚለውን የመብል ሕግ፣ እና የመሳሰሉትን ሁሉ በሐዲስ ኪዳን በዘመነ ወንጌል አላስፈላጊ መሆናቸውን ገለጹ። ሆኖም ግን ቅዱስ ጳዉሎስ ይህን አላስፈላጊነቱን እርሱም ባለበት በኢየሩሳሌም ጉባኤ የተወሰነውንና ራሱም ብዙ ጊዜ በመልእክታቱ ምንም ጥቅም እንደሌለው የተናገረበትን ግዝረትን ለጊዜው ከሰዎቹ ደካማነት የተነሣ ለእነርሱ ጥቅም ሲል ይህን ፈጽሟል። የደካሞችን ድካም መሸከም ተገቢ ነውና። ክርስትና እኔ በቅቻለሁ፣ ይህን ያህል ጾም እችላለሁ፣ ይህን ያህል ቀኖና እችላለሁ፣ ስለዚህ ሌላውም እንደ እኔ ይሸከም ማለት ሳይሆን የራስን ዓላማና ጥንካሬ ሳያጓድሉ ነገር ግን የሌላውን ድካም መረዳትና መሸከም ነው። የሰዎችን ድካም የማይረዳ ሰው ክርስትና ያልገባው አጉል አርበኛ ነው። በራሳቸው ጥንካሬ የሚመኩና በደካሞች የሚፈርዱ ሰዎች እነርሱም አንድ ቀን ደካማነታቸውን መረዳታቸው አይቀርም።

ቅዱስ ጳዉሎስ ሌሎችን ለመጥቀም እርሱ ያልሆነውን እስከመሆን እንደደረሰ ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

«ከሰው ሁሉ አርነት የወጣሁ ስሆን የሚበልጡትን እንድጠቅም እንደ ባሪያ ረሴን ለሁሉ አስገዛለሁ። አይሁድን እጠቅም ዘንድ ከአይሁድ ጋር እንደ አይሁዳዊ ሆንሁ፤ ከሕግ በታች ያሉትን እጠቅም ዘንድ፣ እኔ ራሴ ከሕግ በታች ሳልሆን ከሕግ በታች ላሉት ከሕግ በታች እንደላሁ ሆንሁ፤ ሕግ የሌላቸውን እጠቅም ዘንድ፣ ያለ እግዚአብሔር ሕግ ሳልሆን ነገር ግን በክርስቶስ ሕግ በታች ሳለሁ፣ ሕግ ለሌላቸው ሕግ እንደሌለኝ ሆንሁ፤ ደካሞችን እጠቅም ዘንድ ለደካሞች እንደ ደካማ ሆንሁ፤ በሁሉ መንገድ አንዳንዶችን አድን ዘንድ፣ ከሁሉ ጋር በሁሉ ነገር እንደ እነርሱ ሆንሁ። በወንጌልም ማኅበረተኛ እሆን ዘንድ ስለ ወንጌል ሁሉን አደርጋለሁ።» ፩ቆሮ. ፱፥፲፱-፳፫። ይህ ታላቅ ሐዋርያ ሰዎችን ይጠቅም ዘንድ ለአይሁዳዊውም፣ ከሕግ በታች ላሉትም፣ ሕግ ለሌላቸውም (ለአሕዛብ)፣ ለደካሞችም የሚድኑበትን መንገድ ለማስፋት የሚቻለውን ሁሉ እንዳደረገ እናያለን።

ሐዋርያውን «ክርስቶስን እንደመሰልኩ» ያሰኘውም ይህ ነው። አዎ ክርስቶስ እኛን ከወደቅንበት ለማንሣት ወደእኛ ራሱን ዝቅ አድርጎ እንደመጣና ስለ እኛ በባሕርዩ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የማይስማማውን መራብን፣ መጠማትን፣
መሰደብን፣ መገረፍን፣ መሞትን ሁሉ ለእኛ
ሲል ከእኛ እንደተቀበለ እኛም ለሌሎች
መጠቀምና መዳን የሚቻለንን ያህል ማድ
ረግ ይገባናል:: ጌታችን ሲፈትነው የቀ
ረበውን ሕግ አዋቂ «በወንበዴዎች እጅ
ለወደቀው መንገደኛ ባልንጀራ የሆነው
ማንኛው ይመስልሃል?» ብሎ ሲጠይቀው
እርሱም «ምሕረት ያደረገለት» አለ፡ ኢየሱስም
«ሒድ አንተም እንዲሁ አድርግ» እንዳ
ለው ሁላችንንም እርሱ ቁስላችንን ፈውሶ
ከወደቅንበት አንሥቶ ለክብር እንዳበቃን
ይህንን የእርሱን ቸርነትና ውለታ መክ
ፈል ባንችልም ነገር ግን ለሌሎች መልካም
በማድረግ ቸርነቱን መግለጥ ይገባናል::

፪. መብልን መተው - ከአሕዛብነት
ወደ ክርስትና ከመጡት ፍቅረ መብልዕ
ድል ያደረጋቸው አንዳንዶች «እኛ ለጣዖት
የተሠዋውንም ቢሆን ባርከን ብንበላው
እኛ እንቀድሰዋለን እንጂ እርሱ አያረክሰ
ንም» በማለት ከማመናቸው በፊት የነበ
ረው ልማዳቸው እየሳባቸው በጣዖት ቤት
እየተገኙ ለጣዖት የተሰዋውን ይበሉ
ነበር:: በርግጥ አንድን ክርስቲያን የሚያ
ረክሰው አፍአዊ ነገር የለም:: «እግዚአብ
ሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ነውና፣
ከምስጋናም ጋር ቢቀበሉት የሚጣል
ምንም የለም፤ በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት
የተቀደሰ ነውና::» ፩ጢሞ.፬፥፬-፭:: ርኩ
ሰት የሚመጣው ጌታችን እንዳስተማረን
በሰው ሕሊና በኀልዮ ተፀንሰው በነቢብና
በገቢር አድገው በሚፈጸሙ ከውስጥ
ከሚመነጩ ነገሮች እንጂ ሰው ከሚመገ
በው ምግብና ከውጫዊ ነገሮች አይደ
ለም:: የክርስትናና የዘመነ ኦሪት አንዱ
ልዩነትም በኦሪቱ ብዙ ውጫዊ የሆኑ
የሚያረክሱ ነገሮችና ተያያዥ የማንጻት
ሥርዓት የነበራቸው ሲሆን በክርስትና
ግን የሚያምኑ ሁሉ በክርስቶስ ደም
አንድ ጊዜ ተቀድሰዋል:: ከዚያ በኋላ ለሚ
ከሠቱ ችግሮች መታጠቢያው ከውስጥ
የሚወጣ የንስሐ ዕንባ ነው:: ቅዱስ
አትናቴዎስ «... ከሦስቱ አንዱ ባለሟል
አድርጎ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ
ዮርዳኖስ በዝቶ እንዲወጣ በዝቶ የሚ
ወጣ፥ ዮርዳኖስ እንዲያነጻ የሚያነጻ ከው
ስጥ የሚፈስ አንብዐ ንስሐ /የንስሐ
እንባ/ ነው::» እንዳለ ቅ. አት.

ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ይህንን
ምክንያት የተጠቀሙት ለጣዖት የሚቀር
በውን መሥዋዕት ለመብላት ካላቸው
ፍቅር የተነሣ ነበር:: በዚህም ዐውቀ
ናል፣ በቅተናል የሚሉት ወደ ጣዖት ቤት
ሲሄዱና ለጣዖት ተብሎ የተሰዋውን ሲበሉ
በማየት ሌሎች ጀማሪዎች የሆኑ አማንያን
ይሰናከሉ ጀመር:: ሰው ከእኔ ይሻላል
ያለውን ያያልና ፍጹማን ነን የሚሉትን
በማየት ጀማሪዎቹ በጣዖት ቤት መገኘ
ትና መሥዋዕቱን መብላት ምንም ጉዳት
የሌለው እየመሰላቸው በዚያው እየተሳቡ
ወደ ጣዖት ለመመለስ፤ ክርስትናንና ጣዖ
ትን፣ የክርስቶስን ጽዋና የአጋንንትን ጽዋ
ለመደባለቅ ተነሡ:: በዚህ ጊዜ ቅዱስ
ጳውሎስ እንዲህ በማለት ጻፈ:- «መብል
ግን ወደ እግዚአብሔር አያቀርበንም፤
ባንበላም ምንም አይጎድለንም፣ ብንበላም
ምንም አይተርፈንም:: ዳሩ ግን ይህ
መብታችሁ ለደካሞች እንቅፋት እንዳይ
ሆንባቸው ተጠንቀቁ:: አንተ ዕውቀት
ያለህ በጣዖት ቤት በማዕድ ስትቀመጥ
አንድ ሰው ቢያይህ፣ ደካማ ሰው ቢሆን

## ክርስትና እኔ በቅቻለሁ፣ ይህን ያህል ጾም እችላለሁ፣ ይህን ያህል ቀኖና እችላለሁ፣ ስለዚህ ሌላውም እንደ እኔ ይሸከም ማለት ሳይሆን የራስን ዓላማና ጥንካሬ ሳያጎድሉ ነገር ግን የሌላውን ድካም መረዳትና መሸከም ነው:: የሰዎችን ድካም የማይረዳ ሰው ክርስትና ያልገባው አጉል አርበኛ ነው::

ለጣዖት የተሰዋውን ለመብላት ኅሊናው
አይታነጽበትምን? በአንተ ዕውቀትም ይህ
ደካማ ይጠፋል፣ እርሱም ክርስቶስ የሞተለት
ወንድም ነው:: እንግዲህ ወንድሞችን
እየበደላችሁ፣ ደካማም የሆነውን ኅሊናቸውን
እያቆሰላችሁ ክርስቶስን ትበድላላችሁ::»
፩ቆሮ.፰፥፰-፲፫::

ወንድምን መበደል ክርስቶስን መበደል
ነው:: ወንድምን ማስደሰት ደግሞ ክርስቶስን
ማስደሰት ነው:: የክርስቶስን ውለታ የም
ንገልጠው ለሌሎች መልካም በማድረግ
ነው:: «እኔን ከተመቸኝ ሌላው የራሱ
ጉዳይ» የሚለው የክርስትና አስተሳሰብ
አይደለም:: ቅዱስ ጳውሎስ የእነዚያን አስ ተ
ሳሰብና ድርጊት ስህተትነት ከገለጸ በኋላ
ስለ ራሱ እንዲህ አለ:- «ስለዚህም መብል
ወንድሜን የሚያሰናክለው ከሆነ ወንድሜን
እንዳላሰናክለው ለዘላለም ከቶ ሥጋ አል
በላም::»

፫. ገንዘብ አለመቀበል - ጌታችን ሐዋ
ርያትን ሲልካቸው ምንም ነገር እንዳ
ይዙ ነገር ግን በዚያው በሚሄዱበት የዕ
ለት ምግባቸውን እንዲያገኙ «ለሠራተኛ
ምግቡ ይገባዋልና» በማለት ከምእመናን
ምግባቸውን እንዲያገኙ አዟል:: ማቴ.፲፥፲::
ቅዱስ ጳዉሎስ ግን ከሚያስተምራቸው
ምእመናን ለኑሮው የሚያስፈልገውን የዕ
ለት ምግብ ማግኘት መብቱ ቢሆንም
እርሱ ግን ከእነርሱ ምንም ገንዘብ ሳይቀ
በል ድንኳን እየሰፋ ራሱን ይረዳ ነበር::
ይህን ያደረገው ሰው ገንዘብ አምጣ ሲባል
ደስ እንደማይለው በመረዳቱ ይህ ነገር
ለእነርሱም ወንጌልን በንጹሕ ልብ እንዳ
ይቀበሉ፣ እርሱም እንዲሁ በነጻነት እንዳ
ያስተምር ዕንቅፋት እንዳይሆን በማሰብ
ነበር::

በተለይ የቆሮንቶስ ምእመናን ገንዘብ
ይወዱ ነበርና:: ከዚህም የተነሣ ብዙዎቹ
ዳኞችና ባለ ሥልጣናት ገና አረማውያን
በነበሩበትና ክርስትና ገና እየተስፋፋ
በነበረበት በዚያ ዘመን አንዱ ክርስቲያን
ሌላውን ወንድሙን በገንዘብ ምክንያት
እየከሰሰ ከማያምኑ ፈራጆች ፊት እየቀ
ረቡ እነዚህ ክርስቲያኖች «እኛ አገራችን
በሰማይ ነው ይላሉ፣ ነገር ግን በዚህ
ዓለም ገንዘብ ተጣልተው ይካሰሳሉ» እያሉ
ክርስትናን ያስነቅፉ ነበር:: «እንደዚህ
ነውን? በወንድሞች መካከል ሽማግሌ
ሊሆን የሚችል አንድ አስተዋይ ሰው
በእናንተ ዘንድ አይገኝምን? ነገር ግን
ወንድም ወንድሙን ይከሳል፣ ይህም
በማያምኑ ፊት ይደረጋል:: እንግዲህ የእርስ
በርስ ሙግት እንዳለባችሁ በእናንተ ጉድ
ለት ነው:: ብትበደሉ አይሻልምን? ብት
ታለሉስ አይሻልምን ነገር ግን እናንተ

ትበድላላችሁ፣ ታታልሉማላችሁ፣ ያውም
ወንድሞቻችሁን::» ያለው ይህንን ሲገ
ልጽ ነው:: ፩ቆሮ. ፮፥፭-፰::

እንዲህ በገንዘብ ፍቅር ምክንያት
ከሚካሰሱ ሰዎች ምንም ነገር መቀበል
አልፈለገም:: ወንጌልን ሰብኮ ወደ እግዚአብ
ሔር እንዲቀርቡና በጥምቀት ልጅነትን፣
የሰማያዊ መንግሥት ወራሽነት ተስፋን
እንዲያገኙ ምክንያት ከሆናቸው ከእነርሱ
ለዕለታዊ ኑሮው አስፈላጊ የሆነ ነገር
ቢቀበል ይህ መብቱ መሆኑን በብዙ ነገር
አስረዳ፤ እንዲህ በማለት:- «ልንበላና ልን
ጠጣ መብት የለንምን? ወይስ ሥራ ለመተው
መብት የሌለን እኔና በርናባስ ብቻ ነንን?
ከቶ በገዛ ገንዘቡ በወታደርነት የሚያገለ
ግል ማነው? ወይስ ወይን ተክሎ ፍሬውን
የማይበላ ማነው? ወይስ መንጋ እየጠ
በቀ ከመንጋው ወተት የማይጠጣ ማነው?
ይህን በሰው ሥልጣን ብቻ እላለሁን?
ሕግስ ደግሞ ያን አይልምን? የሚያበራ
የውን በሬ አፉን አትሰር ተብሎ በሙሴ
ሕግ ተጽፎአልና:: እግዚአብሔር ስለ
በሬዎች ይገደዋልን? ይህን የሚለው ስለ
እኛ አይደለምን? የሚያርስ በተስፋ
ሊያርስ የሚያበራይም እንዲካፈል በተ
ስፋ ሊያበራይ ስለሚገባው በእውነት ስለ
እኛ ተጽፎአል:: እኛ መንፈሳዊ ነገር የዘ
ራንላችሁ ከሆንን የእናንተን ሥጋዊ ነገር
ብናጭድ ትልቅ ነገር ነውን? በመቅደስ
የሚያገለግሉ ከመቅደስ የሆነውን ነገር
እንዲመገቡ፣ በመሰዊያውም የሚጸኑ ከመ
ሠዊያው እንዲካፈሉ አታውቁምን? እን
ዲሁ ደግሞ ወንጌልን የሚሰብኩ ከወን
ጌል ቀለብ እንዲቀበሉ ጌታ ደንግጎአል::
እኔ ግን በዚህ ሁሉ ምንም አልተጠቀ
ምሁም:: እንዲህ እንዲሆንልኝ ይህን
አልጽፍም::» ፩ ቆሮ.፱፥፯-፲፩፤፲፫-፲፭::
ይህን ካለ በኋላ ለምን በዚህ መብት እን
ዳልተጠቀመ ሲገልጽ «ነገር ግን የክርስ
ቶስን ወንጌል እንዳንከለክል በሁሉ እንታ
ገሣለን እንጂ በዚህ መብት አልተጠቀም
ንም:: ማንም ትምክህቴን ከንቱ ከሚያደ
ርግብኝ ሞት ይሻለኛልና» አለ:: ፩ቆሮ
፱፥፲፪::

በተለያዩ ሰዎች ሕይወት አንጻር ስ
የት እንደሞከርነው ራሳቸውን ብቻ ለመ
ጥቀም የተሯሯጡና ለሌላው ግድ ያል
ነበራቸው ሁሉም የራሳቸውን ጥቅም
እንዳሰቡት አለማግኘታቸውን፣ ይልቁንም
ሕይወታቸው እንኳ ሳይቀር ለአደጋ የተ
ጋለጠ እስኪሆን ድረስ መቸገራውን፤
በአንጻሩ ደግሞ የራሳቸውን ፍላጎት መሥ
ዋዕት በማድረግ ሌሎችን ያስቀደሙና
ከራሳቸው ይልቅ ለሌሎች ያሰቡ መጠቀ
ማቸውን ያየናቸው ምሳሌዎች ሁሉም

ወደ ፵ ገጽ ዞሯል

# በውኑ ዓለም ሳይፈጠር ...

ከገጽ ፳ የዞረ

ከሆነ ለምን በሥራውን ትተው አዋልድ ላይ ዘመቱ? የሚሉትን በአጭሩ እንደሚከተለው እናቀርባለን::

፩. በተጠና ስልት ስለሚሔዱ፡- ተሐድሶዎች የራሳቸው አባል ለማድረግ የሚታገሉት እንደሌሎች ፕሮቴስታንቶች ሁሉ የተዋሕዶ ምእመናንን ነው:: ለምእመናን ለገጠሩ፣ ለተማረውና ላልተማረው፣ መጽሔት፣ ጋዜጣ፣ መጻሕፍትን ለሚያነበው እና በልማድ ለሚኖረው፣ እንዲሁም ለካህናትና ለመርጌቶች የተለያዩ ስልቶችን ቀይሰዋል:: ለምሳሌ የገጠር መርጌቶችን «እኛ የተዋሕዶ ሊቃውንት ነን» በማለት ሥልጠና በመስጠት ከሥልጠናውም በኋላ ደመወዝ በመስጠት የተቻላቸውን በማድረግ ላይ ናቸው:: እንደ አዲስ አበባ፣ ባሕርዳር፣ መቀሌ፣ ጎንደርና ደሴ ባሉት ከተሞች ለሚኖሩ ካህናትና ዲያቆናትም የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ለመውሰድ የተቻላቸውን ሁሉ ጥረት ያደርጋሉ::

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በከተማ ላሉና ለተማሩ ምእመናን እንዲሁም መካከለኛ ዕውቀት ላላቸው ካህናት ጭምር ደግሞ የታቀደው በዚህ አዋልድ ላይ የተቀናጀ አጠራጣሪ ጽሑፍ በማውጣት ማስኰብለል ነው:: «የተለየ ነው» የምንለውንም ማኅበሩ ባሳተመው «የገሃነም ደጆች» መጽሐፍ ምዕራፍ ስምንት ላይ በሰፊው መመልከት ይቻላል:: ለዚህ ጽሑፍ ግን እነርሱ አጥንተው ይፋ ካደረጉት ጽሑፋቸው ላይ መጻሕፍት ላይ ለምን መዝመት እንዳስፈለጋቸው የገለጹትን በማቅረብ ወደሚከተለው ነጥብ እንሸጋገራለን::

በወቅቱ መዲና መጽሔት «ጥንታዊቷን የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለማፈራረስ የተዘጋጀ ምስጢራዊ ሰነድ» በሚል ርእስ ያቀረበችው ጽሑፍ ላይ «የኢተቤን [ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን] ጥንታዊ መሠረተ እምነት አመስግኖ ለመግለጽም ሆነ በኋላ የገቡትን የስሕተት ትምህርቶች ለመቃወም ሲባል በእጇ ከሚገኙ ከነባር መጻሕፍተ ሊቃውንቷ የድጋፍ ማስረጃዎችን መጥቀስ እጅግ ስልታዊና መስህብ ነው:: ለሥነ ጽሑፍም ተወዳጅነትና ተቀባይነትን በአተቤ ዘንድ ያስገኝለታል:: ... የግእዝ ቃላትም በሥነ ጽሑፍ ውስጥ እንዲፈርጥ መግባታቸው እንደውበት ሰጪ ብቻ መቆጠር የለብትም:: ሥነ ጽሑፍን የእኛ ነው ያሰኘዋል» በማለት ሥልታቸውን አስቀድመው ገልጸዋል:: /መዲና መጽሔት÷ ቁጥር 001፣ ጥር ፲፱፻፺ ዓ.ም ዕትም፣ ገጽ.፳፱፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ የገሃነም ደጆች፣ ገጽ. ፪፻፬/

፪/ ለመመሳሰል፡- ይህ ስልት በሁለተኛነት የሚጠቀሙበት ራሳቸውን ትክክለኛዎቹ ተዋሕዶዎች አድርገው ለመቅረብና ተመሳስሎ ለመኖር ነው:: ግእዞቹን እየጠቀሱ፣ እየቆንጻጸሉ እና እየቆራረጡ የሚቆረቆሩና ለተዋሕዶ የሚቀኑ በመምሰል ለማሳት ይጠቀሙበታል:: አዋልዱን እያገላበጡ ለእነርሱ የሚመች የሚመስላቸውን በማውጣት ሲጽፉና ሲሳደቡ፤ ከፕሮቴስታንት የተለዩ ተደርገው እንዲቆጠሩ በማሰብም ሊሆን ይችላል:: ምክንያቱም የኢትዮጵያ ሕዝብ በቅርብ አውሮፓዊ ጠባይን በአገራችን እያስፋፋና ለእነርሱም ባሕል እየተጋደለ ያለውን አውሮፓዊ ፕሮቴስታንት የሚያውቀው መጽሐፍ ቅዱስን ይዞ ሌሎቹን አያስፈልጉም ሲል ነው:: እነዚህኞቹ ግን ስልቱን ወይም የማሳሳቻ መንገዱን ከመጽሐፍ ቅዱስ አውጥተው አዋልድ ላይ በማድረጋቸው ኦርቶዶክስን በመመሳሰል ለፕሮቴስታንትነት ለመሥራት ይጠቀሙበታል:: በቅርብ ጊዜያት በተለይ ከአዲስ አበባ ለዝግጅት ክፍላችን በአካልም በስልክም ከሚደርሱን መልእክቶች ብዙዎቹ በዚህ የመመሳሰል ስልት ብዙ ሰዎችን እያሳቱ እንደሆነ የሚገልጹ ናቸው:: ኮርስ እንሠጣለን፣ ትምህርተ ተዋሕዶን እናሳውቃለን በማለት፤ በስመ አብ ብሎ በሚጀመርና የቅዱሳን ሥዕሎችም በሚደረጉባቸው ጽሑፎቻቸው ተመሳስለው ከቀረቡ በኋላ ጭራሽ እንደ ውዳሴ ማርያም ያሉትን የጥንት ጽሑፎች ሁሉ አያስፈልጉም ለማለት በቅተዋል:: ታዲያ ከዚህ በላይ ሌላ ፕሮቴስታንትነት ወዴት አለ? በዚሁ አጋጣሚ ምእመናንን ማሳሰብ የምንፈልገው በየስፍራ የሚሰጡ ትምህርቶችን መጀመሪያውኑ ለምን ትቀበላላችሁ? እባካችሁ ዘመኑ ሰይጣን የሠለጠነበት ስለሆነ ወደ እውነተኛው፣ ሕጋዊው ትምህርት ይፋዊ በሆነ መንገድ ወደሚሰጡባቸው ሰንበት ት/ቤቶችና ሌሎች የቤተ ክርስቲያን ጉባኤያት ታደሙ::

ሌሎቹን ስልቶቻቸው በሌላ ሰፊ መድረክ ወይም መጽሐፍ ማግኘት ስለሚቻል ለዛሬው በዚህ እናጠቃልለውና ለመጨረሻ የሚሆን አንድ አሳብን እናንሳ:: «ታዲያ ገድላት ሁሉ ችግር የለባቸውምን? አዋልድስ ሁሉ ትክክል ናቸውን?» የሚል ጥያቄ ያላቸውን ሰዎች ለመርዳት አጭር መፍትሔ ጠቁመን እንለፍ::

## ስህተት ያለባቸው አዋልድ ሊባሉ አይገባቸውም

ቤተ ክርስቲያንም ሆነች እኛም በአቅማችን የምንላችሁ የተጻፉት ሁሉ ትክክል ናቸው፡ በግእዝና በብራና የሚገኘውም ሁሉ የእኛ ነው የሚል አይደለም:: ይሁን እንጂ ስለአዋልድና ስላለፋባቸው ሁኔታዎች ስለ ቤተ ክርስቲያንም ተጨባጭ ሁኔታ ሳንገነዘብ ዝም ብለን የፕሮቴስታንት አምባሳደሮች በሚሉት የምንነዳ ከሆነ ከቤተ ክርስቲያን የምስጢር ምንጭ ሳንቀምስ ሰይጣን ያደፈረሰውን ያልጠራ ያልተባ የኑፋቄ ጉርፍ እንጋታለንና እንጠበቅ ነው የምንለው::

አዋልድ የሚባሉት እንደ ስማቸው ዐሥራው መጻሕፍትን የሚመስሉ የእነርሱ ልጆች እነዚያን የሚተረጉሙ፣ የሚያመሰጥሩ፣ የተሰወረውን ገልጸው በምስጢር የታፈፈውንም አፍታትተው ለሰው በሚቀልለው መንገድ የሚያቀርቡ፤ እውነት ናቸውን? ሊያደርጉ ይችላሉን? ተብለው የሚጠየቁትን የወንጌል ትዕዛዛትም ሊፈጽሙ የሚችሉና ተፈጽመው የሚያውቁ መሆናቸውን የሚያስረዱት እንጂ ከዚህ ሀሳብ የወጣ መልእክት ያላቸው አዋልድ ሊባሉ፤ በስሙም እንኳን ሊጠሩ አይገባቸውም:: ስለዚህ አንድን መጽሐፍ አዋልድ ነው ብለን እስከተቀበልነው ድረስ ስሕተት አለበት ልንለው አንችልም:: አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሆነ መጽሐፍ /ለምሳሌ የማቴዎስ ወንጌል/ ቅዱስ መጽሐፍ ነው ካልን በኋላ ስሕተት አለበት ልንል እንደማንችለው ሁሉ ለአዋልድም እንዲሁ ነው:: ምክንያቱም መጽሐፍን ስሕተት አለበት በሚለው ከተስማማንበት «ቅዱሳት» ከሚባሉት ተርታ ልናስወጣው ይገባናል እንጂ ቅዱስም ነው ስህተትም አለው ልንል አንችልም:: አዋልድንም ከመጀመሪያው ስሕተት ናቸው ካልን ዲቃሎች ወይም የመናፍቃን ጽሑፎች ካለበላዚያም ሌላ ልንላቸው እንችላለን እንጂ አዋልድ ልንላቸው አይገባም:: አዋልድ ውስጥ ካስገባናቸው በኋላ ደግሞ የማይጠቅሙ መጻሕፍት ናቸው ልንላቸው አንችልም::

ይሁን እንጂ እውነተኞቹ አዋልድ ላይ ደግሞ ችግር ተፈጥሮ አያውቅም መናፍቃን አልደፈሯቸውም:: ማለት አይደለም:: ይህንንም በቀላሉ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ልንረዳው የምንችለው ጉዳይ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ጊዜ ከሰማይ የወረደ ሳይሆን በትንሹ በሁለት ሺሕ ዘመናት ወስጥ በተለያዩ አበው የተጻፈና በየጊዜውም የእነዚያ ቅዱሳን ሰዎች ሥራ በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት የተዘጋጀ መሆኑ እየታወቀ ብቻ ሳይሆን እየተጠበቀም ጭምር ነው እኛ ጋር የደረሰው:: በተለይ በወንጌልና በሐዋርያት መልእክቶች አንጻር ግኖስቲኮች የራሳቸውን የፈጠራ ወንጌሎችና መልእክታት አዘጋጅተው ግማሽ እውነት የያዙ የሐሰት መጻሕፍቶቻቸውን ካዘነቡአቸው በኋላ እውነተኞችን ለይቶ በቅድስናቸው ጠብቆ ለመኖር የተከፈለው መሥዋዕትነት ቀላል አይደለም:: ከዚህም በኋላ ቢሆን መጽሐፍ ቅዱስ ከቋንቋ ወደ ቋንቋ ሲተረጎም፣ ከአንዱ ወደ አንዱ ተገልብጦ ሲወሰድ ብዙ ችግሮች ገጥመውታል:: ተቆርጦ የወጣ፣ አዲስ የተጨመረ፣ ቃሉ የተለወጠው፣ ትርጉሙ የተዛባው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ብዙ ነው:: ይህንንም በእኛ ሀገር በተለያዩ ዘመናት ከታተሙት የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶች በተለይም በኦሮምኛና በሌሎች ቋንቋዎች ከተዘጋጁት በቀላሉ ልንረዳው የምንችለው ነው:: ይህ ሁሉ ችግር መኖሩ ግን መጽሐፍ ቅዱስን ስህተት ነው፣ አያስፈልግም ሊያሰኘው አይችልም:: ነገር ግን ተጠንቶ ከጥንቶቹ ቅጂዎች በተለይም ከዕብራይስጡ፣ ከግሪኩና ከግእዙ ወይም ከሱርስቱ ተገናዝቦ ይዘጋጅልን፤ የጠመመው ይቃናልን፣ የጎደለው ይሞላልን ሊባል ይችላል፤ የሚደረገውና እየተደረገ ያለውም ይኸው ነውና:: አዋልድም ላይ በተመሳሳይ መልኩ በማጥናት የጥንት ቅጂዎችን በማፈላለግ የተበረዙትን፣ የተጨመረባቸውን፣ የተፋቀባቸውን ተመሳሳይ ችግር የገጠማቸውን በማስተካከል ወጥና ቋሚ (Standard) ማዘጋጀት የተማሩትና የሚያውቁት ሁሉ ሓላፊነትም ግዴታም ነው::

ወደ ፵፫ ገጽ ዞሯል





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# «መንፈስ ቅዱስ ...»

ከገጽ ፳ የዞረ

ስመ ግዛት ሹመት ደጅ ሲጸኑ ስላዩአቸው ተቆጡባቸው። ማር.፲፥፴፭-፵፭።

ይህ አስተሳሰባቸው ከትንሣኤውም በኋላ አልለቀቃቸውም ነበር። ክርስቶስ የማዳን ሥራውን ፈጽሞ ወደ አባቱ ሊያርግ ሳለ እርሱ ሊጠብቁ የሚገባቸውን የተስፋውን ቃል እየነገራቸው እነርሱ ግን «ጌታ ሆይ፦ በዚህ ወራት ለእስራኤል መንግሥትን ትመልሳለህን?» ብለው ጠየቁት። የሐዋ.፩፥፮። ውሳጣዊ ዓይናቸው የተገለጠውና የእግዚአብሔር መንግሥት ምንነት የገባቸው መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ነበር። አንዱ በሌላው ላይ ለመሠልጠን ሳይሆን አንዱ ለሌላው ለመታዘዝና ሌላውን ለማገልገል የሚሽቀዳደሙ ሆኑ። ዓላማቸው ሁሉ የክርስቶስ ክብር፣ የሰዎች ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ብቻ ሆነ። የሚያስጨንቃቸው በዚህ ዓለም እንዴት ሀብት ንብረት እንደሚያገኙና እንደሚሾሙ ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን ነገር ብቻ ሆነ። የዚህን ዓለም ሹመትና ክብር፣ ሀብትና ሕይወት የሚፈልጉ ሳይሆን «ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ፣ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና» በማለት ከዚህ ዓለም ወጥተው ወደ ክርስቶስ ለመሄድ የሚናፍቁ ሆኑ። ፊል.፩፥፳፫። ሞትን ፈርተው ተበታትነው የነበሩት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ግን ሞትን የማይፈሩ ብቻ ሳይሆን ወደ ክርስቶስ የሚሄዱበት የቀና መንገድ አደረጉት።

ከላይ እንደተመለከትነው ይህ በዓል የሐዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችበት ቀን ነው። እነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅና ሌሎችም ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ይህችን ቀን «የቤተ ክርስቲያን የልደት ቀን፣ የበዓላት በዓል» ብለዋታል። ደገኛውና ታላቁ አባት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስለዚህች ዕለት ሲናገር «ዛሬ ከበረከት ሁሉ ጫፍ ላይ ደርሰናል፣ ከበዓላት በኵር ደርሰናል፣ ጌታችን ቃል የገባልንን ተስፋ ፍሬውን አግኝተናል» ብሏል። እንዲሁም «እግዚአብሔር ሊሰጥ የሚችለውን የመጨረሻውን ሥጦታ በምልዓት ሰጥቶናል ... ይህ ሥጦታ ምንድን ነው; መንፈስ ቅዱስ ነው።› ብሏል።

ቅዱሳን ሐዋርያት ከምድራዊ አስተሳሰብ ማለትም በዚህ ዓለም አንዱ በሌላው ላይ ለመሰልጠንና ለመግዛት ከነበራቸው ደካማ አስተሳሰብ ነጻ ወጥተው የክርስቶስ መንግሥት ክብር ምንነት የገባቸው በመንፈስ ቅዱስ ነው። በተለያየ ነገር ይፈሩና ይደነግጡ የነበሩት ምንም ነገር የማይመልሳቸው፣ ሰይጣን ራሱ እንኳ ተዋግቶ ድል ያላደረጋቸው ጽኑዓን የሆኑት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው። የክርስቶስ ትምህርቱ፣ ዓላማውና የማዳን ምስጢሩ፣ በአጠቃላይ ለሰው ያሰበውና ያዘጋጀው ነገር ተሰውሮባቸው አስተሳሰባቸው እንደ ፍልፈል ወደ መሬት የነበረው ተለውጦ «እኛ አገራችን በሰማይ ነው» የሚሉ የሆኑት በመንፈስ ቅዱስ ነው። የዚህን ዓለም ሕይወት «ድንኳን» አሉት፤ እንዲህ ብለዋልና፦ «ድንኳን የሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ የዘላለም ቤት የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሠራ ሕንፃ እንዳለን ዕናውቃለንና።... ከሰማይም የሚሆነውን መኖሪያችንን እንድንለብስ እንናፍቃለን» ፪ቆሮ. ፭፥፩-፪። ይህ አስተሳሰብ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ከመሆን የሚገኝ ነው።

እኛም በጥምቀት የምንቀበለው ጸጋ መንፈስ ቅዱስ እነርሱ የተቀበሉትን መንፈስ ቅዱስ ነው። ስለዚህ የተቀበልነውን ጸጋ መንፈስ ቅዱስ በመጀመሪያ የእርሱ ማደሪያ የሆነውን ሰውነታችንን በኃጢአት እንዳናቆሽሽና እርሱን እዳናሳዝነው መጠንቀቅ ይኖርብናል። «ለቤዛ ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ» እንደተባልን። ኤፌ.፬፥፴። ሰው ከመሆን የተነሣ የተለያየ መሰናክሎችና ሰውነታችንን የሚያሳድፉ ድቀቶች ቢገጥሙን በንስሐ እናስወግዳቸው። ንስሐ እስከገባንበት ድረስ የማይታጠብ የኃጢአት ቆሻሻ የለምና። እግዚአብሔርን ከማሳዘን በላይ የሚያስፈራ ነገር የለምና። በንስሐ መታጠብ ለሁላችንም ያስፈልገናል። የዚህን ዓለም ጊዜያዊነትና ሓላፊነት ለመረዳት፣ እግዚአብሔር በአባታዊ ቸርነቱ ያዘጋጀልንን ክብር ለማወቅና ዐውቀንም ለመዘጋጀት የምችለው በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ማስተዋል ስንችል ነው። ያደረብንን ጸጋ መንፈስ ቅዱስ በኃጢአት ሳናሳዝን የእግዚአብሔር ቤትነታችንን በንጽሕና ስንጠብቅ ነው።

በዚህም ላይ የተሰጠን ጸጋ መንፈስ ቅዱስ እንዲሁ ለከንቱ ሳይሆን ሥራ ሠርተን እግዚአብሔርን እንድናከብር ነው። «መልካሙን ሥራችሁን አይተው የሰማዩን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ» እንደተባልን በውስጣችን ያለውን መንፈስ ቅዱስ በሥራ መግለጥ ይጠበቅብናል። ማቴ.፭፥፲፮። ጸጋ ያልተቀበለ ክርስቲያን የለም። እያንዳንዳችን በጥምቀት ልጅነት ስናገኝ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ተሰጥቶናል። «እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጠን። ስለዚህ ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ምርኮን ማረከ፣ ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ» በማለት ሐዋርያው እንደገለጸው። ኤፌ. ፬፥፯-፰። ስለዚህም በዚህ ዓለም ምኞትና አሳብ ባዝነን እንዳንቀርና የልጅነት ተስፋችንን እንዳናጣ በጥንቃቄ መኖር ይገባናል።

ሐዋርያትን ያጸና አምላክ እኛንም እንዲያጸናንና ክብሩን ለመውረስ እንዲበቃን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን።♦

# በውኑ ዓለም ሳይፈጠር...

ከገጽ ፴፬ የዞረ

በዚህ መንገድ ደግሞ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሠርታለች ማለት አይቻልም። ለዚህ ዋና ዋና ምክንያቶቹ ሁለት ናቸው። የመጀመሪያው ከራሷ ልጆች ሾማ ሲኖዶስ ኖሯት በዚህ መንገድ እንድትሔድ ሁኔታዎች ሳይመቻቹ ለ፲፱፻፶ ዓመታት መምጣቷ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሊቃውንቶቿም ቢሆን ዕረፍት ያገኙበት ዘመን ጥቂት መሆኑ ነው። በተለይ ከ፲፭ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስካሁን ድረስ ሀገራቱ ባላቋረጠ ጦርነትና የውስጥ ለውስጥ ግጭት ውስጥ እንደቀጠለች ናት። ይህም ሊቃውንቱን ለመከራከርና ሃይማኖታቸውን ዘመኑ በሚፈቅደው መንገድ ለመጠበቅ እንጂ አስተውለውና ተረጋግተው በሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት እንደተደረገው መጻሕፍት ላይ ጥናት አድርገው ለይተና ጠብቆ ለማስቀመጥ አላስቻላቸውም።

ከእነዚህ ሁኔታዎች አንጻር ተአምረ ማርያምንም ተመልሰን ማየት እንችላለን። ከውጭ ሀገር የተተረጎሙትን፣ በሀገራችን ተጽፈዋል የተባሉትን እና በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ የመጣውን የመቅድሙን ትርጉም እዚህ እኛ ሀገር ላይ የተጨመረበትና ሌሎቹንም በጥንቃቄ ማጥናት የመጀመሪያው ተግባር መሆን አለበት። በሁለተኛው ደረጃ በዚያ ዘመን የነበሩትን ችግሮች ለመፍታት የተጠቀሙባቸው ሃይለ ቃላት አሁን ላለው ግን በትርጉም መዛባት የሚያስከትለው ጥያቄ ካለ እነዚህን ለይቶ አውጥቶ እንደ ዘመኑ ትውልድ በማያሻማ መንገድ ሊረዳው በሚችለው ቋንቋ መግለጽ አሁን የማያስፈልጉ የሚባሉም ካሉ እነርሱን አቅርቦ በሲኖዶስ ማስወሰን ይጠይቃል።

ይህን መጠቆም ያስፈለገው የተቀደሰ ሆኖ ወይም ሰውን የሚጠቅም ነገር ሆኖ ሰይጣን ዝም ብሎ የሚመለከተው ነገር ስለሌለ ነው። ስለዚህ በተለያዩ ዘመናት ሊገቡ የሚችሉ ነገሮችን ከመጀመሪያው ከጥንቱ ለይቶ ለማየትና እውነተኛውን ነገር ይዞ ለመጓዝ ትክክለኛና ከሐዋርያት ጀምሮ አባቶች የሔዱብት መንገድ እያለ ጨልጦና ገርኝቶ መንቀፍና ማጣጣል ይቅርታ የሌለው ፍጹም ስሕተት ነው። ይህ ሥራ ግን መቼም ቢሆን ሊሠራ የሚገባውና ቤተ ክርስቲያንም ትክክለኛዎቹን በማሳወቅ ምእመናን ለመጠበቅ ሳትጠቀምባት የኖረችው መንገድ በመሆኑ፣ የሌሎቹም አኀት አብያተ ክርስቲያናት ልምድ ለእኛ መንገድ መሪ ሊሆን የሚችል በመሆኑ በእኛ ሀገርም ተግባር ላይ ሊፈጸም የሚገባው ነው። ተፈጸመ።♦

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

ሐመርን ያንብቡ፣
በሐመር ይጻፉ።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# በማዕከለ ክበኤ ...

ከገጽ ፲ የዞረ

ክርስቲያናት በሰሜን በደቡብ፣ በምሥራቅ እና በምዕራብ ኢትዮጵያ አሥርተዋል።

* ገንዘብ ማስቀረጽና ማሳተም:- በገንዘቡ ላይ በመስቀል ምልክት አስቀርጸዋል:: በዚህም በዓለም የመጀመሪያዎቹ ነገሥታት ናቸው::
* በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም የሚገኘውን ከኢትዮጵያ ተወስዶ የነበረውን የዴር ሡልጣን ገዳም እንዲመለስ አድርገዋል::

አብርሃ ለ፵፪ አጽብሐ ለ፶፭ ዓመታት ያህል ኢትዮጵያን ሲያስተዳድሩ ቆይተው አብርሃ ጥቅምት ፬ ቀን በ፫፻፴፪ ዓ.ም፣ አጽብሐም ጥቅምት ፬ ቀን በ፫፻፷፭ ዓ.ም ዐርፈዋል:: ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ቅዱሳን ነገሥታት ዘወትር በጸሎት ታስባቸዋለች:: /የኢትዮጵያ ታሪክ ከአክሱም እስከ ዛጉዬ፤ ገጽ ፵፪-፵፭/

## ዴር ሡልጣን

ኢትዮጵያ በኢየሩሳሌም የታሪክ ርስት ባለመብት የሆነችው በንግሥተ ሳባ ዘመን ነው:: «ንግሥተ ሳባ /ኩሽ/ ኢየሩሳሌም በሄደችበት ዘመን ንጉሥ ሰሎሞን በገዛ እጁ ከሰጣት ሌላ የወደደችውን ሁሉ ከእርሱም የለመነችውን ሰጣት:: እርስዋም ተመልሳ ወደ ምድርዋ ሔደች» ይላል የጉዞዋ ታሪክ ፩ኛ ነገ.ምዕ.፲÷፲፫::

ንጉሥ ሰሎሞን ለንግሥተ ሳባ የሰጣት ቦታ በኢየሩሰሌም ቤተ መቅደስ አጠገብ ያለው ርስት ነው:: የኢትዮጵያ የታሪክና የቅድስና ይዞታ የሚገኘው ጌታችን ከተሰቀለበት ቀራንዮ ጋር ተያይዞ ነው:: ዴር ሡልጣን /የመንግሥት ይዞታ/ የተባለው ከንጉሥ ሰሎሞን ጀምሮ ኢትዮጵያውያን በእንግድነት ወደ ኢየሩሳሌም ሲሔዱ የሚጠቀሙበት ቦታ ነው:: /ንቅዐ ንጹሕ ዜና ሐዋርያት፤ ገጽ. ፶፩/ ንግሥት ማክዳ በነገሡ በሃምሳ ዓመት ወደ ኢየሩሳሌም እንደሄደችና ዘመኑም እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ፬ሺ፬፻፲፫ ዓ.ዓ መሆኑን በክብረ ነገሥት እንረዳለን:: የዴር ሡልጣንም ይዞታ ለኢትዮጵያ ርስት ሆኖ የተሰጠው በዚህ ዓመተ ዓለም ነው::

በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ የታሪክ ርስት ማስረጃዎች ከሆኑት አንዱ በቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት፣ የኢትዮጵያ ነገሥታት አብርሃና አጽብሐ ስለ ዴር ሡልጣን ለቆስጠንጢኖስና ለእናቱ ለእሌኒ ንግሥት የላኩት ደብዳቤ ነው:: ደብዳቤው:- «በኢየሩሳሌም ዴር ሡልጣን የሚባል ቦታ ንጉሥ ሰሎሞን ለእናታችን ለሳባ ኩሽ ንግሥት ሰጥቷታል:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የአሕዛብ ነገሥታት ኢየሩሳሌምን እስኪያጠፉት ድረስ በአባቶቻችን በኢትዮጵያውያን ነገሥታት እጅ እንደ ነበረ በታሪክ አይታችኋል:: ከሽማግሌዎችም ጠይቃችሁ እንድትመልሱልን እንለምናችኋለን:: እግዚአብሔርን የሚፈራ ለሕዝበ ክርስቲያን የሚራራ ርስትን የሚተክል እንጂ የማይነቅል ቆስጠንጢኖስ የሚባል ደግ ንጉሥ ነገሠ፣ የክርስትና ሃይማኖት በቆስጠንጢኖስ በረታ፣ ታወቀ የሚል ወሬ ብንሰማ እጅግ አጥብቆ ደስ አለን:: አንቺም ክብርት ንግሥት ሆይ ደግ ክርስቲያን መሆንሽን ሰምተናል:: የእናት ልመና ፊት አያስመልስ አንገት አያስቀልስ ነውና፣ ለንጉሡ ለልጅሽ ነግረሽ ርስታችንን አስመልሽልን» ብለው ጽፈው ልከው ነበር::

እሌኒ ንግሥት ለልጇ ለቆስጠንጢኖስ ስለ ኢትዮጵያ እንዲህ በማለት ነገረችው:- «የሳባ ንግሥት የሰሎሞንን ጥበብ ሰምታ ሕገ ኦሪትን ተቀብላ ወደ ሀገሯ ተመልሳለች:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያውያን በሕገ ኦሪት አምነው ለእግዚአብሔር ይገዙ ነበር:: አሁን በዘመናችንም በፍሬምናጦስ ስብከት አምነው ክርስቲያኖች እንደሆኑ ላኩልን:: ከዚህም ጋር በኢየሩሳሌም ከቤተ መቅደስ አጠገብ ሰሎሞን ለሳባ ንግሥት የሰጣት የቦታ ርስት ነበር:: በአሕዛብ ነገሥታት ጊዜ ግን ቀረብን:: አሁንም እናንተ መልሱልን ብለውናልና በክርስትና ሃይማኖትም ወንድሞቻችን ስለሆኑ ልንመልስላቸው ይገባናል አለችው::» ንጉሥ ቆስጠንጢኖስም የኢትዮጵያን ነገሥታት አብርሃና አጽብሃ የላኩትን መልእክት አይቶ፣ ታሪክ ተመልክቶ፣ ከሽማግሌዎችም ተረድቶ የእናቱንም ምክር ሰምቶ ተደሰተ:: በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያን ርስት በቆስጠንጢኖስ ንጉሥና በእሌኒ ንግሥት ትእዛዝ እንደቀድሞው ለኢትዮጵያውያን ርስት ተደርጎ ተመለሰ::

የጀርመኑ ሊቅ ፕሮፌሰር ሊትማን ባሳተመው መጽሐፍ፣ «ዴር ሡልጣን ዘወሀበቶሙ እሌኒ ንግሥት ለመነኮሳተ ኢትዮጵያ፡ እሌኒ ንግሥት ለኢትዮጵያ መነኮሳት የሰጠቻቸው የዴር ሡልጣን ገዳም» ነው ብሏል:: ይህ ሁሉ የሆነው እሌኒ ንግሥት ጌታችን የተሰቀለበትን መስቀል ተቀብሮበት የነበረውን የጎልጎታን ኮረብታ አስጠርጋ መስቀሉን ካስወጣች በኋላ ነው:: ይኸውም የሚታወቀው ፕሮፌሰር ሊትማን፡ «ከወዳጆ አገር ታሪክ» ብሎ በጻፈው የዴር ሡልጣን ታሪክ ባሳተመው «ወእምድኅረ ኩስተርት ወግረ ጎልጎታ እሌኒ ንግሥት ወሀበቶሙ ለመነኮሳት ኢትዮጵያ ዘተቀብረ ውስቴቱ መስቀለ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በጎልጎታ ውስጥ እሌኒ መስቀሉን አስቆፍራ ወይም አስጠርጋ ካዘጋጀች በኋላ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል የተቀበረበትን ቦታ ለኢትዮጵያውያን መነኮሳት ሰጥታቸዋለች::» ብለዋል::

ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ መነኮሳት በዴር ሡልጣን ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ፫፻፳፮ ዓ.ም ቤት ሠርተው ተቀመጡ:: በሌላ ታሪክ የኢትዮጵያ ሰዎች ይህን የኢየሩሳሌምን የዴር ሡልጣን ቦታ ከቆስጠንጢኖስ ንጉሥና ከእሌኒ ተቀብለው የያዙት በ፫፻፴ ዓ.ም ነው ይላል:: ከዚህ ዘመን ጀምሮ ከሦስት መቶ ዓመታት በላይ ኢትዮጵያውያን በሰላምና በዕረፍት በታሪክ ይዞታቸው ተቀምጠዋል::

/የታሪክ መስተዋት፣ ፲፱፻ ፹፡ ገጽ ፲፮-፲፯/

*ይቆየን*

# «ቤተ ክርስቲያን ስትከፈል፤ ...»

ከገጽ ፲፫ የዞረ

ቤተ ክርስቲያን ግን ከሁለት ሺሕ ዓመት በላይ አንድ ሆና የቆየች ናት:: እስከ ዛሬም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ግንጣይ በውስጥም በውጭም የለም:: አሁን ግን ይህን መሰል ሁኔታ መታየቱ በጣም አሳሳቢ ነው:: እንደ እኔ እምነት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም ጭምር ሓላፊነት አለባት:: በዚህ አጋጣሚ ታሪካዊ የሆነችው ቤተክርስቲያን ስትከፈል ዳር ቆመን ማየት የለብንም:: ወገንተኛም መሆን ተገቢ አይደለም:: እኛ ወገንተኛነታችን ለአንዲት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ነው:: ጊዜያዊ አለመግባባት አለ፤ ያ አለመግባባት እንዲፈታ ጥረት ማድረግ፣ ጸሎት መጸለይ ከእያንዳንዱ ምእመን የሚጠበቅ ነው:: መታገል ያስፈልጋል:: ምእመኑም ሓላፊነቱን ተገንዝቦ የድርሻውን መወጣት አለበት:: ወዲያና ወዲህ የምን ዋልል ከሆነ አስቸጋሪ ነው:: የዓለም አቀፋዊ ጉባኤ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ያሉት ምእመናን የተከሰተውን ችግር አውቀው ለቤተ ክርስቲያናችን አንድነትና ህልውና እንዲጸልዩ ያለሰለሰ ጥረት ያካሒዳል::

*ሐመር:- ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ካለመረዳት፣ የቤተ ክርስቲያኒቷን ታሪክ ካለመገንዘብ የችግሩን አፈታት ካለማወቅ የተነሣ በጭፍኑ ድጋፎች ሊኖሩ ይችላሉ:: በአንጻሩ ገለልተኛም ሊኖር ይችላል:: እነዛን ችግሮች ለመፍታት የምሁራን /የቤተ ክርስቲያንም ሆነ ዘመናዊ ትምህርት የተማሩ/ ድርሻቸው ምን መሆን አለበት? ሚዲያዎችስ ምን ማድረግ አለባቸው?*

ኢንጂኒየር ተረፈ:- ምሁራን ትልቅ ሓላፊነት አለባቸው:: በዛሬው አነጋገር ምሁራን ማለት የፈረንጅ ትምህርት የተማረ ሰውን የሚመለከት ይመስላል:: በእኔ አስተያየት ምሁር ማለት ገዳም ውስጥ ያሉ መነኮሳት፣ ካህናት ቄሶች በአጠቃላይ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣ ጥልቅ የሆነ ትምህርት ያላቸው በሙሉ ምሁራን ናቸው:: በተገኘው መድረክ በሰበካ ጉባኤያችን በመወያየት ድምፃቸውን ሊያሰሙ ያስፈልጋል:: ሚዲያው ደግሞ የአሁኑን ድክመት፣ መለያየት ባያጋንነው እና በተቻለ መጠን እንደ አለቀ ነገር እንዳይወስደው ያስፈልጋል:: አዎን ልዩነት ታይቷል:: ተሰምቷል:: የሐሳብ ልዩነት ተንጸባርቋል:: ነገር ግን በመነጋገር በመወያየት ወደ አንድነት ማምጣት ያስፈልጋል:: ቤተክርስቲያኒቱን የሚያከብሩ፣ ሀገርንም የሚወዱ ሁሉ በተቻለ መጠን ልዩነት እንዳይባባስ ወደ አንድነት እንዲመጣ የተቻላቸውን ማድረግ ከሁሉም በላይ መጸለይ ይጠበቅባቸዋል:: ልዑል እግዚአብሔር ለሁላችንም መቻቻልን መግባባትን እንዲሰጠን እንለምነዋለን::

*ሐመር:- እግዚአብሔር ይስጥልን::*

ኢንጂኒየር ተረፈ:- አሜን::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## የበስመ አብ... ከገጽ ፳፩ የዞረ

> «እውነተኛ ክርስቲያን ከቤቱ ሲወጣና ወደቤቱ ሲገባ ሲተኛና ከእንቅልፍ ሲነቃ፥ ልብሱን ሲለብስ፥ ምግቡን ለመመገብ ሲቀመጥ፥ እንዲሁም በሥራው ሁሉ ያማትባል። የማማተብ መሠረቱ ከየት ነው ብሎ ሰው ቢጠይቃችሁ መሠረቱ ትውፊት ነው፤ ሥርዓት አጸናው፤ እምነት ደግሞ አረጋገጠው በሉት»

እንዲሆን ነው።» ለዚህም ነው ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት «ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠሃቸው» ያለው መዝ.፶፱፥፬። የኢየሩሳሌሙ ቅዱስ ቄርሎስም «ብጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያለህን እምነት ማሳወቅ አትፍራ፤ በሁሉም ነገር በምግብና በመጠጥ፣ ከቤት ስትወጣና ወደቤት ስትገባ ሁሉ በድፍረት አማትብ» ብሏል።

### ፭ኛ. አጋንንትን የምናርቅበት ስለሆነ

አስቀድመን ሊቃውንት ስመ ሥላሴን በመቅድምነት ሲጽፉ የሥራ መጀመሪያነቱን ለማረጋገጥ ጽፈውታል ማለታችን የሚታወስ ነው። በዚህ መሠረት ነቢየ እግዚአብሔር ሰፎንያስ «በመካከልሽም የዋህና ትሑት ሕዝብን አስቀራለሁ፤ በእግዚአብሔርም ስም ይታመናሉ።» (ሶፎ.፫፥፲፪) ብሏል። ክርስቲያን የሆነ ሁሉ በዚህ ስም አምኖና ታምኖ ማናቸውንም ሥራ በሚጀምርበት ጊዜ በመስቀል አምሳያ ጣቶቹን አመሳቅሎ ፊቱን፣ ደረቱን፣ እግሩንና ቀኝ ትከሻውን አማትቦ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ባለ ጊዜ ሠራዊተ ዲያብሎስ ይደነግጣሉ፣ ይሸሻሉ፣ ይርቃሉ እንደትቢያ ይበናሉ። ጌታችን አጋንንትን በእግዚአብሔር ስም በማማተብ ማራቅ እንደሚቻል ሲነግረን «እኔ ግን በእግዚአብሔር ጣት አጋንንትን የማወጣ ሲሆን ...» ብሏል። ሉቃ.፲፩፥፳።

ምግባር ከሃይማኖት አስተባብሮ ይዞ የሚገኝ ክርስቲያን ሁሉ ማንኛውንም ሥራ ከመጀመሩ በፊት ይህንን ስም በማስታወስና በማስቀደም ሲያማትብ ሠራዊተ ዲያብሎስን መድረሻ መተንፈሻ ያሳጣቸዋል። ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት «በአንተ ጠላቶቻችንን እንወጋቸዋለን፣ በስምህም በላያችን የቆሙትን እናዋርዳቸዋለን።» እንዲል መዝ.፵፫፥፭። በዚህ ወቅት የጀመሩት ሥራ ሁሉ ይቃናል፤ የተሳካ ይሆናል። ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት «ረድኤታችን ሰማይንና ምድርን በሠራ በእግዚአብሔር ስም ነው።» ብሎ እንደተናገረው በረድኤት እንጎበኛለን፤ በአጋንንት ላይ ድልን እንቀዳጃለን። በቅዱስ ወንጌል እንደተጻፈው «ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው ጌታ ሆይ አጋንንት በስምህ ተገዝተውልናል አሉት» የሚለው ቃል ስሙ አጋንንትን የሚያስደነግጣቸውና የሚገሥጻቸው መሆኑን የሚያስረዳ ነው። ሉቃ.፲፥፲፯። እነዚህ ሰባ ሁለቱ አርድዕት ምንም እንኳን ለአገልግሎት አዲስ የነበሩ ቢሆንም አጋንንትን የማውጣት ሥልጣን ተሰጥቷቸው እንደነበረ እንመለከታለን። ይህም ጌታ «የሚያምኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ» በማለት የገባው ቃል ኪዳን ይፈጸም ዘንድ ነው። ማር.፲፮፥፲፯። ቅዱሳን አባቶቻችን ሐዋርያት ሁሉ በዚህ ቃል ኪዳን መሠረት አጋንንትን ሲያወጡ እንደነበረ በመጽሐፍ ቅዱስ ተመዝግቦ ይገኛል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በፊልጵስዩስ በአጋንንት መንፈስ በመታገዝ እየጠነቆለች ለጌቶቿ ገንዘብ ታስገባ የነበረችውን ሴት ከአደረባት ጋኔን መፈወሱ ለዚህ አንድ አስረጅ ነው። የሐዋ.፲፮፥፲፰። ይህ ሁሉ እንግዲህ የእግዚአብሔር ቅዱስ ስም የአጋንንትን ሠራዊት ሲያንቀጠቅጣቸው የሚኖርና ዛሬም ቢሆን በራቸው መሆኑን የሚያ ስገነዝብ ነው። ስለዚህ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ እንል ዘንድ ይገባናል፤ እጅግ ጠቃሚያችን ነውና። ለዚህም ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳዉሎስ «በሰማይና በምድር ከም ድርም በታች ያሉት ለኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይንበርከኩ ...» ያለው። ፊል.፪፥፲

### እንዴትና ለምን እናማትብ?

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ብሎ ማማተብ የተገባ መሆኑን ከነምክንያቱ ተመልክተናል። ስለሆነም አመልካች ጣታችንን ዘርግተን መሐል ጣታችንን በማጠፍ መስቀልኛ ሠርተን «በስመ አብ ብሎ በግንባር ላይ ወወልድ ብሎ በደረት ላይ ወመንፈስ ቅዱስ ብሎ በግራ ትከሻ ላይ አሐዱ አምላክ ብሎ በቀኝ ትከሻ ላይ በመስቀል አምሳል የቀኝ እጅ ጣቶችን አመሳቅሎ ማማተብ ይገባል። ጌታችንም ምሳሌ ለመሆን በዚህ ሁኔታ አጋንንትን ያወጣ ነበርና። ሉቃ.፲፩፥፳። እኛም በመስቀል አምሳል ስናማትብ በኃይለ እግዚአብሔር ተማምነን ጠላታችንን ዲያብሎስን መካዳችን፣ ማሳፈራችንም ነው። እንግዲህ እኛ «በስመ አብ» ብለን በግንባራችን »ወወልድ» ብለን በደረታችን «ወመንፈስ ቅዱስ» ብለን በግራ ትከሻችንና አሐዱ አምላክ ብለን በቀኝ ትከሻችን ላይ በመስቀል አምሳል እናማትባለን። ይህም የሆነው ለእያንዳንዱ የራሱ ምስጢርና ትርጓሜ በመኖሩ ነው። እስቲ አንድ በአንድ እንመልከት፦

#### ሀ. በስመ አብ ብሎ በግንባር ላይ ማማተብ

መጽሐፍ ቅዱስ «በግንባራቸውም ላይ ስሙና የአባቱም ስም የመንፈስ ቅዱስም ስም ተጽፎ ነበር።» (ራእ.፲፬፥፪) ተብሎ እንደተጻፈ በዚህ ስም በግንባር ላይ ማማተብ ወልድ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በአንድነት በሦስትነት በዘባነ ኪሩብ በየማነ አብ ቅድመ ዓለም ሲሠለስ ሲቀደስ መኖሩን ለማስረዳት ነው። ሰይጣናት በሰውነ ግን ባር ላይ ሆነው ደም እየፈሰሱ እየስቆጡ ወንድም ከወንድም ባልንጀራን ከባልንጀራ መልካም ባልና ሚስትን አባትና ልጅን ወገንን ከወገን ለማለያየት እጅ ለእጅ አያይዘው ቃል በቃል አነጋግረው በዐይን ጥቅሻ በከንፈር ንክሻ ሰውን ሁሉ ኃጢአት ለማሠራት ሌት ከቀን ይጥራሉ። ቅዱስ ጴጥሮስ «ባለጋራችሁ ዲያቢሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና» እንዳለ። ፩ኛ ጴጥ.፭፥፰።

ከዚህ የምንረዳው ዲያብሎስ በሰው ልጆች መካከል መተሳሰብ መግባባት እንዳይኖር ያደርጋል። በቅዱስ ወንጌል «ሰዎች ሲተኙ ግን ጠላት መጣና በስንዴው መካከል እንክርዳድ ዘርቶ ሄደ።» እንደ ተባለ እግዚአብሔር ፍቅርን በዘራበት ሕይወት ሁሉ እርሱ እንክርዳድ ጥላቻን፣ ቂማን፣ ግድያን ይዘራል። ይህን ተረድቶ ቢያማትብበት እንደ ጢስ በኖ ከግንባር ላይ ይጠፋል።

እንዲሁም ቅዱስ ዮሐንስ «ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ አንድ ልጅም በአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን።» ዮሐ.፩፥፲፬ ያለውን እንድናስብ እንድናይ ያደርገናል፤ ስለዚህ በስመ አብ ብለን በግንባር ላይ እናማትባለን።❖

ይቆየን



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል የግእዝ ቋንቋ ያለውን የማይተካ ዘርፈ ብዙ ሚና በማጤንና የአንባብያንን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ይህን «አቡጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት» የተሰኘ ዓምድ ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ መክፈቱ ይታወሳል:: በዓምዱ የሚቀርበው ትምህርት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራንና ተማሪዎች በሚያዝያ ወር 1997 ዓ.ም በተቋቋመው «የልሳነ ግእዝ ወዳጆች ማኅበር» የሚዘጋጅ ነው:: ማኅበሩ ለግእዝ ቋንቋ ፍላጎት ያላቸውን ሁሉ በቋንቋው ማንበብ፣ መጻፍና መናገር የማስቻል፣ በቋንቋው የተጻፉትን ዕድሜ ጠገብ መጻሕፍት በመመርመር ያካበቱትን ልዩ ልዩ ሀብት ለትውልድ የማቆየት ዓላማና ግብ አንግቦ የተነሣ ነው::

*መ/ር ደሴ ቀለብ*

*ባለፈው ትምህርታችን ግሶች በቀዳማይ፣ በካዕለይ እና በዘንድ ወይም በትእዛዝ አናቅጽ ዝርዝር ርባታ ጊዜ የሚኖራቸውን የለውጥ ሒደት፣ መሠከዕ እና ጠባይ ለማየት ሞክረናል:: በዚህ ትምህርታችን ደግሞ ንኡስ አንቀጽ እና ቦዝ አንቀጽ ያላቸውን መሠከዕ፣ ቅርጽ፣ ጠባይ እና አገልግሎት እንመለከታለን:: ለማስታወስ ያህል ዐቢይ አንቀጽ ያሏቸውን የባለፈትን ትምህርታት ማዘከር እናስቀድማለን::*

## ቦዝ አንቀጽ /Gerund/

ቦዝ አንቀጽ በራሳቸው ነገርን ሰብስበው ከማያስሩ፣ ከማይጠቀልሉ የንኡሳን አናቅጽ ክፍል የሚመደብ ሲሆን የነገሩን መኾን፣ መከናወን፣ መከሠት ..... ያለማሰር ጠቁሞ ነገሩን /ሐረጉን/ መቋጨት፣ መፈጸም ግን ተስኖት ለተቀዳሚው ወይም ለተከታዩ ቃለ አንቀጽ /ማሰሪያ አንቀጽ የተገዛ፣ የተጠበቀ...... ነው::

ምሳሌ:-

በአማርኛ - በላ

| ተውላጠ ስም | ገባሪ/ደራጊ | አግባሪ-አድራጊ፣አስደራጊ |
|---|---|---|
| እኔ | በልቼ | አብልቼ፣ አስበልቼ |
| አንተ | በልተህ | አብልተህ: አስበልተህ |
| አንቺ | በልተሽ | አብልተሺ: አስበልተሽ |
| እናንተ | በልታችሁ | አብልታችሁ፣ አስበልታችሁ |
| እናንቺ /እነ አንቺ/ | በልታችሁ | አብልታችሁ: አስበልታችሁ |
| እኛ | በልተን | አብልተን፣ አስበልተን |
| እሱ | በልቶ | አብልቶ: አስበልቶ |
| እሷ | በልታ | አብልታ፣ አስበልታ |
| እነርሱ | በልተው | አብልተው፣ አስበልተው |
| እነርሷ | በልተው | አብልተው፣ አስበልተው |

ማስታወሻ:- «በልቼ» የሚለው ቃል ያልተቋጨ፣ ያልተፈጸመ በመጀመሪያ የተደረገ ድርጊት ሲሆን /ሲመስል በራሱ ጊዜን/ tense የማይገልጽ ከመብላት በኋላም ምን እንደሚሆን፣ እንደሚያደርግ በተስፋ፣ ባልተፈጸመ ነገር የሚጠብቅ ነው:: በልቼ መጣሁ ፣ እመጣለሁ፣ አልመጣም.... ሊሆን ይችላል:: በልማዳዊ ንግግር ግን «በልቼ» ሲባል በልቻለሁና አልበላም ይመስላል:: «አብልጬ» ብል አብልጬ እወደዋለሁ ወይም እጠለዋለሁ ሊሆን ይችላል:: በልቼም - «በልቼ አላውቅም» ቢባል ምን ሊያግደው ይችላል? አንዳንዴ አሉታንም ያመለክታልና:: ምሳሌ:- በሊዖ /በልቶ/ ሖረ /ሔደ/ ሳይሠራ፣ ሳያገለግል፣ ሳይከፍል ..... ወዘተ::

### ቦዝ በግእዝ

ቦዝ በግእዝ ከላይ የጠቀስናቸውን የአማርኛ መንገዶች የሚመስል እና አንዳንድ የራሱን ቅርጽ እና ለየት ያሉ ዐመሎች ይከተላል::

በልዐ = በላ      በሊዕ/በሊዖት = መብላት

*፩. በዐሥሩ መራሕያን*

| | | | |
|---|---|---|---|
| አነ | በሊዕየ፣...... | በልቼ፣........ | (I) having eaten,....... |
| አንተ | በሊዐከ፣...... | በልተህ፣..... | (you) having eaten,...... |
| አንቲ | በሊዐኪ፣...... | በልተሽ፣..... | (you)having eaten,... |
| አንትሙ | በሊዐክሙ፣... | በልታችሁ፣... | (you) having eaten,... |
| አንትን | በሊዐክን፣.... | በልታችሁ፣.... | (you) having eaten,..... |
| ንሕነ | በሊዐነ፣...... | በልተን፣........ | (We) having eaten,.......... |
| ውእቱ | በሊዖ፣....... | በልቶ፣........ | (He) having eaten,.......... |
| ይእቲ | በሊዓ፣..... | በልታ፣..... | (She) having eaten,.......... |
| ወእቶሙ | በሊዖሙ፣... | በልተው፣... | (They) having eaten,.......... |
| ውእቶን | በሊዖን፣.... | በልተው፣.... | (They) having eaten,.......... |

*ምሳሌ፦*

| | |
|---|---|
| በሊዕየ መጻእኩ = በልቼ መጣኹ | having eaten, I came, I had come |
| ተንሢእየ ሖርኩ = ተነሥቼ ሔድኩ | having risen, I went, I had gone |
| በሊዐነ መጻእነ = በልተን መጣን | having eaten, I came, I had come |

## የእስልምና እና ...

ከገጽ ፲፩ የዞረ

አክራሪዎች ከሚያነሡት ሐሳብ ብን ጀምር እንኳ ምንም ይባል ምን ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያና ጅማ ራሱ በግልፅ በታሪክ መድረክ እንደተዘገበው ከግራኝ ወረራ አስቀድሞ ጥንቱኑ፤ በኋላም አብያተ ክርስቲያናት የተተከሉበት የክርስቲያናዊው ደጋማ የዐፄ ግዛት መንግሥት የነበረ መሆኑ በራሳቸው በእስላም የታሪክ ጸሐፊዎች ብቻ ሳይሆን በግራኝ አሕመድ ታሪክ ጸሐፊም ጭምር ተመዝግቦአል:: /Arab-Fagih, Historire de la conqete de Abyssinie XVI Sicle, tr. anded by F. Basset (1987) PP. 222-227 see specially the letter of Ras Wasen Seged to Gran.)

ነገሩ ይህ ከሆነ ታዲያ በሽብር ቡድኖች እየታገዙ በእስላም ኅብረተሰብ ጉያ ከላይ እስከ ታች ተመሳስለውና ተዋሕደው ሓላፊነት የጎደለውና በወንጀል የረከሰ ሰብእናቸውን በኢትዮጵያ ላይ ሊፈጽሙ እንደማይችሉ ራሱ የእስላሙ ኅብረተሰብ፣ መንግሥትና ሌላውም ሊያሳያቸው ይገባል:: ስለሆነም ጠቅላላ የእስልምና ጉዳዮች ጽ/ቤት ያስተላለፈው ውግዘት እንደሚያስመሰግነው እየመሰከርን በክልሉና በሌላም ቦታ አክራሪነትን የሚያስፋፉትን ኀይሎች እጅ ይዞ እንዲሰጥ ጥብቅ የሆነ ሰላማዊ ጥሪያችንን በዚሁ አጋጣሚ ሳናስተላልፍ አንቀርም:: ውግዘቱ ከልብ ነበር ማለት የሚቻለውም ያን ጊዜ ነውና::

ዛሬ ላይ ቆመን ስንመለከት ከተከሰቱት ፖለቲካዊና መልክአ ምድራዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች አንጻር መንግሥት ከአክራሪዎች ጋር የሚያደርገው ፍጥጫ ለአገሪቱ ወሳኝ ምእራፍን ይከፍታል፤ ከፍቷልም:: ስለዚህ አሁንም አፋጣኝ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ ያለበት መሆኑን የሚያሳዩ ነገሮች አሉ::

ውጤቱ ሽብርና ጭፍጨፋ የሆነው አክራሪነት ከአሁን ቀድሞ በነበረው መልክ
ቢቀጥል ምን ይፈጠራል? የሚለውን ማጤ
ንም ወሳኝ ነጥብ ነው:: በግልጽ ሰው
አፉን ሞልቶ ሊናገር የሚችለው ነገር
ቢኖር መንግሥት የመሠረተውን ገዢውን
ፓርቲም ሆነ ሰፊውን ሕዝብ ለጉዳት
እንደሚያጋልጡ ግልጽ ነው:: የሽብር
ጭፍጨፋዎች በሕገ መንግሥቱ የተደነገ
ገውን አንቀጽ ፳፰ የሚጻረሩ በመሆና
ቸው ሕዝብ በመንግሥት መዋቅር ሊያ
ገኝ የሚገባውን ሰብአዊ መብትና ፍትህ
ያጣል:: ይህ ደግሞ ወደ ሥርዓት አልበ
ኛነት ሌላ አደጋም ሊያመራ የሚችል አቅም
/Potential/ አለው:: ድርጊቱ ዓለም አቀፍ
ወንጀል በመሆኑ በዓለም አቀፍ ፍርድ
ቤት ድረስ ሊታይ ያስችለዋል:: ዓለም
አቀፍ የሆነው የሽብር ወንጀል ፈጻሚ
ዎችም ካልጠፉ ነገ ጠዋት በሶማሌና
በሌላው ያሉትን አጋሮቻቸውን የሚቃወ
መውን መንግሥት ሳይጉዱ ይተኛሉ ማለት
ዘበት ነው:: ውሎ ሲያድር ደግሞ በዓለም
ላይ የታዩትን የዩጐዝላቪያ ፩ኛው ዓለም

ወደ ፴፱ ገጽ ይዞራል





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ማስታወሻ፦ በሊዕየ = በልቼ እንደ አማርኛው በግእዙ በልማዳዊ ንግግር በልቻለሁ ሊባል ይቻላል:: እንደ ሁኔታው::

*፪. ቦዝ ከቀዳማይ አንቀጽ ጋር*

ኀደገ = ተወ ሖረ = ሔደ

| | | | |
|---|---|---|---|
| አነ | ኀዲግየ | ሖርኩ | having left, I went |
| አንተ | ኀዲገከ | ሖርከ | having left, You went |
| አንቲ | ኀዲገኪ | ሖርኪ | having left, You went |
| አንትሙ | ኀዲገክሙ | ሖርክሙ | having left, You went |
| አንትን | ኀዲገክን | ሖርክን | having left, You went |
| ንሕነ | ኀዲገነ | ሖርነ | having left, We went |
| ውእቱ | ኀዲጎ | ሖረ | having left, He went |
| ይእቲ | ኀዲጋ | ሖረት | having left, She went |
| ውእቶሙ | ኀዲጎሙ | ሖሩ | having left, They went |
| ውእቶን | ኀዲጎን | ሖራ | having left, They went |

ፈቀደ = ፈለገ፣ ወደደ

መጽአ = መጣ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፈቂድየ | መጺእኩ | ወድጄ መጣሁ | = having liked, I came |
| ፈቂደከ | መጺእከ | ወድደህ መጣህ | = having liked, you came |
| ፈቂደኪ | መጺእኪ | ወድደሽ መጣሽ | = having liked, you came |
| ፈቂደክሙ | መጺእክሙ | ወድዳችሁ መጣችሁ | = having liked, you came |
| ፈቂደክን | መጺእክን | ወድደን መጣችሁ | = having liked, you came |
| አፍቀረ | አፈቀረ፣ | ወደደ | = having liked, you came |
| አፍቂርየ | ተሰቀልኩ: | ወድጄ ተሰቀልኩ | = having liked, you came |
| አፍቂርየ | አውሰብኩ፣ | ወድጄ አገባሁ | = having liked, you came |

*፫. ቦዝ ከካልአይ አንቀጽ ጋር*

ወድቀ = ወደቀ ተንሥአ = ተነሣ

| | | | |
|---|---|---|---|
| አነ | ወዲቅየ | እትነሣእ | =ውድቄ፣ ከወደቅኩ በኋላ እነሣለሁ |
| አንተ | ወዲቀከ | ትትነሣእ | |
| አንቲ | ወዲቀኪ | ትትነሥኢ | |
| አንትሙ | ወዲቀክሙ | ትትነሥኡ | |
| አንትን | ወዲቀክን | ትትነሥአ | |
| ንሕነ | ወዲቀነ | ንትነሣእ | |
| ውእቱ | ወዲቆ | ይትነሣእ | |
| ይእቲ | ወዲቃ | ትትነሣእ | |
| ውእቶሙ | ወዲቆሙ | ይትነሥኡ | |
| ውእቶን | ወዲቆን | ይትነሥአ | |

ሰገደ = ሰገደ ዘመረ = አመሰገነ /ቀደሰ ቤት/

| | | |
|---|---|---|
| አነ | ሰጊድየ | እዜምር |
| አንተ | ሰጊደከ | ትዜምር |
| አንቲ | ሰጊደኪ | ትዜምሪ |
| አንትሙ | ሰጊደክሙ | ትዜምሩ |
| አንትን | ሰጊደክን | ትዜምራ |
| ንሕነ | ሰጊደነ | ንዜምር |
| ውእቱ | ሰጊዶ | ይዜምር |
| ይእቲ | ሰጊዳ | ትዜምር |
| ውእቶሙ | ሰጊዶሙ | ይዜምሩ |
| ውእቶን | ሰጊዶን | ይዜምራ |

*፬. ቦዝ ከትእዛዝ አንቀጽ ጋር*

አርመመ = ዝም አለ ሖረ = ሔደ

| | | |
|---|---|---|
| አነ | አርሚምየ | እሑር |
| አንተ | አርሚመከ | ሑር |
| አንቲ | አርሚመኪ | ሑሪ |
| አንትሙ | አርሚመክሙ | ሑሩ |
| አንትን | አርሚመክን | ሑራ |
| ንሕነ | አርሚመነ | ንሑር |
| ውእቱ | አርሚሞ | ይሑር |
| ይእቲ | አርሚማ | ትሑር |
| ውእቶሙ | አርሚሞሙ | ይሑሩ |
| ውእቶን | አርሚሞን | ይሑራ |

## የእስልምና እና ... ከገጽ ፴፰ የዞረ

ጦርነት እና የአርሜኒያን ዐይነት ቀውስ ብሎም በአገራችን የግራኝን የመሰሉ ሁኔታዎች በቀላሉ ሊፈጥር ይችላል። በዘመናችን በጣም በተቀራረበው ዓለም /Globalized Structure/ ካየነው ደግሞ ወደ አፍሪካ ቀንድ ከዚያም ወደ ክፍለ ዓለማት ብሎም በአስጊ ደረጃ ወደ ዓለም ሁከት ሊሸጋገር የሚችል ዓላማና ኀይል ያለው የወንጀል ሰንሰለት መሆኑ አሌ የማይባል የአደባባይ ምስጢር ነው:: «አስደንጋጭ የጥፋት እቅድ» ዘመን ቁጥር ፳፫ መስከረም ፲፱፻፺፱፣ ኢ.ፕ.ድ. ገጽ. ፮-፲፫/

የእስልምና አክራሪ የሽብር ቡድኖች ሳይበደሉ እንደተበደሉ ሳይጨቆኑ እንደ ተጨቆኑ አድርገው የሚያራግቡትና የሚሰብኩት ትምህርት /አንዳንዴ የሐሰት ፊልም ሁሉ በማቀነባበርና በመሥራት ማሰራጨቱ ከቀጠለ ወደፊት የሚያደርሰውን አስከፊ ጉዳት ከአሁኑ መተንበይ ይቻላል:: see Daily monitor newspaper (vol.XIV-No.13 Jan 15,2007) "Egypt seizes al-Jazeera reporter."p.2/ ይህም ሁናቴ አሁን በምንኖርበት ዓመት ምሕረትና ዐሥርት ዓመታት ያቀዱት ግባቸው መሆኑ ግልጽ ነው:: ይህንን ድርጊታቸውን እያቀጣጠሉ ወደ ጭፍጨፋ ሲያመሩ በተደጋጋሚ አይተናል:: መላው ክርስቲያንም «የሚሠሩትን አያውቁም ...» በማለት አምላኩን መስሎአል:: /ሉቃ.፳፫፥፴፬/

አክራሪ እስላሙ ጥፋቱን ለመሸፋፈን ባቋቋማቸው ተቋማት የሚናገረው ድርጊት ደግሞ ሌሎች ሁኔታዎችን እንድናጤን የሚገፋፋ ነው:: ወደ እስልምና ያልዞሩትን ክርስቲያኖች ሕገ ወጥ ሰፋሪ ናቸው፣ ... ሌላም ሌላም ናቸው በማለት ለማስወጣት መጣር አሁንም ችግሩን በጊዜና በሁኔታ የሚያሰፋው እንጂ መፍትሔው አይደለም:: እስከሰለሙ ድረስ ባለሀገሮች የሚሆኑበት እስካልሰለሙ ድረስ ሕገ ወጥ ሰፋሪ የሚሆኑበት የሕግ መሠረትም መቅረብ ይኖርበታል:፣ ሕግና መንግሥት ባሉበት ሀገር ላይ እነዚህን ነገሮች መፈጸም ለሀገርና ለሕዝብ የሚጥለውን ታሪካዊ የጥፋት መሠረት አርቆ ካለማየት ከሆነም ተመልሶ ራስን ለመፈተሽ አሁንም በቂ ጊዜ አለ:: አክሱምንና ላሊበላን በማንሣት የተጨቆኑ ለመምሰል እንደ ጅራፍ ራስ ገርፎ ራስ ከመጮኽ በፊት በእነዚህ ክርስቲያኖች ላይ የሚያደርሱትን ግፍ አቁሞ ሕጋዊ በሆነ መንገድ አብሮ ለመኖር መጣር የተሻለው መንገድ ነበር:: እሳትን አንድዶ የጠላቶቼን ቤት ብቻ ምረጥ ማለት አይቻልም:: ከነደደ በኋላ የራስን ቤትም ማዳን አይቻልምና:: ስለዚህ ወደ ጥንቱ መመለስ የሚጠበቅ መሆኑን በመጠቆም የጋራ ሓላፊነታችን ለመወጣት ማሳሰብ ከሁሉም ወገን ምሁራን የሚጠበቅ ይሆናል:: ይህ ካልሆነ ግን በተፈጠረው ሁኔታ የቆሰለው የክርስቲያኑ ልብ ተደራራቢ ክስተቶችን በአስተውሎት ከተረዳ በኋላ ተፈጥሮአዊ ሰውነቱ አስገድዶት ለሚያነሣው አጸፋ ተጠያቂው አሁንም ነገር ቀስቃሾች መሆናቸውን ከወዲሁ ሊረዱት የሚገባ ጉዳይ ነው::✦

ተፈጸመ

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

*ማስታወሻ፦*

ከዘንድ አንቀጽ ጋር ብቻ አይመችም:: አይቻልም:: አያስኬድም:: ከንኡስ አንቀጽ ጋር ግን እንደ ልማዳዊ ንግግር ልናስኬደው እንችላለን:: እንጂ ግእዛዊ ሕጋዊነት አይታይበትም:: አማርኛ ዝም ብየ መምጣት፣ በልቼ መሔድ:: ዞሮ ዞሮ ማሰሪያ የለ ውምና:: በዘንድም ቢሆን በልማዳዊ ንግግር መጺአ ይሑር መጥቶ ይሒድ ዘንድ ....:: ማለት ይቻላል:: ሌላ ግስ ያስፈልገዋል እንጂ::

*፭. ቦዝ ዝርዝር /ሳቢ ሲሆን*

በግእዝ ዝርዝር የሚያናግሩ ግሶች በቦዝም ጊዜ መሳባቸውን ሳይለቁ ተሳቢውን ቃል በሕጉ መሠረት ሳድሱን ወደ ግእዝ፣ ካእቡን ወደ ሳብዕ፣ ሣልሱን በመለወጥ ወደ ኀምስ ራብዑን፣ ኀምሱን፣ ሳብዑን ራሳቸውን አስችለው ይረባሉ፣ ይጸፋሉ::

ምሳሌ፦

| | | |
|---|---|---|
| ኀደገ | = | ተወ |
| ኀዲጎ ተስዐ | = | ዘጠናውን ትቶ |
| አፍቂሮ ብእሲቶ | = | ሚስቱን ወዶ |
| ሰቂሎሙ አምላኮሙ | = | አምላካቸውን ሰቅለው |
| ተዋሒዶ ሰብአ | = | ሰውን ተዋሕዶ |
| ለቢሶ ሥጋ | = | ሥጋ /ን/ ለብሶ |
| መኒኖ ዓለመ | = | ዓለምን ንቆ |

*፮. ቦዝ ቸልታ ኾኖ ሲቀር*

ቦዝ ቸልታ ኾኖ ሲቀር ስንል ኹለት ተቃራኒነት ያላቸው ግሶች /ቃላት አንዱ ቦዝ ኾኖ ተሸንፎ፣ ብላሽ፣ አላስፈላጊ ኾኖ ሲቀርና ሁለተኛው ግን የነገሩ መቋጫ፣ አሸናፊ ውጤት /ተቃራኒ/ ሲሆን ነው:: ቦዝ የኾነው ምን ጊዜም የተጻፈ ግዱፍ ምንም የማያ መጣ የማይጸና መኾኑን ያሳያል::

ምሳሌ፦

| | | |
|---|---|---|
| መዊቶ ሐይወ | = | ሞቶ ዳነ |
| ቀዲሖ ከዐወ | = | ቀድቶ አፈሰሰ |
| ወዲቆ ተንሥአ | = | ወድቆ ተነሣ |
| አሚኖ ክህደ | = | አምኖ ካደ |

*፯. አእመረ = ዐወቀ አእምሮ/አእምሮት = ማወቅ*

ቀዳማይ ንኡስ አንቀጽ

ንኡስ አንቀጽ /Infinitive

| | | | |
|---|---|---|---|
| አነ | አእምሮትየ | ማወቄ | my knowing |
| አንተ | አእምሮትከ | ማወቅህ | your knowing |
| አንቲ | አእምሮትኪ | ማወቅሽ | your knowing |
| አንትሙ | አእምሮትክሙ | ማወቃችሁ | your knowing |
| አንትን | አእምሮትክን | ማወቃችሁ | your knowing |
| ንሕነ | አእምሮትነ | ማወቃችን | our knowing |
| ውእቱ | አእምሮቱ | ማወቁ | his knowing |
| ይእቲ | አእምሮታ | ማወቋ | her knowing |
| ውእቶሙ | አእምሮቶሙ | ማወቃቸው | their knowing |
| ውእቶን | አእምሮቶን | ማወቃቸው | their knowing |

ዑቀትየ = አእምሮ/ትየ = my knowledge ከዚህ በላይ ቦዝ ሳይሆን ጥሬ ዘር ነው::

*ቦዝ /Gerund/*

| | | | |
|---|---|---|---|
| አነ | አእሚርየ | ዐውቄ | (I) having known |
| አንተ | አእሚረከ | ዐውቀህ | (you having known |
| አንቲ | አእሚረኪ | ዐውቀሽ | (You) having known |
| አንትሙ | አእሚረክሙ | ዐውቃችሁ | (You) having known |
| አንትን | አእሚረክን | ዐወቃችሁ | (You) having known |
| ንሕነ | አእሚረነ | ዐውቀን | (We) having known |
| ውእቱ | አእሚሮ | ዐውቆ | (He) having known |
| ይእቲ | አእሚራ | ዐውቃ | (She) having known |
| ውእቶሙ | አእሚሮሙ | ዐውቀው | (They) having known |
| ውእቶን | አእሚሮን | ዐውቀው | (They) having known |

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

*ይቆየን*

*ለራስ ጥቅም ...* 

ተባብረው አሳይተውናል:: ስለዚህ ራስ ወዳድነትን፣ ስግብግብነትንና አጉል ብል ጣብልጥነትን ወደ ጎን ትተን በፍጹም ፍቅር ሌሎችን ለማስቀደም እንሞክር:: የእኛ ጥቅም የሚጠበቀው እንዲህ ሌሎችን ስናስ ቀድም ነውና::

እግዚአብሔር ሁላችንንም እርስ በርስ አንድ ሊያደርገን ስለ ወደደ በአንዱ ጥቅም ላይ የሌላውም ጥቅም እንዲመሠረት አደረገ፤ ዓለሙ በሙሉ እንዲህ ባለ ሁኔታ የተ ያያዘ ነውና:: በተግባረ እድና በጥበባት ሥራ ዎች፣ በንግድና በግብርና፣ በውትድርናና በሌሎችም ሥራዎች ሁሉ የራሱን ጥቅም ለማግኘት አስቀድሞ ሌሎችን መጥቀም ይኖ ርበታል:: ለሌሎች ሳያስብና የሚጠቅማቸ ውን ነገር ሳያደርግ ራሱን ሊጠቅም የሚችል የለምና:: ገበሬው ለራሱ የሚበቃውን ብቻ አያመርትም፤ ለሌሎችም እንዲተርፍ አድ ርጎ የቻለውን ያህል ያመርታል እንጂ:: ወታ ደሩም ራሱን ለማ ዳንና ለመጠበቅ ሳይሆን አገሩንና ሕዝቡን ለመጠበቅ ራሱን ለአደጋ ያጋልጣል:: ለሌ ሎች ሲል የራሱን አካልና ሕይወት ለሞት ሳይቀር አሳልፎ በመስ ጠቱ ይሸለማል:: ይህን ካላደረገ ግን የሚ ሸለምበትና የሚከበርበት ምክንያት የለም:: ነጋዴውም ቤቱ የሚያመጣውና የሚገ ዛው ለራሱ የሚበቃውን ብቻ ሳይሆን ለሌ ሎች የሚሸጠውንም ነው:: ደንበኞቹን የማይጠቅም ነጋዴ ከትንሽ ጊዜ በላይ ነጋዴ ሆኖ ሊቀጥል አይችልም:: እንግዲህ ገበሬውም ሆነ ነጋዴው፣ ወታደሩም ሆነ ሌላው ራሱ የሚጠቀመው ለሌላው በሚያደርገው ጥሩ ነገር አንፃር ነው ማለት ነው:: «እያንዳ ንዱ ሰው ይህን የሚያደርገው ለሌላው አስቦ ሳይሆን ለራሱ ብሎ ነው» የሚል ይኖራል:: አዎ፣ ትክክል ነው:: ለሌሎች በማድረጉ ራሱ የማይጠቀም ቢሆን ኖሮ ለሌሎች መልካም ለማድረግ የሚያነሳሳው በቂ ምክንያት አይኖረውም ነበር:: ሰዎች እንዲህ ያለ ሁኔታ ባይኖርባቸው ኖሮ የሌ ላውን ጥቅም ለማሰብ ሕሊናቸውን አያነሳ ሱም ነበርና:: ስለዚህ እግዚአብሔር በመለ ኮታዊ ጥበቡ ነገሮችን እንዲህ አንድ አድ ርጎ አስተሳስሮአቸዋል:: በመጀመሪያ የሌ ሎችን ጥቅም ካላሰቡና ካላደረጉ በስተቀር ከራሳቸው ጥቅም እንዳይደርሱ አድርጓልና::

ስለዚህ ሲሆን ለሌሎች ካለን እው ነተኛ ፍቅር የተነሣ የእነርሱን ዕድገትና መልካም ነገር ማግኘት እናስቀድም:: ነገር ግን ምናልባት አስተሳሰባችን ለዚህ ደረጃ ካልደረሰልንም ቢያንስ ለራሳችን ጥቅም ስንል ሌሎችን እናስቀድም:: እኛ ለሌሎች በእውነት ስናስብ እግዚአብሔር ደግሞ ለእኛ ያስባል:: አብርሃም ለሎጥ ሲያስብ እግዚአብሔር ደግሞ ለእርሱ እንዳሰበለት ማለት ነው:: እኛ የሌሎችን ጥቅምና መል ካም ነገር ስንመኝና ስናስብ እግዚአብሔር ይህንኑ እንዲያውም በበለጠ ለእኛ ያደርግ ልናል:: እኛ ለሌሎች ግድ ሳይኖረን ለራሳ ችን ብቻ ካሰብን ግን እግዚአብሔር ላያ ስብልን ይችላል:: «ናሁኬ ኢኮነ ለዘበደረ ወለ ዘሮጸ - እንግዲህ ለሮጠ ወይም ለቀደ አይ ደለም» ተብሏልና:: ሮሜ ፱፥፲፮::ቁ

*ተፈጸመ*

*ዋቢ ድርሳን - የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ የቀዳማዊ ቆሮንቶስ መልእክት ትርጓሜ*



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# «የሰው ቫይረስ ...»

እንደምን ከረማችሁ። እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ። አሁንም እንደ ልማዴ እጓዛለሁ የት ደርሰሃል አትበሉኝ። የገጠመኝ ግን ሳላጫውታችሁ። መንገድ የለመደው እግሬ ያለማረፍ ሲጓዝ ሰሞኑን አንድ የኮምፒዩተር ባለሙያ ጋር አገናኘኝና ራሱን አስተዋውቆኝ መጓዝ ጀመርን። የት ትሔዳለህ? አልኩት። እርሱም አንድ የወዳጆቼ ኮምፒዩተር በቫይረስ ምክንያት አልሠራላቸው ስላለ እርሱን ለማስለቀቅ መድፍነ ቫይረስ /Anti Virus/ ልጭንላቸው እሔዳለሁ አለኝ። ሁልጊዜም አእምሮዬ ውስጥ እየተመላለሰ ያልተረዳሁት ነገር ስለነበር ባለሞያውን በማግኘቴ ደስታ እየተሰማኝ ምንነቱን እንዲያስረዳኝ ጠየቅሁት።

«የኮምፒዩተር ቫይረስ ማለት በሰውና በእንስሳት ላይ በሽታን እንደሚያመጡት ሕዋሳት ያለ ነገር አይደለም ...» ባለሞያው ማስረዳት ጀመረ። ታዲያሳ ምንድን ነው? «ይህ በሰዎች የሚፈጠር ወይም የሚሠራ የኮምፒዩተር ፕሮግራም /Software/ ነው።» ታዲያ እንደዚህ ከሆነ ኮምፒዩተሩን እንዳይሠራ የሚያደርገው /በሽተኛ የሚያደርገው/ እንዴት ነው? የኔ ጥያቄ ነበር። ባለሞያው በእኔ የጨዋ ጥያቄ እየሳቀና እየተገረመ በርጋታና በፈገግታ ወደ አፉ ቀድመው የሚመጡ የእንግሊዝኛ ቃላትን ወደ ኋላ እየመለሰ በሚችለው አማርኛ እየተረጐመና መረዳታቸው በመታወቁ ለአማርኛ በቀረቡ ቀላል የእንግሊዝኛ ቃላትም ጭምር ማስረዳቱን ቀጠለ።

ይህ «የሚያስቸግረው እንዲህ ነው። እኛ ኮምፒዩተሩን አንድ ነገር እንዲሠራ ስናዝዘው፣ ቫይረሱ ደግሞ እንደነገሩኩህ ፕሮግራም ነውና ሌላ ሥራ ይፈጥርለታል። በዚህ ጊዜ እኛ ያዘዝነውን ትቶ በሌላ ነገር ሲደክም ስለሚውል እኛ የምንፈልገውን አይሠራልንም። እንደገናም ለማስተካከል ሌላ ትእዛዝ ብንሰጥ አሁንም ቫይረሱ ሌሎች ሥራዎች ስለሚጨምርበት ኮምፒዩተሩ እንደኛ የበለጠ እየተንቀረፈፈ፣ አስቸጋሪ እየሆነ ይሔድና ይሔን መድፍነ ቫይረስ /Anti virus/ ካልጫንበት ሥራ መሥራት ወደማይችልበት ደረጃ ይደርሳል። በአጭሩ ይህን ይመስላል» አለኝ ባለሞያው። የኮምፒዩተር ባለሞያዎች የሆናችሁ ከነገረኝ የዘለልኩት ወይም በደንብ መግለጽ ያልቻልኩት ቢኖር እንዳትቀየሙኝ። ጉድለቱ ከእኔ መረዳት ነውና ይቅር በሉኝ። በእኔ መረዳት ግን ቫይረሱ እንዲህ ስለማይመስለኝ በእጅጉ ተገርሜ ይኸማ «ሰው ነው» በለኛ አልሁት። እናንተስ ምን ትሉታላችሁ? የእናንተን እንጃ እኔ ግን ሰውን ይመስላል ያልሁብትን ላስረዳ።

ባለሞያው እንደ ነገረኝ ኮምፒዩተሩ በጤና የሚሠራ ፕሮግራም፣ የሚታመምበት ቫይረሱም፣ የሚድንበት መድፍነ ቫይረሱም ሁሉም ፕሮግራሞች በሰው የተሠሩ ሶፍትዌሮች /software/ እንደሆኑት ሁሉ ይህ በእግዚአብሔር የተፈጠረው ሰውም ሦስት ዓይነት ይመስለኛል። የመጀመሪያው ሥራውን በአግባቡ በሰላም፣ በመግባባት፣ በትጋትና በታማኝነት የሚሠራው ነው። ሁለተኛው ደግሞ ይህን የሚሠራውን ሰው የሚያውክ በመረበሽ ሌላ ሥራ የሚፈጥር፣ ትጋትን የሚያስተጓጉልና ሰላምን በመንሣት የሠራተኞችንም የሥራ መንፈስ የሚያጠፋው ነው። ይህ ሰው በየመሥሪያ ቤቱ መኖሩ ደግሞ ከሁላችሁም የተደበቀ አይደለም። ሦስተኛውም ቢሆን ቁጥሩ ትንሽ ይሆናል እንጂ እነዚህን ቫይረስ መሰል ጠባይ ያላቸውን ሰዎች ለማጽዳትና ሥራ ለማሠራት የሚጥሩ መድፍነ ቫይረስ /አለቆች/ መኖራቸው የታወቀ ነው። እኔን የገረመኝ ደግሞ አንዳንዱ የኮምፒዩተር ቫይረስ መድፍነ ቫይረሱን ለማስጮኼን እንኳን የሚያስቸግር /አላስገባም የሚል/ መሆኑ ነው። በአለቃ ዘመዳቸው /በባላቸው፣ በሚስታቸው፣ በወንድማቸው፣ በአጎታቸው፣ .../ ተመክተው ማንም አይቅረበኝ አትንኩኝ የሚሉት ሰዎች አይመስሉም?

እኔ መንገደኛው ወንድማችሁ በሕይወቴ የቀሩብኝ ነገሮች እንዳሉ በውል የተረዳሁት በዚህ ቀን ነበር። ተምረውት የማይጠቅምና በዚያም ራስን እያዩ ራስን ለማስተካከል የማይረዳ ነገር እንደ ሌለ እያወጣሁ እያወረድሁ በኅሊናዬ ሰጠምኩ። ከዚህ በኋላ ባለሞያውን አልሰማሁትም። በኮምፒዩተሩ ላይ የሚጭነውን በእኔ ላይ ጭኖታልና እኔም የራሴን ጭንቅላት ማጽዳት /Clean ለማድረግ/ ጀመርኩ።

ቀስ እያለ ነገሮች ግልጽ እያሉ ይታዩኝ ጀመር። በጸሎት የሚተጉትን ለማዘግየት ሰይጣን የሚፈጥረውን አሰብኩ። መላእክት ደግሞ መድፍነ ቫይረስ /ሰይጣን/ መሆናቸው ነው አልኩኝ። የመጀመሪያ ትርጓሜ። በዚህ ግን መቀጠል አልቻልኩም። ለምን ሰይጣን ላይ ቸኩልኩበት። በርግጥ እንደ ኮምፒዩተሩ ቫይረስ ሰዎች ሥራ ላይ እንደ ዕርጎ ዝንብ ጥልቅ ብለው ዝግየታ የሚፈጥሩ የሰው ቫይረሶች አይኖሩ ይሆንን? የባለሞያውን ገለጻ ማስታወስ ጀመርኩ። ቫይረስ ማለት ለዚሁ ተብሎ የተሠራ ራሱን የቻለ ፕሮግራም። በእውነት ይገርማል። ሙሉ ሰው ሆነው ተፈጥረው ሥራቸው ሥራ የሚሠራውን ሰው ማደናቀፍ የሆኑትን ምን እንበላቸው? በበጎው ሥራ አንጻር ሌላ ሥራ የሚፈጥሩልንንስ? ለአንዱ የመልካም ሥራ ትእዛዝ ዐሥር የማዘግያ ትእዛዝ በራሳቸው የሚያዥጎደጉዱልንንስ?

ባለሞያው እንደ ነገረኝ ቫይረስ በኮምፒዩተሩ ያሉ መረጃዎችን ሁሉ ያጠፋል። ታዲያ በየመሥሪያ ቤቱስ ሰነድ የሚያጠፋ፣ ካዝና የሚሠረሥሩ፣ ፋይል የሚያጠፉ ስንት አሉ? አቤት እግዚኦ! እንደዚህማ ከሆነ የሰው ቫይረስ ሳይበልጥ ይቀራልን? እንዲህ ዓይነት የሰው ቫይረሶች የሌሉበት መሥሪያ ቤትስ ይኖር ይሆንን? ሂደ መንገደኛው ልቤ ተጓዝ ንጉደ፣ የባለሞያውን ገለጻ እያስታወሰ። ባለሞያው ቫይረስ ፎቶ፣ ሥዕል እንኳን ቢኖር መልኩን ይለውጠዋል፣ ማንነቱን ያጠፋብሃል ብሎኝ ነበር። ሰውስ እንዲህ ያደርግ የለምን? የሰዎችን ሥራቸውን ጥላሸት ቀብቶ የሚሸለሙበትን እንዲገደሉበት፣ መታየት የሚገባውን እንዳይታይ የሚያደርግ ስንት አለ? በትንሿ አቅሜ እያወጣሁ እያወረድሁ በየመሥሪያ ቤቱ ስገባ ቫይረሱ እየበዛብኝ ተቸገርሁ። በእውነት የሀገራችን እድገት ፈቅ ያላለው ለካ የሚሠሩ ሰዎች ጠፍተው ሳይሆን የሚያዘገዩትና የብልጽግና ፋይሎችን እያጠፉ በድህነት ፋይል የሚተኩ ቫይረሶች በመኖራቸው ነው። እውነት ነው የሚፋጠኑ ሰዎች አልጠፉም፣ የሚያዘገዩት ቫይረሶች ግን በጥቁር በዝተው ከሥራ አቀመዋቸዋል። የእውነት ውሎችና ስምምነቶች፣ ለብልጽግና በር የሚከፍቱ የትጉሃን ባለሞያዎች ጥናቶችም ተሠርተው ተቀምጠው ነበር። ነገር ግን ቫይረሶቹ እነዚህን እያጠፉ እነርሱ በተሠሩበት ፕሮግራሞች የሚሠሩ የሐሰት ውሎችን፣ ሰነዶችንና ጥናቶችን ተክተውባቸዋል። ኮንትራቱን ለመስጠት፣ የጨረታውን አሸናፊ ለመለየት፣ «ተገናኝተን ካልተነጋገርንበት እንቸገራለን» የሚሉትንስ ምን ዓይነት ቫይረስ እንበላቸው? ከፈቀዱ በኋላስ የጥናት ለውጥ ሲመጣ ምን ያህሉን ለእኛ ትፈቅዳላችሁ እያሉ ከተቋረጮች ጋር እየተደራደሩ የደሃይቱን ሀገር ገንዘብ እንደ ምስጥ አፈር የሚያደርጉትንስ? ሥራቸውን ሠርተው ለክፍያ በሚመጡበት ጊዜ ለእኔ «ይህን ያህል ካልተሰጠኝ ገንዘቡ አይለቀቅም» የሚለው የሒሳብ ባለሞያስ?

የባንክ ቤት አካባቢው ደግሞ ለየት ይላል ይባላል። አንዳንዱማ በፕሮጀክቱ ዓይነት ነው የሚቀበለው። ፕሮጀክቱ አትራፊ ከሆነ ሃያ በመቶ፥ ለይስሙላና ለገንዘብ ማውጫ ብቻ ከሆነና ማስያዣውን ባንኩ እንዲወርሰው ከታሰበ ደግሞ እስከ ሃምሳ በመቶ ይገባኛል የሚልም የሰው ቫይረስ አለ ይባላል። አቤት እግዚኦ! ከታላቅ እስከ ታናሽ ከባለሙያ እስከ ባለሥልጣን ያለውን ሁሉ ሳስበው ሰው ሰው ሳይሆን ቫይረስ ቫይረስ እየሸተተኝ ሳለሁ ድንገት ከሐሳቤ ባነንሁ። ተመስገን ጌታዬ! ኧረ ሁላችንም እንበድላለን ብቻ አንተው ይቅር በለን። ትውልዱንም ታደግ እያልሁ የጸጸት ሐሳቤን ሳልጨርስ እንደገና ሌላው መጣብኝ። ሙዳየ ምጽዋት የሚሰብረው፣ መባውን የሚዘርፈው ... እባክህን ልቡናዬ ተመለስልኝ። እንደፈረደበት ያው ሰበካ ጉባኤ ይጨነቅበት። በቃ ይህ የሰው ቫይረስ ግን ያልገባበት ቦታ ይኖር ይሆን? ላገኝ አልቻልኩም። እንኳን በእኛ ዘመን ከጌታም ጋር ከነበሩት ሐዋርያት የዐሥራት በኵራት ገንዘቡን በየዕለቱ የሚዘርፈው ይሁዳ አብሮ ነበር። ዮሐ.፲፪፥፮። ዳዊት በትንቢቱ «ተዘከር እግዚኦ ከመ መሬት ንሕነ» ያለው «... ከመ ቫይረስ ንሕነ» ማለቱ ይሆን? አዲስ ትርጓሜ። ቫይረሱ ሁሉ የኮምፒውተሩም ሌላውም ያው የአፈር ውላጅ አይደል። በእውነት እንደዚህ ብለንም ይቅር ባለን። እንደገና ሌላ ሐሳብ ...

የኮምፒዩተር ቫይረሶች በሰዎች ሆን ተብለው እንደሚሠሩት እነዚህ በየመሥሪያ ቤቱ ያሉትን የሰው ቫይረሶችስ ሆን ተብለው ያዘጋጇቸው አካላት ይኖሩ ይሆንን? መንገደኛው ልቤ አሁንም አላረፋም ይጠይቃል። በኮምፒዩተር ውስጥ የተጫኑትንና በስምምነት ይሠሩ የነበሩትን ፕሮግራሞች ሁሉ ቫይረሱ እንደ ባቢሎን ሰዎች ቋንቋቸውን እየደባለቀ አላግባባ እንደ ሚለው የትጉሃን ባለሞያዎችን ቋንቋ እያቀያየረ የሚያጣላ፣ ሰላማቸውን የሚያሳጣ ስንት የሰው ቫይረስ አለ? ... አሁንም እጓዛለሁ። ከዚህ በኋላ ኅሊናዬ ሊመለስ ሰውነቴም ሊያርፍ አልቻለም።

ለመሆኑ ቫይረሱን /የኮምፒዩተሩ/ አስተካክሎ ሌላ የሚሠራ ፕሮግራም /ሶፍት ዌር/ ማድረግ ይቻል ይሆን? የእኔ አዲስ ጥያቄ። ባለሞያው እንደገና ትዝ ያለኝ በዚህ ጊዜ ነበር። ደግነቱ አልወረደም። ባለሞያው ማስረዳት ጀመር። ቫይረሱን ማጥፋት ነው እንጂ አስተካክሎ ማሠራት አይቻልም። ከብዙ ገለጻ ጋር። በቃ! እኔም ትንሽ ደስታ ተሰማኝ ተስፋዬም ተሻሻለ። የሰው የቫይረስ ግን ሰው ነውና መሻሻል ይችላል። ራሱን አስተካክሎ መሥራት፣ በፍቅርና በሰላም በመግባባትም መኖር ይችላል። በቃ የሰው ቫይረስና የኮምፒዩተር ቫይረስ ልዩነታቸው ሰው ሊስተካከል መቻሉ ያኛው ደግሞ አለመቻሉ ነው። ቫይረስም ሆኖ ሰው ተስፋ አለው። ለካስ ከሞተ አንበሳ ያልሞተ ውሻ ይሻላል ማለት ይኼ ነው።፨


የመባዕ እና የስጦታ ዕቃዎች ማከፋፈያ
በዚህ ሱቃችን ውስጥ
ከውጭ የምናስመጣቸውን ንዋያተ ቅድሳት
የተቀመመ የሽቱ ዕጣን
የተለቀመ ዘቢብ እና ጧፍ
የስጦታ ዕቃዎች
እንዲሁም ሌሎች ንዋያት ያገኛሉ።
አድራሻ- መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተክህነት ፊት
ለፊት ከንዋያተ ቅድሳት /ቁጥር 2/ ማከፋፈያ ሱቃችን ዝቅ ብሎ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
ዋጋ 3.50

©ማኅበረ ቅዱሳን

ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፣እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው፡፡